መልስ ፡ ሰጭው ፡ ኩባንያ ፡ የዲሬክተሮቹን ፡ ጥያቄ ፡ ስላልተቀበለው ፡ የይግባኝ፡ ባይ ፡ ኩባንያ ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ እንዲደረግ ፡ ከወሰነና ፡ ስብሰባ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ የማኅበሩ ፡ ፕሬዚዳንትና ፡ ዲሬክተሮች ፡ ሐሳባቸውን ፡ ለስብሰባው ፡ አቅር በው ፡ የፕራይስ ፡ ወተር ፡ ሀውስ ፡ ሪፖርት ፡ ተነቦ ፡ ሲያልቅ ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባው ፡ የማኸዉን ፡ ውል ፡ ባለመቀበል ፡ ውድቅ ፡ አድርጐ ፡ ለገኸው ፡ የወጣው ፡ ፩፻፶ሺ ፡ ብር ፡ ወደ ፡ ማኅበሩ ፡ ሳጥን ፡ እንዲመለስ ፡ ቦርዱ ፡ በሕግ ፡ እንዲያስገድድ ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥቷል ፡ (የከ ፲፩ኛ ፡ ማስረጃ ፡)

ጠቅላላው ፡ ስብሰባ ፡ ውሳኔ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ኩባንያ ፡ ገንዘ ቡን ፡ ለመመለስ ፡ ፈቃደኛ ፡ ስላልሆነ ፡ የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ጠበቃ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ፡ ይደረግልኝ ፤ በማለት ፡ አከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ አቀረቡ ። መልስ ፡ ሰጭ ውም ፡ ውሉ ፡ ሊፈርስ ፡ አይገባውም ፤ በማለት ፡ መከላከያቸውን ፡ አቅርበው ፡ ሁለ ቱም ፡ ወገኖች ፡ በሰፊው ፡ ከተከራከሩ ፡ በኋላ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ ውሉ ፡ ሕጋዊ ፡ ስለሆነ ፡ ሊፈርስ ፡ አይገባውም ፤ ከሳሹም ፡ የ ፻፶ሺ ፡ ብር ፡ ዳኝነት ፡ በሙሉ ፡ ሊከፍሉ ፡ ይገባል ፤ በማለት ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ፍርድ ፡ ሰጥቷል ።

ከፍርድ ፡ የተለዩት ፡ ፩ኛው ፡ ዳኛ ፡ ግን ፡ በከሳሹ፡ ኩባንያ ፡ ፕሬዚዳንትና ፡ በተ ከሳሹ ፡ ኩባንያ ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ በኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፴፪ ፡ ስር ፡ ለተጻፈው ፡ ተቃራኒ ፡ ስለሆነ ፡ ፍርስ ፡ ሊሆን ፡ ይገባዋል ፤ ሲሉ ፡ ፈር ደዋል ።

የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ኩባንያ ፡ ጠበቃ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ይሻርልኝ ፤ በማለት ፡ ይህንን ፡ ይግባኝ ፡ አቅርበዋል ። የይግባኙም ፡ ማመልከቻ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ባጭሩ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተው ፡ ነው ።

የኩባንያው ፡ ዲሬክተሮች ፡ ቦርድ ፡ ለባላምበራስ ፡ አሸብር ፡ ሙሉ ፡ የፕሬዚዳ ንት ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቷቸዋል ። እሳቸውም ፡ የሚሠሩት ፡ በኩባንያው ፡ ዓላማና ፡ በን ግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

መልስ ፡ ሰጭ ፡ ኩባንያ ፡ ከአቶ ፡ ራህመቶ ፡ ሙክታር ፡ ወራሾች ፡ ላይ ፡ የሚጠይቀ ውን ፡ መብት ፡ በሙሉ ፡ ግምቱ ፡ ፻፴፷ሺ ፡ ብር ፡ የሆነውን ፡ አክሲዮን ፡ በ፻፶ሺ ፡ ብር ፡ በኩባንያው ፡ ስም ፡ ገዝተዋል ። ውሉን ፡ ከመዋዋላቸው ፡ በፊት ፡ ግዴታቸው ፡ እንደ መሆኑ ፡ መጠን ፡ የኩባንያውን ፡ አባሎች ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ ስብሰባ ፡ ባለአክ ሲዮኖችን ፤ አላማከሩም ፡ ፈቃድም ፡ አላገኙም ። ዲሬክተሮቹና ፡ ባለ ፡ አክሲዮኖቹ ፡ ያወቁት ፡ ውሉ ፡ ተፈርሞ ፡ ገንዘቡ ፡ ለመልስ ፡ ሰጭ ፡ ከተከፈለ ፡ በኋላ ፡ ነው ፤ ባወ ቁም ፡ ጊዜ ፡ ወዲያውኑ ፡ ተቃውመዋል ።

የባለ ፡ አክሲዮኖችም ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ ለመልስ ፡ ሰጭው ፡ ያለአግባብ ፡ የተ ከፈለው ፡ ፩፻፶ሺ ፡ ብር ፡ እንዲመልስ ፡ ውሳኔ ፡ አስተላልፏል ።

በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ይበልጡን ፡ የተመሠረተው ፡ በኩባን ያው ፡ መመሥረቻ ፡ ደንብ ፡ በአንቀጽ ፡ ፷፱ ፡ እና ፡ ፴ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ለኩባንያው ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቷል ፤ በማለት ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ ለፕሬዚዳንቱ ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ የራሱን ፡ የኩባንያውን ፡ አክሲዮኖች ፡ የመግዛት ፡ ወይም ፡ በመያዣ ፡ የመቀበል ፡ ሥልጣን ፡ የለበትም ። እን ደዚህ ፡ ያለው ፡ ሥልጣንም ፡ በንግድ ፡ ሕግ፡ቍጥር ፡ ፫፻፴፪ ፡ መሠረት ፡ በባለአክሲዮ ኖች ፡ ስብሰባ ፡ ካልተፈቀደ ፡ በቀር ፡ የማይጸና ፡ መሆኑ ፡ ተደንግጓል ።

ፕሬዚዳንቱ ፡ በፈረሙት ፡ ብቻ ፡ ኩባንያው ፡ የብድሩን ፡ መብት ፡ መውሰዱንና ፡ በአክሲዮኖቹም ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ መቀበሉን ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተቀብሎታል ።

የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፴፪ ፡ በኩባንያውና ፡ በባለ ፡ አክሲዮኖች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ ብቻ ፡ የሚመለከት ፡ በመሆኑ ፡ እና ፡ ፫ኛ ፡ ወገኖችን ፡ ስለማይመ ለከት ፡ የቍጥር ፡ ፫፻፴፪ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ሊሆን ፡ አይች ልም ፤ በማለትም ፡ ውሣኔ ፡ ሰጥቷል ። ሕጉ ፡ የባለ ፡ አክሲዮኖችንም ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ንም ፡ መብት ፡ ለመጠበቅ ፡ የተደነገገ ፡ ነው ። ስለዳኝነት ፡ አከፋፈልም ፡ የተሰጠ ፡ ውሳኔ፡ ትክክል፡አይደለም ። በአነስተኛ፡ድምፅ፡በተሰጠው፡ፍርድ፡በብድር፡ስም፡ ለሐጂ፡ ራሕሙቶ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ብድር ፡ አልነበረም ። በብድር ፡ ስም ፡ የተደረገ ፡ የአክሲዮኖቹ ግዢ ፡ ነበር ። ግዢም ፡ ባይሆን ፡ በአክሲዮኖቹ ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ፈጥሯል ። የመብቱ ፡ ማስተላለፍ ፡ ጉዳይ ፡ በኩባንያው ፡ ላይ ፡ ሊጸና ፡ የሚችለው ፤ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፴፪ ፡ የተደነገጉት ፡ ቢፈጸሙ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ስላልሆነ ፡ የአነስተኛው ፡ ድምጽ ፡ ይጸናልኝ ፤ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድም ፡ ይሻርልኝ ፤ በማለት ፡ ነው ።

የመልስ ፡ ሰጪ ፡ ኩባንያ ፡ ጠበቃም ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በአነስተኛ ፡ ድምጽ ፡ የተፈረደው ፡ፍርድ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ፡ ሕጋዊ ፡ ስለሆነ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲጸናና ፡ ይግባኙ ፡ እንዲሰናበት ፡ ይደረግልኝ ፤ በማለት ፡ መልስ ፡ ሰጥተዋል ። በመልሳቸውም ፡ ውስጥ ፡ ያቀረቡት ፡ ክርክር ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ቀጥሎ ፡ እንደተጻፈው ፡ ነው ።

ስለዳኝነቱ ፡ ገንዘብ ፡ አከፋፈል ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ትክ ክል ፡ ነው ፤ ስሕተት ፡ አይደለም ፤ ምክንያቱም ፡ ምንም ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት፡ ይሠረዝልኝ ፡ የሚል ፡ ማመልከቻ ፡ ቢያቀርቡ ፡ በዚያው ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ገንዘ ቡም ፡ እንዲመለስልኝ ፡ ብለው ፡ ጽፈዋል ።

እንዲሁም ፡ ሲሆን ፡ ፩፻፺፯ሺ ፡ ብር ፡ እንዲመለስላቸው ፡ የሚጠይቅ ፡ ስለሆነ ፡ ለዚሁ ፡ የተወሰነውን ፡ የዳኝነት ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍሉ ፡ የተሰጠው፡ ውሳኔ፡ትክክል፡ነው። ስለ ፡ ብድሩ ፡ ገንዘብ ፡ ሐጂ ፡ ራሕሙቶ ፡ በጠየቁት ፡ ጊዜ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ኩባንያ ፡ ገንዘብ ፡ አበድሯቸዋል ። በአነስተኛ ፡ ድምጽ ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ አንዳች ፡ ፍንጭ ፡ ሳያገኝ ፡ ሌላ ፡ ትርጉም ፡ ሊሰጠው ፡ ፈለገ ፡ እንጂ ፡ ብድሩ ፡ ምሥጢራዊ ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ነገር ፡ የለበትም ። አንድ ፡ ሰው ፡ አክሲዮን ፡ ለመግዛት ፡ የሚያስችለው ፡ ገንዘብ ፡ ከፈለገበት ፡ እንዲበደር ፡ የሚከለክለው ፡ ሕግ ፡ የለም ። የይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ክር ክር ፡ ትክክል ፡ ከሆነ ፡ ስለዋስትና ፡ የሚሰጥ ፡ አክሲዮን ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፪ ፡ (ሀ) በያይነቱ ፡ ትርጉም ፡ ሊሰጠው ፡ ነው ።

መልስ ፡ ሰጭ ፡ ኩባንያ ፡ የብድር ፡ መብቱን ፡ ለይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ኩባንያ ፡ በሸጠ ፡ ጊዜ ፡ ባለአክሲዮን ፡ አልነበረም ፡ ከኩባንያው ፡ ውጭ ፡ ያለ ፡ ፫ኛ ፡ ሰው ፡ ነበር ።

ባላምበራስ ፡ አሸብርም ፡ የኩባንያው ፡ ፕሬዚዳንት ፡ በመሆናቸው ፡ በኩባንያው ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ሰፊ ፡ ስልጣን ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ። በሁለታችን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የሺያጭ ፡ ውል ፡ የሐጂ ፡ ራሕመቶን ፡ አክሲዮን ፡ ሳይሆን ፡ በሐጂ ፡ ራሕመቶ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የብድር ፡ መብት ፡ ለመሸጥ ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ ነው ፤ እንዲሁ ፡ ያለው ፡ ውል ፡ በሕግ ፡ ያልተከለከለ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በይግባኝ ፡ ባይ ፡ ኩባንያ ፡ ደንብ ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፱-፴-፴፭- ፵፩ ፡ መሠረት ፡ የተፈቀደ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ኩባንያ ፡ የይግባኝ ፡ ባይን ፡ ኩባንያ ፡ ፕሬዚዳንትም ፡ ሆነ ማንንም ፡ ለማታለል ፡ ያላደረጉት ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የፈጸሙት ፡ ስለሆነ ፡ ይኸው ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ መከላከያ ፡ ነው ።

በሕግ ፡ በኩል ፡ ስለቀረበው ፡ ክርክርም ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፴፪ ፡ ለዚህ ፡ ነገር ፡ አግባብ ፡ የለውም ። ይህ ፡ ቍጥር ፡ የራስን ፡ አክሲዮን ፡ ስለመግዛት ፡ ሲናገር ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ኩባንያ ፡ ግን ፡ የራሱን ፡ አክሲዮን ፡ አልገዛም ። ይኸውም ፡ ቍጥር ፡ ስለኩባንያውና ፡ ስለባለ ፡ አክሲዮኖች ፡ ግንኙነት ፡ ሲናገር ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ኩባንያ ፡ ግን ፡ በይግባኝ ፡ ባይ ፡ ኩባንያ ፡ ውስጥ ፡ ባለ ፡ አክሲዮን ፡ አይደለም ። የዚሁ ፡ ቍጥር ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፡ ማኅበረተኛው ፡ ከኩባንያው ፡ ብድር ፡ ሲበደርና ፡ አክሲዮኖችን ፡ መያዣ ፡ ለመስጠት ፡ ሲፈልግ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ያመለክታል ። በዚህ ፡ ነገር ፡ የሐጂ ፡ ራሕመቶ ፡ ወራሾች ፡ ከኩባንያው ፡ ብድር ፡ አልወሰዱም ። አክሲዮኖቹንም ፡ መያዣ ፡ አልሰጡም ። ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፡ ተገቢነት ፡ አለው ፡ ቢባል ፡ እንኳ ፡ ተፈጻሚነቱ ፡ ከቍጥር ፡ ፫፻፳፫ ፡ እና ፡ ፬፻፲፮ ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ ስለሆነ ፡ ቅን፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ የ፫ኛ ፡ ሰው ፡ መብት ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ የመልስ ፡ ሰጭው ፡ ኩባንያ ፡ ጠበቃ ፡ ተከራክረዋል ።

ይግባኝ ፡ ባይ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ደጋግመው ፡ ጠቅሰውት ፡ ነበር ፤ በማለትም ፡ ስለንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፳፫ ፡ ሰፊ ፡ ክርክር ፡ በመስጠት ፡ ጽፈዋል ። እኛም ፡ ክርክራቸውን ፡ በጥንቃቄ ፡ መርምረናል ። በከሳሽ ፡ ፭ኛ ፡ ማስረጃ ፡ ስለ ተመለከተው ፡ ውል ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ "የብድር ፡ ውል ፡ ነው" የሚሉትን ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የአነስተኛው ፡ ድምጽ ፡ በሰጠው ፡ ፍርድ ፡ የተደረገው ፡ ስምምነት ፡ ከብድር ፡ ውል ፡ ጋር ፡ ዝምድና ፡ የለውም ፤ እንደሚመስለን ፡ የብድሩ ፡ ዓላማ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ባልተገለጸ ፡ ምክንያት ፡ በሐጂ ፡ ራሕመቶ ፡ በኩል ፡ ለተከሳሽ ፡ ኩባንያ ፡ የአክሲዮን ፡ መብት ፡ ለመስጠት ፡ ነው ፤ ብሏል ።

እኛም ፡ ይህንኑ ፡ የብድር ፡ ውል ፡ ስንመረምረው ፡ ተበዳሪው ፡ ሐጂ ፡ ራሕመቶ ፡ ከብድሩ ፡ ገንዘብ ፡ አንዳች ፡ የሚያገኙት ፡ ጥቅም ፡ የላቸውም ፤ የብድሩ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲውል ፡ የታሰበው ፡ የቄራዎቹ ፡ ማኅበር ፡ አክሲዮን ፡ ለመግዣ ፡ ነው ፡ ብድሩም ፡ እንዲቆይ ፡ የተደረገው ፡ የቄራዎቹ ፡ ማኅበር ፡ ለተቋቋመበት ፡ ለ፳፫ ፡ ዓመት ፡ ነው ። ከአክሲዮኑ ፡ የሚገኘውን ፡ ትርፍ ፡ ጥቂት ፡ እንኳን ፡ ለተበዳሪው ፡ ሳይቀር ፡ የሚቀበለው ፡ አበዳሪው ፡ ነው ። የአክሲዮኑ ፡ የስም ፡ ባለቤት ፡ የተባሉት ፡ ሐጂ ፡ ራሕመቶ ፡ አክሲዮኖቹን ፡ ለመስጠት ፡ ለማዘወር ፡ የማይችሉ ፡ መሆናቸው ፡ ተገልጿል ።

አበዳሪውም ፡ ለዚሁ ፡ ገንዘብ ፡ በአክሲዮኖቹ ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ መብት ፡ በቀር ፡ አክሲዮኑ ፡ ቢከስር ፡ በተበዳሪው ፡ ሌላ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ አንዳች ፡ መብት ፡ የለውም ፤ ተበዳሪውም ፡ ኃላፊነት ፡ የለባቸውም ። እንግዲህ ፡ ሐጂ ፡ ራሕመቶ ፡ የመልስ ፡ ሰጭ ፡ ኩባንያ ፡ ሠራተኛ ፡ ስለነበሩ ፤ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ኩባንያ ፡ በሳቸው ፡ መሣሪያነት ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ እጣውን ፡ መግዛቱ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። በድምጽ ፡ የተለዩት ፡ ዳኛ ፡ "ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባልተገለጸ ፡ ምክንያት ፡ በሐጂ ፡ ራሕመቶ፡ በኩል ፡ ለተከሳሹ ፡ ኩባንያ ፡ አክሲዮን ፡ መብት ፡ ለመስጠት" የተደረገ ፡ ነበር ፤ ያሉትን ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ደር

ሶበታል ፡፡ በኩባንያው ፡ መመሥረቻ ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ አክሲዮኖቹን ፡ በመቶ ፡ ስልሣ ውን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በመቶ ፡ አርባውን ፡ ብቻ ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ ተወላጆች ፡ እን ዲገዙ ፡ ስለተወሰነ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ኩባንያ ፡ በስሙ ፡ የገዛ ፡ እንደሆነ ፡ ከተፈቀ ደው ፡ ከመቶ ፡ አርባው ፡ ውጭ ፡ እንዳይሆንበት ፡ በመስጋት ፡ በሐጂ ፡ ራህመቶ ፡ በኩል ፡ ሊያገኘው ፡ የማይችለውን ፡ መግዛቱ ፡ ነው ፡፡

ከከሳሽ ፡ ፪ኛ ፡ ማስረጃ ፡ የምንረዳው ፡ በሐጂ ፡ ራሕመቶ ፡ ስም ፡ የተገዙት ፡ አክ ሲዮኖች ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ የማይሰጡ ፡ ስለሆነ ፡ እነዚህ ፡ አክሲዮ ኖች ፡ በበለጠ ፡ ወይም ፡ በአነሰ ፡ ዋጋ ፡ ለኢትዮጵያውያኖች ፡ ተሸጠው ፡ ገቢው ፡ ለሚ ስተር ፡ አ- ቤስ- ኩባንያ ፡ እንዲሆን ፡ ሁለቱም ፡ ባለጉዳዮች ፡ መስማማታቸውን ፡ ነው ፡፡

ስለዚህ፡ሐጂ፡ራሕመቶ፡ሙክታር፡መብታቸውን፡በሙሉ፡ለሚስተር፡አ- ቤስ፡ኩባንያ፡ መልቀቃቸውን ፡ ያረጋግጣል ፡፡ ሐጂ ፡ ራሕመቶ ፡ አክሲዮኑን ፡ ሲሸጡ ፡ አ- ቤስ ፡ ዋጋውን ፡ እንዲቀበል ፡ ተስማምተዋል ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡

መልስ ፡ ሰጭው ፡ ኩባንያ ፡ እውነተኛ ፡ አበዳሪ ፡ ከሆነ ፡ የአክሲዮኑ ፡ ዋጋ ፡ ባነሰ ፡ ጊዜ ፡ ልዩነቱን ፡ ከተበዳሪው ፡ ይቀበል ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ አክሲዮኑ ፡ ተሸጦ ፡ ባወጣው ፡ ዋጋ ፡ ብቻ ፡ ለምን ፡ ይወሰን ፡ ነበር ? አክሲዮኑ ፡ ጥቅም ፡ ባለመስጠቱስ ፡ ምን ፡ የሚነካው ፡ ነገር ፡ አለና ፡ ነው ፡ ይሸጥ ፡ ለማለት ፡ የደረሰው ? የራሱ ፡ አክሲ ዮን ፡ ስለሆነና ፡ ጥቅሙንም ፡ የሚወስድ ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ ለመሆኑ ፡ በከሳሽ ፡ ፩ኛ ፡ ማስ ረጃ ፡ ስለተጻፈ ፡ ጥቅም ፡ በማጣቱ ፡ እንዲሸጥ ፡ መወሰኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፡፡

አክሲዮኑም ፡ በተሸጠ ፡ ጊዜ ፡ ገቢው ፡ ለመልስ ፡ ሰጪው ፡ ኩባንያ ፡ ስለሆነ ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ የሐጂ ፡ ራሕመቶ ፡ ሙክታር ፡ የነበረው ፡ አክሲዮን ፡ የባለቤትነት ፡ መብቱ ፡ በዚህ ፡ ውል ፡ ዞሯል ፡፡ ለሐጂ ፡ ራሕመቶ ፡ የቀረው ፡ የአክሲዮን ፡ መሸጥ ፡ ተግባር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ፡፡ በከሳሽ ፡ ፪ኛ ፡ ማስረጃ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ የማይሰጥ ፡ መሆኑን ፡ የገለጸውን ፡ አክሲዮን ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ በማስ መሰል ፡ በ፩፻፶ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ሸጦታል ፡ (የከ ፡ ፬ኛ ፡ ማስረጃ) ፡፡ በውሉም ፡ ላይ ፡ በዚሁ፡ የመብት ፡ ማስተላለፍ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ወለድና ፡ ተጨማሪ ፡ የተያያዘ ፡ ዋጋ ፡ በማመዛ ዘን ፡ ዋጋው ፡ ፩፻፶ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ እንዲሆን ፡ ተወስኗል ፡ ይላል ፡፡ በከሳሽ ፡ ፩ኛና ፡ ፪ኛ ፡ ማስረጃዎች ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ወለድ ፡ ስለሌለ ፡ አክሲዮኖቹም ፡ ጥቅም ፡ የማይሰጡ ፡ መሆናቸው ፡ ስለተገለጸ ፡ መልስ ፡ ሰጪው ፡ የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ኩባንያ ፡ ገንዘብ ፡ ለመው ሰድ ፡ የፈጠረው ፡ ዘዴ ፡ ነው ፤ ከማለት ፡ በቀር ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የለውም ፡፡

መልስ ፡ ሰጭው ፡ ስለቅን ፡ ልቦና ፡ ያደከመ ፡ ክርክር ፡ አቅርቧል ፡፡ እኛ ፡ ግን ፡ ከመጀመሪያው ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ የመልስ ፡ ሰጭው ፡ አድራ ጐት ፡ በክፉ ፡ ልቦና ፡ እንጂ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የተመሠረተ ፡ ሆኖ ፡ አላገኘነውም ፤ ምክንያቱም ፡ መጀመሪያ ፡ አክሲዮኖችን ፡ በቅንነትና ፡ በግልጽ ፡ ሳይሆን ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ ስለገዛ ፤ ፪ኛ ፡ አክሲዮኖቹ ፡ ጥቅም ፡ የማይሰጡ፡መሆኑን ፡ ሲያውቅ ፡ ለተገኘ ፡ ገዢ ፡ ይሸጥ ፡ እንኳን ፡ ሳይል ፡ ለይቶ ፡ ለኢትዮጵያውያኖች ፡ እንዲሸጥ ፡ ስላለ ፡ ፫ኛ ጥቅም ፡ ወለድ ፡ የሌለውን ፡ አክሲዮን ፡ ጥቅም ፡ ወለድ ፡ አለው ፤ በማለት ፡ ከዋጋው ፡ በላይ ፡ ጨምሮ ፡ በ፩፻፶ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ስለሸጠ ፡ ነው ፡፡

መልስ ፡ ሰጭው ፡ በይግባኝ ፡ ባይ ፡ ኩባንያ ፡ መመሥረቻ ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ በቍ ጥር ፡ ፳፱ ፡ እና ፡ ፴ ፡ ለፕሬዚዳንቱ ፡ ሰፊ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶታልና ፡ ውሉ ፡ይረጋል ኛል ፤ ለሚሉት ፡ በመመሥረቻው ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ ለዲሬክተሮቹ ፡ ሰፊ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ በሕግ ፡ ለተፈቀዱት ፡ ሥራዎች ፡ እንጂ ፡ ከሕጉ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡

እንዲሠሩ ፡ አይደለም ። ሥልጣን ፡ ቢሰጣቸውም ፡ ሕግ ፡ አይቀበለውም ። በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፴፪ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ባለአክሲዮኖቹ ፡ መፍቀድ ፡ አለ መፍቀዳቸውን ፡ የውጪ ፡ ሰው ፡ ለማወቅ ፡ ያዳግተው ፡ ይሆናል ። ለሌላ ፡ ጉዳይ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮም ፡ ግድ ፡ ካላወቀ ፡ ለማለት ፡ ያስቸግር ፡ ነበር ።

ይህ ፡ ቍጥር ፡ የሚመለከተው ፡ የራስን ፡ አክሲዮን ፡ ለመግዛት ፡ ወይም ፡ ለማስ ያዝ ፡ ስለሆነና ፡ ባለአክሲዮኖችን ፡ የሚነካ ፡ ነገር ፡ ስለሆነ ፡ መፈቀድ ፡ አለመፈቀ ዱን ፡ ለማወቅ ፡ ለባለ ፡ አክሲዮኑ ፡ አዳጋች ፡ አይሆንበትም ። መልስ ፡ ሰጭ ፡ ኩባን ያም ፡ በእጅ ፡ አዙርም ፡ የሠራው ፡ ቢሆን ፡ የአክሲዮኑ ፡ ባለቤት ፡ ስለሆነና ፡ አክሲዮ ኑም ፡ ጥቅም ፡ የማይሰጥ ፡ መሆኑን ፡ እንኳን ፡ ለማወቅ ፡ የቻለ ፡ ስለሆነ ፡ ይህንን ፡ አያ ውቅም ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ አያስችልም ።

በጠቅላላውም ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ኩባንያ ፡ ከይግባኝ ፡ ባይ ፡ ኩባንያ ፡ ፕሬዚዳ ንት ፡ ጋር ፡ የተዋዋሉት ፡ ውል ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፴፪ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የባለ ፡ አክሲዮኖቹ ፡ ፈቃድ ፡ ሳይገኝ ፡ የተፈጸመ ፡ ውል ፡ ነው ።

በተጨማሪም ፤ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ እና ፡ ፪፻፲፯ ፡ የተመለከተውን ፡ መሠ ረት ፡ በማድረግ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የተመለከተውን ፡ ስንመረምር ፡ ይህ ፡ ውል ፡ በቍጥር ፡ ፪ሺ፩፻፺ ፡ መሠረት ፡ በባለ ፡ አክሲዮኖች ፡ ጉባዔ ፡ መጽደቅ ፡ ወይም ፡ መፍረስ ፡ ነበረበት ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የባለ ፡ አክሲዮኖቹ ፡ ጉባዔ ፡ ውል ፡ እንዲ ፈርስ ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥቶበታል ። እንዲህም ፡ ሲሆን ፡ ውሉ ፡ እንዲጸና ፡ የሚደግፍበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ። በኩባንያው ፡ መመሥረቻ ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ ለውጪ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ እንዲሸጥ ፡ የተፈቀደው ፡ አክሲዮን ፡ በመቶ ፡ አርባ ፡ ሲሆን ፡ የመልስ ፡ ሰጪው ፡ አክሲዮን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ነውና ፡ አክሲዮኑ ፡ ወደ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ መመለስ ፡ አለ በት ፤ እንዳይባልም ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የቀረበልን ፡ ክርክር ፡ የለም ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ በከሳሽ ፡ ፲፩ኛ ፡ ማስረጃ ፡ ላይ ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ድርሻ ፡ ከመቶ ፡ ሶስት ፡ የማ ይበልጥ ፡ ለመሆኑ ፡ ተገልጿል ።

ብዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ በከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ የተሰጠውን ፡ አነስተኛውን ፡ ድምጽ ፡ በመደገፍና ፡ የድምጽ ፡ ብልጫውን ፡ ፍርድ ፡ በመለወጥ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ኩባንያ ፡ ከይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ኩባንያ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ጋር ፡ ያደረጉት ፡ በከሳሽ ፡ ፱ኛ ፡ ማስረጃ ፡ የተመለከተው ፡ ውል ፡ እንዲፈርስና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪ሺ፩፻፺፫ ፡ (፩) ፡ እና ፡ ፩ሺ፰፻፲፩ ፡ መሠረት ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ የተቀበሉትን ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሃምሣ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ለይግባኝ ፡ ባይ ፡ ኩባንያ ፡ እንዲመልሱ ፤ እንዲሁም ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ በዚህ፡ነገር ፡ የዳኝነት ፡ ገንዘብ ፡ ሊከፈል ፡ ይገባል ፤ ብሎ ፡ የወሰነውን ፡ የተከፈለው ፡ በሚገባ ፡ ስለሆነ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ለዳኝነት ፡ የተከፈለ ውን ፡ በደረሰኝ ፡ ኪሣራ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለይግባኝ ፡ ባይ ፡ እንዲከፍሉ ፡ ፈርደ ናል ።

እንደ ፡ ፍርዱ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይተላለፍ ።
መጋቢት ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ- ም- ።

SUPREME IMPERIAL COURT

Div. No. 4

Justices:

Vice Afenegus Tebebu Beyene

Ato Wolde Hanna Gebre Kidan

Ato Tekola Wolde Kidan

THE ETHIOPIAN ABATTOIRS' ASSOCIATION v. A. BESSE COMPANY

Civil Appeal No. 11/57

Contracts — Invalidation — Effect of Invalidation - Arts. 1, 216, *Comm. C., Arts.* 2190, 2193(1), 1815, *Civ. C.*

Companies — Purchase by a company of its own shares — Art. 332, *Comm. C.*

On appeal from a majority decision of the High Court rejecting the appellant company's request that the court invalidate the contract whereby the respondent company sold its rights over shares of the appellant company to the chairman of the appellant company.

Held: Decision reversed.

1. The granting of wide powers to the director of a company under the memorandum of association does not amount to an authorization by a meeting of the shareholders to make contracts under Art. 332 of the Commercial Code.

2. A contract made without an authorization by a meeting of the shareholders under Art. 332 of the Commercial Code must be ratified or repudiated in a meeting of the shareholders, in accordance with Art. 2190, Civ. C.; where the contract is repudiated by a meeting of the shareholders, then the contract must be invalidated.

After the Ethiopian Abattoirs' Association, the appellant, was established, A. Besse Company, the respondent, loaned to Hadji Rahmato Muktar a sum of $196,600 to be repaid in a period of 25 years.

In the contract of loan, the borrower entered into an obligation that the money would be used to buy shares in the Ethiopian Abattoirs' Association and that the borrower would not donate or transfer the ownership of the shares to a third party without the written consent of the lender. Since the loan is interest-free, the lender receives the profit derived from the shares from time to time.

Plaintiff's first piece of evidence: The loan was later reduced to $136,600. Since no profit was derived from the shares, in 1950 E.C., the lender and the borrower agreed that the shares should be sold to Ethiopians at a price either lower or higher than the original buying price and that the sum thus obtained should be given to the lender.

Plaintiff's second piece of evidence: In 1965 the respondent company sold its right over the sum of $136,600 referred to above for $150,000 to the chairman of the appellant company. The directors of the appellant company repeatedly ex-

pressed their objection to the respondent company on the ground that the sum of $150,000 should be paid back since the sale was illegal. But the respondent company did not accept the request of the directors.

Plaintiff's fourth piece of evidence: Since the respondent company rejected the request of the directors, the general meeting of the appellant company was convened and held. At the general meeting, the chairman and directors expressed their views to the general meeting and the report of Price Waterhouse was read. The general meeting repudiated the contract of sale and passed a resolution that the Board legally compel the respondent to return to the treasury of the association, the sum of $150,000 used for the purchase.

Plaintiff's eleventh piece of evidence: As the respondent company was unwilling to reimburse the money after the general meeting had passed a resolution, the advocate of the appellant filed a suit in the High Court for the invalidation of the contract. The respondent submitted a statement of defense alleging that the contract should not be invalidated. After both made a lengthy argument, the High Court in a majority opinion gave a judgment that the contract may not be invalidated since it was legal, and that the plaintiff must pay the court fee for the sum of $150,000.

But the dissenting judge expressed his opinion that the contract made between the chairman of the appellant company and the defendant company must be invalidated since it was inconsistent with Art. 332 of the Commercial Code of Ethiopia.

The advocate of the appellant company has lodged this appeal for the reversal of the majority opinion of the High Court. The facts of the petition are briefly as follows:

The board of directors of the company granted full power to Balambaras Ashebir as chairman. It is clear that the chairman executes his duty in accordance with the objectives of the company and the Commercial Code.

He bought for $150,000 in the name of the company the right claimed by the respondent company against the heirs of Ato Rahmato Muktar, the estimate of which was $136,000. Though it was his obligation to consult the members of the company or the sharehoders in the general meeting before the contract had been completed, he did not do so and therefore was not officially authorized to act. It was only after the contract had been signed and the money had been paid to the respondent that the directors and shareholders knew of the chairman's action. When they learnt of the action, they immediately objected.

The general meeting of the shareholders then passed a resolution that the respondent must pay back the sum of $ 150,000 which was unduly paid.

The majority opinion was mostly based on the assumption that the chairman of the company has been granted full power under Arts. 29 and 30 of the memorandum of association of the company. But the scope of power granted to him does not enable him to buy the shares of a company or to receive shares as a pledge. Under Art. 332 of the Commercial Code it is stated that the power to do this is not valid unless it has been authorized by the meeting of the shareholders. The judgment has confirmed the fact that the company acquired the right of ownership of the loan and that it received the shares in pledge as a result of the contract signed by the chairman.

Since Art. 332 of the Commercial Code applies only to the relationship between a company and its shareholders, and not to third parties, the court held that (4) of Art. 332 is inapplicable to this case. The purpose of the law is to protect the rights of shareholders and creditors. The decision with respect to the payment of the court fee is also incorrect. According to the opinion of the dissenting judge, the sum given to Hadji Rahmato under the disguise of a loan was not actually a loan. It was a purchase of shares executed under the disguise of loan which created a pledge if there was actually no purchase. It is only if the provisions of Art. 332 of the Commercial Code were satisfied that the transfer of a right would be binding on the company. Therefore, the minority opinion should be affirmed and the majority opinion should be reversed.

Counsel for the respondent company in his response petitioned for the dismissal of the appeal on the ground that the minority opinion of the High Court is erroneous and that the majority opinion should be affirmed since it was proper. The facts as contained in the argument of the petition of the respondent are as follows:

The majority opinion with respect to the payment of the court fee was correct because when he filed the suit with the High Court the appellant in his statement of claim asked for the repayment of the money in addition to his petition for the cancellation of the contract. Thus, it is clear that since in his statement of claim he asked for the repayment of $150,000, the decision ordering him to pay the court fee fixed for that sum was correct.

When Hadji Rahmato asked for a loan, the respondent company gave it to him. The minority opinion gave a different interpretation without anything to support it; however, there is nothing obscure or illegal about the loan. There is no law that forbids a person from borrowing a sum sufficient to buy shares. If the view of the appellant is correct, it would lead to various interpretations of Art. 332 of the Commercial Code with regard to pledged shares.

When the respondent company sold its claim to the loan to the appellant company, it was not a shareholder; it was a third party. Balambaras Ashebir was the chairman of the company, who was granted wide powers under the articles of association. The contract of sale between them was not a contract to sell the shares of Hadji Rahmato. It was only to sell the claim to the loan against Hadji Rahmato. And such a contract, besides its not being rendered void by the law, is permitted under Arts. 29, 30, 31 and 44 of the memorandum of association. Moreover, since the respondent company acted in good faith and did not try to defraud the chairman of the appellant company or anyone else, this may be an adequate defense.

As for the contention based on the legal provisions Art. 332 of the Commercial Code, it is inapplicable in this case. This article discusses the acquisition of one's own shares through purchase. But the appellant company did not purchase its own shares. The same article discusses the relationship between a company and its shareholders. The respondent company, however, is not a shareholder in the appellant company. Sub Art. (4) of the same article lays down the requirements to be fulfilled when a shareholder in a company borrows a sum from it and seeks to pledge his shares. In this case the heirs of Hadji Rahmato did not receive a loan and did not pledge their shares. Even if Sub Art. (4) is considered relevant, it must be applied in accordance with Arts. 363 and 416, and therefore the right of a third party in good faith is reserved.

The respondent has written a lengthy argument on Art. 363 of the Commercial Code on the ground that the appellant had repeatedly referred to it in the High Court. We have carefully considered their arguments. Concerning the contract which was referred to in plaintiff's piece of evidence and which was alleged to be a contract of loan, by the respondent, the dissenting judge stated that the contract entered into was not related to the contract of loan. According to his opinion the purpose of the loan was to confer the ownership of the shares upon the defendant company through Hadji Rahmato for a reason that was not disclosed to the court.

On examination of the contract of loan, we find no profit whatsoever which Hadji Rahmato, the borrower, derives from the loan. The loan is used for the purchase of the share of the Ethiopian Abattoirs' Association. And the loan is for a duration of 25 years from the date in which the Ethiopian Abattoirs' Association was established. Not even a fraction of the profit derived from the share was reserved for the borrower; all went to the lender. It is also expressed that Hadji Rahmato, the nominal owner of the shares, may not donate or transfer the shares.

If the association goes bankrupt, the lender has no claim whatsoever against the property of the borrower except over the shares. The borrower is not responsible. Thus, it is clear that the respondent company indirectly bought the shares through the instrumentality of Hadji Rahmato, since the latter was an employee of the respondent company. As for the opinion of the dissenting judge that the ownership of shares was transferred to the defendant company through the medium of Hadji Rahmato, it is clear from the memorandum of association, that 30% of the shares could be bought by Ethiopians and only 40% by foreigners. The respondent company bought indirectly for fear that if it bought in its name the prescribed limit of 40% would be exceeded.

When we examine the plaintiff's second piece of evidence, since the shares bought in the name of Hadji Rahmato were not profitable at the time, both parties agree that the sum obtained through the sale of shares to Ethiopians at a lower or higher selling price should be due to the company of Mr. A. Besse.

Therefore, Hadji Rahmato confirms that he made a complete transfer to the company of Mr. A. Besse. A. Besse agreed to receive the price when Hadji Rahmato sold the shares.

If the respondent company had been the actual lender, why should it have decided to receive any price instead of receiving the difference from the borrower when the value of the share was reduced? And if the share was unprofitable what interest had he to demand the sale of the share? As it is written in the plaintiff's first piece of evidence, since the share was its own and since it itself receives the profit, it is clear that the decision to sell was made because the stock was unprofitable.

Since the sum was received by the respondent company when the share was sold, the ownership of shares nominally owned by Hadji Rahmato was transferred by the contract. It may be said that the only duty Hadji Rahmato was responsible for was the sale of the shares. They sold for $150,000 which was stated to be unprofitable under plaintiff's second piece of evidence. Plaintiff's fourth piece of evidence states that the price was estimated in the contract at $150,000 by reckoning what was paid for the transfer of ownership, plus the interest and additional related expenses. As it was stated in the plaintiff's first and second pieces of evidence, since there is no interest and since no profit is derived from the shares,

there is no sufficient reason to give other than that this was an excuse devised by the respondent to take the money of the appellant.

The respondent has repeatedly raised the defense of good faith. But we have come to the conclusion that the act of the respondent did from beginning to end arise out of bad faith and not out of good faith. This is because: firstly, it bought the shares indirectly and not openly and in good faith, secondly, it was agreed that the shares should be sold only to Ethiopians instead of to any buyer when it knew that the shares were unprofitable; and thirdly, it sold the shares which had no profit and interest as though it had, these for $150,000 which was beyond its price.

As for the petition of the respondent that the contract should be valid since the chairman was granted wide power under Arts. 29 and 30 of the memorandum of association of the appellant company, it is only to do those acts prescribed by law that directors are granted wide power under the articles of association. They are not granted power to do acts which are inconsistent with the law. Even if they are granted it will not be supported by the law. It may be difficult for a third party to know whether or not the shareholders gave an authorization on the basis of Art. 332 of the Commercial Code. Had it been in other cases it would have been difficult to say that he should have known it.

Since this article refers to the possibility of buying and pledging one's own shares and since it affects the interest of the shareholders, it would not be difficult for a shareholder to know whether or not an authorization has been granted. And since the respondent company is, though indirectly, the owner of the shares and since it was able to know that the shares were unprofitable, it is impossible to say that it did not know this.

In general, the contract entered into by the respondent company and the chairman of the appellant company was a contract made without the authorization of the shareholders according to Art. 332 of the Commercial Code.

Moreover, when we examine the Civil Code on the basis of Arts. 1 and 216 of the Commercial Code, since this contract must be ratified or repudiated in a meeting of shareholders in accordance with Art. 2190, a resolution was passed in the meeting of the shareholders repudiating the contract; and in such a case there is no reason to justify the validity of the contract. It is impossible to say that the shares must be transferred back to the appellant on the ground that, though the memorandum of association of the company limits to 40% the number of shares that may be bought by foreigners, the shares of the respondent exceeds this limit; not only is the contention not based on this fact, but it has also been stated in the plaintiff's eleventh piece of evidence that the shares of foreigners do not exceed 3%.

Therefore, having supported the minority opinion of the High Court and having reversed the majority opinion, we have decided that the contract which was made between the respondent company and the chairman of the appellant company and which was referred to under the plaintiff's fourth piece of evidence must be invalidated; that the respondent must pay back to the appellant company the sum of $150,000 in accordance with Arts. 2193 (1) and 1815, and that the respondent must on receiving receipt pay the court fees paid by the appellant and $500 for expenses incurred since the decision of the High Court ordering the payment of the court fees and the fact that the payment was made in this case were proper.

Let it be remitted to the High Court to be executed in accordance with the judgment.

Megabit 14, 1957 E.C.

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤
አራተኛ ፡ ችሎት ፡

ዳኞች ፤

ም/ አፈንጉሥ ፡ ጥበቡ ፡ በየነ ፤
አቶ ፡ ወልደሐና ፡ ገብረ ፡ ኪዳን ፤
አቶ ፡ ተኰላ ፡ ወልደ ፡ ኪዳን ።

አቶ ፡ ናጂ ፡ ሰይድ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤
አብዱል ፡ መሊክ ፡ መሐመድ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፤

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍጥር ፡ ፲፱፻፷፰/፷፱ ዓ ፡ ም ።

የውል ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚመለከት ፡ ማስረጃ ፡ — ፊርማን ፡ ስለመካድ ፡ — ፊርማን ፡ ወይም ፡ ጽሕፈትን ፡ በመሐላ ፡ ስለመካድ ፡የጽሕፈት፡ወይም፡ የፊርማ፡ምርመራ—የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ፪ሺ፯ ፡ ፪ሺ፰።

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተከሳሹ ፡ ፊርማውን ፡ በመሐላ ፡ ከካደ ፡ በኋላ ፡ ከሳሹ ፡ የተከሳሹ ፡ ፊርማ ፡ ይመርመርልኝ ፤ ለማለት ፡ አይችልም ፡ ሲል ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ።

ውሳኔ ፤ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፈረደው ፡ ውድቅ ፡ ሆኗል ።

፩/ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪ሺ፰ ፡ መሠረት ፡ በመሐላ ፡ የተካደ ፡ ፊርማ ፡ ወይም ፡ ጽሕፈት ፡ በአዋቂዎች ፡ እንዲመረመር ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

፪/ አንድ ፡ ወገን ፡ አንድን ፡ ፊርማ ፡ ወይም ፡ ጽሕፈት ፡ ሲክድ ፡ ፊርማው ፡ ወይም ፡ ጽሕፈቱ ፡ እንዲመረመር ፡ ወዲያው ፡ ማዘዝ ፡ የባለጉዳዮቹና ፡ የመርማሪውን ፡ ጊዜ ፡ ይቆጥባል ።

ፍርድ ።

ይግባኝ ፡ ባይ ፡ በመልስ ፡ ሰጭው ፡ ዋስትና ፡ ለባለ ፡ ገንዘቡ ፡ ለኒኮላ ፡ ላዛራዲስ ፡ ፱ሺ፯፻፲፱ ፡ ብር ፡ ከ፺፫ ፡ ሣንቲም ፡ ስለከፈልኩት ፡ መብታቸውን ፡ አስተላልፈውልኛልና ፡ የከፈልኩትን ፡ ገንዘብ ፡ ይመልሱልኝ ፡ በማለት ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ አቅርበዋል ።

መልስ ፡ ሰጭው ፡ እንኳንስ ፡ እኔ ፡ ዕዳ ፡ ሊኖርብኝ ፡ የኔ ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ አለኝ ፡ ብዬ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ አቅርቢያለሁ፤ብለው፡ስለካዱ፡ ይግባኝ ፡ ባይ፡ ሰነዶችን ፡ አቅርበዋል ። መልስ ፡ ሰጭው ፡ ፊርማውን ፡ በመካዳቸው ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ፊርማቸውን ፡ በመሐላ ፡ ይካዱ ፤ ብለው ፡ አመለከቱ ። መልስ ፡ ሰጭም ፡ የኔ ፡ ፊርማ ፡ አይደለም ፤ ብለው ፡ በመሐላ ፡ ክደዋል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ፊርማው ፡ ይመርመርልኝ ፤ ሲፈርሙ ፡ የነበሩ ፡ ምስክሮችም ፡ ይመስክሩልኝ ፤ ብለው ፡ ቢያመለክቱ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ በመሐላ ፡ ከመሰከርኩ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ምስክር ፡ አይሰማም ፤ ፊርማውም ፡ አይመረመርም ፤ ክሱ ፡ ይሠረዝልኝ ፤ ብለው፡ተቃወሙ። ፍርድ ፡ ቤቱም፡ተከሳሹ ፡ ፊርማዬ ፡ አይደለም ፡ ብለው

በመሐላ ፡ ካረጋገጡ ፡ በኋላ ፤ ከሳሹ ፡ እንደገና ፡ ፊርማው ፡ ይመርመርልኝ ፡ ሊሉ ፡ አይገባቸውም ፤ በማለት ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ክሱን ፡ ሠርዞታል ፤ በድምጽ ፡ የተለዩት ዳኛ ፡ ግን ፡ ፊርማው ፡ ሊመረመር ፡ ይገባል ፤ በማለት ፡ ተለይተዋል ።

ይግባኝ ፡ ባይ ፡ አለአግባብ ፡ ተፈረደብኝ ፡ በማለት ፡ ይህንን ፡ ይግባኝ ፡ አቀረቡ ። መልስ ፡ ሰጭው ፡ ፍርዱ ፡ ይጽናልኝ ፤ ብለው ፡ መልስ ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ አሁን ፡ ፊር ማዬ ፡ ነው ፡ የተባለው ፡ ሰነድ ፡ ቢመረመር ፡ አልቃወምም ፤ ብለዋል ።

እኛም ፡ ነገሩን ፡ እንደመረመርነው ፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪ሺ፯ ፡ የግል ፡ በሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ የተጻፈ ፡ ሰነድ ፡ የቀረበለት ፡ ሰው ፡ የኔ ፡ አይደለም ፡ ለማለት ፡ የፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ ጽሕፈቱን ፡ ወይም ፡ ፊርማውን ፡ ግልጥ ፡ አድርጐ ፡ መካድ ፡ አለ በት" ይላል ። ይኸውም ፡ ግልጥ ፡ ክህደት ፡ በመሐላ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ መሐላ ፡ ቢሆን ፡ በቍጥር ፡ ፪ሺ፰ ፡ መሠረት ፡ ከመመርመር ፡ ሊድን ፡ አይችልም ። እንዲያውም ፡ "ፊርማዬ ፡ አይደለም" ብሎ ፡ ያለጥንቃቄ ፡ በሚደረገው ፡ ንግግር ፡ ብቻ ፡ ለምርመራ ፡ እየላኩ ፡ የነገረተኞቹንም ፡ ሆነ ፡ የፊርማ ፡ መርማሪዎቹን ፡ ጊዜ ፡ ከማባከን ፡ "ፊርማዬ አይደለም" የሚለው ፡ ሰው ፡ ፊርማውን ፡ በጥንቃቄ ፡ መርምሮ ፡ ፊርማው ፡ አለመሆኑን ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ይህንኑ ፡ በመሐላ ፡ ሲያስታውቅ ፡ ለምርመራ ፡ እንዲላክ ፡ ቢደረግ ፡ በመሐላ ፡ የሚደረገው ፡ ክህደት ፡ የሚአስከትለውን ፡ ውጤት ፡ በመፍራት ፡ ብቻ ፡ ብዙ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ሊቀንስ ፡ ይችላል ።

ስለዚህ ፡ ፊርማው ፡ ይመርመር ፡ ተብሎ ፡ በአነስተኛው ፡ ድምጽ ፡ የተሰጠውን ፡ ሐሳብ ፡ በመደገፍ ፤ ፊርማው ፡ አይመርመር ፡ በማለት ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ የተሰጠ ውን ፡ ፍርድ ፡ ለውጠን ፤ ፊርማው ፡ በቴክኒካዊ ፡ ምርመራ ፡ ተጣርቶ ፡ ሊረጋገጥ ፡ ይገባል ፡ ብለን ፡ ፈርደናል ።

የይግባኙን ፡ ዳኝነት ፡ በደረሰኝ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ይክፈሉ ። ኪሣራ ፡ በየራሣ ቸው ፡ ይቻቻሉ ። ከፍተኛው፡ ፍርድ ፡ ቤት፡ ሰነዱን፡አስመርምሮ ፡ በሚገኘው ፡ የምር መራ ፡ ውጤት ፡ መሠረት ፡ እንደገና ፡ ፍርድ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ የፍርዱ ፡ ግልባጭ ፡ ይተ ላለፍለት ።

መስከረም ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ።

SUPREME IMPERIAL COURT

Div. No. 4

Justices:

Vice Afenegus Tebebu Beyene

Ato Woldehana Gebre Kidan

Ato Tekola Wolde Kidan

NADJ SAID v. ABDUL MELIK MOHAMMED

Civil Appeal No. 978/57

Proof in relation to contracts — Disclaiming signature — Disclaiming signature or handwriting under oath — Verification of signature or handwriting — Civ. C. Arts. 2007-1, 2008.

On appeal from a decision of the High Court striking out the suit on the ground that the plaintiff may not require an examination of the signature of the defendant after the defendant has denied the same under oath.

Held: Decision reversed.

1. A signature or handwriting denied under oath may be examined by experts by virtue of Art. 2008. Civ. C.

2. Ordering the verification of a signature or handwriting immediately after a party has denied under oath that the same is his, saves the time of the litigants and that of the examining expert.

The appellant has filed a suit in the High Court alleging that having paid to Nicola Lazaridis, the creditor, the amount of $9719.95 as guarantor to the respondent, he has been subrogated to the rights of the creditor and hence the respondent should pay him the said amount.

Since the respondent has not only denied any debt but also alleged that the appellant owes him some money, the appellant has introduced some documents. The respondent, having disdained his alleged signature, has formally denied the same under oath on the application of the appellant.

Later, the appellant argued that the signature be examined, that persons who have seen the respondent replied that neither the witnesses should be introduced nor the signature be examined since he has given his affidavit under oath and that the suit be struck out. The majority of the Court has struck out the suit on the ground that the plaintiff should not ask that the signature be examined after the defendant has denied under oath that it is his signature. The minority judge dissented, saying that the signature should be examined.

The respondent, after replying that the judgment appealed against is valid, has said that he does not oppose the examination of his signature.

As we examined the matter, Art. 2007-1 of the Civil Code states that "he against whom a non-authenticated instrument is set up shall, where he intends not to recognize it as his own, formally disdain his alleged handwriting or signature". Whether this express denial is under oath or not, the signature or the handwriting cannot escape examination under Art. 2008. Even more, instead of wasting the time of the litigants and that of the handwriting experts by sending the signature or the handwriting to be examined just because the party carelessly disclaimed it, the fear of the result of denial under oath would reduce much litigation, if the handwriting or the signature is sent to be examined only after the party has disclaimed it under oath having carefully examined it.

We therefore change the majority decision, and rule supporting the minority so that the signature be technically examined and proved.

The respondent shall pay the Court fees for the appeal according to receipt. The parties shall bear their own costs. So that the High Court shall get the document examined and give judgment in accordance with the result obtained, a copy of this judgment shall be sent to the High Court.

Maskaram 6, 1958 E.C.

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤
አራተኛ ፡ ችሎት ።

ዳኞች ፤

ም/ አፈንጉሥ ፡ ጥበቡ ፡ በየነ ፤
አቶ ፡ ወልደ ፡ ሐና ፡ ገብረ ፡ ኪዳን ፤
አቶ ፡ ካብትህ ፡ ይመር ፡ አፍራሴ ።

፩ኛ/ አቶ ፡ ገብሬ ፡ ጀማነህ ፣
፪ኛ/ ወይዘሮ ፡ ጀማነሽ ፡ በልሁ ፣ ይግባኝ ባዮች ፤
አቶ ፡ ታረቀኝ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፤

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍጥር ፡ ፲፱፻፵፰/፶፯ ዓ ፡ ም ።

የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሕግ ፡ — ስለ ፡ መወለድ—አባት ፡ ነው ፡ ስለሚያሰኝ ፡ ግምት ፡ — ልጅነትን ፡ ለመካድ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡ — የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ፯፻፵፮ ፣ ፯፻፶፫ ።

የመልስ ፡ ሰጭ ፡ አባትነት ፡ በሕግ ፡ ለሌላ ፡ በተወለዱበት ፡ ወቅት ፡ የእናታቸው ፡ ባል ፡ ለነበሩት ፡ ሰው፡ የተሰጠ ፡ ቢሆንም ፣ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ከተባሉት ፡ ሰው ፡ አለመወለዳቸውን ፣ የአንድ ፡ የሌላ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ የተለዩ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ መሆናቸውን ፡ የቃል ፡ ምስክር ፡ አቅርበው ፡ ሊያስረዱ ፡ ይችላሉ ፤ ሲል ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ።

ውሳኔ ፤ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ተሽሯል ።

፩/ አንድ ፡ በሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ የተወለደ ፡ ልጅ ፡ ሕጉ ፡ "አባት ፡ ነህ" ፡ ሲል ፡ አባትነቱን ፡ የሰጠውን ፡ የእናቱን ፡ ባል ፡ በመካድ ፡ "አባቴ ፡ አይደለህም" ፣ በማለት ፡ ሊከስና ፣ የቃል ፡ ምስክሮች ፡ አቅርቦ ፣ የተወለደው ፡ እናቱ ፡ ከጋብቻዋ ፡ ውጭ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ከነበራት ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ ሊያስረዳ ፡ አይችልም ።

ውሣኔ ።

ይግባኝ ፡ ባዮች ፣ ወንድማችን ፡ አቶ ፡ ደምሴ ፡ ነጋሽ ፡ ዘር ፡ ሳይተካ ፡ ነሐሴ ፡ ፪ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሞት ፡ ስለተለየን ፣ ከኛ ፡ የቀረበ ፡ ዘመድ ፡ የለውምና ፡ ወራሾች ፡ እኛ ፡ መሆናችንን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይወቅልን ፤ በማለት ፡ እከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቍጥር ፡ ፲፪/፶፮ ፡ ያስተዳደር ፡ ፋይል ፡ ከፍተዋል ።

መልስ ፡ ሰጪው ፡ ታረቀኝ ፡ በሞግዚቱ ፡ አማካይነት ፣ የሟቹ ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፤ በማለት ፣ ወ/ከበቡሽ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ደግሞ ፡ የሟች ፡ ሚስት ፡ ነኝ ፤ በማለት ፡ በተቃዋሚነት ፡ ቀረቡ ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፣ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ባይ ፡ በተለይ ፡ ያስተዳደር ፡ ፋይል ፡ ይክፈት ፤ ብሎ ፡ በማዘዙ ፣ የሕፃኑ ፡ ሞግዚት ፡ ቍጥር ፡ ፪፫፬/፶፮ ፡ የሆነውን ፡ ያስተዳደር ፡ ፋይል ፡ ከፈቱ ። ያሁን ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ በተቃዋሚነት ፣ ሕፃኑ ፡ የሟች ፡ ልጅ ፡ አይደለም ፤ በማለት ፡ ተቃውሞአቸውን ፡ አቅርበዋል ።

የአመልካቹ ፡ ሞግዚት ፡ ልጁ ፡ ከአቶ ፡ ደምሴ ፡ ለመወለዱ ፡ ምስክሮች ፡ ላቅርብ ፡ ብለው ፡ ቢያመለክቱ ፡ ተቃዋሚዎቹ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ምስክር ፡ ሊሰማ ፡ አይገባም ፤ በማለት ፡ ተቃውመዋል ። የሰጡትም ፡ ምክንያት ፡ ያመልካቹ ፡ እናት ፡ ወይ/ዘውዲቱ ፡ ኃይሌ ፡ መምሬ ፡ ብርሃኑ ፡ ለተባሉት ፡ ቄስ ፡ ሚስት ፡ ሆነው ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ወልደው ፡ የሚኖሩ ፡ ሲሆኑ ፡ በልጆቹ ፡ መካከል ፡ አመልካችን ፡ ለይተው ፡ ያቶ ፡ ደምሴ ፡ ልጅ ፡ ብለው ፡ ሊያስመሰክሩ ፡ አይገባቸውም ፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ አባት ፡ መባል ፡ የሚገባቸው ፡ ቄሱ ፡ ናቸው ፤ በማለት ፡ ነው ።

ያመልካች ፡ ተከራካሪም ፡ መልስ ፡ ሲሰጡ ፡ ይህ ፡ ክርክር ፡ ሊቀርብ ፡ የሚገባው ፡ አባቱ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ልጁን ፡ ያልተቀበለው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ነበር ፤ ሟቹ ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ልጁ ፡ መሆኑን ፡ አውቆ ፡ ልጅነቱን ፡ ተቀብሎ ፡ ቀለብ ፡ እየሰጠ ፡ አሳድጎታል ። ያመልካች ፡ እናት ፡ በባሏ ፡ ላይ ፡ አመልካችን ፡ ካቶ ፡ ደምሴ ፡ ነጋሽ ፡ ስለአረገዘችው ፡ ባሏ ፡ የነበሩት ፡ ሰው ፡ ይህንኑ ፡ አውቀው ፡ በተነሣው ፡ ጠብ ፡ ምክንያት ፡ ከቤቷ ፡ አስወጥተዋት ፡ እወንድሟ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ የወለደችው ። ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ እቤቷ ፡ አልገባችም ። ሟቹም ፡ ይህንኑ ፡ አውቆ ፡ ልጁን ፡ ተቀብሎ ፡ አሳድጎታል ። በምስክር ፡ ለማስረዳትም ፡ የምፈልገው ፡ ይህንኑ ፡ ስለሆነ ፡ ምስክሮች ፡ እንዲሰሙ ፡ ይታዘዙልኝ ፤ በማለት ፡ ተከራክረዋል ።

ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ይጠቅሙናል ፡ የሚሏቸውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ እየጠቀሱ ፡ ከተከራከሩ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አመልካች ፡ ከመወለዱ ፡ በፊት ፡ ገና ፡ በእናቱ ፡ ማሕፀን ፡ እንዳለ ፡ የእናቱ ፡ ባል ፡ የነበረው ፡ ከሌላ ፡ የተረገዘ ፡ መሆኑን ፡ አውቆ ፡ እናቱን ፡ በእርግዝናዋ ፡ ከቤቷ ፡ አስወጥቷት ፡ ይህንን ፡ ልጅ ፡ የወለደች ፡ ከወንድሟ ፡ ቤት ፡ ለመሆኗ ፤ ሟቹ ፡ አቶ ፡ ደምሴ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ልጅነቱን ፡ ተቀብሎ ፡ ገንዘብ ፡ እየከፈለ ፡ ያሳደገው ፡ ለመሆኑ ፡ ማስረጃ ፡ የሚገኝ ፡ ከሆነ ፡ ይህንን ፡ አጣርቶ ፡ ማወቅ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ስለታየን ፡ ይመሰክሩልናል ፡ የሚሏቸው ፡ ሰዎች ፡ ቀርበው ፡ ይመስክሩ ፤ ብሎ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቷል ።

ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ምስክሮች ፡ እንዲሰሙ ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ነውና ፡ ትእዛዙ ፡ ይሻርልን ፤ ብለው ፡ ይህንን ፡ ይግባኝ ፡ ሲያቀርቡ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ትእዛዙ ፡ ሕጋዊ ፡ ነውና ፡ ይፀናል ፤ በማለት ፡ መልስ ፡ ሰጥተው ፡ ተከራክረዋል ።

እኛም ፡ መዝገባቸውንና ፡ ክርክራቸውን ፡ ከመረመርን ፡ በኋላ ፡ ያመልካቹ ፡ እናት ፡ ሕጋዊ ፡ ባል ፡ መምሬ ፡ ብርሃኑ ፡ የተባሉት ፡ አመልካች ፡ ልጄ ፡ አይደለም ፤ በማለት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሰው፡አስወግደው፡እንደሆነ ፡ ጠይቀን ፡ ነበረ ። ሚስታቸውን ፡ ከሰው ፡ ልጁን ፡ ለማስወገዳቸው ፡ መዝገብ ፡ አለኝ ፤ ብለው ፡ መዝገቡ ፡ ይገኝልኛል ፡ ላሉበት ፡ ለአዲስ ፡ አበባ ፡ ፫ኛ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከተጻፈ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገቡን ፡ ፈልጎ ፡ ያላገኘ ፡ መሆኑን ፡ አስታውቆናል ።

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፲፬ ፡ እንደተጻፈው ፡ በጋብቻው ፡ ጊዜ ፡ የተጸነሰው ፡ ወይም ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ አባቱ ፡ ያው ፡ የእናቱ ፡ ባል ፡ ነው ። በቍጥር ፡ ፯፻፫ ፡ እንደተመለከተውም ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡ አይደለም ፤ ብሎ ፡ የመካድ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ የልጅ ፡ አባት ፡ ነህ ፡ ተብሎ ፡ በሕጋውያን ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ የልጅ ፡ አባትነት ፡ የሚሰጠው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ እናቲቱ ፡ ወይም ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ባይ ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ልጁ ፡ ራሱ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ፤ ተብሎ ፡ ተጽፋል ።

ይህንንም ፡ ሕግ ፡ ስንመለከተው ፡ ፩ ፡ ሰው ፡ ሚስቱ ፡ በዝሙት ፡ ከሌላ ፡ ወንድ ፡ ብትወልድም ፡ ባልየው ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ ገልጾ ፡ መክሰሱ ፡ ክብሩን ፡ የሚነካበት ፡

ሆኖ ፡ ታይቶት ፤ ክብሩን ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲል ፡ በላዩ ፡ ከሌላ ፡ የተወለደውን ፡ ልጅ ፡ እንደራሱ ፡ ልጅ ፡ አድርጎ ፡ ቢቀበለው ፡ ወይም ፡ ይህንን ፡ ያልፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ ልጄ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ክሶ ፡ ከልጅነቱ ፡ ቢአስወግደው ፡ ራሱ ፡ አመዛዝኖ ፡ የሚአደርገው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የሱ ፡ ልጅ ፡ አይደለም ፤ ብሎ ፡ ለመክሰስ ፡ አይችልም ፡ ማለት ፡ ነው ። የአመልካች ፡ እናት ፡ ሕጋዊ ፡ ባል ፡ መምሬ ፡ ብርሃኑን ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ አመልካችን ፡ ልጄ ፡ አይደለም ፤ በማለት ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ያቀረቡት ፡ ክስ ፡ የለም ። እንዲሁም ፡ ሲሆን ፡ አባቱ ፡ ልጄ ፡ አይደለም ፡ ብለው ፡ ሳይከሱ ፡ አመልካቹ ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ተወልጃለሁ ፡ ብሎ ፡ መከራከሩ ፡ ከላይ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ በግልጽ ፡ ተቃራኒ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ አመልካች ፡ እናቱ ፡ በባሏ ፡ ላይ ፡ ከሚቴ ፡ ካቶ ፡ ደምሴ ፡ እኔን ፡ ለመውለዷ ፡ በምስክር ፡ ላስረዳ ፤ የሚሉትን ፡ ሕግ ፡ ስለማይቀበለው ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምስክሮች ፡ እንዲሰሙ ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ሽረን ፤ በዚህ ፡ ነገር ፡ አመልካች ፡ ምስክር ፡ ሊያሰሙ ፡ አይገባም ፡ ብለን ፡ ወስነናል ። ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ለይግባኝ ፡ የከፈሉትን ፡ የዳኝነት ፡ በደረሰኝ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ይክፈሉ ፤ ኪሣራ ፡ በየራሳቸው ፡ ይቻቻሉ ። እንደውሳኔው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ግልባጭ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይተላለፍ ።

ኅዳር ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ።

SUPREME IMPERIAL COURT

Div. No. 4

Justices:

Vice Afenegus Tebebu Beyene

Ato Woldehana Gebre Kidan

Ato Kabteh Yimer Afrasie

GEBRE JEMANEH and JEMANESH BELEHU v. TAREKEGN

Civil Appeal No. 638/57

Family law — Filiation — Presumption of Paternity — Institution of action to disown — Civil Code Arts, 741, 790.

On appeal from the order of the High Court allowing the respondent to introduce witnesses to prove the fact that the respondent is the child of a deceased despite the fact that the paternity of the respondent is attributed by law to another person, the lawful husband of the respondent's mother at the time of his birth.

Held: High Court order reversed.

1. A child born in a lawful marriage may not institute proceedings to contest the status of the person to whom his paternity is attributed by law and introduce witnesses to prove the fact that he is the child of another person with whom his mother had relations during the marriage.

Appellants opened a probate file No. 12/56 with the High Court requesting that they be declared as the heirs to the succession of their brother, the deceased, who died on Nehassie 2, 1955 without leaving any descendants and whose only nearest relatives in the line entitled to the succession were the appellants.

The respondent appeared as the son of the deceased through his guardian, and the wife of the deceased appeared as such. Considering the contention of both sides, the High Court ordered respondent to open a separate probate file, and accordingly his guardian opened probate file No. 164/56. The present appellants had denied the contention of respondent.

The guardian applied to the court to produce witnesses to ascertain that respondent is the son of the deceased. The appellants objected to the hearing of any witness on such issue, their reason being that the mother of the respondent was married to a man from whom she had many children, and that she could not bring witness to prove that only one of them is the son of the deceased, who was not her husband; according to the Civil Code her husband the priest should be the father of the respondent.

The guardian of the respondent stated in reply that the argument of the appellants would have been appropriate if the deceased had not recognized his child while he was alive. But in this case the deceased recognizing and accepting the respondent as his child had looked after him and supported him in every respect.

It is true that the respondent was conceived while his mother was with her lawful husband. But as the result of this the mother of the respondent was separated from her lawful husband and the respondent was born at his uncle's house. After that also she never returned to her husband's home. The deceased knowing all this had accepted his son and it was under his responsibility that the respondent was brought up.

The respondent applied to the High Court to be allowed to submit witnesses to ascertain all these facts.

After both sides argued on the basis of the Civil Code provisions they thought relevant to their contentions, the High Court found it necessary to ascertain whether, during the pregnancy period the lawful husband of the mother of the present respondent knew that the child was conceived from another man and as the result, separated from her while she was still pregnant, whether the baby was born at her brother's house and whether the deceased recognizing the respondent as his son brought him up by maintaining him, and therefore ordered that witnesses be heard.

This appeal was brought on the contention that such order allowing to hear witnesses was illegal and that it be reversed; while the respondents insist that the order given by the High Court was legal.

This Court in the process of examining the arguments and evidence on each side asked the respondent whether the lawful husband of his mother had brought an action in a court in connection with the fact that the respondent was not his son, and the respondent answered that such action was brought with the Addis Ababa Woreda Court, No. 3. Accordingly this court wrote to the Woreda Court to have the file, to which the court answered that it could not find any such file in spite of its thorough search.

According to Art. 741 of the Civil Code, the father of any child conceived during married life is the lawful husband of the mother at the time. According to Art. 790, the one who is entitled to institute an action to disown a child is the one to whom paternity of the child is attributed by law. It is clearly expressed that neither the mother, nor the man who claims the paternity, nor the public prosecutor can apply to institute such action.

The effect of this provision is that even if a child is born between two persons not bound by lawful wedlock but the mother is already legally married and the lawful husband of the mother knows the facts of the birth, the choice of whether to bring an action to disown the child, declaring it to be illegitimate or to disregard such a proceeding for the reason of keeping the integrity and honour of his family intact, depends solely on the lawful husband's own discretion.

Up to this day the lawful husband of the respondent's mother has not instituted any action to disown the respondent under Article 790 of the Civil Code. Therefore in the absence of such action brought by the lawful husband, the one to whom paternity of the child is atributed by law, the action by which the son is proceeding to disown his lawful father is in contradiction to the above cited provisions.

Therefore the order given by the High Court to hear witnesses on this issue is illegal and we consequently reverse the order.

The court fees paid by the appellants should be refunded to them on the basis of their receipts, and other damages resulting from the suit be shared equally between the parties on each side.

The copy of this judgment should be sent to the High Court for execution as decided.

Hidar 2, 1958 E.C.

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤
አራተኛ ፡ ችሎት ።

ዳኞች ፤

ም/አፈንጉሥ ፡ ጥበቡ ፡ በየነ ፤

አቶ ፡ ወልደሐና ፡ ገብረ ፡ ኪዳን ፤

ብላታ ፡ ደምሴ ፡ ወርቅ ፡ አገኘሁ ።

አ- ቤስ ፡ ኩባንያ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሊሚትድ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤

፩ኛ/ አቶ ፡ ሰሎሞን ፡ ግደይ ፤

፪ኛ/ አቶ ፡ አብርሃ ፡ መኰንን ፤ መልስ ፡ ሰጭዎች ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፯፻፸፫/፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ።

የንግድ ፡ ሕግ ፡ — ስለ ፡ ቼክ ፡ — የአውጪው ፡ ኃላፊነት ፡ — የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፰፻፵፱ ፡ እና ፡ ፰፻፵፯ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ — የውል ፡ ግዴታዎች ፡ — ማስረጃ ፡ የማቅረብ ፡ ግዴታ ፡ — የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪ሺ፩ ፡ እና ፡ ፪ሺ፲፱ ፡ (፩) ።

ይግባኝ ፡ ባይ ፡ አንደኛው ፡ መልስ ፡ ሰጪ ፡ በሁለተኛው ፡ መልስ ፡ ሰጪ ፡ አማካይነት ፡ ፩፻ ፡ ሳጥን ፡ ባትሪዎች ፡ ስለገዛኝ ፡ ዋጋውን ፡ ሁለቱም ፡ እንዲከፍሉኝ ፡ ይደረግልኝ ፡ ሲል ፡ ያቀረበውን ፡ ክስ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስላልተቀበለው ፡ ውሳኔውን ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ይግባኝ ።

ውሳኔ ፤ ስለ ፡ ፩ኛው ፡ መልስ ፡ ሰጪ ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ተገልብጦ ፡ ስለሁለተኛው ፡ መልስ ፡ ሰጪ ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ጸንቷል ።

፩/ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፰፻፵፯ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቼክ ፡ ፈርሞ ፡ ለሌላ ፡ ከሰጠ ፡ ለአከፋፈሉ ፡ ዋስ ፡ ይሆናል ፤ ይህ ፡ ዋስትና ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ፈራሽ ፡ አይሆንም ፤ ተብሎ ፡ መተርጐም ፡ አለበት።

፪/ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪ሺ፩ ፡ (፩) ፡ እና ፡ ፪ሺ፲፱ ፡ (፩) ፡ ስር ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ መኖሩን ፡ ለማረጋገጥ ፡ አንድ ፡ የተፈረመበት ፡ ቼክ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ሆኖ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

፫/ አንድ ፡ ሰው ፡ እቃ ፡ ሲገዛ ፡ ዋጋውን ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ጽኑ ፡ በሆነ ፡ ቼክ ፡ ከከፈለ ፡ እቃው ፡ ለማን ፡ እንደተሰጠ ፡ ለማስታወስ ፡ በማይቻልበት ፡ እና ፡ የቼኩ ፡ መከፈያ ፡ ጊዜ ፡ ደርሶ ፡ ክስ ፡ እቀረበበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ከቆየ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የገዛሁት ፡ እቃ ፡ አልደረሰኝም ፡ ብሎ ፡ በመከራከር ፡ ቼኩን ፡ ለመሰረዝ ፡ አይችልም ።

ፍርድ ።

፩ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ በ፪ኛው ፡ ተከሳሽ ፡ አማካይነት ፡ ባትሪ ፡ ይገዙን ፡ ስለነበር ፡ እ-ኤ-አ- በአፕሪል ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ፩፻ ፡ ሳጥን ፡ ባትሪዎች ፡ ገዝተው ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፩፻፯ ፡ የሆነውን ፡ ፋክቱር ፡ ፈርመው ፡ በቼክ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፸፱ሺ፬፻፲፪ ፡ ገንዘቡን ፡ ከፍለዋል ፤ ቼኩን ፡ የጻፉና ፡ ያመጡት ፡ ባትሪዎቹንም ፡ ለ፩ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ የወሰዱላቸው ፡ ፪ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ናቸው ። ቼኩ ፡ የተጻፈው ፡ እ-ኤ-አ- ሜይ፡፳፩/፷፪ ፡ ዓ፡ ም ፡ ሲሆን ፡

ለባንክ ፡ ብናቀርበው ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ የለም ፡ ስለተባለ ፡ ገንዘባችን ፡ ማለትም ፡ ፯ሺ ፱፻ ፡ ብር ፡ ሳይከፈለን ፡ ቀርቷል ።

ተከሳሾቹ ፡ ባንድነትና ፡ በነጠላነት ፡ ገንዘቡን ፡ እንዲከፍሉ ፡ ይደረግልን ፡ ብለው ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በመልስ ፡ ሰጭዎቹ ፡ ላይ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቍጥር ፡ ፲፱፻፷፩/፺፫ ፡ ክስ ፡ አቅርበዋል ።

፩ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ቼኩን ፡ ፈርሜአለሁ ፡ የተረከብኩት ፡ ባትሪ ፡ የለም ፤ ቍጥር ፡ ፩ሺ፩፻፯ ፡ የሆነውን ፡ ፋክቱር ፡ አልፈረምኩም ፤ ላልተረከብኩት ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ አይገባኝም ፤ ብለው ፡ መከላከያቸውን ፡ አቅርበዋል ።

፪ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ "ለከሳሽ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ አሻሻጭ ፡ ሆኜ ፡ ተቀጥሬአለሁ ፤ ባትሪዎቹን ፡ ፩ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ወስደዋል ፡ የተባለው ፡ እውነት ፡ አይደለም ፤ ቼኩንና ፡ ፋክቱሩን ፡ የጻፍኩ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ እኔ ፡ አስረካቢ ፡ አይደለሁም ፤ ኃላፊነትም ፡ የለብኝም" ፤ በማለት ፡ መከላከያቸውን ፡ አቅርበዋል ።

ከሳሹ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃዎቻቸውን ፡ ካቀረቡና ፡ ምስክሮቻቸውንም ፡ ካስመሰከሩ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሁለት ፡ ተከሳሾች ፡ አንድነት ፡ ተጣምረው ፡ የተከሰሱበት ፡ በማይገባ ፡ ነው ፤ ብሎ ፡ አትቶ ፡ ቼክ ፡ የፈረመ ፡ ሰው ፡ ቼኩ ፡ እንዲከፈል ፡ ላዘዘለት ፡ ሰው ፡ ባለዕዳ ፡ መሆኑ ፡ ቢታወቅም ፡ ቼክ ፡ የፈረመው ፡ ሰው ፡ እንዲከፍል ፡ በሚከሰስበት ፡ ጊዜ ፡ መክፈል ፡ አይገባኝም ፡ ሲል ፡ ካዘዘለት ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ በማንሳት ፡ ሊከላከል ፡ ይችላል ። ይኸውም ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፳፻፶ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጧል ። አቶ ፡ ሰሎሞን ፡ ግደይ ፡ ቼክ ፡ መፈረማቸውን ፡ ቢያምኑም ፡ ከከሳሽ ፡ ጋር ፡ የፈጸሙትን ፡ ውል ፡ ከሳሽ ፡ የተሸጠውን ፡ ዕቃ ፡ ባለማስረከብ ፡ ሳይፈጽም ፡ ስለቀረ ፡ መክፈል ፡ አይገባኝም ፡ ያሉት ፡ በሚገባ ፡ ነው ፤ የቼኩ ፡ መፈረም ፡ ለዕቃው ፡ ማስረከብ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ አይደለም ።

ከዕቃው ፡ ደረሰኝ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ፊርማ ፡ አቶ ፡ ሰሎሞን ፡ የእኔ ፡ አይደለም ፡ ብለዋል ። ከሳሽ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪ሺ፳ ፡ መሠረት ፡ የተካደው ፡ ፊርማ ፡ እንዲመረመር ፡ ማድረግ ፡ ይገባው ፡ ነበር ፤ ይህንንም ፡ ፈጽሞ ፡ ስላልተገኘ ፡ ፩ኛና ፡ ፪ኛ ፡ ማስረጃዎች ፡ በአቶ ፡ ሰሎሞን ፡ ላይ ፡ አይጸኑባቸውም ። አቶ ፡ አብርሃም ፡ መኰንንም ፡ ቼኩንና ፡ ፩ኛ ፡ የከሳሽን ፡ ማስረጃ ፡ መጻፋቸው ፡ ቢታመንም ፡ የተሸጠውን ፡ ባትሪ ፡ መረከባቸውን ፡ የሚያሳይ ፡ ማስረጃ ፡ የለምና ፡ ሁለቱም ፡ ተከሳሾች ፡ የተከሰሱበትን ፡ ገንዘብ ፡ ሊከፍሉ ፡ አይገባቸውም ፡ በማለት ፡ ፍርድ ፡ ሰጥቷል ።

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ በማይገባ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ይህንን ፡ ይግባኝ ፡ አቅርበዋል ። በይግባኝ ፡ ማመልከቻቸውም ፡ ያቀረቡት ፡ ባጭሩ ፡ ፪ኛ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ በይግባኝ ፡ ባይ ፡ ኩባንያ ፡ ውስጥ ፡ የዕቃ ፡ ሺያጭና ፡ የማስረከቢያ ፡ ክፍል ፡ ኃላፊ ፡ ነበሩ ፤ ክርክር ፡ የተነሣባቸውን ፡ ባትሪዎች ፡ ለ፩ኛው ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ለማስረከብ ፡ ሲሉ ፡ በኩባንያው ፡ ካሚዮን ፡ ጭነው ፡ ካሚዮኑን ፡ ራሳቸው ፡ እየነዱ ፡ መውሰዳቸው ፡ ተመስክሯል ።

፩ኛ ፡ መልስ ፡ ሰጭም ፡ ሸቀጡን ፡ ተረክበው ፡ ወደፊት ፡ የሚከፈል ፡ ቼክ ፡ ፈርመው ፡ ሰጥተዋል ። ዕቃውን ፡ ያልተረከቡ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ቼክ ፡ ባልሰጡም ፡ ነበር ። ቼኩንም ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ ሸቀጡ ፡ አልደረሰኝም ፡ የሚል ፡ መቃወሚያ ፡ ለይግባኝ ፡ ባይ ፡ አላቀረቡም ። ዕቃውን ፡ ባይረከቡ ፡ ኖሮ ፡ ቼኩ ፡ ይመለስልኝ ፡ ብለው ፡ ይጠ

ይቁ ፡ ነበር ። ገንዘብ ፡ የለም ፡ በመባል ፡ ቼኩ ፡ ከባንክ ፡ ከተመለሰና ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ክስ ፡ ካቀረብኩ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ ዕቃው ፡ አልደረሰኝም ፡ያሉት ። ፪ኛውን ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ አብሬ ፡ የከሰስኩት ፡ ዕቃው ፡ ላንደኛው ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ደርሷል ፤ ስላሉ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ከሁለቱ ፡ አንዱ ፡ ክስ ፡ ያቀረብኩበትን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍሉ ፡ ፍርድ፡ ይሰጠኝ ፡ የሚል ፡ ነው ።

፪ቱ ፡ መልስ ፡ ሰጭዎችም ፡ በከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ ባቀረቡት ፡ መከላከያ ፡ መሠረት ፡ ለየራሳቸው ፡ ጽፈው ፡ ባገባቡ ፡ የተሰጠ ፡ ፍርድ ፡ ስለሆነ ፡ ይጸናል ፤ በማለት ፡ በጽሑፍ ፡ በቃልም ፡ ተከራክረዋል ።

እኛም ፡ የግራ ፡ ቀኙን ፡ ክርክርና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ በጥንቃቄ ፡ መርምረናል ። ፍ/ቤቱ ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ የጠቀሰው ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፰፻፶፱ ፡ "አምጪው ፡ ቼኩን ፡ ሲያገኝ ፡ አውቆ ፡ ባለዕዳውን ፡ ለመጉዳት ፡ ካላደረገ ፡ በቀር ፡ በቼኩ ፡ መሠረት ፡ የተከሰሱት ፡ ሰዎች ፡ ከአውጪው ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ በፊት ፡ አምጪ፡ ከሆኑት ፡ ጋር ፡ በግል ፡ ግንኙነታቸው ፡ ላይ ፡ በተመሠረቱት ፡ ልዩነቶች ፡ አምጪውን ፡ ሊቃወሙት ፡ አይችሉም" ይላል ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ይህንን ፡ የጠቀሰው ፡ ቼኩ ፡ ወደ ፡ ፫ኛ ፡ ሰው ፡ ካልዞረና ፡ መጀመሪያ ፡ በተቀበለው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ከሆነ ፡ ቼኩን ፡ የጻፈው ፡ ሰው ፡ ያለውን ፡ መከላከያ ፡ ከማቅረብና ፡ ከመቃወም ፡ አይከለከልም ፡ ለማለት ፡ ነው ። ፩ኛ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ቼኩን ፡ የሚቃወሙበት ፡ መከላከያ ፡ ካላቸው ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ መቃወሚያው ፡ አይቀርብብኝም ፡ በማለት ፡ አልተከራከሩም ። በ፩ኛ ፡ መልስ ፡ ሰጭና ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አስተያየት ፡ ቼኩን ፡ የጻፈው ፡ ሰው ፡ ቼኩን ፡ የጻፍኩት ፡ ገንዘብ ፡ ሳልቀበል ፡ ስለሆነ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፡ ብሎ ፡ መናገሩ ፡ ብቻ ፡ ቼኩን ፡ ዋጋ ፡ ለመስጠት ፡ በቂ ፡ መከላከያ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ያልንበት ፡ ምክንያት ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ዕቃው ፡ ያልደረሳቸው ፡ ለመሆናቸው ፡ ቼኩንም ፡ የፈረሙት ፡ በመታለል ፡ ወይም ፡ ይህንን ፡ በመሰለ ፡ ነገር ፡ ለመሆኑ ፡ ምንም ፡ ያስረዱት ፡ ነገር ፡ ስለሌለ ፡ ነው ።

በዚሁ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፰፻፶፬ ፡ "አውጪው ፡ ላከፋፈሉ ፡ ዋስ ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡ ዋስትና ፡ ኃላፊነት ፡ ለመዳን ፡ የሚጻፈው ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ እንዳልተጻፈ ፡ ይቆጠራል" ፡ ይላል ።

ይህም ፡ የሚያሳየው ፡ ቼኩን ፡ ጽፎ ፡ ፈርሞ ፡ የሰጠ ፡ ሰው ፡ በቼኩ ፡ ለተጻፈው ፡ ገንዘብ ፡ ኃላፊነት ፡ ስላለበት ፡ ይህ ፡ ኃላፊነት ፡ በጥቃቅን ፡ ምክንያት ፡ ሊፈርስ ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ሲሆን ፡ አውጭው ፡ ቼኩን ፡ ከጻፈ ፡ በኋላ ፡ የሚያሰርዝበት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያጋጠመው ፡ እንደሆነ ፡ ወዲያው ፡ ተከታትሎ ፡ በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ፡ እንጂ ፡ መከፈያው ፡ በሚደርስበት ፡ ቀን ፡ ልከፍለው ፡ የማይገባኝ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በመናገር ፡ ብቻ ፡ ኃላፊነቱ ፡ ሊወገድለት ፡ አይችልም ፡ ማለት ፡ ነው ።

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፩ ፡ "(፩) አንድ ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ የሚጠይቅ ፡ ሰው ፡ ለግዴታው ፡ መኖር ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ። (፪) እንዲሁም፡ ግዴታው ፡ ፍርስ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ተለውጧል ፡ ወይም ፡ ቀርቷል ፡ የሚለው ፡ ወገን ፡ ይህንኑ ፡ ግዴታ ፡ ያፈረሰውን ፡ የለወጠውን ፡ ወይም ፡ ያስቀረውን ፡ ተግባር ፡ ማስረዳት ፡ አለበት" ፤ ይላል ።

እንዲሁም ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፲፱ ፡ "(፩) አንድ ፡ ሰው፡ አንድ ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል፡ ቃል ፡ የሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ባለዕዳ ፡ መሆኑንም ፡ ያመነ ፡ እንደሆነ ፡ እከፍልሀለሁ ፡ የተባለው ፡ ወይም ፡ ዕዳው ፡ የታመነለት ፡ ሰው ፡ የዚህን ፡ ምክንያት ፡ ማረጋ

ገጥ ፡ አለበት ። (፪) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በሚገባ ፡ የተሰጠ ፡ ቃል ፡ እንዳለ ፡ ይቆጠራል ። (፫) የግዴታው ፡ ምክንያት ፡ ስለመደበቁ ፡ ማስ ረጃ ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ ይህንኑ ፡ ማስረዳት፡ያለበት ፡ ለግዴታው ፡ ሌላ ፡ ሕጋዊ ፡ ምክንያት ፡ አለ ፡ የሚለው ፡ ሰው ፡ ነው ።" ይላል ።

በነዚህ ፡ በሁለት ፡ ቁጥሮች ፡ መሠረት ፡ ይህንን ፡ የቀረበልንን ፡ ክርክር ፡ የመረ መርን ፡ እንደሆነ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የከሰሱበት ፡ ገንዘብ ፡ በመልስ ፡ ሰጭው ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ በመሆኑ ፡ ሰጪው ፡ በፈረሙት ፡ ቼክ ፡ አስረድተዋል ። ቼኩና ፡ ፊር ማው ፡ የራሳቸው ፡ መሆኑንም ፡ ፩ኛ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ሲያምኑ ፡ ይህ ፡ ቼክ ፡ ዋጋ ቢስ ፡ የሚሆንበትን ፡ አፍራሽ ፡ ማስረጃ ፡ አላቀረቡም ።

መልስ ፡ ሰጭው ፡ ያቀረቡት ፡ ምክንያት ፡ "ዕቃው ፡ አልደረሰኝም፡" ብቻ ፡ ነው ። እውነት ፡ እንደሚሉት ፡ ዕቃው ፡ ካልደረሳቸው ፡ ቼኩን ፡ እንደፈረሙ ፡ ወዲያው፡ ዕቃው ፡ አልደረሰኝም ፡ ብለው ፡ በሁለት ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ለምን ፡ አይቃወሙም፡ ነበር ? ቼኩን ፡ ጽፈው ፡ የሰጡት ፡ በኤፕሪል ፡ ፲፫/፹፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሲሆን ፡ የቼኩ ፡ መከፈያ፡ ሜይ ፡ ፳፰/፹፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነበር ። የመክፈያው ፡ ቀን ፡ ደርሶ ፡ ቼኩ ፡ ለባንክ ፡ ቀርቦ ፡ ገንዘብ ፡ የሌላቸው ፡ መሆኑ ፡ ተመልክቶበት ፡ ከተመለሰና ፡ ክስ ፡ እቀረበባቸው ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ዕቃው ፡ አልደረሰኝምና ፡ ቼኩ ፡ ይሠረዝልኝ ፡ የሚል ፡ መቃወሚያ ፡ አላቀረቡም ።

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ባትሪው ፡ ከዕቃው ፡ ግምጃ ፡ ቤታቸው ፡ ወጥቶ ፡ የተሰጠ ፡ ለመ ሆኑ ፡ የዕቃ ፡ ደረሰኙን ፡ አቅርበው ፡ አስረድተዋል ።

መልስ ፡ ሰጭው ፡ በዕቃው ፡ ደረሰኝ ፡ ላይ ፡ የተፈረመው ፡ ፊርማ ፡ የኔ ፡ አይደ ለም ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚቃወሙት ። ዕቃ ፡ አስረካቢዎች ፡ እተረካቢው ፡ ነጋዴ ፡ ሱቅ ፡ ወስደው ፡ ቢገኙ ፡ እራሱ ፡ ባይገኝ ፡ ለተገኘው ፡ ሰው ፡ አስረክቦ ፡ መመ ለስ ፡ የተለመደ ፡ በመሆኑ ፡ ምናልባት ፡ ከሱቅ ፡ የተገኘው ፡ ሰው ፡ በ፩ኛው ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ስም ፡ ፊርሞ ፡ እንደሆነ ፡ ይህንን ፡ ለማጣራትና ፡ ማን ፡ እንደተረከበው ፡ ለማ ወቅ ፡ የሚቻለው ፡ ፩ኛ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ሳይዘገይ ፡ ወዲያው ፡ ዕቃው ፡ አልደረሰኝም ብለው ፡ ቢያስታውቁ ፡ ነበር ። የቼኩ ፡ መክፈያ ፡ ጊዜ ፡ እስኪደርስ ፡ ከዚያም ፡ እስኪከ ሰሱ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆይተው ፡ የርክክቡ ፡ ሁኔታ ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ እንደተፈጸመ ፡ ለማስታወስ ፡ በተዘነጋበት ፡ ጊዜ ፡ ዕቃው ፡ አልደረሰኝም ፡ ብሎ ፡ በመናገር ፡ ብቻ ፡ ሕጋዊው ፡ ቼክ ፡ ዋጋ ፡ ሊያጣ ፡ ይገባዋል ፡ ማለት ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ ሕሊና ፡ ሊቀበለው ፡ የሚችል ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ይህን ፡ በመሳሰሉ ፡ ጥቃቅን ፡ ምክንያቶች ፡ ቼክ ፡ ዋጋ ፡ የሚያጣ ፡ ከሆነና ፡ የንግድ ፡ ሥራም ፡ የሚታወክ ፡ ከሆነ ፡ ጉዳቱ ፡ ለነጋዴዎች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሃገሪቱንም ፡ ኤኮኖሚ ፡ ጭምር ፡ የሚነካ ፡ ነው ።

አንድ ፡ ሰው ፡ እሱቅ ፡ ሄዶ ፡ የሚፈልገውን ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ገዝቶ ፡ ዋጋውን ፡ በቼክ ፡ ከፍሎ ፡ ይሄዳል ። ቼኩ ፡ ለባንክ ፡ ቀርቦ ፡ ገንዘብ ፡ ባለመኖሩ ፡ ሳይከፈል ፡ ቀርቶ ፡ ባለሱቁ ፡ ገንዘቡን ፡ እንዲያገኝ ፡ በሚጠይቅበት ፡ ጊዜ ፡ ባለዕዳው ፡ ዕቃው ፡ ሳይደርሰኝ ፡ ነበር ፡ የፈረምኩት ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ቼኩን ፡ ዋጋ ፡ የሚያሳጣው ፡ ከሆነ ፡ ነጋዴዎች ፡ በየቀኑ ፡ ከሱቃቸው ፡ ለተሸጡ፡ዕቃዎች፡ ምስክሮች፡ እያስቀመጡ ፡ ሊሸጡ ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሸቀጥ ፡ ሲፈራረሙ ፡ ሊኖሩ ፡ ነው? ይህ ፡ ሊደረግ ፡ ይገባል ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ ቢኖር ፡ ከዘመናዊው ፡ የንግድ ፡ አካሄድ ፡ ውጭ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ዘመናዊው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ በተፋጠነ ፡ ሁኔታ ፡ የሚካሄድ ፡ ነው ። የንግድ ፡ ሥራን ፡ የሚጐትተውንና ፡ የሚያሰናክለውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መቀበል ፡ አይቻልም ። አንድ ፡ ሰው ፡ የሚከፍልበት ፡ ግዴታ ፡ ሳይኖርበት ፡ ቼክ ፡ ጽፎና ፡ ፊርሞ ፡ ለመስጠት ፡ የሚአስገድደው ፡ የለም ።

እሱ ፡ የሌለበትን ፡ አለብኝ ፡ ብሎ ፡ ሳይገደድ ፡ በፈቃድ ፡ ጽፎ ፡ ከሰጠ ፡ በራሱ ፡ ሊያማርር ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ ፡ በማንም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሊያዝን ፡ አይገባውም ።

ስለዚህ ፡ ፭ኛ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ፪ሺ፱፻ ፡ ብር ፡ ያለባቸው ፡ መሆኑን ፡ አውቀው ፡ ቼክ ፡ ፈርመው ፡ ሰጥተው ፡ የመክፈያውም ፡ ጊዜ ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ሲሆን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ዕቃው ፡ አልደረሰኝም ፡ ብለው ፡ ሳይቃወሙ ፡ ከመቆየታቸው ፡ በላይ ፡ አሁንም ፡ ክስ ፡ ከቀረበባቸው ፡ በኋላ ፡ ሳይደርሰኝ ፡ ነው ፡ የፈረምኩት ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ዕቃው ፡ ያልደረሳቸው ፡ ለመሆኑ ፡ ወይም ፡ ሳይደርሳቸው ፡ ለመፈረም፡ የተገደዱበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚአሳይ ፡ አንዳች ፡ ማስረጃ ፡ ስለአላቀረቡ ፤ ዕቃውም ፡ ከይግባኝ ፡ ባይ ፡ መጋዘን ፡ ወጪ ፡ ለመሆኑ ፡ ማስረጃ ፡ ቀርቦ ፡ ሳለ ፡ የዕቃውን ፡ ዋጋ ፡ አጥተው ፡ ሊቀሩ ፡ ስለማይገባ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክሱ ፡ ውድቅ ፡ እንዲሆን ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ለውጠን ፡ ፭ኛ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ የተከሰሱበትን ፡ ሰባት ፡ ሺህ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ብርና ፡ ወለድ ፡ ፋይሉ ፡ ከተከፈተበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ተከፍሎ ፡ እስኪ ፡ ድረስ ፡ ባመት ፡ በመቶ ፡ ዘጠኝ ፡ ሂሣብ ፡ ኪሣራ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለይግባኝ ፡ ባይ ፡ እንዲከፍሉ ፡ ፈርደናል ። ፪ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ አይጠየቁም ፡ በማለት ፡ የከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ግን ፡ በከፊል ፡ አጽንተናል ። እንደ ፡ ፍርዱ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ የፍርዱ ፡ ግልባጭ ፡ ለከፍተኛ ፡ ፍ/ቤት ፡ ይተላለፍ ።

ጥር ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ።

SUPREME IMPERIAL COURT

Div. No. 4

Justices:

Vice Afenegus Tebebu Beyene

Ato Woldehana Gebre Kidan

Blata Demessie Work Agegnehu

A. BESSE ETH. LTD. v. SOLOMON GIDEY and ABRAHAM MEKONEN

Civil Appeal No. 1673/57

Commercial Code — Cheques — Responsibility of the drawer — Arts. 840, 850, *Comm. C.*

Civil Code — Contractual obligations — Burden of proof — Arts. 2001, 2019*(1), Civ. C.*

On appeal from a decision of the High Court rejecting the appellant's request that the Court order the defendants to pay the price of 100 boxes of batteries which defendant No. 1 bought from appellant through defendant No. 2.

Held: Decision reversed with respect to the 1st respondent and affirmed with respect to the 2nd respondent.

1. Art. 840, Comm. C. implies that once a person has signed and given a cheque to another he guarantees its payment. This guarantee cannot be cancelled except for sufficient reason.

2. Producing a signed cheque is sufficient proof of the existence of an obligation for purposes of Arts. 2001(1) and 2019(1), Civ. C.

3. A legally valid cheque may not be cancelled just because the person who gave the cheque in payment for goods he bought, contends that he did not receive the goods at a time when it cannot be remembered how delivery was made, having kept silent until the time when the cheque was payable and suit was filed against him.

The appellant pleaded that, "Defendant No. 1 customarily bought batteries from us through defendant No. 2. On April 13, 1962, defendant No. 1 bought 100 boxes of batteries from us, signed a receipt No. 1107 and paid the price by a cheque bearing the number 169412. The cheque was written and brought to us and the batteries were taken to defendant No. 1 by defendant No. 2. The cheque bears the date Miazia 25/62. When we presented it to the bank, we were told there was not enough money. We are thus not paid the price of the batteries, which is $7,900."

The appellant filed suit, civil case File No. 631/55, in the High Court requesting that the court order the defendants to pay the price of the batteries jointly and singly.

In his statement of defense, defendant No. 1 pleaded, "I have signed the cheque but I did not receive any batteries. I did not sign the receipt numbered 1107. I do not have to pay the price of goods that I did not receive.."

Defendant No. 2, in his statement of defence, pleaded, "I am a salesman of the office of defendant No. 1. It is not true that defendant No. 1 took batteries.

I wrote the cheque and the receipt. My duty is not to deliver and I do not have responsibility" (responsibility for the delivery).

After the plaintiff produced his documentary and oral evidence, the lower Court concluded that the defendants were sued improperly. "Although it is known that a person is indebted to another for whom he has signed a cheque, when he is sued to pay, he has the legal right, as is pointed out in Art. 850 of the Commercial Code, to defend that he does not have to pay by invoking his existing relationship with the person for whom he signed the cheque. Although Ato Solomon (defendant No. 1) has admitted that he signed the cheque, his pleading that since the plaintiff did not, according to the contract, deliver the goods he sold, Ato Solomon does not have to pay, is a proper defence. The signing of a cheque is not sufficient evidence for the delivery of the goods.

"Ato Solomon has denied the signature on the receipt of the goods. The plaintiff should have asked the Court to order verification of the signature as is provided in Art. 2008 of the Civil Code. But since the plaintiff failed to do this, the first and second pieces of evidence will not be binding on Ato Solomon. Even though it is admitted that Ato Makonnen wrote the cheque and plaintiff's first piece of evidence, since there is no evidence to show that the batteries were delivered to him, defendants do not have to pay the price of the batteries."

The appellant has appealed against the judgment of the High Court. In his memorandum of appeal, the appellant in short stated "that evidence has been introduced to show that respondent No. 2 was in charge of the appellant's sales and delivery section. He had loaded the batteries in dispute in a lorry which was driven by him to deliver them to respondent No. 1.

"Respondent No. 1 received the batteries, signed a cheque cashable in the future and gave it to respondent No. 2. Had not the goods been delivered to him, there was no need for him to sign the cheque. After he gave the cheque he did not notify the appellant that he did not receive the goods. If respondent No. 1 had not received the goods, he would have asked that his cheque be returned to him. It was after the appellant failed to cash the cheque and filed suit that respondent No. 1 said that he did not receive the goods. It was because respondent No. 2 stated that the goods were delivered to respondent No. 1 that I sued them together. Therefore, I request that the Court order that one of the two pay me the amount I claimed."

The two respondents in their reply stated that since the judgment of the High Court is proper, it should be affirmed. They gave oral arguments to support their reply.

We have examined carefully the arguments of both sides and the judgment of the High Court. Article 850 of the Commercial Code which was cited by the High Court to show that so long as the cheque is in the hands of the person who first received it, the person who wrote the cheque can present defense and objections against its being cashed reads, "Persons sued on a cheque cannot set up against the holder defenses founded on their personal relations with the drawer or with previous holders, unless the holder in acquiring the cheque has knowingly acted to the detriment of the debtor." Appellant did not object to respondent No. 1's defense against the cashing of the cheque. According to the opinion of the High Court and respondent No. 1, it is a sufficient defense if the person who wrote the cheque states that the cheque has no value since the respondent wrote

it when he did not accept the goods. We say this because the respondent did not produce evidence to show that he had not received the goods and had signed the cheque because of fraud or something of that sort.

Art. 840 of the Commercial Code states, "The drawer guarantees payment. Any provision by which the drawer releases himself from this guarantee shall be of no effect."

What this article shows is that once a person has signed and given a cheque to another he guarantees its payment and this guarantee cannot be cancelled because of petty reasons. In a case like this, if the drawer finds sufficient reason to "cancel" the cheque, he must do it then through the appropriate channels. Failing this, a person cannot, at the time of the payment avoid his liability by stating that he does not have to pay the money.

Art. 2001 of the Civil Code states, "(1) He who demands performance of an obligation shall prove its existence. (2) He who alleges that an obligation is void, has been varied or is extinguished shall prove the facts causing such nullity, variation or extinction."

So also Art. 2019(1) of the Civil Code states, "Where a person has promised to make a payment or acknowledged a debt, the person in whose favour the promise was made or the debt acknowledged need not prove a cause justifying them."

Examination of the case in light of these articles shows that the appellant has satisfied his burden of proof by producing the cheque signed by respondent No. 1. That respondent admitted that the cheque and the signature on it are his. But he did not produce any evidence to show that the cheque is without validity.

The only defense produced by respondent No. 1 is that he did not receive the goods. If, as he contends, he had not received the goods, why did he not then in two or three days time say so? He wrote and gave the cheque on April 13, 1962. The cheque was payable on April 25, 1962. He was silent about the transaction until the appellant tried to cash the cheque without success and filed suit against the two respondents.

In order to prove that the goods have been delivered to the respondent, the appellant has produced the receipt.

The respondent objects on the ground that the signature on the receipt is not his. Since it is customary that people who deliver goods take them to the shop of the buyer and deliver them to him if he is there or to anyone who is in charge of the shop if the owner is not found, if respondent No. 1 had immediately informed the appellant that the goods were not delivered, it would have been possible to know who received them. Both law and conscience prevent us from denying the validity of a legally valid cheque just because respondent No. 1 contends that he did not receive the goods. He contends this at a time when it can no longer be remembered how the delivery was made, having kept silent until the time when the cheque was payable and until the time when suit was filed against him. If a cheque is to lose its validity and if commercial activity is to be disturbed because of such petty reasons, this will harm not only businessmen but the economy of the country as well.

A person goes to a shop, buys the goods he wants, and pays the price in a cheque. When the shop owner asks for his money from the buyer, having first tried to cash the cheque but failed because the person who signed the cheque has not got money at the bank, if the buyer's contention that he signed the cheque without receiving the goods is to be a sufficient defense, won't businessmen insist on selling their goods in the presence of witnesses? Or are sales of all goods to be in writing? It can safely be said that these practices are not in conformity with modern commerce. Modern commercial transactions are carried out in more efficient procedures. Things that hinder commerce and cause it to drag are not acceptable. There is nothing that forces a person to sign a cheque and give it to another. When he does, he creates an obligation to pay or if a person, without being forced, pays when he does not have to pay, he has no one to blame except himself.

The goods were taken out of appellant's store. Since respondent No. 1, knowing he had to pay, signed a cheque which was payable a month later and gave it to the appellant and did not inform the respondent that he did not receive the goods, before the suit was filed against him and did not produce any evidence to show that he was forced to sign the cheque, it is not appropriate that appellant should not get the price of his goods. We reverse the judgment of the High Court and we give the following judgment: Respondent No. 1 shall pay the appellant the $7,900 with 9% interest from the time the suit was filed until the respondent pays the money plus $200 for costs. We affirm the part of the judgment of the High Court that excludes appellant No. 2 from liability. (Let a copy of the judgment be sent to the High Court so that the judgment may be executed).

Ter 26, 1958 E. C.

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤
አዲስ ፡ አበባ ፡ ሁለተኛ ፡ የንግድ ፡ ችሎት ።

ዳኞች ፤

ዶክተር ፡ ዊልያም ፡ ቡሐጂያር ፡

አቶ ፡ ደምሴ ፡ አሸናፊ ፡

አቶ ፡ አጀበው ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡

ጌቲ ፡ ፎርቲ ፡ ከሳሽ ፡
አጉስቲ ፡ ፎርቲ ፡ ተከሳሽ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቍጥር ፡ ፻፸፬/፺፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ — የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ — መደበኛ ፡ ቦታ ፡ — የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፫ ፡ እና ፡ ፩፻፬ ።

የቤተ ፡ ሰብ ፡ ሕግ ፡ — የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ — ትዳርን ፡ ጥሎ ፡ መጥፋት ፡ — የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪፻፲፭ ።

በከሳሽ ፡ የግሪክ ፡ ተወላጅና ፡ በተከሳሽ ፡ የኢጣሊያን ፡ ተወላጅ ፡ መካከል ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የተፈጸመ ፡ ጋብቻን ፡ ለማፍረስ ፡ የቀረበ ፡ ክስ ።

<u>ውሳኔ</u> ፤ በክሱ ፡ መሠረት ፡ የጋብቻው ፡ መፍረስ ፡ ታዟል ።

፩/ መደበኛ ፡ ቦታው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በሆነ ፡ በማንኛውም ፡ ሀገር ፡ ዜጋ ፡ የሚቀርበውን ፡ ክስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የማየትና ፡ የመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

፪/ በፍቺ ፡ ጉዳይ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞችን ፡ መመረጥና ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ የተመለከቱት ፡ የፍት ፡ ሐብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ከሁለት ፡ አንዱ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ውጭ ፡ በሆነበት ፡ ወይም ፡ መኖሪያ ፡ ቦታው ፡ ባልታወቀበት ፡ ጊዜ ፡ አግባብ ፡ የላቸውም ፤ ተፈጻሚም ፡ አይሆኑም ።

ፍርድ ።

በዚህ ፡ ክስ ፡ ከሳሽ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ የሚጠይቁት ፡ በርሳቸውና ፡ በተከሳሽ ፡ መሀከል ፡ በ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መጋቢት ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ (March 7, 1943) (እ፡ኤ፡አ ፡) ግብጽ ውስጥ ፡ የተፈጸመው ፡ ጋብቻ ፡ እንዲፈርስ ፡ ነው ። ለዚህም ፡ ጥያቄ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ከነሐሴ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ የተከሳሽ ፡ ከከሳሽ ፡ ዘንድ ፡ መጥፋት ፡ ነው ። የከሳሽ ፡ አቤቱታ ፡ ክስ ፡ በመሐላ ፡ ከተረጋገጠ ፡ ጽሑፍ ፡ (አፊደቪት) ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ቀርቧል ። በቃለ ፡ መሐላ ፡ የተረጋገጠው ፡ ጽሑፍ ፡ ተከሳሽ ፡ ያለበት፡ ቦታ ፡ በጭራሽ ፡ የማይታወቅ ፡ መሆኑን ፡ ከሳሽ ፡ በእስክንድርያ ፡ ከተማ ፡ በጠበቃ ፡ በኩል ፡ ተከሳሽን ፡ ለማግኘት ፡ ሞክረው ፡ እንደነበርና ፡ ይኸውም ፡ ጥረት ፡ እንዳል ተሳካና ፡ አሁን ፡ ተከሳሽ ፡ ስለመኖራቸውም ፡ ሆነ ፡ ስለመሞታቸው ፡ ከሳሽ ፡ ምንም፡ እንደማያውቁ ፡ ያስረዳል ። ይህንንም ፡ በመመልከት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመጥሪያ ፡ ትእ

ዛዝ ፡ ምትክ ፡ በጋዜጣ ፡ ላይ ፡ እንዲወጣ ፡ ፈቀደ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዲቀርብ ፡ በተቀ ጠረበት ፡ ቀን ፡ (March 28, 1963) መጋቢት ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተከሳሽ ፡ ሳይቀርብ ፡ ቀርቷል ።

የዚህ ፡ ክስ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ ተመልክቷል ። ከዚህም ፡ እንደምናገኘው ፡ ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ በእስክንድርያ ፡ ግንቦት ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፴፫ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) ተጋብተው ፡ ነበር ። ከዚያም ፡ ነሐሴ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተለያዩ ። ከተለያዩበትም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ አብረው ፡ አልኖሩም ፡ ተከ ሳሽም ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ እርዳታ ፡ አልሰጠም ። ተጋብተው ፡ ልጆች ፡ አልወለዱም ፡ ከሳሽ ፡ ወደ ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ከመጣችበት ፡ ጊዜ ፡ ከ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) ጀምሮ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ኖራለች ፡ አሁን ፡ የኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድ ፡ ሠራተኛ ፡ ነች ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ውጭ ፡ ሌላ ፡ መኖሪያ ፡ የላትም ። የተከሳሽ ፡ በሕይወት ፡ መኖር ፡ አለመኖር ፡ አይታወቅም ። በተጨማሪም ፡ ከሳሽ ፡ በክስ ፡ ማመል ከቻዋ ፡ ውስጥ ፡ እርሷ ፡ የግሪክ ፡ ዜጋ ፡ መሆኗንና ፡ ተከሳሽ ፡ ደግሞ ፡ ኢጣሊያዊ ፡ መሆኑን ፡ ገልጻለች ።

በመጀመሪያ ፡ ሊወሰን ፡ (ሊመረመር) የሚገባው ፡ ጭብጥ ፡ ይህ ፡ ጋብቻ ፡ እን ዲፈርስ ፡ የቀረበውን ፡ ክስ ፡ ለማየት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ እንዳ ላቸው ፡ ወይም ፡ እንደሌላቸው ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ለመወሰን ፡ ችግሮች ፡ ገጥመውናል። የመጀመሪያው ፡ ችግር ፡ የመጣው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ግላዊ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ የሚናገሩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ባለመኖራቸው ፡ ሲሆን ፡ ደግሞ ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ የተሰጡት ፡ ፍርዶች ፡ ውጤት ፡ ተመ ሳሳይ ፡ ባለመሆኑ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ እስካሁን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የተሰጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ መጠነኛ ፡ ተመሳሳይነት ፡ ይታይባቸዋል ። ይኸው ፡ የፍርድ ፡ አንድነት ፡ የታየው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ የአንደኛው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ የመ ኖሪያ ፡ ቤት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ መሆኑ ፡ ብቻ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በነ ገሩ ፡ ብያኔ ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ፡ ለማለት ፡ አያስችልም ፡ በማለት ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ከዋለ ፡ ወዲህ ፡ "መደበኛ ፡ ቦታ" የሚባለው ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ የአሜሪካና ፡ የእንግሊዝ ፡ የሕግ ፡ ቅንጅት ፡ ከሚከተለው ፡ ትር ጉም ፡ የተለየ ፡ ፍቺ ፡ ይዟል ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፻፹፫ ፡ የ "መደበኛ ፡ ቦታ" ን ፡ ትርጓሜ ፡ ሲሰጥ ፡ ቍጥር ፡ ፻፹፬ ፡ ደግሞ ፡ የአሳብ ፡ ግምት ፡ የሚወሰድበ ትን ፡ ሁኔታ ፡ ያስረዳል ። በተጠቀሱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠ ረት ፡ ከሳሽ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ "መደበኛ ፡ ቦታ" እንዳላት ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ዜግነት ፡ የተባለው ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጣል ፡ ለሚባለው ፡ ይህንን ፡ አሳብ ፡ በቅርቡ ፡ ብዙ ፡ ፍርዶች ፡ አልተከተሉትም ። ያም፡ሆነ ፡ ይህ ፡ ለአሁኑ ፡ ጉዳይ ፡ አይጠቅምም ። ምክንያቱም ፡ ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ ዜግነታ ቸው ፡ የተለያየ ፡ ነው ። ከሳሽ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ፡ ስላላትና ፡ አሁን ፡ ተከሳሽ ፡ ያለበት ፡ ቦታ ፡ ስላልታወቀ ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ውሳኔ፡ለመስጠት፡ሥልጣን፡አለው።ሊወሰን ፡ (ሊመረመር) ፡ የሚገባው፡ሁለተኛ፡ጭብጥ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በተሰጠው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ መጀመሪያ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሳይመረጡና ፡ ነገሩን ፡ ሳይቆርጡ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊያ የው ፡ ይችላል ፡ ወይ ፡ የሚል ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ አንዱ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ውጭ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ አድራሻው ፡ በማይታወቅበት ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንዳለብን ፡ አያስረዳም ። አሁን ፡ በፊታችን ፡ እንዳለው ፡ ጉዳይ ፡ ባልየው ፡ በሌለበትና ፡ የት ፡ እንዳለ ፡ በማይታወቅበት ፡ ሁኔታ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ የርሱን ፡ ነገር ፡ እንዲመረምሩ ፡ መምረጥ ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ነው ። ስለሆነም ፡ የተጠቀ

ሱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቍጥሮች ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ አያገለግሉም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የተባሉት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ ሳይፈጸሙ ፡ ነገሩን ፡ ለማየት ፡ ይችላል ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ አብረው ፡ ከሚኖሩበት ፡ ቦታ ፡ የአንደኛው ጠፍቶ ፡ መሄድ ፡ መፈታትን ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችል ፡ በቂና ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፳፱) ፡ ለ/ ፡ ተመልከት) ። እላይ ፡ እንደተ መለከተው ፡ ተከሳሽ ፡ ሚስቱን ፡ ጥሎ ፡ ስለጠፋ ፡ በከሳሽና ፡ በተከሳሽ ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ መጋቢት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ፡ ኤ ፡ አ ፡) በእስክንድርያ ፡ ከተማ ፡ የተፈጸመው ፡ ጋብቻ ፡ እንዲፈርስ ፡ አዘናል ። ከጋብቻው ፡ የተገኙ ፡ ልጆች ፡ ስለሌሉና ፡ የጋራም ፡ ሆነ ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ስለሌለ ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ፡ አልተሰጠም ።

HIGH COURT

Addis Ababa, Commercial Division No. 2

Justices:

Dr. W. Buhagiar

Ato Denki Ashenafe

Ato Ajebew Wolde Meskel

GUETTY FORTI v. AUGUSTE FORTI

Civil case No. 174/55

Civil Procedure — Jurisdiction — Domicile — Arts. 183 *and* 184 *Civ. C.*

Family law — Dissolution of marriage — Desertion — Art. 669 *Civ. C.*

Action for dissolution of marriage celebrated in Egypt between plaintiff, a Greek, and defendant, an Italian.

Held: Dissolution of marriage ordered.

1. Ethiopian courts have jurisdiction to entertain a claim instituted by a party domiciled in Ethiopia.

2. The procedure laid down in the Civil Code regarding the appointment and decision of family arbitrators does not apply to the case where one of the parties is outside of Ethiopia or where his whereabouts are unknown.

In these proceedings the plaintiff is praying for a dissolution of the marriage which was celebrated in Egypt on May 7, 1943 (Gr. Cal.) between herself and the defendant; the ground for the dissolution is desertion since August 20, 1943 (Gr. Cal.). The claim of the plaintiff is supported by an affidavit sworn on January 23, 1963 (Gr.Cal.) in which she stated, inter alia, that the whereabouts of the defendant are not known, that attempts through a lawyer in Alexandria to establish communication with defendant have been without success and that she does not know whether the defendant is living or dead. In view of these facts the Court allowed substituted summons through the newspaper but on the appointed date March 28, 1963 (Megabit 19, 1955), the defendant did not appear in answer to the summons.

The facts in this case have been established by means of the affidavit above mentioned. From this it results that the plaintiff and the defendant were married in Alexandria, Egypt, on May 7, 1943 (Gr.Cal.) that the parties separated on August 20, 1943 (Gr.Cal.); that since the separation the plaintiff and the defendant have never lived together and the defendant has not contributed to the support of the plaintiff; that there are no children of the marriage; that the plaintiff came to Addis Ababa, Ethiopia, in the year 1946 (Gr.Cal.) and has lived continuously in this country since that year; she is employed by the Ethiopian Air Lines, and has no home outside Ethiopia. It is not known whether the defendant is living or dead. The plaintiff states in her statement of claim that she is of Greek nationality and the defendant is of Italian nationality.

The first matter to be considered is whether the courts of Ethiopia have jurisdiction to deal with the present prayer for dissolution of marriage. The difficulties arise because the Civil Code of Ethiopia contains no provision dealing with private international law, and decisions on this matter have not been uniform. There has been, however, a certain amount of uniformity in Ethiopian cases in rejecting simple residence of one or the other of the parties as a ground for establishing jurisdiction. Since the coming into force of the Civil Code, "domicile" has acquired a different meaning from that in the Anglo-American systems of law; Article 182 of the Civil Code defines "domicile" and Article 184 creates a presumption as to intention. Under these two articles it is clear that the plaintiff has acquired a domicile in Ethiopia. As to the principle of nationality for establishing jurisdiction it may be said that this has not been frequently followed in recent cases and in any case that principle would not be of much help in the present case where the parties seem to be of different nationality. For these reasons this Court holds that it has jurisdiction in the matter before it, on the ground that the plaintiff has a domicile in Ethiopia and the whereabouts of the defendant are not known.

The second point to consider is whether this Court can take cognizance of the matter before the arbitration provisions of the Civil Code have been complied with. The Civil Code makes no provision for situations where one of the parties is outside Ethiopia or where the whereabouts of one of the parties are not known. Under these circumstances it seems to this Court that the appointment of arbitrators for one of the parties who is absent and whose whereabouts are not known would be meaningless and therefore the said provisions of the Code do not apply and the Court can take cognizance of the matter without the said formalities having been fulfilled.

There is no question that desertion is a good and indeed a serious ground for divorce under the Civil Code (see article 669(b)).

For the above reasons this Court orders the dissolution of marriage celebrated between the plaintiff and the defendant in Alexandria on May 7, 1943 (Gr.Cal.) on the ground of desertion on the part of the defendant. As there are no children of the marriage and as there is no property, common or personal, to be dealt with, no order is made on these points.

Megabit 24, 1955 E.C.

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡
አዲስ ፡ አበባ ፡ የንግድ ፡ ችሎት ።

ዳኞች ፤

ዶክተር ፡ ዊልያም ፡ ቡሐጂያር ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ አውግቸው ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ መንገሻ ፡

ወይዘሪት ፡ ንግሥት ፡ መኰንን ፡ እና ፡ ሌሎች ፡ ከሳሾች ፡
የኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድ ፡ ባለአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ተከሳሽ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቍጥር ፡ ፲፻፩/፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ — የክስ ፡ መዝገብ ፡ መዘጋት ፡ — የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ፷፱ ፡ ፸፩ ፡ እና ፡ ፸፫ ።

ውሳኔ ፡ እንዲሰጥ ፡ የቀረበ ፡ ጥያቄ ።

ውሳኔ ፤ ጥያቄው ፡ ውድቅ ፡ ሆኗል ።

፩/ የግራ ፡ ቀኙ ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ሳይቀርቡ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የክሱ ፡ መዝገብ ፡ ይዘጋል ።

፪/ ከሳሽ ፡ ክርክሩ ፡ እንዲሰማ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፊት ፡ የቀረበ ፡ ምንም ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገቡን ፡ በመዝጋት ፡ ያሰናብተዋል ።

፫/ ማስረጃ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ ከሳሽ ፡ ሳይቀርብ ፡ ቀርቶ ፡ ቀጠሮ ፡ አስፈላጊ ፡ ቢሆን ፡ ትክክለኛው ፡ መድኀን ፡ ለሌላው ፡ ወገን ፡ ሲያመለክት ፡ ኪሣራን ፡ መስጠት ፡ ነው ።

ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ፍራንዝ ፡ ሽናይደር ፡ የተባለውን ፡ አዋቂ ፡ ምስክር ፡ (፩ኛ ፡ የዐቃቤ ሕግ ፡ ምስክር ፡ የሆነውን) መስቀለኛ ፡ ጥያቄ ፡ ለመጠየቅ ፡ ሲባል ፡ ለጥቅምት ፡ ፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተቀጥሮ ፡ ነበር ፡ በተባለው ፡ ቀን ፡ የከሳሾች ፡ ጠበቃ ፡ ሳይቀርብ ፡ ቀርቶ ፡ በላከው ፡ መልእክት ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ምስክር ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አልተመለሰም ፡ በማለት ፡ ምስክሩ ፡ የሚያስተምርበት ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ገልጾልናል ፡ ብሏል ። የከሳሾች ፡ ጠበቃም ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ውጭ ፡ እንደነበረ ፡ ታውቋል ። የተከሳሽ ፡ ጠበቃ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፷፱ ፡ ፸፫ ፡ እና ፡ ፸፱ ፡ ጠቅሶ ፡ የከሳሾች ፡ ማስረጃ ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ እንደሌለው ፡ ተቆጥሮ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጥ ፡ ሲል ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አመለከተ ።

ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ከቀረበ ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ማለፉንና ፡ ከሳሾችም ፡ ሆኑ ፡ ተከሳሽ ፡ ብዙ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ከማቅረባቸውም ፡ በላይ ፡ ከሳሾች ፡ ብዙ ፡ ምስክሮች ፡ ጠርተው ፡ ቃላቸው ፡ የተመዘገበ ፡ መሆኑን ፡ ተመልክተናል ። አሁን ፡ ክርክሩ ፡ ባለበት ፡ ደረጃ ፡ ለከሳሾች ፡ ለመፍረድ ፡ ወይም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ለመፍረድ ፡ እነሱ ፡ ያቀ

ረቡት ፡ ማስረጃ ፡ በቂ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ አይደለም ፡ ለማለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አይገባ ውም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቀረበ ፡ ማስረጃ ፡ መኖሩ ፡ አይጠረጠርም ፡ ይህንንም ፡ ማስረጃ ፡ የተከሳሽ ፡ ጠበቃ ፡ እንደሚለው ፡ ችላ ፡ ማለት ፡ አይቻልም ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቀረበው ፡ ማስረጃ ፡ ችላ ፡ ሳይባልም ፡ ሆነ ፡ ችላ ፡ ተብሎ ፡ ተከሳሽ ፡ የጠቀሰው ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጥ ፡ ሲል ፡ የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ የሚደግፍ ፡ አይደለም ። ቁጥሩ ፡ የሚለው ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ነገሩ ፡ እንዲሰማ ፡ በተወ ሰነበት ፡ ቀን ፡ ሳይቀርቡ ፡ ቢቀሩ ፡ ክሱ ፡ ይሰረዛል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ፡ አይ ልም ። የተከሳሽ ፡ ጠበቃ ፡ የጠቀሰው ፡ ቍጥር ፡ ፭፫ ፡ ደግሞ ፡ ከሳሽ ፡ ክርክሩ ፡ እንዲሰማ፡ በተወሰነበት ፡ ቀን ፡ ያልቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገቡን ፡ በመዝጋት ፡ ያሰናብ ተዋል ፡ ይላል ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ ቍጥር ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆነው ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቀ ረበ ፡ ምንም ፡ ማስረጃ ፡ በሌለበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ማለትም ፡ ክርክሩ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰማ ፡ በተወሰነ ፡ ቀን ፡ ወይንም ፡ በሚቀጥለው ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ ከሳሽ ፡ ሳይቀርብ ፡ ቀርቶ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የቀረበ ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፡ ይህ ፡ ቍጥር ፡ ተፈ ጻሚ ፡ ይሆናል ። ይህንንም ፡ ሁኔታ ፡ ለማብራራት ፡ ከሳሽ ፡ ክስ ፡ አቀረበ ፡ እንበል ፡ የመከላከያ ፡ ጽሑፍ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ ከሳሹ ፡ ፍርድ ፡ ለሱ ፡ መሰጠት ፡ እንደሚገባ ፡ በግልጽ ፡ የሚያሳይ ፡ የጽሑፍና ፡ የቃል ፡ ማስረጃ ፡ ያቀርባል ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እሱ ፡ ባለመቅረቡ ፡ ብቻ ፡ መዝገቡ ፡ እንዲዘጋ ፡ ቢወስን ፡ ተገቢ ፡ አይሆንም ። ተከሳሽ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየውንና ፡ የከሳሽን ፡ ማስረጃ ፡ ለማፍረስ፡ይበቃል ፡ ብሎ፡ የሚገምተውን ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ አሁንም ፡ እድል ፡ አለው ። በዚህ፡ሁኔታ ፡ ከሳሽ ፡ ሳይቀርብ ፡ ሲቀርና ፡ ቀጠሮ ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ተገቢው ፡ መድኅን ፡ ይገባኛል ፡ ብሎ ፡ ለሚያመለክተው ፡ ወገን ፡ ኪሣራ ፡ መወሰን ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተሰጡትን ፡ ምክንያቶች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ተከሳሽ ፡ ፍርድ ፡ እንዲሰጠው ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አልተቀበለውም ። የቀረበ ፡ ማመል ከቻ ፡ ስለሌለ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፈል ፡ አላዘዝንም ።

ኅዳር ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ።

HIGH COURT

Addis Ababa, Commercial Division

Judges:
Dr. W. Buhagiar
Ato Abebe Awgitchaw
Ato Tadesse Mengesha

WOIZERIT NEGEST MAKONNEN et AL. v. E.A.L. SHAREHOLDERS CO.

Civil Case No. 701/55

Civil Procedure — Striking of suit— Dismissal of suit — Arts. 69, 73 *and* 71, *Civ. Pro. C.*

Motion for decision.

Held: Motion denied.

1. Where neither party appears on the date fixed for hearing, a suit may be struck out.

2. Where the plaintiff does not appear on the date fixed for hearing and where no evidence has been brought before the court, the court may dismiss the suit.

3. Where the plaintiff does not appear after evidence has been offered and an adjournment is necessary for some reason, then the proper remedy is not dismissal but rather to grant costs to the other party who applies for such costs.

The case was adjourned to Tekemt 8, 1959, for the purpose of the cross-examination of the expert witness, Franz Schneider, (PW-5); on the said date the advocate for the plaintiffs did not appear but sent a message to Court to the effect that the said witness had not returned to Ethiopia from abroad, or so the advocate was informed by the Haile Sellassie I University, where the witness is a Professor; the advocate for the plaintiffs was himself out of Addis Ababa. The advocate for the defendant prayed the Court that all evidence of the plaintiffs be ignored and that a decision be given; he referred to articles 69, 73 and 74 of the Civil Procedure Code.

It is to be mentioned that this case has been pending for some time and several documents have been submitted by the plaintiffs and the defendant and also several witnesses have been called by the plaintiffs whose testimony has been recorded. It is not for the Court to say at this stage whether the evidence produced by the plaintiffs is sufficient to justify a decision in their favour or a decision against them; but the fact remains that there is evidence before the Court and such evidence cannot, as the advocate for the defendants prays, be just ignored. Article 69 quoted by the defendant does not support his prayer for a decision with or without ignoring the evidence before the Court; under that article a suit may be struck out (not a decision given) when neither party appears on the date fixed for hearing. Article 73 quoted by the advocate for the defendant provides that

when the plaintiff does not appear on the date fixed for hearing, the court shall make an order dismissing the suit; this article, however, applies where there is no evidence whatsoever before the Court; in other words this article can have application when on the first date of hearing or on any subsequent hearing the plaintiff does not appear and there is no evidence before the Court. Let us assume for example that a plaintiff brings a suit in Court and after a defence has been filed he produces documentary and oral evidence which shows clearly that, on that evidence, he is clearly entitled to a judgment in his favour; it would be unjust if the Court were to give a decision dismissing the claim simply because he fails to appear in Court; it is open to the defendant to bring such evidence as he considers necessary and sufficient to rebut the evidence of the plaintiff; when, in such circumstances the plaintiff does not appear and an adjournment is for some reason or other necessary then the proper remedy is to grant costs to the other party who applies for such costs.

For the above mentioned reasons the Court rejects the prayer of the defendant to have a judgment and as there has been no prayer for costs there shall be no order for costs.

Hedar 16, 1959 E. C.

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡

አዲስ ፡ አበባ ፡ አንደኛ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ችሎት ።

ዳኞች ፡

የዳኞቹ ፡ ስም ፡ አልተገለጸም ።

አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰችው ፡ የአልማዝ ፡ ፉፋ ፡ አሳዳሪነትና ፡ ሞግዚትነት ፡ ጉዳይ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቍጥር ፡ ፻፴፪/፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ።

አካለ ፡ መጠን ፡ ስላላደረሱ ፡ ሰዎች ፡ — ስለ ፡ አሳዳሪና ፡ ሞግዚት ፡ — ስለ ፡ አሳዳሪና ፡ ሞግዚት ፡ ተግባሮች ፡ መቋረጥ ፡ — በፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚሾም ፡ አሳዳሪና ፡ ሞግዚት ፡ — ስለአሳዳሪና ፡ ሞግዚት ፡ መሻር ፡— የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ፪፻፲ ፡ ፪፻፲፩ ፡ ፪፻፲፪ ፡ ፪፻፲፫ ፡ ፪፻፲፭ ፡ ፪፻፹፫ ፡ ፪፻፴፱ ፡ (፩) ።

ይህ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ታኅሣሥ ፡ ፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ- ም- ባስተላለፈው ፡ ትእዛዝ ፡ ውስጥ የሾመውን ፡ አሳዳሪና ፡ ሞግዚት ፡ ሽሮ ፡ ትእዛዙን ፡ እንዲሰርዝ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፴፱ (፩) ስር ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ያቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ነው ።

<u>ውሳኔ</u> ፤ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ሰጥቶት ፡ የነበረውን ፡ ትእዛዝ ፡ በአቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ ሰርዟል ።

፩/ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፴፱ (፩) መሠረት ፡ የአንድ ፡ ልጅ ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ፡ እንዲሻር ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችሉት ፡ የልጁ ፡ የሥጋ ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

፪/ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፹፫ ፡ መሠረት ፡ አሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ ሞግዚትነት ፡ ግዴታ ፡ እንጂ ፡ መብት ፡ ስላልሆነ ፡ በቀላሉ ፡ መተው ፡ አይቻልም ። በተጨማሪም ፡ ዳኞች ፡ ጥብቅ ፡ በሆነ ፡ ከፍተኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ ተጠብቀው ፡ ካላደረጉት ፡ በቀር ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ወይም ፡ ሌሎቹ ፡ ወላጆች ፡ ከልጃቸው ፡ አሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ ሞግዚትነት ፡ ሥራቸው ፡ እንዲሻሩ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፹፫ ፡ ታግደዋል ።

፫/ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲፫ ፡ ፪፻፲፭ ፡ የአሳዳሪ ፡ መሾምን ፡ የሚመለከቱ ፡ ቍጥሮች ፡ አይደሉም ፤ አሳዳሪነት ፡ የወላጆች ፡ ግዴታ ፡ ሆኖ ፡ የሚቀር ፡ ነው ።

፬/ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲፩ ፡ መሠረት ፡ የአሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ የመጋቢነት ፡ ግዴታ ፡ የተጣለበት ፡ ሰው ፡ ግዴታውን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ከግዴታው ፡ ራሱን ፡ ነፃ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ፤ እንደ ሞተም ፡ አይቆጠርም ።

ታኅሣሥ ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሚስተር ፡ ሌስሊ ፡ ኤች ፡ ክራመርን ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሰችው ፡ የአቶ ፡ ፉፋ ፡ ደሬሳና ፡ የወይዘሮ ፡ ዘርፍነሽ ፡ ለማ ፡ ሕጋዊ ፡ ልጅ ፡ ለሆነችው ፡ ለአልማዝ ፡ ፉፋ ፡ አሳዳሪና ፡ ሞግዚት ፡ እንዲሆኑ ፡ ሾማቸው ። ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠው ፡ በሚስተር ፡ ክራመር ፡ አመልካችነት ፡ ሲሆን ፡ በማመልከቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ልጅቷን ፡ እሳቸው ፡ እንዲያስተዳድሩ ፡ ያደረገው ፡ የሠላሳ ፡ ሦስት ፡ አመታት ፡ እድሜ ፡ ያለው ፡ በሚቲ ፡ መንደር ፡ የሚኖረው ፡ ወላጅ ፡ አባቷ ፡ ነው ፡ ብለዋል ። ይህም ፡ የሆነው ፡ በሕዳር ፡

ወር ፡ ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሲሆን ፡ አባትዬው ፡ ይህንን ፡ ያደረገበት ፡ ምክንያት ፡ ከሚስቱ ፡ ስለተፋታና ፡ ልጁንም ፡ ማሳደግ ፡ ስላቃተው ፡ ነው ፡ ብለዋል ። በተጨማሪ ፡ ሚስተር፡ ክራመር ፡ ልጅቷን ፡ ከወሰዱበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እንደራሳቸው፡ ልጅ ፡ በማየት ፡ እያበሉ ፡ እያለበሱና ፡ እያስተማሩ ፡ አስቀምጠዋታል ። ለወደፊት ፡ ኑሮዋም ፡ በማሰብ ፡ በገንዘብ፡ በኩል ፡ ዝግጅት ፡ ማድረጋቸውን ፡ ገልጸዋል ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ልጅቷ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመቷ ፡ ነበር ፡ ከእሳቸው ፡ ጋር ፡ ለአምስት ፡ ዓመታት ፡ ያህል ፡ ኖራለች ፡ የራሳቸው ፡ ልጅ ፡ ስለሌላቸው ፡ ልጅቷን ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ከራሳቸው ፡ ጋር ፡ ለማስቀመጥ ፡ ይፈልጋሉ ፡ ወላጆቿም ፡ እሳቸው ፡ በሚያደርጉላት ፡ እርዳታ ፡ ተደስተው ፡ ለእርሷ ፡ ጥቅምና ፡ ደኅንነት ፡ ሲሉ ፡ ከእርሳቸው ፡ ጋር ፡ እንድትኖር ፡ ፈቅደዋል ፡ አሉ ።

የልጅቷ ፡ አባት ፡ አቶ ፡ ፉፋ ፡ ደሬሳ ፡ ለፍ/ቤት ፡ ባቀረበው ፡ ማስረጃ ፡ አል ማዝ ፡ ፉፋ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ የካቲት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ከእሱና ፡ ከሚስቱ ፡ ከወይዘሮ ፡ ዘርፍነሽ ፡ ለማ ፡ የተወለደች ፡ ልጅ ፡ መሆኗን ፡ ገልጿል ። ልጅቷ ፡ ከወላጆቿ ፡ ጋር ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡ አብራ ፡ ከኖረች ፡ በኋላ ፡ የአቶ ፡ ፉፋ ፡ እህት ፡ ከሚስተር ፡ ክራመር ፡ ቤት ፡ በግርድና ፡ ተቀጥራ፡ ትሠራ፡ስለነበረ፡ ልጅቷ፡ ለሚስ ተር ፡ ክራመር ፡ ተወስዳ ፡ እርሳቸውም ፡ የእሷን ፡ ኃላፊነት ፡ ተረከቡ ። አቶ ፡ ፉፋና ፡ ባለቤቱ ፡ ተፋተዋል ። የልጅቷ ፡ እናት ፡ ወይዘሮ ፡ ዘርፍነሽ ፡ ለማ ፡ የባሏን ፡ ቃል ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብላ ፡ አረጋግጣለች ። ሁለቱም ፡ ወላጆች ፡ ልጅቷ ፡ በሚስተር ፡ ክራ መር ፡ ኃላፊነት ፡ ሥር ፡ እንድትቆይ ፡ እንወዳለን ፡ ብለዋል ።

በተጨማሪም ፡ ሚስተር ፡ ክራመር ፡ ልጅቷን ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ ለማድረግ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አመልክተው ፡ ነበር ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ እሳቸው ፡ ያገቡ ፡ ስለሆነና ፡ ሚስታ ቸውም ፡ ፈቃዷን ፡ ስላልሰጠች ፡ የጉዲፈቻ ፡ ትዕዛዝ ፡ እንዳይሰጥ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፺፰ ፡ ምክንያት ፡ ሆነ ። ከሚስቴ ፡ እፋታ ፡ ይሆናልና ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አልማዝን፡የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ አደርጋታለሁ ፡ ብለው ፡ ሚስተር፡ክራመር፡መናገረቸውን፡ መዝገቡ ፡ ያሳያል ። አሁን ፡ ምክትል ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲሽረው ፡ ጥያቄ ፡ አቅርቧል ። ይህንንም ፡ ጥያቄ ፡ ያቀረበው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፷፬ ፡ (፩) ፡ በተሰ ጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ነው ። ያቤቱታው ፡ ምክንያቶች ፡ ባጭሩ ፡ የሚከተሉት፡ ናቸው ።

(ሀ) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፷፫ ፡ አሳዳሪነት ፡ የወላጆች ፡ ግዴታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በቀላሉ ፡ የሚተው ፡ መብት ፡ (ወይም ፡ ሥልጣን) አይደለም ። አሳዳሪነት ፡ ግዴታ ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ ግዴታ ፡ የተጣለበት ፡ ሰው ፡ ሥራው ፡ የሚቀርለት ፡ በአንዳ ንድ ፡ በተወሰኑና ፡ ልዩ ፡ በሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(ለ) በቍጥር ፡ ፪፻፷፪ ፡ የልጆች ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ወላጆች ፡ ከልጆቻቸው ፡ አሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ ሞግዚትነት ፡ ሥራቸው ፡ እንዲሻሩ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ሲሰጥ ፡ ጥብቅ ፡ በሆነና ፡ በከፍተኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ ተጠብቆ ፡ እንዲ ያደርግ ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ ያዛል ።

(ሐ) በቍጥር ፡ ፪፻፲፯ ፡ መሠረት ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ጉዳዩ ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ የታያቸው ፡ እንደሆነ ፡ የልጃቸውን ፡ አሳዳሪነት ፡ ሥልጣን ፡ እራሳቸው ፡ ይዘው ፡ አንድ ፡ ሞግዚት ፡ ለመሾም ፡ ይችላሉ ። በቍጥር ፡ ፪፻፲፰ ፡ መሠረት ፡ ዳኞች ፡ የልጁን ፡ አሳዳሪና ፡ ሞግዚት ፡ የመሾም ፡ ሥልጣን ፡ የራሳቸው ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ ይህን፡ ለማድረግ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከአሳዳሪው ፡ ሌላ ፡ ለልጁ ፡ ሌላ ፡ ሞግ ዚት ፡ ለመሾም ፡ ይችላሉ ። እነዚህ ፡ ቍጥሮች ፡ ስለሞግዚት ፡ መሾም ፡ እንጂ ፡ ስለአ ሳዳሪ ፡ መሾም ፡ አይናገሩም ።

ሚስተር ፡ ክራመር ፡ የምክትል ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ማመልከቻ ፡ በሚገባ ፡ ከደረሳ ቸው ፡ በኋላ ፡ ሕግ ፡ ነክ ፡ ክርክርና ፡ የፍሬ ፡ ነገር ፡ ክርክር ፡ የያዘ ፡ መልስ ፡ ሰጡ ። ስለፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ክርክር ፡ በሰጡት ፡ መልስ ፡ ልጅቷን ፡ አልማዝ ፡ ፉፋን ፡ ወላጆቿ ፡ ዞር ፡ ብለው ፡ ያላይዋት፡መሆኑን ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ከሆናት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮም ፡ እሳቸው በሚገባ ፡ ተጠንቅቀውላት ፡ ያኖሯትና ፡ ያስተማሯት ፡ መሆኑን ፡ ወላጆቿ ፡ ከመፋታ ታቸውም ፡ ሌላ ፡ እሷን ፡ ለማሳደግ ፡ የሚሳናቸው ፡ መሆኑን ፡ እሳቸው ፡ የራሳቸው ፡ የሆነ ፡ ልጅ ፡ ስለሌላቸው ፡ አልማዝን ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ ለማድረግ ፡ ፈልገው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሚስታቸው ፡ ፈቃዷን፡ ስላልሰጠች ፡ ለጊዜው ፡ የነበራቸው ፡ ምርጫ ፡ ከሚስ ታቸው ፡ ተፋትተው ፡ ልጅቷን ፡ በሕግ ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጃቸው ፡ እስኪያደርጓት ፡ ድረ ስ ፡ ለወደፊት ፡ ኑሮዋ ፡ የሚሆን ፡ ንብረት ፡ ማስቀመጥ ፡ (ማጠራቀም) ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚያዝያ ፡ ፳፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ምሕረቱን ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሰጥ ፡ አረጋግ ጧል ፡ ብለዋል ። ሚስተር ፡ ክራመር ፡ ስለ ፡ ሕጉ ፡ ክርክር ፡ ባቀረቡት ፡ መልስ ፡ ወላ ጆቿ ፡ ልጅቷን ፡ መፈለጋቸውንና ፡ ለሷም ፡ ማሰባቸውን ፡ ስላላሳዩ ፡ የአሳዳሪነትና ፡ የሞግዚትነት ፡ ሥራቸው ፡ ቀሪ ፡ ሆኗል ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፲፫ ፡ መሠረትም ፡ እንደሞቱ ፡ ይቆጠራሉ ፡ ስለዚህ ፡ ልጅቷ ፡ ያለአሳዳሪና ፡ ያለሞግዚት ፡ በመቅረቷ ፡ ይህ ፡ ሥራና ፡ ሥልጣን ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፲፪ ፡ መሠረት ፡ ዳኞች ፡ ለመረጧቸው ፡ ሰዎች ፡ ይሰጣል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ እርሳቸውን ፡ (ሚስተር ፡ ክራመርን) ፡ የአልማዝ ፡ ፉፋ ፡ አሳዳሪና ፡ ሞግዚት ፡ አድርጎ ፡ የመረጣቸው ፡ በዚሁ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ ታኅ ሣሥ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ምንም ፡ ለውጥ ፡ ሳይደረግ በት ፡ መጽናት ፡ አለበት ፡ ብለዋል ።

ምክትል ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በቃል ፡ ባቀረበው ፡ ክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ ማመልከቻ ፡ ያቀረበው ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ስሕተት ፡ መስሎ ፡ ስለታየው ፡ ነው ፡ ብሏል ። በተጨማሪም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከታወጀ ፡ ወዲህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጉዳይ ፡ ሲመጣ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ስለሆነ ፡ በታኅሣሥ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ለሕጉ ፡ አተረጓጎም ፡ መጥፎ ፡ አር አያ ፡ ይሆናል ፡ ብሏል ።

የምክትል ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ማመልከቻ ፡ የሚናገረው ፡ ስለጉዳዩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለልጅቷ ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ ትእዛዝ ፡ ማስፈለግ ፡ አለማስፈለ ጉን ፡ ለማወቅ ፡ ሲል ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ በሚገባ ፡ መርምሯል ፡ ወይ ፡ ስለሚለው ፡ ጥያቄ አይደለም ። ማመልከቻው ፡ የሚቃወመው ፡ ሕግ ፡ ነክ ፡ በሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ ትእዛዙ ሕጋዊ ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ለማመልከቻው ፡ የተጻፈው ፡ መል ስ ፡ አንዳንድ ፡ ፍሬ ፡ ነገሮችን ፡ ስለሚጠቅስ ፡ ስለ ፡ እነዚህ ፡ ነጥቦች ፡ መነጋገር ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ።

በመጀመሪያ ፡ የልጅቷ ፡ ወላጆች ፡ ልጅቷን ፡ ለማሳደግ ፡ አቅማቸው ፡ አይፈቅ ድላቸውም ፡ ተብሏል ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ የሚያሳይ ፡ ማስረጃ ፡ ለፍ ርድ ፡ ቤቱ ፡ መቅረቡን ፡ መዝገቡ ፡ አያሳይም ። ምናልባትም ፡ ወላጆቿ ፡ በአቅማቸው ሊያደርጉላት ፡ ከሚችሉት ፡ እርዳታ ፡ አሁን ፡ የሚደረግላት ፡ እርዳታ ፡ ይበልጥ ፡ ይሆ ናል ። ሁለተኛም ፡ ሚስተር ፡ ክራመር ፡ ለልጅቷ ፡ የወደፊት ፡ ኑሮ ፡ በማሰብ ፡ የገን ዘብ ፡ ዝግጅት ፡ አድርገዋል ፡ ተብሏል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ዓይነት ፡ ዝግጅት ፡ መደ ረጉን ፡ የሚያሳይ ፡ ማስረጃ ፡ የለም ። በተጨማሪም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሚስተር ፡ ክራ መር ፡ ከሚስቴ ፡ ልፋታ ፡ ነው ፡ ያሉትን ፡ የተቀበለ ፡ ይመስላል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ መዝ ገቡ ፡ መፋታትን ፡ የሚያስከትል ፡ ምክንያት ፡ መኖሩን ፡ ወይም ፡ ክስ ፡ መቅረቡን ፡ አያሳይም ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መፋታት ፡ የሚፈቀድ ፡ መሆኑና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ልጅቷን

የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ ማድረግ ፡ የሚቻል ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ ይመስላል ። በተጨማሪም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የልጅቷ ፡ ወላጆች ፡ ልጅቷ ፡ ከሚስተር ፡ ክራመር ፡ ጋር ፡ መኖሯን ፡ እንፈቅዳለን ፡ የልጅቷም ፡ አሳዳሪነት ፡ ሥራ ፡ ቢቀርልን ፡ አንቃወምም ፡ ባሉት ፡ የተመራ ፡ ይመስላል ። የልጅቷ ፡ አባት ፡ ከሚስቴ ፡ ተፋትቻለሁ ፡ ብለው ፡ ነበር ፡ የመፋታቱ ፡ ውሳኔ ፡ መቼ ፡ እንደተሰጠ ፡ አይታወቅም ፡ ሆኖም ፡ ይህ ፡ የሆነው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ከጋብቻ ፡ የተወለዱትን ፡ ሕፃናት ፡ አጠባበቅ ፡ ጉዳይ ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ድርጅት ፡ ከመቋቋሙ ፡ በፊት ፡ ይመስላል ።

እላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ምክትል ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የሚለው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተቀበለው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ትክክል ፡ አይደለም ፡ ሳይሆን ፡ እሱ ፡ የሚለው ፡ መሠረታዊና ፡ ሥርዓተ—ነክ ፡ የሆነ ፡ የሕግ ፡ ስሕተት ፡ ተደርጓል ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፪፻፹፬ ፡ (፩) ፡ አንድ ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሞግዚት ፡ እንዲሻር ፡ የሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ በአንድ ፡ የልጁ ፡ የሥጋ ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ግንኙነት ፡ በአለው ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ አስከባሪው ፡ በኩል ፡ ሊደረግ ፡ ይችላል ፡ ይላል ፡ ይህ ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ግልጽ ፡ ነው ። አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ሰው ፡ ዘመዶች ፡ የሞግዚትነቱና ፡ የአሳዳሪነቱ ፡ ሥራ ፡ እንዴት ፡ እንደሚከናወን ፡ በቅርብ ፡ ሆነው ፡ ሊከታተሉ ፡ ይችላሉ ፤ ሕጋዊው ፡ አሳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ፡ ይህን ፡ ሥራውን ፡ የሚያከናውነው ፡ የልጁን ፡ ጥቅም ፡ በሚጐዳ ፡ መንገድ ፡ ከሆነ ፡ የዚህ ፡ ሞግዚት ፡ ወይም ፡ አሳዳሪ ፡ መሻር ፡ ለልጁ ፡ ምቾትና ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ለዘመዶች ፡ የተሰጠው ፡ መብት ፡ (ሥልጣን) ለሕግ ፡ አስከባሪውም ፡ የተሰጠበት ፡ ምክንያት ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ ሰዎች ፡ ጥቅም ፡ የሚጠብቁላቸው ፡ ዘመዶች ፡ በሌላቸው ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ዘመዶቻቸው ፡ በቸልተኝነት ፡ ወይም ፡ በተንኰል ፡ ተነሳስተው ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ምንም ፡ ሳያደርጉ ፡ ሲቀሩ ፡ የእነኝህን ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ሰዎች ፡ ጥቅምና ፡ ምቾት ፡ የሚጠብቅ ፡ ባለሥልጣን ፡ መኖሩ ፡ ለሕብረተ ፡ ሰቡና ፡ በተለይም ፡ ለቤት ፡ ዘመድ ፡ አቋም ፡ ጠቃሚ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። በአሁኑ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ አሳዳሪውና ፡ ሞግዚቱ ፡ እንዲሻሩ ፡ ጥያቄ ፡ ያቀረቡት ፡ በቊጥር ፡ ፪፻፹፬ ፡ (፩) ያልተመለከቱት ፡ ሚስተር ፡ ክራመር ፡ ናቸው ።

ሁለተኛው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፪፻፺፫ ፡ የአሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ የሞግዚትነት ፡ ሥራ ፡ እንዲያከናውን ፡ ተመርጦ ፡ የተሾመው ፡ ሰው ፡ ሥራውን ፡ እንዲያከናውን ፡ ግዴታ ፡ አለበት ፡ ይላል ። ምክትል ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በትክክል ፡ እንዳመለከተው ፡ ይህ ፡ ቊጥርና ፡ የሌሎች ፡ ቊጥሮች ፡ በተለይም ፡ የቊጥር ፡ ፪፻፲፯ ፡ እና ፡ ፪፻፲፰ ፡ መንፈስ ፡ በግልጽ ፡ እንደሚያሳዩን ፡ የአሳዳሪነት ፡ ሥራ ፡ ከባድ ፡ ኃላፊነት ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ግዴታ ፡ የተጣለበትም ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ግዴታውን ፡ እንደፈለገው ፡ ሊያስቀረው ፡ አይችልም ። አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሰ ፡ ሰው ፡ አሳዳሪ ፡ እንዲሆን ፡ የተሾመ ፡ ሰው ፡ የሚሻረው ፡ አንዳንድ ፡ የተለዩና ፡ ጥብቅ ፡ የሆኑ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሲኖሩ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አሳዳሪው ፡ የሚሻረው ፡ የአሳዳሪነት ፡ ሥራውን ፡ የሚያከናውነው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ በሚጐዳ ፡ መንገድ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የልጅቷ ፡ ወላጆች ፡ ኃላፊነታችን ፡ ቢቀርልን ፡ አንቃወምም ፡ ማለታቸው ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ አይሆንም ። ይህ ፡ በቂ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ አቋም ፡ ይፈርስ ፡ ነበር ።

ሦስተኛ ፡ ቊጥር ፡ ፪፻፲፯ ፡ እና ፡ ፪፻፲፰ ፡ ወላጆች ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ዳኞች ፡ ሞግዚት ፡ ለመሾም ፡ መቻላቸውን ፡ ያስረዳሉ ። እነዚህ ፡ ቊጥሮች ፡ ስለአሳዳሪ ፡ መሾም ፡ አይናገሩም ። አንዳንድ ፡ ወላጆች ፡ የልጃቸውን ፡ ንብረት ፡ በሚገባ ፡ ለማስተዳደር ፡ ሳይችሉ ፡ ሲቀሩ ፡ የልጁን ፡ ንብረት ፡ የሚያስተዳድር ፡ አንድ ፡ ሞግ

ዚት ፡ መሾም ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ አሳዳሪነት ፡ የወላጆች ፡ ግዴታ ፡ ሆኖ ፡ የሚ ቀር ፡ ነው ።

ምክትል ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ላቀረበው ፡ መቃወሚያ ፡ ሚስተር ፡ ክራመር ፡ በሰጡት ፡ መልስ ፡ የልጅቷ ፡ ወላጆች ፡ የአሳዳሪነትና ፡ የሞግዚትነት ፡ ሥራቸውን ፡ ባለመፈጸማቸው ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፲፭ ፡ መሠረት ፡ እንደሞቱ ፡ መቆጠር ፡ አለባቸው ፡ ብለዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ቍጥር ፡ የሚለው ፡ ወላጆች ፡ የአስተዳዳሪነትና ፡ የሞግዚትነት ፡ ሥራቸውን ፡ ለማከናወን ፡ ችሎታ ፡ ሲያጡ ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ ይቆጠራሉ ፡ ነው ። የአሳዳሪነትና ፡ የሞግዚትነት ፡ ግዴታ ፡ የተጣለበት ፡ ሰው ፡ ግዴታውን ፡ ባለመፈጸሙ፡ ብቻ ፡ ከግዴታው ፡ ራሱን ፡ ነፃ ፡ እንዲያደርግ ፡ ይህ ፡ ቍጥር ፡ አይፈቅድለትም ። እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፴፫ ፡ ይህን ፡ በግልጽ ፡ ያስረዳል ። ቍጥር ፡ ፪፻፲፭ ፡ የሚመለከተው ፡ የአሳዳሪነት ፡ ወይም ፡ የሞግዚትነት ፡ ሥራውን ፡ ለማከናወን ፡ በሕመም ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ስለተከለከለ ፡ ወይም ፡ እነኚህን ፡ በመሳሰሉ ፡ ምክንያቶች ፡ ችሎታ ፡ ያጣን ፡ ሰው ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፲፭ ፡ መሠረት ፡ እንደሞተ ፡ ተቆጥሮ ፡ አስፈላጊው ፡ የአሳዳሪና ፡ የሞግዚት ፡ ሹመት ፡ እላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ቁጥሮች ፡ በተለይም ፡ ከዘመዶች ፡ መሐል ፡ ምርጫ ፡ ሲደረግ ፡ ሊከተሉት ፡ ስለሚገባው ፡ ተራ ፡ እና ፡ ይህ ፡ ተራ ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባዔ ፡ ሊለወጥ ፡ ስለሚችልበት ፡ መንገድ ፡ በሚናገሩት ፡ ቍጥሮች ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፲ ፡ እና ፡ ፪፻፲፮ ፡ መሠረት ፡ ይከናወናል ። አሁን ፡ ለያዝነው ፡ ጉዳይ ፡ በእነዚህ ፡ በተጠቀሱት ፡ ቍጥሮች ፡ ከተጠቀምን ፡ እነዚሁ ፡ ቍጥሮች ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ስላልተሠራባቸው ፡ ብቻ ፡ ልጅቷ ፡ ያለአሳዳሪና ፡ ያለሞግዚት ፡ ቀርታለች ፡ ብንል ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ አይሆንም ። ስለዚህ ፡ ሚስተር ፡ ክራመር ፡ ሞግዚትና ፡ አሳዳሪ ፡ ሆነው ፡ እንዲሾሙ ፡ ያቀረቡት ፡ የመጀመሪያ ፡ ጥያቄያቸው ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፲፪ ፡ መሠረት ፡ የቀረበ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አንችልም ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ምክንያቶች ፡ መቃወሚያቸው፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

ምናልባት ፡ የታኅሣሥ ፡ ፲ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ምሕረቱን ፡ ትእዛዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሰጠው ፡ ልጅቷ ፡ በገንዘብ ፡ (በንብረት) ፡ በኩል ፡ የምታገኘውን ፡ ጥቅም ፡ በማየት ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ በማድረጉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሱ ፡ ልጆች ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለቤተ ፡ ሰብ ፡ አቋም ፡ ጥቅምም ፡ የወጡትን ፡ ግልጽና ፡ የማያጠራጥሩ ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሳይጠቀምባቸው ፡ አልፏል ።

እላይ ፡ የተሰጡትን ፡ ምክንያቶች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የምክትል ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉን ፡ ማመልከቻ ፡ ተቀብለን ፡ ታኅሣሥ ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ሽረነዋል ። የዚህን ፡ ትእዛዝ ፡ ግልባጭ ፡ ሚስተር ፡ ክራመር ፡ በአስቸኳይ፡ ለአቶ ፡ ፋፋ ፡ ደሬሳና ፡ ለወይዘሮ ፡ ዘርፍነሽ ፡ ለማ ፡ እንዲሰጡ ፡ ይሁን ።

የካቲት ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡

HIGH COURT

Addis Ababa, Civil Division No. 1

Judges:

(Judges' names not reported)

IN THE MATTER OF THE GUARDIANSHIP AND TUTORSHIP OF ALMAZ FUFA, A MINOR.

Civil Case No. 132/56

Capacity of persons — Guardians and tutors — Cessation of the functions of guardian and tutor — Appointment by Court of guardian and tutor — Removal of guardian and tutor — Civil Code Arts. 210, 211, 212, 217, 218, 223, 234*(1)*.

In a petition submitted by the Attorney General by virtue of the powers vested in him under Art. 234(1) of the Civil Code, moving this High Court to quash its order of Tahsas 8, 1956, in which it appointed a guardian and tutor for a minor.

Held: Petition allowed and order quashed.

1. Under Art. 234(1) of the Civil Code, an application for the removal of a guardian or of a tutor may be made only by a relative by consanguinity or by affinity of the minor, or by the public prosecutor.

2. Guardianship is a duty of parents and not simply a right or a privilege which can easily be waived. The courts are enjoined by Art. 233 to declare only with extreme caution the removal of the father or mother or other ascendants as guardians or tutors of their children or descendants.

3. Arts. 217 and 218 do not apply to the appointment of a guardian. Guardianship remains with the parents of a minor.

4. Art. 215 does not allow a person in whom the duty of guardian and tutor is vested to renounce such duty, or be presumed dead, as a result of not fulfilling it.

By an Order dated Tahsas 8, 1956, this Court appointed Mr. Leslie H. Cramer as the guardian and tutor of Almaz Fufa, a minor, the legitimate daughter of Fufa Deressa and Woizero Zerfinesh Lemma. This Order was made on the application of Mr. Leslie H. Cramer, who, in his application, stated that the said child was placed in his custody on Hidar 1950 (Eth.Cal.) by her father, 33 years old, a peasant residing in the village of Metti, as he was divorced from his wife and had no means of supporting the child; that since the said Mr. Cramer had taken custody of the child, he had looked after her as his own child and had fed, clad and sent her to school, and moreover he had made financial arrangement for her future; that the child was then about nine years old and had been living with him for five years or more and as he had no child of his own he wished to keep the child indefinitely and as her parents were satisfied with the care and treatment given to the child they had agreed that the child be entrusted to Mr. Cramer in the interest and welfare of the child.

The Court heard the evidence of the father of the child, Ato Fufa Deressa who stated that the child, Almaz Fufa, was his child born on February 11, 1955 (Gr.Cal.) in wedlock with his wife Woizero Zerfinesh Lemma, that the child remained with the parents for two years and as his sister was a maidservant employed by Mr. Cramer the child was brought to Mr. Cramer who had taken responsibility for the child; he (the witness) and his wife were divorced. The mother, Woizero Zerfinesh Lemma, confirmed the statement made by her husband and both parents said they were satisfied that the child continue to be under the responsibility of Mr. Cramer.

It should also be stated that Mr. Leslie H. Cramer had applied to the Court for the adoption of the child, but as he is married and his wife had not given her consent, Article 798 of the Civil Code was an objection to the making of an order of adoption. The record shows that Mr. Cramer stated that there may be a divorce from his wife and then he will adopt the child.

The Deputy Attorney General has now submitted a petition to this Court moving the Court to quash the order made on Tahsas 8, 1956. The petition is made in virtue of the powers vested in him by Article 234(1) of the Civil Code and the grounds of the petition may be summarised as follows:

(a) under Article 223 of the Civil Code guardianship is a duty of parents and not simply a right or a privilege which can be easily waived; guardianship is a duty and he who is vested with it can only relinquish it in rare and exceptional circumstances.

(b) Article 233 enjoins the Court to declare only with extreme caution the removal of the father or mother or of the other ascendants as guardians or tutors of their children or descendants;

(c) under Article 217 the father or mother may, where they think fit, appoint a tutor to the child, reserving to themselves the functions of guardian, and under Article 218 the Court may for good cause appoint as tutor a person other than the guardian, where it has the right to make such appointment; these articles provide for the appointment of a tutor but not of a guardian.

Mr. Leslie H. Cramer, duly notified of the petition of the Acting Attorney General, submitted a reply dealing with questions of fact and with questions of law. As to questions of fact he submitted that the Court in making the Order of Tahsas 8, 1956 had ascertained that the child Almaz Fufa had been abandoned by her parents and since the age of two she has been looked after by Mr. Cramer who provided care, maintenance and education; that the parents were divorced and had no means to look after the child, that Mr. Cramer not having a child of his own wanted to adopt the child and as there was not the consent of his wife he had no alternative left to secure the future of the child, by acquiring property, for her until he divorces his wife and is able to adopt the child officially. On points of law Mr. Cramer submitted that as the parents had not shown any interest in the child they had ceased to exercise the functions of tutors and guardians and under Article 215 they were to be presumed dead and therefore as the child remained without a guardian and tutor such functions devolved on persons appointed by the Court under Article 212 and it was under this article that the Court appointed Mr. Cramer as the guardian and tutor of Almaz Fufa; for these reasons the Order of Tahsas 8, 1956 should be upheld in its entirety.

It should be mentioned that the Deputy Attorney General stated in the oral argument before the Court that his petition was made because in his opinion the Court was wrong in making the Order of Tahsas 8, 1956, and that, as this was the first case of its kind since the promulgation of the Civil Code, the Order of Tahsas 8, 1956 would create a bad precedent in the interpretation of the Code.

Now, the petition of the Deputy Attorney General is not concerned with the facts, or with the question whether the Court investigated the facts fully and thoroughly to find out whether it is in the interest of the child that the Order be made. The petition of the Deputy Attorney General is attacking the legality of the Order on purely legal grounds. But as the reply to the petition mentions certain facts it is expedient to deal with these points.

In the first place it is stated that the parents of the child have no means to provide for the child; the record of the Court does not show that any evidence was available to show that this is so; it may be that the child is better looked after now than if the parents fulfilled their duties within their means; secondly it is stated that Mr. Cramer has made financial arrangements for her future; again there is no evidence what arrangements have been made. The Court seems also to have borne in mind that Mr. Cramer had stated that he was about to get a divorce from his wife; but there is nothing on the record to indicate that there is a ground for divorce or that proceedings have been initiated; the Court assumed that a divorce would be granted and that then the adoption of the child would be possible. The Court seems also to have been influenced by the declaration made by the parents to the effect that they were satisfied with the existing situation and that they had no objection to being relieved of any future responsibility for the child. The father of the child said the he was divorced from his wife; it is not clear when the divorce took place but it seems to have taken place before the coming into force of the Civil Code, before the institution of the family arbitrators with power to decide about the custody of children had been established.

As stated above, however, the opposition of the Deputy Attorney General is based not on the question whether the facts on which the Court relied were correct or not; his opposition is on points of law, procedure and substantive. In the first place Article 234(1) of the Civil Code provides that the removal of the guardian or of the tutor may be made by any relative of the minor, by consanguinity or by affinity, or by the public prosecutor. The reason for this is obvious; the relatives of the minor are the persons who are closely acquainted with the manner in which tutorship or guardianship is exercised and it is in the interest of the child that the lawful guardian or tutor be removed when those functions are exercised to the detriment of the child's moral or material interest. The public prosecutor is given the same rights as the relatives because it is in the interest of society at large and of the family institution in particular that there should be some authority to protect the moral welfare and the material interests of all minors when there are no relatives who can take action or where the relatives through negligence or for fraudulent motives or for some other reason do not move. In this particular case the application for removal of the guardian and tutor was made by Mr. Cramer who is not one of the persons contemplated in Article 234(1) of the Civil Code.

Secondly, Article 223 of the Civil Code provides that the functions of a guardian or tutor of a minor are compulsory for the person who is vested with them. As the Deputy Attorney General rightly pointed out this article and the spirit of other articles particularly Articles 217 and 218 show clearly that guardianship is a

duty, and a heavy duty at that and he who is vested with this duty cannot relinquish it at his pleasure; a person can be removed from such duties only in rare and exceptional circumstances, that is when the duty is exercised against the moral and material welfare of the minor. It is not sufficient, therefore, for the parents of a child to say that they do not mind being relieved of any responsibility for their child; if it were so the whole concept of the family insitution, as established in Ethiopia, would collapse.

Thirdly, Articles 217 and 218 provide for the appointment of a tutor by the parents or, in certain circumstances, by the Court, these articles do not deal with the appointment of a guardian. There may be cases where the parents are not competent to administer properly any property which the child may have; then in such cases a tutor may be appointed to safeguard the material interest of the child, but the guardianship remains with the parents.

In his reply to the Deputy Attorney General's motion, Mr. Cramer submitted various points; he stated that the parents of the child had ceased to function as guardians and tutors of the child and therefore under Article 215 they are presumed to be dead. What that article says is that when the parents become incapable of performing their duties as guardians and tutors then they are presumed to be dead; that article does not allow a person in whom the duty of guardian and tutor is vested to renounce such duty simply by not exercising it. The article referred to above, that is Art. 233, makes that very clear. Article 215 is intended to cover those cases where a tutor or guardian, becomes incapable of exercising the functions by reason of illness, judicial interdiction and similar cases. In such cases, under that article, a person is to be deemed to be dead and the procedure for the appointment of a guardian and tutor shall apply as specified in the previous articles, (particularly Articles 210 and 211, which deal with the order amongst relatives, to be followed in the appointment, and with modifications to be made to such order by the family council). It is not correct to say that in this case the child remained without a guardian and tutor after applying the said articles, simply because the said articles were not put into operation; therefore, it cannot be said that the original petition for guardianship and tutorship made by Mr. Cramer was made under Article 212. For the above reasons, the objections are not valid at law.

It may be that in making the Order of Tahsas 8, 1956, the Court was guided by the worthy motive of the material welfare of the child, but the fact remains that in doing so the Court side-stepped clear and definite provisions of law, which take into consideration not only the material benefits of minors but also the institution of the family.

For the above reasons the Court allows the petition of the Deputy Attorney General and quashes the Order made on Tahsas 8, 1956. A copy of this Order shall be served on Ato Fufa Deressa and Woizero Zerfinesh Lemma by Mr. Leslie H. Cramer without delay.

Yekatit 2, 1956. E. C.

አንቀጾች ።

“በሕግ ፡ ሳይታወቁ ፡ የሚሠሩ” (“ዲ ፡ ፍክቶ”) ፡ እና ፡ ልማዳዊ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ።

ከፖል ፡ ማካርቲ ።

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አብዛኛው ፡ ክፍሉ ፡ በአውሮፓውያን ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተውን ፡ አንድ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አዘጋጅቶ ፡ አወጣ ። ይህ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አያሌ ፡ አዳዲስ ፡ ፅንሰ ፡ አሳቦችን ፡ የያዘ ፡ ሲሆን ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ ፅንሰ ፡ አሳቦች ፡ ውስጥም ፡ አብዛኞቹን ፡ አሻሽሎአል ። የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ፅንሰ ፡ አሳብ ፡ ከነዚህ ፡ ከተሻሻሉት ፡ ፅንሰ ፡ አሳቦች ፡ አንዱ ፡ ነው ። ሁለት ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በአንድነት ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ የሚያካሂዱባቸው ፡ ድርጅቶች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ከዋሉ ፡ አያሌ ፡ ዘመናት ፡ አልፈዋል ። የእነዚህ ፡ “የሽርክና ፡ ማኅበሮች” ፡ አቋሞች ፡ እና ፡ የሚመለከቱአቸው ፡ የየቀበሌው ፡ ደንቦች ፡ በጣም ፡ የተለያዩ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። ከ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም፡ በፊት ፡ እነዚህን ፡ ድርጅቶች ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ ለማጠቃለል ፡ የተደረገው ፡ ማንኛውም ፡ ሙከራ ፡ አጥጋቢ ፡ ውጤት ፡ ሳያገኝ ፡ ቀርቶአል ። እንደ ፡ አስራ ፡ አምስተኛው ፡ መቶ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ራቅ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡[1] ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሙሉ ፡ ምዕራፍ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ደንቦች ፡ ተጽፈዋል ። በቢዛንታየን ፡ የሕግ ፡ ፅንሰ ፡ አሳቦች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተው ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥቱ ፡ መደበኛ ፡ (“ኦፊሴላዊ”) ሕግ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመንግሥቱ ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ ራቅ ፡ ባሉት ፡ ቦታዎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉ ፡ ያጠራጥራል ። የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ሕግ ፡ ለንግድ ፡ ድርጅቶች፡ ለሽርክና ፡ ማኅበሮችም ፡ ጭምር ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ ለማውጣት ፡ የተደረገውን፡ ሙከራ ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በኢጣሊያን ፡ ወረራ ፡ ምክንያት ፡ የአገር ፡ ውስጥ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ እንዲካሄድ ፡ የተደረገው ፡ ሙከራ ፡ ኢምንት ፡ ነበር ።

በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ሕጉን ፡ የማይከተሉበት ፡ ሕጉም ፡ እነርሱን ፡ የማይመለከትበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ። በአንድ ፡ ሕግ ፡ (የንግድም ፡ ሆነ ሌላ) ፅንሰ ፡ አሳብ ፡ መሠረት ፡ ሕጉ ፡ በመስኩ፡ውስጥ ፡ የሚገኙትን፡ጉዳዮች፡ሁሉ፡ማጠቃለል ፡ አለበት ። ስለዚህ ፡ ፓርላሜንቱ ፡ የንግድ ፡ ሕጉን ፡ ሲያጸድቀው ፡ ሊደርስበት፡ የአሰበው ፡ ግብ ፡ ይህ ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ እንችላለን ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ መቅድም ፡ ውስጥ ፡ ሕጉ ፡ “የንግድን ፡ ድርጅቶች ፡ አቋምና ፡ ተግባር ፡ የሚደነግግ ---” ነው ፡ ብለዋል ። ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የተፈጠሩት ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ሁሉ ፡ ሕጉ ፡ ከጸናበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ በስድስት ፡ ወራት ፡ ውስጥ ፡ ሕጉ ፡ የሚያዘውን ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ ነበረባቸው ። የንግድ ፡ ሕጉ ፡ መኖር ፡ ሳይታወቅ ፡ የተፈጠሩ ፡ የንግድ ፡ ግንኙነቶች ፡ የአሁኑ ፡ ሕጋዊ

1. ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ምዕራፍ ፡ ፴፱ ።

ነታቸው ፡ እንዲረጋገጥ ፡ ከንግድ ፡ ሕጉ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጋራ ፡ መስማማት ፡ አለባቸው፤ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በልማዳዊ ፡ ደንቦች ፡ አይሠሩም ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ሲታይ ፡ ልማዳዊ ፡ ድርጅቶች ፡ አሁንም ፡ አሉ ። ስለዚህ ፡ ዋናው ፡ ፕሮብሌም ፡ እነ ዚህን ፡ ድርጅቶች ፡ የሚያጠቃልሉና ፡ ከንግድ ፡ ሕጉ ፡ ጋራ ፡ የሚስማሙ ፡ ድንጋጌ ዎችን ፡ ማግኘቱ ፡ ነው ።

የንግድ ፡ ሕጉን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለመፈጸም ፡ አስበው ፡ "የሽርክና ፡ ማኅበሮችን ፡" ካቋቋሙ ፡ በኋላ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ የተባሉትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ የማይፈጽሙ ሰዎች ፡ ይገኛሉ ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የውሉን ፡ በጽሑፍ ፡ መሆን ፡ ምዝገባንና ፡ በማስታወቂያ ፡ መግለጽን ፡ የሚመለከቱትን ፡ አስፈላጊ ፡ የመቋቋሚያ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሳይፈጽሙ ፡ ይቀራሉ ። እነዚህን ፡ ድንጋጌዎች ፡ አለመፈጸም ፡ የሚያ ስከትለው ፡ ውጤት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ይተነተናል ። ለጊዜው ፡ ተዋዋዮቹ ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ ውስጥ ፡ የተገለጸው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሽርክና ፡ ማህበር ፡ እንዲቋቋም ፡ ስለፈ ቀዱ ፡ ማህበሩ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማህበር ፡ መታየት ፡ አለበት ፡ ለማለት ፡እን ችላለን ። አንድ ፡ ዓይነት ፡ ልማዳዊ ፡ ድርጅትን ፡ በአእምሮአቸው ፡ ውስጥ ፡ በቀረጹት፡ በሁለት ፡ (ወይም ፡ ከሁለት፡በላይ፡በሆኑ፡) ሰዎች ፡ መካከል፡የሚደረገውን ፡ አንድ ፡ ዓይ ነት ፡ ውል ፡ በምንመለከትበት ፡ ጊዜ ፡ ሁኔታው ፡ ትንሽ ፡ ለየት ፡ ያለ ፡ ይሆናል ። እዚ ህ ፡ ላይ ፡ በሰዎቹ ፡ አእምሮ ፡ የተቀረጸውን ፡ ድርጅት ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ለመቍጠር ፡ ይቻላል ፡ ወይስ ፡ አይቻልም ፡ የሚ ለውን ፡ "አግባብ ፡ ያለው" ጥያቄ ፡ መጠየቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ድርጅቱ ፡ የሽርክና ፡ ማሕበሮችን ፡ በሚመለከቱት ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ከተቋቋመ ፡ ልክ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ የንግድ ፡ ሕጉ ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዲሆንበት ፡ ፈቅደው ፡ እንዳቋቋ ሙት ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማህበር ፡ መተዳደር ፡ አለበት ። የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ አባባል ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመስሉትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ድርጅቶችን ፡ ይመለ ከታል ፡ ወይ ?

<u>አሁን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ።</u>

በኢትዮጵያውያን ፡ መካከል ፡ ስለሚፈጸሙት ፡ የንግድ ፡ ግንኙነቶች ፡ የተደረገው ጥናት ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነው ። የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ጸሐፊ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በሚገኙት ፡ ጉራጌ ፡ ነጋዴዎች ፡ መካከል ፡ ስለሚገኙት ፡ የንግድ ፡ ግንኙነቶች ፡ ቅንጅት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ጥናት ፡ አድርጎአል ። ቢሆንም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ይህ ፡ የጉራጌ ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። የጉራጌው ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ የተ መረጠበት ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ነው ፡— ከላይ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ ሁኔታ ፡ የተደረገ ፡ ጥናት ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ማንኛውም ፡ መረጃ ፡ ሊገኝ ፡ የሚችለው ፡ ከነጋዴዎች ፡ ጋር ፡ በሚደረገው ፡ ውይይት ፡ ነው ። በተ ጨማሪ ፡ የሽርክና ፡ ማሕበሮች ፡ በሌሎች ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡ በዐረቦች ፡ በሕንዶ ችም ፡ ዘንድ ፡ የሚገኙ ፡ ቢሆኑም ፤ በጉራጌዎች ፡ መካከል ፡ በብዛት ፡ የሚሠራባቸው ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ናቸው ። በመጨረሻም ፡ ጉራጌዎች ፡ ቁጥራቸው ፡ አነስተኛም ፡ ቢሆን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከሚካሄደው ፡ ንግድ ፡ ከፍተኛውን ፡ ክፍል ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የምንነጋገርባቸውን ፡ ሕጋዊ ፡ መለኪያዎች ፡ በተመሳሳይ ፡ ሁኔታዎችም ፡ ልንጠቀምባቸው ፡ እንችላለን ። የጉራጌዎች ፡ የንግድ፡ድር ጅት ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ምሳሌ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ይቀርባል ።

እላይ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ጉራጌዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ንግድ ፡ የሚያካሄዱት ፡ በሽ ርክና ፡ ማህበር ፡ አማካይነት ፡ ነው ። አንድ ፡ ነጋዴ፡ ንግድ፡ ለመጀመር፡ ሲያስብ ፡ ንግዱን

የሚያካሂድለትን ፣ አንድ ፣ ታማኝ ፣ ሰው ፣ ይፈልጋል ። የዚህን ፣ ዓይነት ፣ ሰው ፣ ሲያገኝ ፣ አንደኛው ፣ ሥራውን ፣ እንዲያካሄድ ፣ ሁለተኛው ፣ ደግሞ ፣ ገንዘብ ፣ እንዲያዋጣ ፣ ተስማምተው ፣ ንግዱን ፣ ይጀምራሉ ። የሚታመን ፣ ሰው ፣ ካልተገኘ ፣ ነጋዴው፣ አንድ ፣ ሰው ፣ ቀጥሮ ፣ ንግዱን ፣ እንዲያካሄድለት ፣ ያደርጋል ። አብዛኛውን ፣ ጊዜ ፣ የዚህ ፣ ዓይነቱ ፣ አቋም ፣ ፍሬያማ ፣ ከሆነ ፣ ሁለቱ ፣ ወገኖች ፣ ተስማምተው ፣ አንድ ፣ የሽርክና ፣ ማሕበር ፣ ያቋቁማሉ ።[2]

ይህን ፣ በመሰለ ፣ ስምምነት ፣ መሠረት ፣ ሁለቱ ፣ ወገኖች ፣ ትርፉንና ፣ ኪሳራውን ፣ ይካፈላሉ ። ራሳቸውንም ፣ በአንድነት ፣ የንግድ ፣ ድርጅቱ ፣ ባለቤቶች ፣ እንደሆኑ ፣ ይቆጥራሉ ፤ ውሳኔም ፣ አብረው ፣ ለመስጠት ፣ ይችላሉ ። የስምምነቱ ፣ ጊዜ ፣ አልቆ ፣ ብድር ፣ ሁሉ ፣ ከተከፈለ ፣ በኋላ ፣ ያዋጡት ፣ ካፒታል ፣ በዓይነት ፣ ሳይሆን ፣ በዋጋው ፣ መጠን ፣ ይመለስላቸዋል ። ቀሪውንና ፣ የድርጅቱን ፣ ዋጋ ፣ ጭማሪ ፣ ማኅበረተኞቹ ፣ በውለታቸው ፣ መሠረት ፣ ይካፈላሉ ። የሆነ ፣ ሆኖ ፣ የተለያዩ ፣ ሁኔታዎች ፣ ሊኖሩ ፣ ይችላሉ ። አንዳንዴ ፣ ሁለቱም ፣ ወገኖች ፣ እኩል ፣ ካፒታል ፣ ሲያዋጡ ፤ አንዳንዴ ፣ ደግሞ ፣ መጠኑ ፣ የተለያየ ፣ ካፒታል ፣ ያዋጣሉ ። የንግዱ ፣ ድርጅት ፣ ትልቅ ፣ ሲሆን ፣ ማኅበረተኞቹ ፣ ከሁለት ፣ ሰዎች ፣ በላይ ፣ ሆነው ፣ ይገኛሉ ። የሆነ ፣ ሆኖ ፣ በእንደዚህ ፣ ዓይነቱ ፣ ሁኔታ ፣ እንኳን ፣ አብዛኛውን ፣ ጊዜ ፣ መዋጮው ፣ የንግድ ፣ ድርጅቱን ፣ የማካሄድ ፣ ጥበብ ፣ ብቻ ፣ ሆኖ ፣ የሚገኝ ፣ አንድ ፣ ወገን ፣ ይኖራል ።

በጸሐፊው ፣ እምነት ፣ መሠረት ፣ ከላይ ፣ የተገለጠው ፣ የንግድ ፣ አቋም ፣ በንግድ ሕጉ ፣ ውስጥ ፣ ከተጠቀሱት ፣ የሽርክና ፣ ማህበሮች ፣ አንዱ ፣ ስለሆነ ፣ የንግድ ፣ ሕግ ፣ ተፈጻሚ ፣ እንዲሆንበት ፣ ያስፈልጋል ። የንግድ ፣ ሕጉ ፣ የሽርክና ፣ ማኅበር ፣ ውልን ፣[3] እንደሚከተለው ፣ ይገልጻል ፥— "የሽርክና ፣ ማኅበር ፣ ውል ፣ ማለት ፣ ሁለት ፣ ወይም ፣ ብዙ ፣ ሰዎች ፣ መዋጮ ፣ አዋጥተው ፣ በአንድነትና ፣ በሕብረት ፣ የኤኮኖሚ ፣ ተግባር ፣ ያለው ፣ ሥራ ፣ ለመሥራትና ፣ ከሚገኘው ፣ ትርፍም ፣ ሆነ ፣ ከሚመጣው ፣ ዕዳ ፣ ተካፋይ ፣ ለመሆን ፣ የሚስማሙበት ፣ ውል ፣ ነው ።"[4] ይህ ፣ ገለጻ ፣ ለጉራጌ ፣ ልማዳዊ ፣ የንግድ ፣ አቋም ፣ መሠረት ፣ የሆኑትን ፣ ነጥቦች ፣ ሁሉ ፣ የያዘ ፣ ነው ።

---

2. እንደዚህ ፣ ዓይነቱ ፣ ከቀጣሪ ፣ ተቀጣሪ ፣ ግንኙነት ፣ ወደ ፣ ሽርክና ፣ ማኅበር ፣ ግንኙነት ፣ የመለወጡ ፣ ዘዴ ፣ ከመቅጽበት ፣ የሚደረግ ፣ ባይሆንም ፣ የጉራጌዎቹ ፣ ምርጫ ፣ ወደ ፣ ሁለተኛው ፣ የሚያዘነብል ፣ ነው ። ይህ ፣ የሚሆንበትን ፣ ትክክለኛውን ፣ ምክንያት ፣ ለማወቅ ፣ አዳጋች ፣ ቢሆንም ፣ የሽርክናው ፣ ማኅበር፣ ውል፣ የሚይዘውን ፣ መልክ ፣ መሠረት ፣ በማድረግ ፣ ምክንያቱን ፣ በከፊል ፣ ለማጠቃለል ፣ ይቻል ፣ ይሆናል ። እንደዚህ ፣ ያለው ፣ ስምምነት ፣ በልማድ ፣ የሚፈጸመው ፣ በጉርዳ ፣ መልክ ፣ ነው ። ስለ ፣ ጉርዳ ፣ ዝቅ ፣ ብለን ፣ በሰፊው ፣ እንነጋገራለን ። ቢሆንም ፣ ይህ ፣ ቃል ፣ በልማድ ፣ "የወዳጅነት ፣ መተሳሰር" ተብሎ ፣ ይተረጐማል ። በአንደኛው ፣ ወገን ፣ የተወሰደ ፣ ማንኛውም ፣ ዓይነት ፣ የሌላውን ፣ ወገን ፣ ጥቅም ፣ የሚያቃውስ ፣ እርምጃ ፣ እንደ ፣ ከባድ ፣ የግዳጅ ፣ ማፍረስ ፣ ተግባር ፣ ተቆጥሮ ፣ ከሰው ፣ አቅም ፣ በላይ ፣ በሆነ ፣ ኃይል ፣ እማካይነት ፣ የቤተ ፣ ሰብ ፣ ሕመምን ፣ የንብረት ፣ ጥፋትንና ፣ ሞትን ፣ የመሳሰሉትን ፣ ቅጣቶች ፣ እንደሚያስከትል ፣ ይታመናል ። እንደዚህ ፣ ያለው ፣ ውል ፣ በቀጣሪውና፣ በተቀጣሪው ፣ መካከል ፣ ይህን ፣ ያህል ፣ ጥብቅነት ፣ ካለው ፣ ቀጣሪው ፣ ነጋዴ ፣ ተቀጣሪውን ፣ የሽርክና ፣ ማኅበርተኛ ፣ ቢያደርግ ፣ የሚያገኘውን ፣ ጥቅም ፣ ያሳያል ። በሌላ ፣ መንገድ ፣ ስንመለከተው ፣ ደግሞ ፣ "የወዳጅነት ፣ መተሳሰር" ፣ መኖሩ ፣ ውሉን ፣ በማይተዋወቁ ፣ ሰዎች ፣ መካከል ፣ ጥቅም ፣ እንዳይሰጥ ፣ ያደርገዋል ፣ ማለት ፣ ነው ።
3. "የሽርክና ፣ ማኅበር ፣ ውል" ማንኛውም ፣ ዓይነት ፣ የንግድ ፣ ማኅበር ፣ የሚቋቋምበት ፣ ውል ፣ እንጂ ፣ የሽርክና ፣ ማኅበር ፣ ብቻ ፣ የሚቋቋምበት ፣ ውል ፣ አይደለም ። የንግድ ፣ ሕግ ፣ ቍ-፪፻፲ ፣ (፩)ን ፣ ይመለከቷል ።
4. ከዚያው ፣ ቍ ፪፻፲፩ ። በፕሮፌሰር ፣ ኤስካራ ፣ የመጀመሪያ ፣ ረቂቅ ፣ ውስጥ ፣ ("የንግድ ፣ ድርጅት") የሚል ፣ አንድ ፣ ትርጉም ፣ ብቻ ፣ ነበረው ፣ ነገር ፣ ግን ፣ ሕግ ፣ አዘጋጂው ፣ (የፍትሐ ፣ ብሔሩ) ፣ ኮሚሲዮን ፣ ማኅበሩን ፣ ማኅበሩ ፣ ከሚመሠረትበት ፣ ውል ፣ ለመለየት ፣ ይህን ፣ ትርጓሜ ፣ ለወጥ ፣ አድርጎታል።

በመጀመሪያ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ "በአንድነትና ፡ በሕብረት ፡ --- ለመሥራት"[5] መስማ ማት ፡ አለባቸው ። ይህም ፡ በንግዱ ፡ ጉዳይ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በእኩልነት ፡ ደረጃ ፡ ተካፋዮች ፡ ለመሆን ፡ ይችላሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። አንደኛው ፡ ወገን ፡ እንኳን ፡ የአስ ተዳዳሪነት ፡ ሥልጣን ፡ ቢሰጠው ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በከፍተኛ ፡ ውሳኔዎች ፡ ላይ፡ ተካፋዮች ፡ ይሆናሉ ። ይህ ፡ የንግድ ፡ ይዞታ ፡ ከብድር ፡ ውል ፡ ወይም ፡ ከኪራይ ፡ የተለየ ፡ ነው ። ብድርና ፡ ኪራይ ፡ በከፊል ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የሽርክና ፡ ማኅ በር ፡ ውል ፡ ቢመስሉም ፡ አበዳሪውና ፡ አከራዩ ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ ተካፋይነት ፡ የተወሰነ ፡ ነው ።[6] በተጨማሪም ፡ በብድርና ፡ በኪራይ ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ያሉአቸው ፡ ዓላማዎች ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ፤ ይህም ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ የሌላውን ፡ ፍላጐት ፡ በሚቃረን ፡ መንገድ ፡ የሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ይኖራል ፡ ማለት ፡ ነው ። በሽርክና ፡ ማሕበር ፡ ግን ፡ ማሕበረተኞቹ ፡ ሁሉ ፡ በሥራው ፡ መካፈልና ፡ ለተ መሳሳይ ፡ ግብ ፡ መሥራት ፡ አለባቸው ። የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ከሥራ፡ ውልም፡ የተለየ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ በሠራተኛው ፡ በኩል ፡ የበታችነትን ፡ ስለሚያመለክት ፡ ነው ። በማሕበረተኞች ፡ መካከል ፡ ግን ፡ የበላይነትና ፡ የበታች ነት ፡ አቋም ፡ አይገኝም ።[7] ሁለተኛ ፡ ሁሉም ፡ ወገኖች ፡ ለንግዱ ፡ ድርጅት ፡ መዋጮ ማድረግ ፡ አለባቸው ። ከላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ በጉራጌዎች ፡ መካከል ፡ አንደኛው ወገን ፡ የካፒታል ፡ መዋጮ ፡ ሲያደርግ ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ የአገልግሎት ፡ መዋጮ ያደርጋል ። ሁለቱም ፡ ዓይነት ፡ መዋጮዎች ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ።[8] ሶስተኛ ፡ የድርጅቱ ፡ ግብ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ተግባር ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ መፈጸም ፡ መሆን አለበት ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጠቀስናቸው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ የሚያከናውኑት ፡ የጉራጌ ፡ የ "ሽርክና ፡ ማኅበሮች" የዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ተግባር ፡ ያላቸው ፡ መሆናቸው ፡ የማይ ካድ ፡ ነው ።[9] በመጨረሻ ፡ አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማሕበር ፡ ውል ፡ የትርፍንና ፡ የኪሣ ራን ፡ መካፈል ፡ ጉዳይ ፡ መመልከት ፡ አለበት ። ይህ ፡ በጉራጌ ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሕጋዊ ፡ ግንኙነት ፡ "ትርፎችን ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለመከፋ ፈል ፡ ሳይሆን"[10] የሚቋቋም ፡ ተራ ፡ ማኅበር ፡ አይደለም ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ብድሮች ፡ ኪራዮች ፡ ወይም ፡ የሥራ ፡ ውሎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ትርፍን ፡ የሚያከፋፍሉ ፡ ሆነው ፡ ሲገኙ ፡ ኪሣራን ፡ ግን ፡ ዘወትር ፡ የማያከፋፍሉ ፡ መሆናቸውን ፡ መግለጽ ፡ ያስፈልጋል ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተደረገው ፡ ገለጻ ፡ የጉራጌ ፡ የንግድ ፡ ግንኙነቶች ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈውን ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ እንደሚመስሉ ፡ ያስረዳል ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ ራሳቸውን ፡ እንደ ፡ "ማኅበረተኞች" ፡ ከሚቆጥሩት ፡ ከወገኖቹ ፡

5. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ "ኢፌክቲዮ ፡ ሶሲታቲስ" ፡ በመባል ፡ ይጠራል ። ኤስካራ ፡ <u>ኩር ፡ ደ ፡ ድሯ ፡ ኰሜ ርሲያል ፡</u> (፪ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. እ. ኤ. አ.) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፲፪ ፡ ይመለከቷል ።
6. በቂ ፡ ገንዘብ ፡ ለሌላቸው ፡ ኩባንያዎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የገንዘብ ፡ ብድር ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ አበዳሪው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ኩባንያውን ፡ በመምራት ፡ ረገድ ፡ የተግባር ፡ ተካፋይ ፡ እንደሚሆን ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አበዳሪው ፡ እንደ ፡ ሽርክና ፡ ማኅበርተኛ ፡ መቆጠሩ ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ። ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍ. ፭ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ኤስካራን ፡ ገጽ ፡ ፫፻፲፪ ፡ ይመለከቷል ።
7. ስለነዚህ ፡ ልዩነቶች ፡ ዝርዝር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍ. ፭ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ኤስካራን ፡ ከገጽ ፡ ፫፻፲ ፡ እስከ ፡ ፫፻፲፫ ፡ ይመለከቷል ።
8. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፹፱ ፡ (፩) ።
9. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፭ ፡ እንደ ፡ "ንግድ" ከተገለጹት ፡ ሥራዎች ፡ አንዱን ፡ ወይን ም ፡ ከአንድ ፡ የበለጡትን ፡ ሲሠሩ ፡ ይገኛሉ ።
10. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ ፬፻፬ ። ማኅበሮቹ ፡ የኢኮኖሚ ፡ ተግባር ፡ ያላቸውን ፡ ሥራዎች ፡ በማከና ወን ፡ ትርፍ ፡ ለማስገኘት ፡ የተመሠረቱ ፡ አይደሉም ።

ምኞት ፡ ጋራ ፡ የሚስማማ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ድርጅቶቹ ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ በተለይም ፡ እንደ ፡ ሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ መቆጠር ፡ አለባቸው ።[11] ቢሆንም ፡ እነ ዚህ ፡ ማኅበሮች ፡ ሁለት ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ የማይፈጽሙ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ።

በመጀመሪያ ፡ እነዚህ ፡ ውሎች ፡ ቍ ፡ ፪፻፲፬ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ በጽሑፍ ስለማይፈጸሙ ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ።[12] ፡ የጉራጌ ፡ የሽር ክና ፡ ማሕበሮች ፡ የሚቋቋሙት ፡ "የቈጥ ፡ ጉርዳ" በሚል ፡ ሥያሜ ፡ በሚታወቅ ፡ ውል፡ነው። (ቀጥተኛ፡ትርጓሜውም፡ "በንግድ ፡ የወዳጅነት ፡ መተሳሰሪያ" ማለት ፡ ነው፡) ይህ ፡ ውል ፡ የሆነውን ፡ ያኽል ፡ እራሱን ፡ የቻለ ፡ ልማዳዊ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትም ፡ ነው ። በሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ግዴታን ፡ ያስከትላል ። ሁለቱ ፡ (ወይም ፡ ከሁለት ፡ በላይ፡ የሆኑ) ወገኖች ፡ በ"ዳኛ" ፡ (ሽማግሌ)[13] ፊት ፡ ደጋግመው ፡ የተሰፉ ፡ ቃሎችን ፡ ይለዋወጣሉ ። ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ አለመግባባት ፡ ሲፈጠር ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ወደ ፡ ዳኛው ፡ ይሄዳሉ ። ስለዚህ ፡ የሽማግሌው ፡ ሥራ ፡ በምስክርነት ፡ ብቻ ፡ የሚወሰን ፡ አይ ደለም ። ውሉን ፡ በማይፈጽመው ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ መቅሰፍት ፡ ይወርዳል ፡ ተብሎ ፡ ይታ መናል ።[14] የዚህ ፡ ዓይነቱ፡በቃል ፡ የሚፈጸም ፡ ውል ፡ የሚገኘው ፡ ምናልባት ፡ በጉራ ጌዎች ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የሚያትተው ፡ በጽሑፍ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ውሎች ፡ ሳይሆን ፡ "በሥራ ፡ በአገልግሎት ፡ ወይም ፡ በቃል ፡"[15] ስለሚፈጸሙ ፡ የሽርክና ፡ ማሕበሮች ፡ ነው ። እነዚህ ፡ የሽርክና ፡ ማሕ በሮች ፡ በተጻፈ ፡ ውል ፡ ስላልተቋቋሙ ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ። በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ውሉ ፡ እንደሌለ ፡ ተቆጥሮ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ከመዋዋላቸው ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ነበ

11. እነዚህ ፡ አመዳደቦች ፡ ማንኛውንም ፡ ዓይነት ፡ የተወሰነ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ (ካፒታል) ካለማጠቃለላቸ ውም ፡ ሌላ ፡ የያንዳንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ አላፊነት ፡ እንደ ፡ አክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ (የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፫፻፭) ፡ ወይም ፡ የተወሰነ ፡ ኃላፊነት ፡ እንዳለው ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ (የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፭፻፲) ፡ የተወ ሰነ ፡ አይደለም ። ዓላማው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፮ ፡ ትርጓሜ ፡ መሠረት ፡ ንግድ ፡ ነክ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። (የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፲፫) ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ እሽሙር ፡ ማኅበር ፡ የማንኛውም ፡ አባል ፡ ማኅበርተኝነት፡ በድብቅ ፡ አይቀመጥም ፡ (የንግድ ፡ ሕግ፡ ቍ. ፪፻፸፪ ፡ (፩)) ። ስለዚህ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ኅ ብረት ፡ ሽርክና ፡ ማኅበር ፡ መቆጠር ፡ ሲኖርበት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ማማሾቹ ፡ ማኅበርተኞች ፡ የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ሲኖርባቸው ፡ እንደ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ አላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ መቆጠር ፡ አለበት ።

12. ቍ. ፪፻፲፬ ፡ "አይጸናም"፡ ይላል ። ይህ ፡ ቃል ፡ "ፈራሽ ፡ ነው" የሚለው ፡ ሐረግ ፡ የሚሰጠውን ፡ ትር ጉም ፡ ይሰጣል ፡ የሚለው ፡ ክርክር ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ይቀርባል ።

13. ዳኛው ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ይህንን ፡ ጉርዳ ፡ ለምን ፡ ትፈልጋላችሁ ፡ በማለት ፡ ጥያቄ ፡ ያቀርባል ። ሁለቱም፡ ወገኖች ፡ "ሽርክና ፡ እንዲኖረን" ብለው ፡ ይመልሳሉ ። ዳኛው ፡ ቀጠል ፡ አድርጎ ፡ "ይኼ፡ የአርጀርና፡ የወርቲን ፡ ጉርዳ ፡ ነው" ይላል ። (አርጀርና ፡ ወርቲን ፡ የጉርዳን ፡ ውል ፡ የተዋዋሉ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው) ። ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ መልሰው ፡ ይህንኑ ፡ ይናገራሉ ። ደግሞ ፡ በተጨማሪ ፡ ዳኛው ፡ "ይህንን ፡ ጉርዳ ፡ ያፈረሳችሁ ፡ እንደሆን ፡" ሲል ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ "በመስቀል ፡ ቀን ፡ ቡትቶ ፡ ለብሼ ፡ ቅርሜት ፡ ተሸክሜ ፡ እርስዎ ፡ ቤት ፡ (ዳኛው፡ ቤት) ልመና፡ እንድመጣ፡ ያድርገኝ" ይላሉ። እነዚህን፡ ጥያቄዎችና ፡ መልሶች ፡ ሶስት ፡ ጊዜ ፡ ይደጋግማሉ ። በመጨረሻም ፡ ዳኛው ፡ "ጉርዳው ፡ ውላችሁን ፡ ከማፍረስ፡ ይጠብቃችሁ" በማለት ፡ መርቆ ፡ ያሰናብታቸዋል ።

14. ማስታወሻ ፡ ቍ. ፪ን ፡ ከላይ፡ ይመለከቷል ። በተጨማሪም ፡ ከዊልያም ፡ ኤ ሻክ፡ የተደረሰ ፡ ዘ ፡ ጉራጌ ፡ የሚለውን ፡ በአክስፎርድ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ፕሬስ ፡ በ፲፱፻፷፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የታተመ ፡ መጽሐፍ ፡ ይመለከ ቷል። "የቈጥ ፡ ጉርዳ" ለከፍተኛ ፡ የንግድ ፡ ውሎች ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ መሬት ፡ ሽያጭ ፡ ላሉ ፡ ውሎች ፡ የሚጠቅም ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ በነፍስ ፡ ግዳይ ፡ ጊዜ ፡ እርቅ ፡ የሚደረግበት ፡ "የደም" ወይም ፡ "የአንጀት" ጉርዳ ፡ እና ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ጉዳት ፡ እንዳያደርስ ፡ ቃል ፡ የሚገቡበት ፡ "የርብረት" ፡ ጉርዳ ፡ አሉ ።

15. ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ምዕራፍ ፡ ፴፩ ።

ሩበት ፡ ሁኔታ ፡ እንዲመለሱ ፡ መደረግ ፡ አለበት ። ቢሆንም ፡ የ"ሽርክና ፡ ማኅበሮቹ" አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሲሠሩ ፡ የቆዩ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የውል ፡ ፈራሽነት ፡ ደንቦች ፡ የተወሳሰበውን ፡ ሁኔታ ፡ አጥ ብቀው ፡ መመልከት ፡ አለባቸው ።

ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ እነዚህ ፡ የሽርክና፡ማኅበሮች፡ቁ ፡ ፪፻፲፱ ፡ በሚያዘው ፡ መሠ ረት ፡ በማስታወቂያ ፡ የወጡና ፡ የተመዘገቡ ፡ አይደሉም ። የንግድና ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ እንዲመዘገቡ ፡ ጥረት ፡ አድርጎ ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ አሁን ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ አሥር ፡ ሺ ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ተመዝግበው ፡ ይገኛሉ ። ከነዚህ ፡ መካከል ፡ አራት ፡ መቶዎቹ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ናቸው ።[16] ይህ ፡ ቊጥር ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ቊጥር ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ነው ። ይህ ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፡ ነጋዴዎች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በማኅበርተኛነት ሳይሆን ፡ በግል ፡ ስማቸው ፡ ስለሚመዘገቡ ፡ ነው ። የመመዝገብ ፡ ሥርዓት ፡ በኢትዮ ጵያ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ስለሆነ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ጊዜን ፡ ይጠይ ቃል ።[17] የንግድ ፡ ድርጅቶችን ፡ አለማስመዝገብ ፡ በቊ ፡ ፪፻፳፫ ፡ እንደሚከተለው ፡ የተጻፈውን ፡ ውጤት ፡ ያስከትላል ፡- "አንድ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ መኖሩም ፡ የሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ መሆኑም ፡ በሕግ ፡ አይታወቅለትም ።"

የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ውልን ፡ በጽሑፍ ፡ አለማድረግ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበ ሩን ፡ አለማስመዝገብ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤቶች ፡ መመርመር ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዓላማ ፡ ነው ። የጽሑፉ ፡ መሪ ፡ አሳብ ፡ ማኅበሮቹን ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ሕግ ፡ የሽርክና ፡ ማሕበሮች ፡ መቁጠርና ፡ የሕጉን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በሙሉ ፡ ባለመፈጸማቸው ፡ ከሌሎች ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ጥቂት ፡ ለየት ፡ አድርጎ ፡ መመልከት ፡ ነው ። "በሕግ ፡ ሳይታ ወቊ ፡ የሚሠሩ" ("ዲ ፡ ፋክቶ") የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ብለን ፡ ልንሰይማቸው ፡ እን ችላለን ። በጽሑፍ ፡ ያልተደረገ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ስለማይመዘገብ ፡ በመ ጀመሪያ ፡ የምንነጋገረው ፡ ስላልተመዘገቡ ፡ "በሕግ ፡ ሳይታወቁ ፡ የሚሠሩ" ፡ ("ዲ ፡ ፋክቶ") የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ፡ ነው ። ቀጥለን ፡ በጽሑፍ ፡ ስላልተደ ረገ ፡ የሽርክና ፡ ማህበር ፡ ውል ፡ ውጤት ፡ እንነጋገራለን ።

> ቊ ፡ ፪፻፳፫ ፡ "በመዝገብ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መግባት ፡ የተደነገጉት ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተጠናቅቀው ፡ እስኪፈጸሙና ፡ መመዝገቡም ፡ በዚ ሀ ፡ ሕግ ፡ ቊ ፹፯ ፡ መሠረት ፡ ታትሞ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ የንግ ድ ፡ ማኅበር ፡ መኖሩም ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ መሆ ኑም ፡ በሕግ ፡ አይታወቅለትም ።"

<u>በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡—</u> በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግና ፡ በን ግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የመብትና ፡ የግዴታ ፡ ባለቤቶች ፡ ሊሆኑ ፡ የሚችሉት ፡ "ሰዎች" ብቻ ፡ ናቸው ። ቢሆኑም ፡ በሕጎቹ ፡ ውስጥ ፡ "ሰዎች" ተብለው ፡ የሚጠሩት ፡ ሰብ አዊ ፡ ፍጡሮች ፡ ብቻ ፡ አይደሉም ። ሕጉ ፡ ለድርጅቶችም ፡ የሰውነት ፡ አቋም ፡ ሰጥ ቷቸዋል ። ለምሳሌ ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተቆጥሮ ፡ የመብቶችና ፡ የግ ዴታዎች ፡ ባለቤት ፡ ተደርጓል ።[18] እነዚህ ፡ ድርጅቶች ፡ የሰውነት ፡ አቋም ፡ የተሰጣ

---

16. ከ፪፻ ፡ የአክስዮን ፡ ማኅበሮች ፡ ከ፬፻ ፡ ኃላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበሮችና ፡ ከ፱፻ ፡ የግል ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ጋራ ፡ ሲነጣጠር ።

17. የሽርክና ፡ ማኅበሮችን ፡ የመመዝገብ ፡ ጽንሰ ፡ አሳብ ፡ በመጀመሪያ ፡ የተወረሰው ፡ ከ፲፱፻፴፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሀረት ፡ የኩባንያዎች ፡ ሕግ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አልተሰራባቸውም ።

18. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊ. ፫፻፺፬ ።

ቸው ፡ በሕጉ ፡ አማካይነት ፡ ስለሆነ ፡ "ሕጋዊ" ሰዎች ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ። የሽርክና ፡ ማኅበርም ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ የሚያዘውን ፡ ፈጽሞ ፡ ሲገኝ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰው፡ነው ።[19] በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ የተለየ ፡ አንድ ፡ ፍጡር፡ ይሆናል ። የንብረት ፡ ባለቤት ፡ መሆንንና ፡ ንብረትን ፡ መሸጥና ፡ መለወጥ ፡ የመሰሉትን ፡ ተግባሮች ፡ እንደ ፡ ሰዎች ፡ ሆኖ ፡ ሊፈጽም ፡ ይችላል ።

ለሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ የሰውነት ፡ አቋምን ፡ የመስጠት ፡ ተግባራዊ ፡ ጥቅም ፡ የሚታወቀው ፡ ማሕበሩ ፡ በሚፈርስበትና ፡ ሒሳብ ፡ በሚጣራበት ፡ ወቅት ፡ ነው ።[20] ማኅበሩ ፡ አንድ ፡ እራሱን ፡ የቻለ ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ የንብረቱ ፡ ባለቤት ፡ የሚሆነው ፡ ማኅበሩ ፡ እንጂ ፡ ማሕበርተኞቹ ፡ አይደሉም ። ከማሕበሩ ፡ ጋር ፡ የንግድ ፡ ግንኙነት ፡ የሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ የማሕበሩ ፡ ባለ ፡ ገንዘቦች ፡ ወይም ፡ ባለ ፡ ዕዳዎች ፡ ይሆናሉ ። ባለ ፡ ገንዘቦች ፡ ገንዘባቸውን ፡ በመጨረሻ ፡ ከማኅበርተኞቹ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ቢኖራቸውም ፤ ገንዘባቸው ፡ እንዲከፈላቸው ፡ በመጀመሪያ ፡ መጠየቅ ፡ ያለባቸው ፡ ማኅበሩን ፡ እንጂ ፡ ማኅበርተኞችን ፡ አይደለም ።[21]

ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ በቂ ፡ ንብረት ፡ ያለው ፡ የአንድ ፡ የሽርክና ፡ ማሕበር ፡ ሂሳብ ፡ በሚጣራበት ፡ ጊዜ ፡ ባለገንዘቦች ፡ መጀመሪያ ፡ ከማሕበሩ ፡ ንብረት ፡ ይከፈላሉ ።[22] ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ለማሕበረተኞች ፡ የመጀመሪያው ፡ መዋጮ ፡ ዋጋ ፡ ታስቦ ፡ ይከፈላቸዋል ። (ያዋጡት ፡ ንብረት ፡ እራሱ ፡ እንዲመለስላቸው ፡ ለማድረግ ፡ አይችሉም) ።[23] ይህ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ቀሪ ፡ የሚሆነው ፡ ትርፍ ፡ ተብሎ ፡ ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በተቀር ፡ ለማኅበረተኞቹ ፡ በትክክል ፡ ይከፈላል ።[24] የማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ግን ፡ በቂ ፡ በማይሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ሂሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ ማሕበርተኞቹ ፡ መዋጮ፡ በማድረግ ፡ ባለገንዘቦችን ፡ እንዲከፍሉ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።[25]

በዚህ ፡ የአከፋፈል ፡ ተራ ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ ሕጉ ፡ የማኅበሩ ፡ ባለገንዘቦች ፡ ከማሕበረተኞች ፡ በፊት ፡ እንዲከፈሉ ፡ ማድረጉ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ባለገንዘቦች ፡ ከማኅበረተኞችና ፡ በማኅበረተኞችም ፡ በኩል ፡ ከሚጠየቁ ፡ ሰዎች ፡ ቅድሚያ ፡ ተሰጥቶአቸዋል ። ይህ ፡ ቀደምትነት ፡ የተመሠረተው ፡ የማኅበሩን ፡ የተለየ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ በሚፈጥር ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የማሕበሩ ፡ ባለገንዘቦች ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ቀድመው ፡ ከማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ለመካፈል ፡ መብት ፡ አላቸው ። ያንድ ፡ ማኅበርተኛ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ከማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ እንዲከፈለው ፡ በቀጥታ ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ የለውም ። ሊከፈል፡ የሚችለው፡ ከባለዕዳው ፡ ማኅበርተኛ ፡ ንብረት ፡ ነው ። ይህም ፡ ንብረት ፡ ማኅበረተኛው ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ንብረት ፡ የሚጨምር ፡ ነው ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ የአንድ ፡ ማሕበረተኛ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ከማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ እንዲከፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በአከፋፈል ፡ ቅድሚያ ፡ ስለሚሰጣቸው ፡ የግል ፡ ባለገንዘቦች ፡ የሚከፈሉት ፡ የማኅበሩ ፡ ገን

---

19. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቊ. ፪፻፲ ፡ (፪) ።
20. ጀ፡ ሪፔር ፡ ትሬቴ ፡ ኤሌሜንቴር ፡ ደ ፡ ድሯ ፡ ኰሜርሲያል ፡ (፫ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፶፬) ፡ ገጽ ፡ ፪፻፳፰ ።
21. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቊ. ፪፻፲፬ ።
22. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቊ. ፪፻፳፰ ። ማኅበረተኞች ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ከሆኑ ፡ ገንዘባቸው ፡ ይከፈላቸዋል ፡ ግን ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ከተከፈላቸው ፡ በኋላ ፡ ነው ።
23. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቊ. ፪፻፳፱ ።
24. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቊ. ፪፻፴ ፡ (፩) (፫) ።
25. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቊ. ፪፻፳፰ ፡ (፩) ።

ዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ከተከፈሉ ፡ በኋላ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የግል ፡ ባለገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ ንብረት ፡ ባለዕዳው ፡ ማሕበርተኛ ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ንብረት ፡ መጠን ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ ሀ ፡ ለ ፡ እና ፡ ሐ ፡ ከቍጥር ፡ ፪፻፳፫ ፡ እና ፡ በጠቅላላው ፡ ከንግድ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ያቋቁሙ ። ሀ ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ ከመ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ይበደራል ። አሁን ፡ ባለዕዳው ፡ ማኅበሩ ፡ እንጂ ፡ ሀ ፡ ለ ፡ ወይም ፡ ሐ ፡ አይደሉም ። መ ፡ እንዲከፈል ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ ከማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ነው ። በተጨማሪ ፡ በምሳሌአችን ፡ ውስጥ ፡ ሀ ፡ ከሠ ፡ ላይ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ተበድሯል ፡ እንበል ። ሀ ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ ንብረት ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ ሃብት ፡ የለውም ። መ ፡ ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የሚከፈለው ፡ ለማኅበርተኞቹ ፡ ንብረቱ ፡ ከመከፋፈሉ ፡ በፊት ፡ ነው ። ሠ ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ የሀ ፡ ንብረት ፡ እንዲከፈለው ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ። ሆኖም ፡ ሠ ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የሚጠቀመው ፡ በሀ ፡ መብት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሠ ፡ የሚከፈልው ፡ መ ፡ ከተከፈለ ፡ በኋላ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ መ ፡ ከተከፈለ ፡ በኋላ ፡ የማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ካለቀ ፡ ሠ ፡ ሳይከፈል ፡ ይቀራል ። ቀሪ ፡ ንብረት ፡ ካለ ፡ ግን ፡ ሠ ፡ የሚከፈለው ፡ ሀ ፡ ከሚያገኘው ፡ የንብረት ፡ ክፍያ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ማሕበሩ፡ የሶስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ንብረት ፡ ቢኖረው ፡ መ ፡ በመጀመሪያ ፡ ሺ ፡ ብሩን ፡ ይከፈላል ። ቀሪው ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ በማኅበረተኞች ፡ መካከል ፡ ይከፋፈላል ። ሌላ ፡ ስምምነት ከሌለ ፡ በስተቀር ፡ ሶስቱ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ከሁለቱ ፡ ሺ፡ብር፡ሲሶ ፡ ሲሶ፡ይደርሳቸዋል ። ይኸውም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ስልሳ ፡ ስድስት ፡ ብር ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህ፡ አከፋፈል ፡ ሀ ፡ የሚያገኘው ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ስልሳ ፡ ስድስት ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ሠ ፡ የሚያገኘውም ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ እጦት ፡— በቍ. ፪፻፳፫ ፡ እንደተመለከተው ፤ አንድ የሽርክና ፡ ማሕበር ፡ ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ አይኖረውም ፡ ማለት ፡ ማኅበሩ ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ የተለየ ፡ ሆኖ ፡ አይቆጠርም ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ ሁለት ፡ መልክ፡ ያለው ፡ ውጤትን ፡ ያስከትላል ። ለማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ባለቤት ፡ የሚሆን ፡ ሕጋዊ ፡ ሰው ፡ ስለሌለ ፤ የንብረቱ ፡ ባለቤቶች ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ይሆናሉ ። ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ከማኅበሩ ፡ ጋር ፡ ቀጥተኛ ፡ ግንኙነት ፡ ስላላደረጉ ፤ ገንዘብ ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችሉት ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ ነው ።

በምሳሌ ፡ ለመግለጽ ፡ ሀ ፡ ለ ፡ እና ፡ ሐ ፡ ቍ ፡ ፪፻፳፫ ፡ የሚያዘውን ፡ ሳይፈጽሙ ፡ አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማሕበር ፡ አቋቋሙ ፡ እንበል ። ሀ ፡ በማኅበሩም ፡ ስም ፡ ሳደረገው ፡ የንግድ ፡ መለዋወጥ ፡ ማኅበሩ ፡ ለ መ ፡ የአንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ባለዕዳ ፡ ይሆናል ። ማሕበሩ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ቢቋቋም ፡ ኖሮ ፡ መ ፡ ገንዘቡን ፡ ከማኅበሩ ፡ ለመጠየቅ ፡ በቻለ ፡ ነበር ። በምሳሌያችን ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ማኅበሩ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰው ፡ ለመሆን ፡ አልበቃም ፡ ስላልን ፤ መ ፡ ገንዘቡን ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ ከሀ ፡ ከለ ፡ እና ፡ ከሐ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እያንዳንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ሶስት ፡ መቶ ፡ ሰላሳ ፡ ሶስት ፡ ብር ፡ የመክፈል ፡ ግዴታ ፡ ይኖርበታል ።

አሁን ፡ ደግሞ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰውነትን ፡ የተነፈገው ፡ ማኅበር ፡ ሂሣቡን ፡ ሲያጣራ ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ እንመልከት ። እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የንብረቱ ፡ ባለቤት ፡ ስለሆነ ፡ ንብረት ፡ የማከፋፈል ፡ ጉዳይ ፡ ሊነሳ ፡ አይችልም ። እያንዳንዱ ፡ ማሕበረተኛ ፡ የመዋጮውን ፡ ዋጋ ፡ ይሰጣል ። ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ የቀረው ትርፍ ፡ ሆኖ ፡ ለማኅበረተኞቹ ፡ በትክክል ፡ ይከፈላል ። የማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ገንዘባቸው ፡ ከማሕበረተኞቹ ፡ ንብረት ፡ እንዲከፈላቸው ፡ ለማድረግ ፡ ይች

ላሉ ። የሰውነት ፡ መብት ፡ መነፈግ ፡ ሀን ፡ ለን ፡ እና ፡ ሐን ፡ ለመቅጣት ፡ የታሰበ ፡
እንጂ ፡ ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁትን ፡ እንደ ፡ መ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ያሉትን ፡
ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ለመቅጣት ፡ የታቀደ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ባሁኑ ፡ ምሳሌ ፡ መ ፡
ማኅበሩን ፡ በቀጥታ ፡ ለመክሰስ ፡ ከፈለገ ፡ እንዲፈቀድለት ፡ ያስፈልጋል ። በሌላው ፡
በኩል ፤ መ ፡ ማኅበረተኞቹን ፡ በቀጥታ ፡ለመጠየቅ ፡ ይችላል ። በአንደኛውም ፡ ሆነ
በሁለተኛው ፡ መንገድ ፤ መ ፡ ጠቅላላ ፡ ገንዘቡ ፡ ከተገኘው ፡ ንብረት ፡ እንዲከፈለው ፡
ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

የሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ መብት ፡ እጦትም ፡ ትርጉም ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ የሚታየው ፡
ከማኅበረተኞቹ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ በሚኖሩበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ወደ ፡ ምሳ
ሌያችን ፡ እንመለስና ፡ ሀ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ከሠ ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ተበድሯል ፡ እን
በል ። እላይ ፡ ማኅበሩ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ ሲሰጠው ፡ ከማሕበሩ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡
ክፍሎች ፡ እንደ ፡ ሠ ፡ ካሉት ፡ ሰዎች ፡ ያከፋፈል ፡ ቅድሚያ ፡ እንደሚሰጣቸው ፡ አይ
ተናል ። ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ "በማኅበሩ ፡ ስም ፡ የተያዘ ፡ ንብረት"
እንደሌለ ፡ አይተናል ። ስለዚህ ፡ ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎችና ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡
የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ገንዘባቸውን ፡ ለመካፈል ፡ የሚችሉት ፡ ከማኅበርተኞቹ፡
ንብረት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በምሳሌአችን ፡ ውስጥ ፡ መ ፡ የተባለው ፡ የማሕበሩ ፡ ባለገ
ንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ መጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ ንብረት ፡ ብቻ ፡ ነው ።
መ ፡ ከሚጠየቀውም ፡ ገንዘብ ፡ ገሚሱ ፡ የሚከፈለው ፡ ከሀ ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ነው።
ሠም ፡ ከሀ ፡ ንብረት ፡ ለመከፈል ፡ ተመሳሳይ ፡ መብት ፡ አለው ። ሠ ፡ ለማኅበሩ ፡
ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ አለመኖር ፡ ኃላፊ ፡ ስላልሆነ ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ለመጠቀም ፡ ይች
ላል ። "ማኅበሩ" የሶስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ንብረት ፡ አለው ፡ ብለን ፡ እናስብ ። በሕጋዊ ፡
ሰውነት ፡ አለመኖር ፡ ምክንያት ፡ ግን ፡ ትርጉሙ ፡ እያንዳንዱ ፡ ማሕበረተኛ ፡ አንድ ፡
ሺ ፡ ብር ፡ አለው ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሀ ፡ የአንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ንብረት ፡ አለው
ማለት ፡ ነው ። መ ፡ ከያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የገንዘቡ ፡ አንድ ፡ ሶስተኛ ፡ እንዲከፈ
ለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ስለሚችል ፡ ከሀ ፡ ላይ ፡ ሶስት ፡ መቶ ፡ ሰላሳ ፡ ብር ፡ ለመጠየቅ ፡
ይችላል ። ሠ ፡ ደግሞ ፡ ከሀ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ። ሀ ፡ ሌላ፡
ንብረት ፡ ከሌለው ፡ ሠ ፡ ከሀ ፡ ላይ ፡ የሚቀበለው ፡ የዕዳውን ፡ ሶስት ፡ አራተኛ ፡ ወይም
ሰባት ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ ብር ፡ ነው ። መ ፡ ደግሞ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ ብር ፡ ይቀበ
ላል ።(ባለፈው ፡ ምሳሌያችን ፡ ሠ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰላሳ ፡ ስድስት ፡ ብር ፡ እንደሚያ
ገኝ ፡ አይተን ፡ ነበር ።)

<u>የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ይመዝገቡ ፡ የተባለበት ፡ ምክንያት ፡</u> — እስካሁን ፡ ድረስ
ስለ ፡ ቍ ፡ ፪፻፳፫ ፡ ያቀረብነው ፡ አስተሳሰብ ፡ ትክክልነት ፡ እንዳለው ፡ ለማረጋገጥ ፡
ሕግ ፡ አውጭው ፡ ክፍል ፡ ቍ ፪፻፳፫ን ፡ ሲደነግግ ፡ የነበረውን ፡ አሳብ ፡ ማወቅ ፡ ያስ
ፈልጋል ።

አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበርን ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ መንፈግ ፡ የሚያስከትለው ፡ የመ
ጀመሪያው ፡ ውጤት ፡ ለግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ እና ፡ ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ለሚጠ
ይቁት ፡ ሰዎች ፡ በአከፋፈል ፡ ረገድ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ደረጃ ፡ መስጠት ፡ ነው ። ይህ
ውጤት ፡ የደረሰው ፡ ማኅበረተኞች ፡ ማኅበሩን ፡ ባለማስመዝገባቸውና ፡ ባለማ
ስታወቃቸው ፡ ስለሆነ ፡ ማኅበሮች ፡ ይመዝገቡ ፡ የሚለው ፡ ደንብ ፡ ግላዊ ፡ ገንዘብ ፡
ጠያቂዎችን ፡ ከማሕበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ አብልጦ ፡ ለመጠበቅ ፡ የተደነገገ ፡

ይመስላል ።[26] የማኅበሮች ፡ አለመመዝገብ ፡ ግላዊ ፡ ባለገንዘቦችን ፡ አብልጦ ፡ የሚጐዳ፡ ይመስላል ፡ ቢሆንም ፡ አስቀድመን ፡ ይህ ፡ አስተያየት ፡ ትክክለኛ ፡ መሆኑን ፡ መመርመር ፡ አለብን ።

ከሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ የማኅበሩ ፡ መመዝገብና ፡ በማስታወቂያ ፡ መውጣት ፡ ሊጠቅማቸው ፡ ይችላል ፡ ምክንያቱም ፡ የሚፈልጉትን ፡ መረጃ ፡ አለብዙ ፡ ችግር ፡ ከንግድ ፡ መዝገቡ ፡ ለማግኘት ፡ ስለሚችሉ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ማኅበሩ ፡ በእርግጥ ፡ መኖሩን ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ እነማን ፡ እንደሆኑና ፡ የመዋጮአቸውን ፡ ዋጋ ፡ ከንግድ ፡ መዝገብ ፡ ለማግኘት ፡ ይችላሉ ።[27] እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከአንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡[28] ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ሲያደርግ ፡ ግንኙነቱን ፡ የሚፈጽመው ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ አማካይነት ፡ ስለሆነ ፡ የዚህን ፡ ሰው ፡ ሥልጣን ፡ ማወቅ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። የኅብረት ፡ ሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ሥልጣን ፡ የሚወሰነው ፡ በማኅበሩ ፡ የሥራ ፡ ግብ ፡ መጠን ፡ ነው ።[29] የማኅበሩ ፡ የሥራ ፡ ግብ ፡ የሚገኘው ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።[30] ይህን ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ የሚወስን ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ዋጋ ፡ የሚኖረው ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ሲሰፍር ፡ ወይም ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ማወቃቸው ፡ ሲረጋገጥ ፡ ነው ።[31] ይህ ፡ ደንብ ፡ በይበልጥ ፡ የሚረዳው ፡ ማኅበሩን ፡ ነው ፡ ምክንያቱም ፤ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ባያውቁም ፡ ማኅበረተኞች ፡ በሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ ወሰን ፡ ማድረግ ፡ ስለሚችሉ ፡ ነው ።[32] የማኅበሩ ፡ አለመመዝገብ ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ውጤት ፡ አያስከትልም ፤ ምክንያቱም ፡ በማስታወቂያ ፡ ያልወጣ ፡ ነገር ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለማይሆን ፡ ነው ። በማኅበሩም ፡ መመዝገብ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የሚያጡት ፡ ነገር ፡ የለም ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የንግድ ፡ መዝገቡ ፡ ከማኅበሩ ፡ ጋር ፡ የንግድ ፡ ግንኙነት ፡ ለማድረግ ፡ ለሚመኙት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በቂ ፡ መረጃ ፡ ለመስጠት ፡ ቢችል ፡ ባለመመዝገቡ ፡ ማሕበሩን ፡ ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ መንፈግ ፡ በቂ ፡ ቅጣት ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ አይመስልም ።

የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎችን ፡ ጉዳይ ፡ ስንመለከት ፡ ሁኔታው ፡ የተለየ ፡ ይሆናል። ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ካለው ፡ ድርጅቱ ፡ ራሱ ፡ የንብረት ፡ ባለቤት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የግል ፡ ንብረቱን ፡ ለማኅበሩ ፡ ቢያዋጣ ፡ የተባለው ፡ መዋጮ ፡ የሽርክናው ፡

26. የመመዝገብ ፡ ዘዴ ፡ ምናልባት ፡ ብዙ ፡ ፖሊሲዎች ፡ አሉት ። ለምሳሌም ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ (ወይም ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ የሥራ ፡ ማኅበሮች ፡) ተመዝግበው ፡ ሲገኙ ፡ ለቀረጥ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ማስረጃ ፡ ያቀርባሉ ። ያልተመዘገቡ ፡ ማኅበሮች ፡ የገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ ይከፍላሉ ። (የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፻፲፭ን ፡ እና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፬፻፷፰ን ፡ ይመለከቷል) ። እንደዚህም ፡ ያለው ፡ ፖሊሲ ፡ ስለ ፡ ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ መከልከል ፡ ማብራሪያ ፡ አይሰጥም ።

27. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፲፰ ።

28. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፳፱ ፡ (፩) (የሕጉን ፡ የአማርኛ ፡ ወይም ፡ የፈረንሣይኛ ፡ ቅጂ ፡ ይመለከቷል)።

29. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፲፰ ፡ (፬) ።

30. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፳፱ ፡ (፪) ።

31. የሽርክናን ፡ ማኅበር ፡ ስለመመዝገብ ፡ ሕግ ፡ በሌለበት ፡ በዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ የሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ስልጣን ፡ መወሰን ፡ በሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ውጤት ፡ የሚኖረው ፡ ሶስተኛው ፡ ወገን ፡ ስለዚሁ ፡ ወሰን ፡ የሚያውቅ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ማስታወቂያ ፡ እንደተሰጠ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ የለም ። ዩኒፎርም፡ ፓርትነርሺፕ ፡ አክት ፡(ዩ፡ ኤስ ፡ ኤ)፡ ቍ. ፱ (፬) ፡ በጁ ፡ ክሬን ፡ ሃንድ ፡ ቡክ ፡ ኦን ፡ ዘ ፡ ሎው ፡ ኦቭ ፡ ፓርትነርሺፕ ፡ (፪ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፶፪) ፡ ውስጥ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፶፫ ።

32. ኤ ፡ ኮርቢን ፡ ኤ ፡ ትራቲይስ ፡ ኦን ፡ ዘ ፡ ሩልስ ፡ ኦቭ ፡ ኰንትራክት ፡ ሎው ፡ (፲፱፻፶፩) ፡ ፫ልዩም፡ ፮ ፡

ማኅበር ፡ ንብረት ፡ ይሆናል ። የማኅበረተኛውን ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ጉዳይ ፡ ስንመለከት ፡ የዕዳዎቹ ፡ ክፍያ ፡ ሊሆን ፡ ይችል ፡ የነበረው ፡ ገንዘብ ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። አሁን ፡ በተባለው ፡ ገንዘብ ፡ ፈንታ ፡ የአለው ፡ ንብረት ፡ ማኅበረተኛው ፡ በማሕበሩ ፡ ውስጥ ፡ የአለው ፡ ድርሻ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ በማኅበረተኛው ፡ መብት ፡ ሊጠቀሙ ፡ ቢችሉም ፡ ይህ ፡ መብት ፡ ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ፡ ዝቅተኛ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹን ፡ ጉዳይ ፡ ስንመለከት ፡ ማኅበረተኛው ፡ ንብረቱን ፡ ዝቅተኛ ፡ ዋጋ ፡ በአለው ፡ ነገር ፡ ለውጦታል ፡ ለማለት ፡ እንችላለን ።

ቍ. ፩፻፺፫፡ለግል፡ገንዘብ፡ጠያቂዎች፡ ከዚህ፡ሁኔታ፡የሚጠበቁበትን፡ አንድ፡ መንገድ፡ ይፈጥራል።የተበዳሪው፡ማኅበረተኛ ፡ ንብረት ፡ የማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ የሚሆነው ፡ ማኅበሩ፡ የተመዘገበና ፡ በማስታወቂያ ፡ የወጣ ፡ ሲሆን ፡ ብቻ፡ነው ። ይህ ፡ በሚሆንበት፡ጊዜ፡የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ማኅበሩ ፡ ከመቋቋም ፡ እንዲታገድ ፡ ለማድረግ ፡ አይችሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ አስቀድሞ ፡ ከባለዕዳው ፡ ማኅበረተኛ ፡ ድርሻ ፡ ላይ ፡ ገንዘባቸው ፡ እንዲከፈላቸው ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ። ይህ ፡ ጠቃሚ ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፡ ማኅበሩ ፡ ተቋቁሞ ፡ ሥራ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ማኅበረተኛው ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ንብረት ፡ እና፡ማኅበሩ ፡ ሳይጀመር ፡ ያዋጣው ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ አንድ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ይህም፡ማኅበሩ፡ሥራ፡ስላልጀመረ፡የባለዕዳው ፡ ማኅበርተኛ ፡ ንብረት፡ሊቀነስ፡አይችልም ፡ ማለት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ ስለሌሉ ፡ በአከፋፈል ፡ ረገድ ፡ የግል ፡ ባለገንዘቡ ፡ ወደ ፡ መጨረሻ ፡ የሚደረግበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ።

ሕጋዊ ፡ ህላዌ ፡ ቍ. ፩፻፺፫ ፡ ላልተመዘገበና ፡ በማስታወቂያ ፡ ላልወጣ ፡ ማኅበር ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ከመንፈጉም ፡ በላይ ፡ "መኖሩም ፡ አይታወቅለትም" ይላል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የቍ. ፩፻፺፫ ፡ ትርጉም ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ፤ ምክንያቱም ፡ ሕጋዊ ፡ ህላዌ ፡ እንደ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ መብት ፡ በአንግሎ - አሜሪካን ፡የሕግ ቅንጅት ፡ ውስጥ ፡ የታወቀና ፡ የማይለወጥ ፡ ትርጉም ፡ ስለሌለው ፡ ነው ። በፈረንሣይ ፡ ሕግም ፡ ሁኔታው ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ። ሕጋዊ ፡ ሕላዌና ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ መገመት ፡ በሕግ ፡ አውጪው ፡ በኩል ፡ እንዳልታሰበበት ፡ ስለሚያስቆጥር ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ትርጉም ፡ ሊኖረው ፡ እንደሚችል ፡ መፈለግ፡ተገቢ ፡ ነው።

ማኅበሩ ፡ "መኖሩም ፡ አይታወቅም" ሲባል፡ሕጉ፡ጭራሽ፡በማኅበሩ፡ጉዳይ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ አያስፈልገውም ፡ ማወቅም ፡ የለበትም ፡ የሚል ፡ ትርጉም ፡ ሊሰጠው ፡ ይችላል ። የዚህ ፡ አስተሳሰብ ፡ ምሳሌ ፡ በአሜሪካን ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። አንድ ፡ ማኅበር ፡ የተቋቋመው ፡ እንደ ፡ ቍማርና ፡ እንደ ፡ ዘረፋ ፡ ላሉት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ተግባሮች ፡ ከሆነ ፡ የአሜሪካን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እነዚህን ፡ ድርጅቶች ፡ ፈጽሞ ፡ ባለማወቃቸው ፡ በማኅበረተኞች ፡ መካከል ፡ ሂሣብ ፡ እንዲጣራ፡ እንኳን፡ ሳይፈቅዱ፡ ቀርተዋል ።[32] የሚገባውን ፡ የማስታወቂያ ፡ ዘዴ ፡ አለመፈጸም ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ያስከትላል ፡ ማለት ፡ ቅጣቱን ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ ስለሚያደርግ ፡ ተገቢ ፡ አተረጓጐም ፡ አይመስልም ።

ሌላ ፡ ትርጓሜ ፡ ደግሞ ፡ ማኅበሩ ፡ "መኖሩ ፡ አይታወቅም" ሲባል ፡ ማኅበሩ ፡ ያለው ፡ ሕጋዊ ፡ ባልሆነ ፡ ሁኔታ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ። ይህ ፡ የታወቀ ፡ ስለሆነ ፡ መደጋገም ፡ አያስፈልግም ፤ ስለዚህ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የተሰጡት ፡ ትርጓሜዎች ፡ አጥጋቢ ፡ አይደሉም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሌላው ፡ ትርጓሜ ፡ ደግሞ ፡ የማኅበሩ ፡ ሕጋዊ ፡ ህላዌ ፡ ማጣት ፡ የማኅበር ፡ ውሉን፡ የማይጸና ፡ ያደርገዋል ፡ የሚል ፡ ነው ። ይህ ፡ አተረጓጎም ፡ ሕጋዊ ፡ ሕላዌ ፡ የተባለውን ፡

ከሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ የመለየት ፡ ጥቅም ፡ አለው ። የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ደንብ ፡ አስደናቂ ፡ ሆኖ ፡ መታየት ፡ የለበትም ፤ ምክንያቱም ፡ እንደ ፡ ፈረንሣይና[33] ፡ እንደ ፡ ሊባኖን ፡[34] ባሉት ፡ አገሮች ፡ አለማስመዝገብ ፡ ስምምነቱን ፡ ፈራሽ ፡ ስለሚያደርገው ፡ ነው ። የውሉ ፡ አለመጽናት ፡ የመጀመሪያና ፡ ዋናው ፡ ውጤት ፡ ውሉን ፡ የማይፈጸም ፡ ማድረጉ ፡ ነው። ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደምናየው ፡ የስምምነት ፡ አለመጽናት ፡ ከሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ መነፈግ ፡ የከበደ ፡ "ቅጣት" ነው ።

ይህ ፡ እንዳይሆን ፡ የሚያደርጉ ፡ ሁለት ፡ ክርክሮች ፡ አሉ ። በመጀመሪያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ "ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ውል ፡ ጉዳይ ፡ የተወሰኑ ፡ የማስታወቂያ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አለመፈጸም፡ ውሉን ፡ ፈራሽ ፡ አያደርገውም፡"[35] ይላል ። ይህ ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ በማይሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ሕጉ ፡ ተመሳሳይ ፡ በሆነ ፡ ግልጽ፡ ቋንቋ ፡ መደንገግ ፡ አለበት ። "መኖሩ ፡ አይታወቅም" የሚሉት ፡ ቃላት ፡ ግልጽ ፡ ስላልሆኑና ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ ውጤቱ ፡ ይህ ፡ እንዲሆን ፡ ከፈቀደ ፡ በግልጽ ፡ ቋንቋ ፡ "ፈራሽ" ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ለመደንገግ ፡ ይችል ፡ ስለነበር ፡ ይህ ፡ ክርክር ፡ ደካማ ፡ ይሆናል ።

ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡ ቍ. ፪፻፲፬ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ቋንቋ ፡ በጽሑፍ ፡ ያልተደረገ ፡ የማኅበር ፡ መቋቋሚያ ፡ ስምምነት ፡ አይጸናም ፡ ይላል ። ሕግ ፡ አውጪው ፡ አለማስመዝገብም ፡ ተመሳሳይ ፡ ውጤት ፡ እንዲኖረው ፡ ፈልጎ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ በተመሳሳይ ፡ ቋንቋ ፡ ይጠቀም ፡ ነበር ። ቍ. ፪፻፴፫ን ፡ ውሉን ፡ እንደማይጸና ፡ እንደሚያደርገው፡ አድርጎ ፡ መተርጎም ፡ ነገሩን ፡ መደጋገም ፡ ይሆናል ። ያልተጻፈ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ሊመዘገብ ፡ አይችልም ። ቍ. ፪፻፳፫ ፡ ውሎች ፡ እንዳይጸኑ ፡ የሚያደርግ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ስላልተጻፉ ፡ ስምምነቶች ፡ ሌላ ፡ ቍጥር ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተገለጸው ፡ መሠረት ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ ማኅበሩ ፡ "መኖሩም"አይታወቅም ሲል ፡ ያልተመዘገቡ ፡ ማኅበሮች ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ የተለየ ፡ ሰውነት ፡ የላቸውም ፡ የሚለውን ፡ በአንክሮ ፡ ለመግለጽ ፡ አስቦ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ያስፈልጋል ።

<u>የሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ መብት ፡ እጦት ፡ በሌሎች ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሕግ ፡ ክፍሎች ፡ ላይ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።</u>

ከላይ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ የሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ መብት ፡ መነፈግ ፡ ዋና ፡ ትርጉሙ፡ የሚታወቀው ፡ ማኅበሩ ፡ ፈርሶ ፡ ንብረቱ ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በሚከፋፈልበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ማኅበሩ ፡ በሚሠራበትም ፡ ጊዜ ፡ የሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ ጉዳይ ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆንባቸው ፡ አንዳንድ ፡ ጥያቄዎች ፡ ሊነሱ ፡ ይችላሉ ። እነዚህም ፡ ስለ ፡ መዋጮ ፡ ጉዳይ ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ሥልጣንና ፡ ስለ ፡ አላፊነት ፡ መወሰን ፡ ናቸው ።

---

33. የጁላይ ፡ ፳፬ ፡ ፲፰፻፷፯ ፡ ሕግ ፡ (የፈረንሣይ) ፡ በዴክር ፡ ኤል ፡ ፴ ፡ ኦክቶበር ፡ ፲፱፻፴፭ ፡ ቍ ፶፰ ፡ በኮድ ፡ ደ ፡ ኮሜርስ ፡ (ፔቲ ፡ ኮድ ፡ ዳሎዝ ፡ ፶፰ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፷፪)፡ ውስጥ ፡ ገጽ ፡ ፶፪ ፡ እንደተሻሻለ ። በመጀመሪያ ፡ የንግድ ፡ ልምድ ፡ ተከትሏል ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ። ይሁን ፡ እንጂ፡ በፈረንሣይ ፡ አገር ፡ የደረሱትን ፡ ችግሮች ፡ ለማስወገድ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፴፫ን ፡ ፕሮፌሰር ፡ ኤስካራ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ በሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ ያስገቡት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ጂዮፍሬ ፡ ነበሩ ።

34. ኮድ ፡ ደ ፡ ኮሜርስ ፡ (ሊባኖስ) ፡ ቍ. ፵፬ ፡ ኢ. ቦስታኒ ፡ ኮድ ፡ ሊባኒስ ፡ ኤን ፡ ቴክስት ፡ ፍራንሴ ፡ (፲፱፻፶፰) ። ይህን ፡ የሚያቀርበውን ፡ ሳይመዘግቡ ፡ የቀሩትን ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ በመከልከል ፡ የሚቀጣውን ፡ የታይላንድን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፩ሺ፲፭ ፡ (፲፱፻፷፪) ፡ ይመለከቷል ።

35. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፩ሺ፯፻፹ ፡ (፫)

መዋጮዎች ፡— ማኅበሩ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ ሲኖረው ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ የንብረት ፡ ባለ ቤት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ከማኅበሩ ፡ ንብረቶች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ማኅበረተኞች ፡ የሚያደርጉት ፡ መዋጮ ፡ ነው ፤ ማኅበረተኞቹ ፡ የመዋጮአቸው ፡ ባለቤቶች ፡ ሆነው ፡ አይቀዩም ፤ ባለቤትነቱ ፡ ያልተከፋፈለ ፡ የጥቅም ፡ ማግኛ ፡ መብት ፡ በማሕበሩ ፡ ላይ ፡ ይኖራቸዋል ፤ ማኅበሩ ፡ ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ ባልተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ራሱ ፡ የንብረት ፡ ባለቤት ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። እዚህ ፡ ላይ ፡ የሚነሣው ፡ ጥያቄ ፡ እያንዳንዱ ፡ ማኅበረ ተኛ ፡ የራሱ ፡ ንብረት ፡ ባለቤት ፡ ይሆናል ፡ ወይስ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ በጠቅላላው ፡ ላዋ ጡት ፡ ንብረት ፡ የጋራ ፡ ባለቤቶች ፡ ይሆናሉ ፡ የሚል ፡ ነው ።[36] ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ መል ስ ፡ ለማግኘት ፡ አስቀድመን ፡ መገንዘብ ፡ ያለብን ፡ የሽርክናው ፡ ማሕበር ፡ ውል ፡ በወ ገኖቹ ፡ መካከል ፡ የሚጸና ፡ መሆኑን ፡ ነው ። ስምምነታቸው ፡ በጽሑፍ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ውሉ ፡ ባይመዘገብም ፡ የሚጸና ፡ መሆኑን ፡ አይተናል ። ማኅበሩ ፡ የሕጋዊ ፡ ሰው ነት ፡ መብት ፡ ባልተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ የንብረቱ ፡ የጋራ ፡ ባለቤቶች ፡ ይሆ ናሉ ። ይህን ፡ መፍትሔ ፡ እያንዳንዱን ፡ ማኅበረተኛ ፡ የራሱ ፡ ንብረት ፡ ባለቤት ፡ ከማድረግ ፡ የተሻለና ፡ በርትዕ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ የሚያደርጉት ፡ ሁለት ፡ ነጥቦች ፡ አሉ ።

በመጀመሪያ ፡ ይህ ፡ መፍትሔ ፡ የተዋዋዮቹን ፡ ፍላጎት ፡ የሚያረካ ፡ ይሆናል ። በአንድ ፡ የተለመደ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ በተለይ ፡ የተሰየሙ ፡ የንብረት ፡ ዓይነቶችን ፡ ለማዋጣት ፡ ቢችሉም ፡ ያዋጡት ፡ ንብረት ፡ እን ዲመለስላቸው ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችሉም ። አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ሊጠይቅ ፡ የሚችለው የመዋጮውን ፡ ዋጋ ፡ ብቻ ፡ ነው ።[37] ማኅበሩን ፡ ኪሣራ ፡ ካጋጠመው ፡ በኪሣራው ፡ ማኅበረተኞቹ ፡[38] በሙሉ ፡ ተካፋዮች ፡ መሆን ፡ አለባቸው ፡ እንጂ ፡ መዋጮአቸው ፡ በኪሣራው ፡ ምክንያት ፡ የጠፋባቸው ፡ ብቻ ፡ መካፈል ፡ የለባቸውም ። እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የመዋጮው ፡ ባለቤት ፡ ሆኖ ፡ ይኑር ፡ ማለት ፡ ይህን ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር፡ ውል ፡ ዋና ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ የሚያፋልስ ፡ ይሆናል ። በዚህም ፡ የሚጎዱት ፡ እንደ ፡ ገንዘብ ፡ ያሉትን ፡ የሚያልቁ ፡ ነገሮች ፡ ያዋጡ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ናቸው ። ለምሳሌ ፡ ሀ ፡ ለና ፡ ሐ ፡ በጽሑፍ ፡ ማኅበር ፡ ለማቋቋም ፡ ይስማማሉ ፤ ስምምነታቸ ውን ፡ ግን ፡ አያስመዘግቡም ፤ ሀና ፡ ለ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ሲያ ዋጡ ፡ ሐ ፡ ደግሞ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ የሚያወጣ ፡ መሣሪያ ፡ ያዋጣል ። ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ የንግድ ፡ ድርጅቱ ፡ ያለው ፡ ንብረት ፡ መሣሪያውና ፡ ሦስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ይሆናል ። በኪሣራው ፡ ምክንያት ፡ ሐ ፡ መዋጮውን ፡ መልሶ ፡ ለመውሰድ ፡ መብት ፡ ካለው ፡ ሀና ፡ ለ ፡ ብቻ ፡ ሰባት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ የሆነውን ፡ ኪሣራ ፡ ይችላሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ያልፈለጉት ፡ ውጤት ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

ሁለተኛ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ የመዋጮዋቸው ፡ የግል ፡ ባለቤቶች ፡ ሆነው ፡ ይኖ ራሉ ፡ ማለት ፡ አንዳንድ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎችን ፡ ብቻ ፡ የመጠበቅና ፡ ሌሎ ችን ፡ የአለመጠበቅ ፡ ውጤት ፡ ያስከትላል ። ወደ ፡ ምሳሌያችን ፡ እንመለስና ፡ ማኅ በሩ ፡ ከመቋቋሙ ፡ በፊት ፡ ለ ፡ ከመ ፡ ላይ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ሲበደር ፡ ሐም ፡ ከሠ ፡ ላይ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ተበድሯል ፡ እንበል ። ሀ ፡ እና ፡ ለ ፡ ሌላ ፡ ንብረት ፡ የላቸውም ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ኪሣራ ፡ ይፈጠራል ። ሠ ፡ ከሐ ፡ ላይ ፡

---

36. ከመዋጮዎቹ ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ የሆኑት ፡ ንብረቶች ፡ እንደ ፡ ትርፍ ፡ ይቆጠራሉ ። በማኅበረተኞቹ ፡ ስም ፡ የተገኙ ፡ ስለሆኑም ፡ የማኅበረተኞቹ ፡ የጋራ ፡ ንብረቶች ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

37. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቊ. ፪፻፷፬ ።

38. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቊ. ፪፻፸ ፡ (፪) ።

አምስት ፡ ሺ ፡ ብሩን ፡ ለማግኘት ፡ ይችላል ፤ ምክንያቱም ፤ የሐ ፡ ንብረት ፡ ስለሚመልስለት ፡ ነው ። መ ፡ ግን ፡ ለማግኘት ፡ የሚችለው ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ ይሆናል ፤ ምክንያቱም ፥ ከቀረው ፡ ሶስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ለና ፡ ሐ ፡ ተካፋዮች ፡ ስለሚሆኑ ፡ ነው ። መ ፡ እና ፡ ሠ ፡ ሁለቱም ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ የአላቸው ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ቢሆኑም ፥ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ውጤት ፡ አላጋጠማቸውም ፡ ማለት ፡ ነው ።

<u>የሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ሥልጣን</u> ፡— የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ሥልጣን ፡ ማናቸውንም ፡ የሽርክናውን ፡ ማኅበር ፡ ዓላማ ፡ የማይቃወሙ ፡ ግዴታዎችን ፡ ለመፈጸም ፡ የሚያስችል ፡ ነው ።[39] የዚህ ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ መሠረት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ሲባል ፡ ካለው ፡ ሥልጣን ፡ በጣም ፡ የበለጠ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ይህ ፡ መሾም ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ "በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ የተደረገ" የሥልጣን ፡ አሰጣጥ ፡ ሆኖ ፡ ስለሚቆጠር ፡ ነው ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ሥልጣን ፡ "የአስተዳደር ፡ ሥራን" ብቻ ፡ ለማከናወን ፡ የሚያስችል ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይተረጐማል ።[40] አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ያልተመዘገበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የ"ሥራ ፡ አስኪያጁ" ወኪልነት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ እንጂ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ አይደለም ፡ ማለት ፡ ነውን ? ይህ ፡ ከሆነ ፡ አንድ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ሰፊ ፡ ሥልጣን ፡ የአለው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ከአንድ ፡ ወኪል ፡ ጋር ፡ ከተዋዋለ ፡ ይህን ፡ ወኪል ፡ ከሥልጣኑ ፡ ወሰን ፡ ወጥቶ ፡ የተዋዋለ ፡ ወኪል ፡ ሆኖ ፡ ሊያገኘው ፡ ይችላል ። በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ "የሽርክናው ፡ ማኅበር" ፡ በውሉ ፡ አይገደድም ።

ማኅበርተኞቹ ፥ ወኪላቸው ፡ ማለት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ የአንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ሥልጣን ፡ እንዲኖረው ፡ ከፈለጉ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ችግር ፡ አይገጥመንም ። ይህን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ደንቦች ፡ ለአተረጓጐም ፡ ብቻ ፡ የሚረዱ ፡ ደንቦች ፡ ናቸው ። የወኪሉ ፡ የሥልጣን ፡ ወሰን፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚረጋገጠው ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በነበራቸው ፡ ፈቃድ ፡ መሠረት ፡ ነው ።[41] ችግር ፡ ሊገጥመን ፡ የሚችለው ፡ ተዋዋዮቹ ፡ የሥራ ፡ አስኪያጁን ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ፡ ለማጥበብ ፥ ፈቃድ ፡ ከነበራቸው ፡ ነው ። በንግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፥ የሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ሥልጣን ፡ የሚወሰነው ፡ "የውል ፡ ቃሎች ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ የሚሆኑበት ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ የተመዘገቡ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ አኳኋኑን ፡ የሚያውቁ ፡ መሆናቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው" ፡[42] ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ የንግድ ፡ ሁኔታ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንዲሆን ፡ የሚረዳ ፡ እንደ መሆኑ ፡ መጠን ፡ መከበር ፡ አለበት ። የሽርክና ፡ ማኅበሩ ፡ ስለአልተመዘገበ ፥ የሥራ ፡ አስኪያጁን ፡ ሥልጣን ፡ የሚያጠቡት ፡ ወሰኖች ፡ እንደ ፡ መቃወሚያ ፡ የሚያገለግሉት ፡ አኳኋኑን ፡ ማወቃቸው ፡ በተረጋገጠባቸው ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

<u>የተወሰነ ፡ አላፊነት</u> ፡— ሁለት ፡ ዓይነት ፡ አላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ተቋቁሞ ፡ በአለመመዝገቡ ፡ የሚደርሰው ፡ ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ እጦት ፡ የሁሉንም ፡ ማኅበርተኞች ፡ አላፊነት ፡ ያልተወሰነ ፡ ያደርገዋል ፡ ወይ ፡ የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ይነሳል ።

39. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፪፻፹፱ ፡ (፩) ፡ (የፈረንሣይኛውን ፡ ቅጂ ፡ ይመለከቷል) ።
40. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፡ ፪ሺ፪፻፫ ።
41. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪ሺ፩፻፹፩ ፡ (፩) ።
42. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፹፱ ፡ (፪) ።

ሁለት ፡ ዓይነት ፡ አላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ የሁሉም ፡ ሳይሆን ፡ የአንዳንዶቹ ፡ ማኅበረተኞች ፡ አላፊነት ፡ የተወሰነ ፡ የሚሆንበት ፡ ድርጅት ፡ ነው ።[43] የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያላቸው ፡ ማኅበረተኞች ፡ መኖራቸው ፡ እንደ ፡ እሽሙር ፡ ማኅበር ፡ የተካፋዮች፡ ስም ፡ ሳይደበቅ ፡ ለሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ይገለጻል ። ስማቸውም ፡ በተመዘገበው ፡ የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ይዘረዘራል ።[44] በሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ዘንድ ፡ ያልተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ እንዳላቸው ፡ አድርጎ ፡ ሊያሳስት ፡ የሚችል ፡ አድራጎት ፡ ካላሳዩ ፡ በስተቀር ፡ የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያላቸው ፡ ማኅበረተኞች ፡ አላፊነታቸው ፡ ለማኅበሩ ፡ ግዴታዎች ፡ ብቻ ፡ እንዲሆን ፡ አድርገው ፡ እንዲወስኑ ፡ ሕጉ፡ ይፈቅድላቸዋል ። የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያለው ፡ ማኅበረተኛ ፡ በሽርክናው ፡ ማኅበር፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ቢገባ ፡ በአሠራሩ ፡ ለደረሱት ፡ ግዴታዎች ፡ ከማኅበሩ ፡ ጋር ፡ ባንድነትና ፡ ሳይከፋፈል ፡ ያለወሰን ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።[45]

ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ በግልጽ ፡ ከሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ጋራ ፡ የሚዋዋሉ ፡ የሶስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መብት ፡ (ጥቅም) አብልጦ ፡ የሚጠብቅ ፡ ነው ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በተወሰነ ፡ አላፊነትና ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መኖር ፡ መካከል ፡ ግንኙነት ፡ መኖሩ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ባይሰጠው ፡[46] እና ፡ የተመዘገበ ፡ ባይሆንም ፡[47] ስለ ፡ እውነተኛው ፡ አላፊነታቸው ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ እንዲሳሳቱ ፡ ካልተደረጉ ፡ በቀር ፡[48] ጥቂቶቹ ፡ ማኅበረተኞች ፡ የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ሊኖራቸው ፡ ይችላል ።[49] የሶስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መብት ፡ የመጠበቅ ፡ ዓላማ ፡ ከተከበረ ፡ በአልተመዘገበ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ የሚገኙት ፡ ማኅበርተኞች ፡ የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ብቻ ፡ እንዲኖራቸው ፡ የማይደረግበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ። በአንድ ፡ ጉዳይ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ እንዲሳሳቱ ፡ ተደርገዋል ፡ ለማለት ፡ የሚቻለው ፡ የጉዳዩን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በማየት ፡ ነው ። ሆኖም ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ የአልተመዘገበ ፡ ከሆነ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በይበልጥ ፡ ሊሳሳቱ ፡ መቻላቸውን ፡ መካድ ፡ ያዳግታል ። የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያለው ፡ ማኅበረተኛ ፡ ከሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጋራ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ሁሉም ፡ ባይሆኑ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ግንኙነቶች ፡ ያልተወሰነ ፡ አላፊነትን ፡ ያስከትሉበታል ።

አለመመዝገብና ፡ በማስታወቂያ ፡ አለመግለጽ ፡ ለሽርክና ፡ ማኅበር ፡ መፍረስ ፡ "ትክክለኞች ፡ ምክንያቶች" ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተመለከትነው ፡ የአልተመዘገቡ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመለከቱት ፡ ችግሮች ፡ የሚነሱት ፡ ማኅበሩ ፡ በሚፈርስበትና ፡ ሒሳብ ፡ በሚጣራበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ አለመመዝገብም ፡ ብቻውን ፡ ለሽርክና ፡ ማኅበር ፡ መፍረስ ፡ ምክንያት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። በንግድ ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ "ትክክለኞች ፡

43. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፸፯ ።
44. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፸፩ ፡ (፩) ።
45. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፸፰ ።
46. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፫፻፩ ፡ (፫) ። "እንደ፡ ሥራዎቹ ፡ ብዛት ፡ ወይንም ፡ ከባድነት ፡ በተለይ ፡ ለማኅበሩ፡ ግዴታዎች ፡ ሁሉ ፡ ወይንም ፡ ለአንዳንድ ፡ ግዴታ ፡ ብቻ ፡ ሳይከፈል ፡ አላፊ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ለመወሰን ፡ ይቻላል ።"
47. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፹፪ (፫) ።
48. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፹፪ (፬) ።
49. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፪፻፹፯ ፡ (፬) ።

ምክንያቶች ፡ ኖረውት ፡ ከማኅበርተኞቹ ፡ አንዱ ፡ ባቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ማኅበሩ ፡" ሊፈርስ ፡ ይችላል ።[50] ከሕግ ፡ ውጭ ፡ በሆነው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ማኅበረ ተኛ፡የሆነ ፡ ሰው ፡ ከሁኔታው ፡ ለመውጣት ፡ ፍላጐት ፡ ይኖረዋል ። ይኸንንም ፡ ለማ ድረግ ፡ ከሚያስችሉት ፡ መንገዶች ፡ አንዱ ፡ ማኅበሩን ፡ ማፍረስ ፡ ነው ።

ማኅበረተኛው ፡ ማኅበሩን ፡ ለማፍረስ ፡ "ትክክለኞች ፡ ምክንያቶች" አሉት ፡ ማለት ፡ የሽርክናው ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ውሉ ፡ (በጽሑፍ ፡ ከሆነ) የሚጸና ፡ ነው ። የሚፈርሰው ፡ ድር ጅቱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ከመጀመሪያ ፡ ጀምሮ ፡ ውሉ ፡ ዋጋ ፡ እንደሌለው ፡ ቢቆጠር ፡ ኖሮ ፡ ያለፈውን ፡ ሁኔታ ፡ ይነካ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የማኅበሩ ፡ መፍረስ ፡ ያለፈውን ፡ ሁኔታ አለመንካቱ ፡ ማጠራጠር ፡ የለበትም ። ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደምንመለከተው ፡ በሕግ ፡ የማይጸና ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውልን ፡ ማንኛውም ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ሊቃወም ፡ ሲችል ፡ "በትክክለኞች ፡ ምክንያቶች" መሠረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ ማኅበረተኛው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

This problem is illustrated in both of its aspects by the severance pay provisions, Article 36 of the Employment Act and Article 9 of Legal Notice No. 302. Article 36 divides employees into two classes: those earning more than one hundred dollars per month, and those earning one hundred dollars per month or less. Severance pay for the first group of employees who have been employed for five years or more is three months' pay plus an additional half month's pay for each year of service over five; for those who have worked less than five years, it is reduced proportionately. For the second group of employees, severance pay is one quarter of a month's pay for each year of employment.

Article 9 of Legal Notice No. 302 makes no distinction between employees on the basis of the amount of their wage. For any employee who has been employed for one year or more, severance pay is thirty times the employee's average daily wage, with a twenty-five per cent increment for each year of employment after

36. They certainly contemplated this where more favourable conditions were provided by agreements between employers and employees, and such private agreements are classed together with legislation as "legal arrangements" by the saving provisions.

the first one. Regardless of the length of service, however, an employee is not entitled to more than 180 times his average daily wage.

In comparing these two provisions, there is an initial problem as to the meaning of "average daily wage" in Legal Notice No. 302 – whether it means the employee's wages during a period of time divided by the *total number of days* in the period or his wages during the period divided only by the *number of work days*. It seems that it probably was intended to mean the former, but on either interpretation the general conclusion is the same: Legal Notice No. 302 provides greater severance pay for employees earning one hundred dollars per month or less and also for employees earning more than one hundred dollars per month who have been employed for less than a certain number of years – on the interpretation of average daily wage suggested here, that number is approximately two.[37] For employees earning more than one hundred dollars per month who have been employed for longer than this, the Employment Act provides the greater amount of severance pay. Thus, whether Article 36 of the Employment Act or Article 9 of Legal Notice No. 302 is the more favourable to employees depends on which employees one means.

The two provisions also present the question of under what circumstances. The amount of severance pay fixed by law is of no concern to an employee whose employment is terminated under circumstances that do not meet the requirements of the severance pay provision. Although Legal Notice No. 302 provides for the greater amount of severance pay for what is probably the majority of employees, the Employment Act entitles employees to severance pay under a broader range of circumstances.

The Employment Act provides for severance pay in all circumstances with two exceptions. The exceptions are (1) where the employee is dismissed for certain kinds of misconduct, which are enumerated in Article 33 and (2) where the employee himself terminates the employment contract. The first exception applies to all employees. The second, however, does not apply to employees earning more than one hundred dollars per month with at least five years of service or to other employees with at least two years of service; these employees are entitled to severance pay even when they, rather than the employer, terminate the employment contract.

Legal Notice No. 302 in effect works from the opposite direction; rather than specifying the cases in which an employee is *not* entitled to severance pay, it specifies the one case in which he *is* entitled to it, which is where the employer dismisses the employee without good cause. Comparing this case with the circumstances under which an employee would be entitled to severance pay under the Employment Act, Legal Notice No. 302 appears to be less favourable to employees in two respects. First, under the legal notice an employee is never entitled to severance pay if he terminates his employment himself. Second, good cause for dis-

37. Under the Employment Act, an employee earning more than one hundred dollars per month with less than five years of service is entitled to severance pay equal to three fifths of a month's pay for each year of service. For an employee with only one year of service, this is clearly less than the amount provided by Legal Notice No. 302 (three-fifths of a month's pay versus a full month's pay); for an employee with two years' service the two amounts are nearly equal (one and a fifth months' pay versus one and a quarter months' pay); and a few months after completion of the second year of service the amount provided by the Employment Act becomes the greater.

missal exists in at least two instances in which the employee is guilty of no misconduct. These are where, "in the circumstances, it would not be reasonable to expect the contract to be extended or renewed," and where "the situation filled by the employee is abolished in good faith."[38] In both of these instances, it appears, an employee would be entitled to severance pay under the Employment Act.

Now, how does one apply the more favourable standard to this mixture of advantages and disadvantages on each side? One alternative is to take the best of each: the Employment Act to control on the question whether any severance pay is due and also on the amount of severance pay where it is the more generous in that respect; Legal Notice No. 302 to control on the amount of severance pay where it is the more generous. This alternative requires, however, not merely the separation of one related provision from another, but the selection of only the most favourable parts of single provisions and their combination to form a hybrid provision that is like no provision in either law. That this is what this alternative requires does not make the alternative clearly wrong - the questions of eligibility for severance pay and of the amount of severance pay for each group of employees *could* have been dealt with in separate provisions, and the fact that they were not may be regarded as merely a problem of form. But the same sort of doubts about the intent of the draftsmen and legislature that would arise in the hypothetical case of daily and weekly work hours arises here in the actual case of eligibility for and the amount of severance pay.

A second alternative is somehow to weigh the advantages and disadvantages of each provision and declare one or the other the more favourable on the whole. The difficulty with this alternative is that a standard of measurement is lacking. It is not difficult to compare an eight-hour day and six-day week with a nine-hour day and five-day week, because there is an obvious standard against which each can be measured - the total number of hours per week. But there is no very obvious standard against which to measure a greater amount of severance pay for some employees on one hand against a greater amount for others and a greater number of cases in which severance pay will be due on the other; and such standards as do suggest themselves - such as the average amount of severance pay for all employees discounted by the likelihood that no severance pay will be due - are neither possible of application with the data available nor, probably, suitable for judicial application in any event.

Considering the legal and practical problems raised by both of these alternatives, there may be an understandable temptation to meet the problem by a kind of local option - allow the workers of each enterprise to decide which provision *they* think is more favourable. Despite the practical advantages of this course, however, it seems of doubtful legality. From the combination of Article 36 of the Employment Act and Article 9 and the saving provision of Legal Notice No. 302, certain severance pay rights are conferred on Eritrean employees. As the preceding discussion has shown, it is not easy to determine what those rights are, but difficulties of interpretation do not relieve a court of law of its obligation to make the interpretation and decide the case accordingly. Let us suppose, then, that in an enterprise it is decided by the employees that Article 9 of Legal Notice No. 302 should control. However, a minority of employees—presumably those with higher monthly

38. Civ. C., Art. 2575.

wages and long service—disagree. If one of this minority of employees is dismissed and goes to court to obtain the severance pay that would be due to him under the Employment Act, would the court be justified in dismissing his case simply on the ground that a majority of his employees had chosen Legal Notice No. 302? It seems that it would not. Rather, the court would be obligated to determine whether, under the court's interpretation of the relevant provisions, the Employment Act does govern as the employee claims. If the court determines that it does, the employee would be entitled to judgment accordingly, the decision of a majority of his fellow employees notwithstanding.[39]

The second reason for concluding that not all of the Employment Act's labour condition provisions were repealed is that some establish minimum standards on points not dealt with at all by either Legal Notice No. 302 or the Labour Standards Proclamation.[40] Such provisions may be regarded as being of necessity "more favourable" to employees than the corresponding provisions of Legal Notice No. 302 and the Labour Standards Proclamation—since there are no such corresponding provisions—or as simply not being within the ambit of the Ethiopian laws' repeals provisions in the first place. On either view, such provisions have not been repealed.

Summary

In considering the present legal status of the Eritrean Employment Act of 1958, the history of the act falls into three parts. The first is the period from enactment of the law to the end of the Federation. During this period, the law could have been repealed or modified only by subsequent Federal or Eritrean legislation. Since there appears not to have been any such legislation dealing with the subject matter of the Employment Act, the act apparently remained in full force to the end of the Federation.

The end of the Federation constitutes the second part of the act's history. The Federation's end could have had the effect of repealing all Eritrean legislation, and even the provisions of the Imperial order ending the Federation probably would not have saved more than a part of such legislation if those provisions had been interpreted narrowly. In any event, however, the provisions have been broadly interpreted to save all or nearly all Eritrean legislation from repeal, and the Employment Act continued in force after the end of Federation.

Since the end of Federation, there have been four pieces of Ethiopian legislation dealing with the subject matter of the Employment Act.

The effect of this legislation on the Employment Act appears to have been as follows:

39. It may or may not follow that, on this hypothetical court's interpretation of the law, judgment should go against one of the majority of employees who sought to enforce his alleged rights under Legal Notice No. 302 against the employer. Two questions would be presented: First, again the question of the interrelationships between provisions and, in this case, within a single provision: Can provisions be divided up so that some employees enjoy the advantages of one part of Article 36 of the Employment Act while other employees enjoy the advantages (to them) of one part of Article 9 of Legal Notice No. 302? Second, if the provisions can be divided up, does the court agree with the apparent judgment of the majority of employees that for them Legal Notice No. 302 is the more favourable?

40. E.g., neither the legal notice nor the proclamation deals with the liability of the employer for work-connected sickness and accidents.

1. Three kinds of provisions appear to have been repealed:
   a. Provisions relating to labour unions and employers' associations, which appear to have been repealed when the Labour Relations Decree was reenacted as the Labour Relations Proclamation in 1963;
   b. Provisions relating to labour inspection, which appear to have been repealed in part by the Labour Inspection Service Order of 1964 and in part by the Labour Standards Proclamation of 1966; and
   c. Minimum labour condition provisions that are not as favourable to employees as corresponding provisions of Legal Notice No. 302 or of the Labour Standards Proclamation, which appear to have been repealed respectively, by the promulgation of the legal notice in 1964 by the enactment of the proclamation in 1966.
2. Two kinds of provisions appear *not* to have been repealed:
   a. Minimum labour condition provisions more favourable to employees than corresponding provisions of either Legal Notice No. 302 or the Labour Standards proclamation: and
   b. Minimum labour condition provisions for which there are no corresponding provisions in either Legal Notice No. 302 or the Labour Standards Proclamation.

ያላግባብ ፡ በመበልጸግ ፡ ላይ ፡ የሚመሠረት ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ በመጨረሻ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ሲገኝ ፡ (ሰብሲዲያሪቲ ፡ ሲኖረው) ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ መሠረተ አሳብ ፡ በፈረንሳይና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ።

ከሠመረአብ ፡ ሚካኤል ።

መግቢያ ፡

የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዓላማ ፡ ያላግባብ ፡ በመበልጸግ ፡ ላይ ፡ የሚመሠረት ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ በመጨረሻ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ሲገኝ ፡ (ሳብሲዲያሪቲ ፡ ሲኖረው) ነው ፡ የሚለው ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ በፈረንሣይ ፡ ሕግና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የሚሰጠውን ፡ ትርጉም ፡ መመርመር ፡ ነው ። የሚከተለው ፡ ስለ ፡ ጽሑፉ ፡ አቀራረብ ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡ ነው ።

የነገሩን ፡ አመጣጥ ፡ ለመረዳት ፡ ይረዳን ፡ ዘንድ ፡ የሮማውያን ፡ ሕግና ፡ የፈረንሣይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስላላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ምን ፡ እንደሚሉ ፡ ባጭሩ ፡ እንመለከታለን ። ቀጥለንም ፡ የፈረንሣይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ የሚለውን ፡ አሳብ ፡ እንዴት ፡ አንድ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የግዴታዎች ፡ ምንጭ ፡ ለመሆን ፡ እንዳበቁት ፡ እንመለከታለን ።

ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ያላግባብ ፡ በመበልጸግ ፡ ላይ ፡ የሚመሠረት ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ "በመጨረሻ ፡ ደረጃ" ላይ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጸው ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ትርጓሜ ፡ እንዳለው ፡ የሚያሳይ ፡ ይሆናል ። ወደዚህ ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ ከመግባታችን ፡ በፊት ፡ "በቂ ፡ ምክንያት" ፡ የሚለውን ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ ባጭሩ ፡ እንመረምራለን ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ በሁለቱ ፡ መሠረተ ፡ አሳቦች ፡ መካከል ፡ ግንኙነት ፡ ስላለና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ ለመረዳት ፡ ሁለቱን ፡ አሳቦች ፡ ጠንቅቆ ፡ ማወቅ ፡ ስለሚያስፈልግ ፡ ነው ።

ይህ ፡ "የመጨረሻ ፡ ደረጃነት ፡" ("ሳብሲዲያሪቲ") ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ አያሌ ፡ መሠረተ ፡ አሳቦችን ፡ ያዘለ ፡ በመሆኑ ፡ አራት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮችን ፡ በመተንተን ፡ የሚብራራ ፡ ይሆናል ። ከያንዳንዱ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ግርጌ ፡ የፈረንሣይ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ያቀረቧቸው ፡ መፍትሔዎችና ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውሳኔዎች ፡ ቀርበዋል ። ከዚያም ፡ "የመጨረሻነት ፡ ደረጃ ፡" ("ሳብሲዲያሪቲ") ፡ የሚለውን ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ ለምን ፡ እንደተፈጠረ ፡ የሚገልጹትን ፡ ባሕረ ፡ አሳቦችንና ፡ ይህ ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ "በቂ፡ ምክንያት"፡ ከሚለው ፡ አሳብ፡ ጋር፡ እንዴት፡እንደሚደራረብ፡እንመለከታለን። የዚህ፡ዓይነቱ፡አቀራረብ፡ጠቃሚነቱ፡ በሁለት፡ ረገድ ፡ ነው ። በመጀመሪያ ፡ በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ የሚገልጽ ፡ ይሆናል ፤ በይበልጥ ፡ ደግሞ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስለዚህ ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ በግልጽ ፡ የተነገረ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ስለማይገኝ ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ ለማብራራት ፡ ለምናደርገው ፡ ሙከራ ፡ አንድ ፡ የሃሳብ ፡ ምንጭ ፡ በመሆን ፡ ያገለግላል ።

ክፍል ፡ ፩ ፡

"ያላግባብ ፡ መበልጸግ" ፡ ተብሎ ፡ ስለሚታወቀው ፡ ባሕረ ፡ አሳብ ፡ እና ፡ በርሱም ፡ ተመርኩዘው ፡ ስለሚነሱ ፡ ክሶች ፡ ታሪካዊ ፡ መግለጫ ።

፩/ የሮማውያን ፡ ሕግ ፡

"ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡" ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ አሳብ ፡ የተፈጠረው ፡ በሮማ ውያን ፡ ሕግ ፡[1] ቢሆንም ፤ ማንኛውንም ፡ አላግባብ ፡ የሚገኝ ፡ ብልጽግና ፡ የሚያወግዝ ፡ "የዚህ ፡ ዓይነት ፡ አጠቃላይ ፡ ደንብ ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ።"[2] ሮማውያን ፡ ያደረጉት ፡ በሌላው ፡ አላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ የተበደለ ፡ ሰው ፡ የገንዘብ ፡ ካሣ፡ ለመቀበል ፡ የሚያስችሉትን ፡ በቍጥር ፡ የታወቁ ፡ ክሶችን ፡ (ኮንዲክሲዮኔስ) ፡ ማቋቋም ፡ ነበር ።

በተጨማሪ ፡ ቻሊስ ፡ የተባለ ፡ ጸሐፊ ፡ "በሮማውያን ፡ ሕግ ፡ ያላግባብ ፡ የተበለጸገበትን ፡ ንብረት ፡ ለማስመለስ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይቻል ፡ ነበር"[3] ፡ ሲል ፡ ጽፏል ። ከነዚህም ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ አክስዮ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡— ተብሎ ፡ የሚጠራው፡ ነበር። በዚህም ፡ ክስ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ባርያ ፡ አለ ፡ ጌታው ፡ ፈቃድ ፡ ውል ፡ ተዋውሎ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ያገኘውን ፡ ብልጽግና ፡ ለጌታው ፡ ቢያስተላልፍ ፡ ሃብቱ ፡ ያላግባብ ፡ የተቀነሰበት ፡ ወገን ፡ ከጌትየው ፡ ሃብቱን ፡ ለማስመለስ ፡ ይችል ፡ ነበር ።

ይህ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ የሚባለው ፡ ክስ ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ ሌሎችንም ፡ ያላግባብ ፡ ሁኔታዎችን ፡ አጠቃለለ ።

ይህን ፡ ዕድገት ፡ ኒኮላስ ፡ እንደሚከተለው ፡ ገልጾታል ።

"ይህ ፡ አክስዮ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ተብሎ ፡ የታወቀው ፡ የክስ ፡ አቀራረብ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ትርጉም ፡ የተሰጠው ፡ በሮማውያን ፡ ሕግ ፡ በኮዴክስና ፡ ዳይጀስት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ አንዳንድ ፡ ሃሳቦች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ። እነርሱም ፡ ተከሳሹ ፡ የበለጸገው ፡ በከሳሹና ፡ በአንድ ፡ ነፃ ፡ በሆነ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ሳቢያ ፡ በተደረገ ፡ ውል ፡ ቢሆንም ፤ አክስዮ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ እንዲያመጣ ፡ ይፈቅዱለት ፡ ነበር ። ቀስ ፡ ብለው ፡ ተችዎችም ፡ በመጀመሪያ ፡ ከሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ጋር ፡ በተፈጸመ ፡ ውል ፡ ለተፈጠረ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ እንዲቀርብ ፡ ሲፈቅዱ ፡ በመጨረሻ ፡ ደግሞ ፡ ለማንኛቸውም ፡ መበልጸግ ፡ እንዲከፈት ፡ ፈቀዱ"።[4]

---

1. ማዞ ፡ ኤ ፡ ማዞ ፡ ሴሶን ፡ ደ ፡ ድርዎ ፡ ሲቪል ፡ ፪ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ቀ— ፲፱፻፲፫ ፡ ገጽ ፡ ፲፱፻፴፮ ።
2. ደብልዩ ፡ በክላንድ ፡ ኤ ፡ ቴክስት-ቡክ ፡ ኦቭ ፡ ሮማን ፡ ሎው ፡ (፫ኛ ፡ እትም ፡ በ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ የተሻሻለ) ፡ ገጽ ፡ ፭፻፵፭ ።
3. ጂ ፡ ቻሊስ ፡ ዘ ፡ ዶክትሪን ፡ ኦቭ ፡ አንጀስቲፋይድ ፡ ኤንሪችሜንት ፡ ኢን ፡ ዘ ፡ ሎው ፡ ኦቭ ፡ ዘ ፡ ፕሮቪንስ ፡ ኦቭ ፡ ኩቤክ ፡ (፪ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) ፡ ገጽ ፡ ፪ ።
4. ቢ ፡ ኒኮላስ ፡ "አንጀስቲፋይድ ፡ ኤንሪችሜንት ፡ ኢን ፡ ዘ ፡ ሲቪል ፡ ሎው ፡ ኤንድ ፡ ሉዊዚያና ፡ ሎው፡ ቱሌን ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፡ ቮልዩም ፡ ፴፮ ፡ (፲፱፻፷፩-፷፪ ፡ እ- ኤ- አ-) ፡ ገጽ ፡ ፮፻፲፱ ።

፪/ የፈረንሣይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በተደነገገበትና ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ ጊዜያት ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ።

በሌላ ፡ ሰው ፡ በመገልገል ፡ በቂ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ጥቅም ፡ ማግኘት ፡ የተከለከለ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ አጠቃላይ ፡ ሕግ ፡ በፈረንሣይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ አይገኝም ።[5]

ቢሆንም ፡ ከዚህ ፡ አጠቃላይ ፡ ሕግ ፡ የመነጩ ፡ ዝርዝር ፡ ሕጎች ፡ ይገኛሉ ።[6] ኮሊንና ፡ ካፒታ ፡ ሁኔታውን ፡ እንደሚከተለው ፡ ይገልጻሉ ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ያገኘበት ፡ ሁኔታ ፡ ከመጀመሪያ ፡ የማይጸና ፡ ወይም ፡ ወደፊት ፡ የማይጸና ፡ የሚደረግ ፡ ከሆነና ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ንብረቱን ፡ እንዲመልስ ፡ ሲገደድ ፤ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ አስፈላጊና ፡ ጠቃሚ ፡ ወጪ ፡ በማድረግ ፡ የንብረቱን ፡ ዋጋ ፡ ከፍ ፡ አድርጎት ፡ እንደሆን ፡ ንብረቱ ፡ የጨመረውን ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ሊያስቀር ፡ ይችላል ። ቍ ፡ ፲፻፲፭ ፡ እና ፡ ፲፻፲፪ ፡ ስለ ፡ ውርስ ፡ ንብረት ፡ መመለስ ፡ ጉዳይ ፡ ሲያብራሩ ፡ እላይ፡ የተባለውን ፡ እንደጠበቁ ፡ ነው ። በቍ ፡ ፩ሺ፫፻፸፫ ፡ መሠረት ፡ የመጀመሪያው ፡ ሽያጭ ፡ መልሶ ፡ የመግዛት ፡ መብቱን ፡ ሊጠቀምበት ፡ ቢፈልግ ፡ ለጥንት ፡ ገዢው ፡ ስላደረገው ፡ ወጪ ፡ ተገቢውን ፡ ካሣ ፡ መክፈል ፡ አለበት ። በሚከተሉትም ፡ ቍጥሮች ፡ ይህ ፡ የተጠበቀ ፡ ሆኗል ። ይኸውም ፡ በቍ ፡ ፩ሺ፫፻፹፩ ፡ መሠረት ፡ ዕቃ ፡ የተመለሰለት ፡ ሰው ፡ ለባለ ፡ ይዞታው ፡ (በቅን ፡ ልቡና ፡ ዕቃውን ፡ ባይዝም ፡) ካሣ ፡ መክፈል ፡ አለበት ፤ በቍ ፡ ፩ሺ፱፻፵፯ ፡ ዕቃ ፡ በአደራ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ለዕቃው ፡ ጥበቃ፡ ስለሚያወጣው ፡ ወጪ ፡ መክፈል ፡ እንዳለበት ፡ በቍ ፡ ፪ሺ፹ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ አበዳሪ ፡ መያዣውን ፡ ለመጠበቅ ፡ ስላወጣው ፡ ወጪና ፡ በቍ ፡ ፱፻፸፰ ፡ መሠረት ፡ አንደ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ መያዣ ፡ የሆነውን ፡ ንብረት ፡ ሲያጣ ፡ ወይም ፡ መንግሥት ፡ ሲወስድበት ፡ ስለሚከፈል ፡ ካሣ ፡ የሚናገር ፡ ነው ።[7] ቍ ፡ ፰፻፵ ፡ ፰፻፵፩ ፡ ፰፻፵፫ ፡ ፰፻፸ ፡ ፰፻፸፩ ፡ እና ፡ ፰፻፸፯ ፡ በዋና ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚጨመሩ ፡ ነገሮች ፡ የሚያትቱ ፡ ሲሆኑ ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ንጥረ ፡ ሃሳብ ፡ ይከተላሉ ። በተጨማሪ ፡ ቍ ፡ ፩ሺ፬፻፵፯ ፡ ስለ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ሲናገር ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ፡ ድንጋጌ፡ ያደርጋል ።

በ፲፱ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ሁለተኛ ፡ አጋማሽ ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግን ፡ አንድ ፡ የግዴታዎች ፡ ምንጭ ፡ እንዲሆንና ፡ አክሲዮ ፡ ደ ፡ ኤን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ተብሎ ፡ የታወቀውን ፡ ደግሞ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የክስ ፡ አርእስት፡ ለማድረግ ፡ ንቅናቄ ፡ ጀመሩ ። ከመሪዎቹም ፡ መካከል ፡ አብሪና ፡ ሮው ፡ ሲገኙ ፡ እነርሱም ፡ ፔይማ ፡ ደ ፡ ሊንዱና ፡ ኾርስቲዮን ፡ ዳፌር ፡ የተባሉትን ፡ እንደ ፡ ሁለት ፡ የአለአግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ምሳሌዎች ፡ ብቻ ፡ በመቁጠር ፤ ደ ፡ ኢንሬም ፡ ቬርሶ ፡ የተባለው ፡ ክስ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ መጎዳት ፡ ምክንያት ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ሃብት ፡ በዳበረ ፡

---

5. ፕላንዮል ፡ ኤ ፡ ሪፔር ፡ ትሬቴ ፡ ፕራቲክ ፡ ደ ፡ ድርዋ ፡ ሲቪል ፡ ፍራንሴ ፡ (፪ኛ ፡ እትም ፡ በፒ- ኤስማን ቦልዩም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፯፻፶፪ ፡ ገጽ ፡ ፵፯ ።
6. ፕላንዮል ፡ ኤ ፡ ሪፔር ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ (፫) ፡ እስከ ፡ ቍ ፡ ፯፻፪ ፡ ገጽ ፡ ፵፯ ፡ ድንጋጌዎቹ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡ ይላሉ ፦ ቍጥር ፡ ፰፻፵፰ ፡ ፰፻፵፩-፯ ፡ ፰፻፸- ፸፩ ፡ ፲፻፲፭-፲፪ ፡ ፩ሺ፪፻፵፩ ፡ ፩ሺ፫፻፲፪ ፡ ፩ሺ፫፻፹፩ ፡ ፩ሺ፬፻፵፯ ፡ ፩ሺ፯፻፸፫ ፡ ፩ሺ፲፻፲፬ ፡ ፩ሺ፱፻፷፯ ፡ ፩ሺ፪፻፵፯ ፡ ፪ሺ፹ ፡ ፪ሺ፩፻፪ ፡ (፫) ፡ ፪ሺ፩፻፸፫ ።
7. ኤ ፡ ኮሊን ፡ ኤ ፡ ኤች ፡ ካፒታ ፡ ኩር ፡ ኤሌሜንቴር ፡ ደ ፡ ድርዋ ፡ ሲቪል ፡ ፍራንሴ ፡ (፯ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ እ - ኤ- አ-) ፲ቦልዩም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፪፻፴፰ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፳፫-፪፻፳፬ ።

ቋጥር ፡ መስጠት ፡ የሚገባው ፡ የክስ ፡ አርእስት ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ አስተያየታቸውን ፡ አቅ ርበዋል ።[8] በመጀመሪያ ፡ የካሳሲዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ አሳብ ፡ ችላ ፡ ብሎት ፡ ቆየ ። ነገር ፡ ግን ፡ በሺ፰፻፸፫ ፡ ዥርስትዮን ፡ ደፌር ፡ አኖርማል ፡ በተባለ ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ የተመረኮዘ ፡ ክስ ፡ በመፍቀዱ ፡ መጠን ፡ የአብሪና ፡ ሮውን ፡ አስተያየት ፡ ተቀብሎ ታል ።[10]

ትንሽ ፡ ቆይቶ ፡ በተነሳ ፡ ጉዳይ ፡[11] የካሳስዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያላግባብ ፡ መበል ጸግን ፡ የክስ ፡ አርእስት ፡ ለማድረግ ፡ ስላልፈለገ ፡ በተመሳሳይ ፡ ዘዴ ፡ ተጠቅሚል ። በቡድየር ፡ ጉዳይ ፡[12] ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ዘዴ ፡ ትቶ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግን ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የግዴታዎች ፡ ምንጭ ፡ አደረገው ። በአብ ሪና ፡ ሮው ፡ አሳብ ፡ የተመራ ፡ ቢሆንም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ የሚለ ውን ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ የሰጠው ፡ ትርጓሜ ፡ እነርሱ ፡ ካቀረቡት ፡ የተለየ ፡ ነበር ።[13] ተከትለው ፡ በመጡ ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮች ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የጸሐፊዎቹን ፡ እቅድ ፡ ተቀብሎታል ።[14]

በብሪያኖ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ተገለጠው ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ መቅረብ ፡ የሚችለው ፡ የሚከተሉት ፡ ተሟልተው ፡ ሲገኙ ፡ ነው ።

ሀ/ የተከሳሽ ፡ መበልጸግ ፡

ለ/ የከሳሽ ፡ ሃብት ፡ መቀነስ

ሐ/ በመበልጸጉና ፡ በሀብት ፡ መቀነሱ ፡ መካከል ፡ የአፈጻጸም ፡ ግንኙነት ፡ ሲኖር፣

መ/ ለመበልጸጉ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አለመኖሩ ፡

ሠ) ከሳሽ ፡ በውል ፡ ወይም ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ በሚፈጠር ፡ ግዴታ ፡ ክስ ፡ ማቅ ረብ ፡ የማይችል ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ። የመጨረሻው ፡ ሁኔታ ፡ በጸሐፊዎች ፡ ዘንድ ፡ አክስዮ ፡ ደ ፡ ኢን፡ ሬም ፡ ቬርሶ፡ተብሎ ፡ የታወቀው ፡ ክስ ፡ የተከታይነት ፡ ደረጃ ፡ ብቻ ፡ እንዳለው ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ፡ በሚል ፡ መንገድ ፡ ተተርጉሟል ።

በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ይህ ፡ በክስ ፡ ረገድ ፡ የተከታይነት ፡ ደረጃ ፡ የሚለው ፡ አነ ጋገር ፡ በትክክል ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለመወሰን ፡ እንሞክራለን ።

---

8. ማዞ ፡ ኤ ፡ ማዞ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቅ– ፲፱፻፺፬ ፡ ገጽ ፡ ፲፱፻፴፯ ።
9. ከዚያው ፡ ቅ– ፲፱፻፺፩ ፡ ገጽ ፡ ፲፱፻፴፯፣ በተጨማሪም ፡ ሮው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክሱን ፡ እንዲፈቅድ ፡ ማስደረ ጉን ፡ ይናገራሉ ።
10. ከሳሽ ፡ ኮምዩን ፡ ደ ፡ ላን-ሺንያ ፡ ተከሳሽ ፡ ጉይ ፡ ዲ- ፩ሺ፰፻፸፫ ፡ ፩፬፻፶፯ ።
11. ከሳሽ ፡ ላሚር ፡ ተከሳሽ ፡ ሻምቦ ፡ ሲንዲክ ፡ ደ ፡ ላ ፡ ፈየት ፡ ላሙር ፡ ዲ- ፩ሺ፰፻፺፩- ፩፻፵፱ ፡ የፕላኖል ፡ ማስታወሻ ።
12. ከሳሽ ፡ ዡልያ ፡ ፖቱር- ሚራን ፡ ተከሳሽ ፡ ቡዲየ ፡ ዲ ፡ ፩ሺ፰፻፺፪- ፩ሺ፰፻፺፯ ፡ ስለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እርምጃ፣ መግለጫ ፡ ኒኮላስ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ ፡ እና ፡ ፕላንዮል ፡ ኤ ፡ ሪፔር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ ፡ ቅ– ፯፻፺፪ ፡ ገጽ ፡ ፵፱ ፡ ይመለከታል ።
13. የጸሐፊው ፡ አሳብ ፡ አብሪ ፡ ኤ ፡ ሮው ፡ ኩር ፡ ደ ፡ ድርዋ ፡ ሲቪል ፡ ፍራንሴ ፡ (፬ኛ ፡ እትም) ፡ ቅ– ፰፻፸፰ ውስጥ ፡ እንደተገለጠው፣ በኤፍ ጉሬ ፡ ላንሪሽማ ፡ አ ፡ ዴፓንስ ፡ ዶትሩዊ ፡ (፲፱፻፵፬ ፡ እ- ኤ- አ-) ‘ቅ- ፩፻፹፫ ገጽ ፡ ፩፻፹፰ ፡ ውስጥ ፡ ተጽፎአል ።
14. ከሳሽ ፡ ክላየት ፡ ተከሳሽ ፡ ሲኪ-ደ፡ ላ ፡ ኮንግራጋሲዮ ፡ ደ ፡ ሚሲዮነር ፡ ደ ፡ ላስ ፡ ሳሌት ፡ ኤስ- ፩ሺ፱፻፲፰- ፩-፵፩ ፡ እና ፡ ከሳሽ ፡ ቪይ ፡ ደ ፡ ባኬር- ደ- ቢጐር ፡ ተከሳሽ ፡ ብሪያን ፡ ዲ- ፩ሺ፱፻፳- ፩-፬፻፪ ።
15. ፕላንዮል ፡ ኤ ፡ ሪፔር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ ፡ ቅ– ፯፻፷፩ ፡ ገጽ ፡ ፷፯ ።

የፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ አላግባብ ፡ በመበልጸግ ፡ ምክንያት ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ሁኔታዎች ፡ አብራርቶ ፡ ሲያስረዳ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ክሱ፡ የተከታይነት ፡ ወይም ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃነት ፡ ምንም ፡ ሳይጠቅስ ፡ በደፈናው ፡ ክሱ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሌላው ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ምክንያት ፡ አላግባብ ፡ በሚበለጽግበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ይላል ።[16]

ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ አርእስተ ፡ ክስ ፡ ተከታይነት ፡ ወይም ፡ የሁለተኛነት ፡ ደረጃ ፡ (ሳብሲዲያሪቲ)፡

ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚናገረው ፡ ስላላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ አርእስተ ፡ ክስ፡ ተከታይነት ፡ ደረጃ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። አስቀድመን ፡ ግን ፡ "ምክንያት" ስለሚባለው ፡ መሠረተ ሐሳብ ፡ ባጭሩ ፡ መናገር ፡ ይጠቅማል ። ለዚህም ፡ ሁለት ፡ ምክንያት ፡ አለው ። በመጀመሪያ ፡ በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የዚህን ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ ጉዳይ ፡ ስንመረምር በአንድ ፡ በኩል ፡ "ምክንያት" ከሚለው ፡ ጋር ፡ የተሳሰረ ፡ ሆኖ ፡ ስለምናገኘው ፡ ነው። ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ "የተከታታይነት" ጉዳይ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ አለመኖሩን ፡ ለማወቅ ፡ "ምክንያት" ከሚባለው ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ መልሳችን፡ ማግኘት፡ ስላለብን፡ ነው። በፈረንሣይ፡ ሕግ፡ ውስጥ፡ በሁለቱ ፡ መሠረተ፡ አሳቦች፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ መደራረብ ፡ ለመረዳትና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ "የተከታይነት ፡ ወይም ፡ የሁለተኛነት ፡ ደረጃ" ፡ የሚለው ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ መኖር ፡ አለመኖሩን ፡ ለመመርመር ፡ ለአንድ ፡ ብልጽግና ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ለመሆን ፡ የሚችሉትን፡ ነገሮች ፡ ማወቅ ፡ ይኖርብናል ። ቀጥለንም ፡ በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ "ተከታይነት" ፡ እንዲሁም ፡ ይህ ፡ ንጥረ ፡ ሃሳብ ፡ ስለተፈጠረበት ፡ ምክንያትና ፡ በመጨረሻም በዚሁና ፡ በ"በቂ ፡ ምክንያት ፡" መካከል ፡ ስላለው ፡ መደራረብ ፡ እንነጋገራለን ።

፩/ "በቂ ፡ ምክንያት ፡"

በፕላንዮልና ፡ ሪፔር ፡ አስተያየት ፡—

"መበልጸግ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሚኖረው ፡ በውል ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ ከሕጋዊ ፡ ወይም ፡ ከተፈጥሮ ፡ ግዴታ ፡ የተገኘ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።"[17]

ስለዚህ ፡ በበለጸገው ፡ ወገንና ፡ ሃብቱ ፡ በተቀነሰበት ፡ ወገን ፡ መካከል ፡ ውል ፡ ሲኖርና ፡ ለዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ ሁኖ ፡ ሲገኝ ፡ እንደ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ይቆጠራል ።

እንዲሁም ፡ የበለጸገው ፡ ወገን ፡ ከአንድ ፡ ካለ ፡ ምክንያት ፡ ከበለጸገ ፡ ሰው ፡ ጋር፡ ሲዋዋልና ፡ ይኸው ፡ ሰው ፡ ውሉን ፡ ለመፈጸም ፡ የበቃው ፡ ካለምክንያት ፡ ባገኘው ፡ ብልጽግና ፡ ቢሆንም ፡ ውሉ ፡ በደንቡ ፡ መሠረት ፡ ተዋውሎ ፡ የበለጸገው ፡ ወገን ፡ ላገኘው ፡ ብልጽግና ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል ።[18] ጸሐፊዎቹ ፡ ይኸንን ፡ ሁኔታ ፡ በም

16. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፪ሺ፩፻፷፪ ።
17. ፕላንዮል ፡ ኤ ፡ ሪፔር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ ፡ ቍ ፡ ፳፻፶፯ ፡ ገጽ ፡ ፶፯ ።
18. ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ ፡ ቍ ፡ ፳፻፶፱ ፡ ገጽ ፡ ፷፩ ።

ሳሌ ፡ ሲያስረዱ ፡ የሚከተለውን ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ[19] ይጠቅሳሉ ። አንድ ፡ ቤት ፡ የተከራየ ፡ ሰው ፡ ሰራተኛ ፡ ቀጥሮ ፡ ቤቱን ፡ አሳደሰ ። በኪራዩ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ተከራዩ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚያደርገው ፡ መሻሻል ፡ አከራዩ ፡ ምንም ፡ እንደማይከፍለው፡ተጠቅሶ ፡ ስለነበረ ፡ ሠራተኛው ፡ ተከራዩ ፡ ሳይከፍለው ፡ የቀረውን ፡ ገንዘብ ፡ አከራይን፡ ከሶ ፡ ቢጠይቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥያቄውን ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀረ ።

እንዲሁም ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ መበልጸግ ፡ የተገኘው ፡ በሌላው ፡ ቸርነት ፡ ወይም ፡ የተፈጥሮ ፡ ግዴታ ፡ መፈጸም ፡ ከሆነ ፡ ሃብቱ ፡ የተቀነሰበት ፡ ወገን ፡ አክስዮ ፡ ዴ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ የተባለውን ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አይችልም ።[21]

በመጨረሻም ፡ የመበልጸግ ፡ ምንጭ ፡ ሕግ ፡ ይሆናል ። አንድ ፡ ሰው ፡ ሕግ ፡ የሚያዘውን ፡ ግዴታ ፡ በሚፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡ የበለጸገው ፡ ወገን ፡ አለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት፡ በልጽጓል ፡ አይባልም ።[22]

ሌሎች ፡ ጸሐፊዎች ፡ ፕላንዮልና ፡ ሪፔር ፡ ከጠቀሷቸው ፡ ምንጮች ፡ ሌላ ፡ ስለማ ይጠቅሱና ፡ አስተያየታቸውም ፡ ከነዚሁ ፡ ጸሐፊዎች ፡ በምንም ፡ ያህል ፡ ስለማይለ ያይ ፡ መዘርዘሩ ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ።[23]

፪ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ አርእስተ ፡ ክስ ፡ የተከታይነት ፡ ጠባይ ።

ከሳሹ ፡ ሊከስበት ፡ የሚችል ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ እንዲኖረው ፡ አይገባም ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ ብዙ ፡ ትርጓሜ ፡ ሊሰጠው ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፡ ባርተን ፡ ሊሰጡት ፡ ስለሚችሉት ፡ ትርጓሜዎች ፡ የሚከተለውን ፡ አስተያየት ፡ ይሰጣል ።

"የተከታይነት ፡ ጠባይ ፡ በሶስት ፡ ሊተረጎም ፡ ይችላል ። በመጀመሪያ ፡ ከሳሽ ፡ ይህን ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ ተከሳሹ ፡ የበለጸገበት ፡ ሁኔታ ፡ በተከሳሹ ፡ ሆን ፡ በሌላ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ዓይነት ፡ ክስ ፡ ሊቀርብበት ፡ የማይችል ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መተርጎም ፡ ይቻላል ። ሁለተኛ ፡ ከሳሹ ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ መመስረት ፡ ሲችል ፡ ይህን ፡ ሳይፈጽም ፡ በመቅረቱ ፡ የክስ ፡ ማቅረብ ፡ ችሎታውን ፡ ሲያጣ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ሶስተኛ ፡ ደግሞ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችል ፡ የነበረው ፡ ሌላው ፡ ክስ ፡ ክሱ ፡ ሊቀርብበት ፡ ይቻል ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ በመክሰሩ ፡ ምክንያት ፡ የማይጠቅም ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መተርጎምም ፡ ይቻላል ።"

እነዚህንና ፡ እነሱን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ጥርጣሬዎች ፡ ለማስወገድና ፡ "የተከታይነት ፡ ጠባይ ፡" የተባለው ፡ ሁኔታ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለመወሰን ፡ አራት ፡ የተለያዩ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮችን ፡ በመውሰድ ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ የሕግ ፡ ደራስያን ፡ የሚያቀርቡትን ፡ መፍትሔ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ለነዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሰጡትን ፡ ውሳኔ ፡ እንመረምራለን ።[24]

---

19. ከሳሽ ፡ ሄርቤር ፡ ተከሳሽ ፡ ጧይ ፡ ሃርዲ ፡ ኤ ፡ ሻንሶ ፡ ዲ ፡ ፩ሺ፱፻- ፪ - ፩፻፶፬ ።
20. ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቍ ፡ ፯፻፳ ፡ ገጽ ፡ ፳፫-፳፬ ።
21. ከዚያው ።
22. ለምሳሌ ፡ ማዞ ፡ ኤ ፡ ማዞን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ ፡ ቍ- ፯፻፪—፯፶፳ ፡ ገጽ ፡ ፯፻፵-፯፻፵፩ ፤ ኮሊ ፡ ኤ፡ ካፒታ ፡ ትሬቴ ፡ ደ ፡ ድርዋ ፡ ሲቪል ፡ (፲፱፻፶፱ ፡ እ- ኤ- አ-) ፡ ፫ልዩም ፡ ፪ ፡ ቍ- ፩ሺ፫፻፳፩-፩ሺ፫፻፳፫ ፡ ገጽ ፡ ፯፻፵፱- ፯፻፶ ።
23. ማስታወሻ ፡ ቍ- ፲ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፳፩ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፸፳ ፡ በኦብሪ ፡ ኤ ፡ ሮው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ፡ (፭ኛ ፡ እትም ፡) ፫ልዩም ፡ ፱ ፡ ውስጥ ፤ በቻሊስ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰ ፡ ውስጥ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳ ፡ላይ ፡ የተጠቀሰ ።

፭/ ከሳሹ ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይችል ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ሕጉ ፡ ዕንቅፋት ፡ ስለሆነበት ፡ ማለትም ፡ አንድ ፡ የሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ስለሚከለክለው ፡ ያንን ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬሞ ፡ ቬርሶ ፡ የተባለውን ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይችላልን ? ለምሳሌ ፡ ከሳሽ ፡ በውል ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችል ፡ ነበር፤ነገር፡ግን፡ሕጉ፡ በሚያዘው፡ጊዜ፡ውስጥ፡ክሱን ፡ ስላላቀረበ፡ በይርጋ ፡ ይታገዳል።

ጸሐፊዎች ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ድምጽ ፡ በእንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ የተባለውን ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አይቻልም ፡ ይላሉ ። ለዚህም ፡ የሚሰጡት ምክንያት ፡ ይህ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በጊዜው ፡ ያለውን ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ ማናወጽ ፡ ይሆናል ፡ የሚል ፡ ነው ።[25] የሚከተሉት ፡ ከፕላንዮልና ፡ ሪፔር ፡ እንዲሁም ፡ ከማዞና ፡ ማዞ ፡ የተውጣጡ ፡ አጫጭር ፡ ንባቦች ፡ የሕግ ፡ ደራሲያን ፡ ዓይነተኛ ፡ አስተያየቶች ፡ ናቸው ።

ፕላንዮናልና ፡ ሪፔር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ዓይነት ፡ ክስ ፡ በሕግ ፡ በታገደ ፡ ጊዜ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ሲቀርብ ፡ አንቀበልም ፡ ያሉትን ፡ በመደገፍ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ ያበረክታሉ ።

ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በሕግ ፡ በታገደ ፡ ክስ ፡ ፈንታ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ መተካት ፡ አይችልም ፡ ያሉበት ፡ ግልጽ ፡ ምክንያት ፡ ክሱን ፡ መቀበል ፡ ስለ ፡ ማስረጃ ፡ ስለ ፡ ይርጋ ፡ ስለ ፡ መብት ፡ መቅረትና ፡ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ክስ ፡ ፍጻሜነት ፡ ያሉንን ፡ ሕጎች ፡ እንደማፍረስ ፡ ስለሚቆጠር ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ሕጎች ፡ ያንዱን ፡ ወገን ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ የሚያጸድቁ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ መፍረስ ፡ የለባቸውም ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ተበዳሪ ፡ የተበደረውን ፡ ገንዘብ ፡ ባለመመለሱ ፡ ያላግባብ ፡ በልጽጓልና ፡ በይርጋ ፡ ምክንያት ፡ ከብድሩ ፡ ነፃ ፡ አይሆንም ፡ ማለት ፡ አይገባም ፡ ስለ ፡ ይርጋ ፡ ስለ ፡ ጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ የተደነገገውን ፡ ሕግ ፡ መሻር ፡ ይቻላል ። ነገር፡ ግን ፡ በአክስዮ ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ አማካይነት ፡ እነዚህን ፡ ሕጎች ፡ መሻር ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ሸፍጥ ፡ እንደመፈጸም ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ።[26]

እንደ ፡ ፕላንዮልና ፡ ሪፔር ፡ በጠቅላላ ፡ በነዚህ ፡ ሁኔታዎች ፡ አላግባብ ፡ መበልጸግን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የሚቀርበውን ፡ ክስ ፡ ሳያወግዙ ፡ ማዞና ፡ ማዞ ፡ እያንዳንዱን ፡ ሁኔታ ፡ ለብቻው ፡ በመመርመር ፡ ሕጉ ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ የሚከለክልባቸውን ፡ ሁኔታዎች ፡ ያጠናሉ ። እነርሱም ፡ "ሕጉ ፡ ለከሳሹ ፡ የፈቀደለት ፡ ሌላ ፡ የክስ ፡ አርእስት በይርጋ ፡ ሲታገድ ፡ የደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ እንዲቀርብ ፡ መፍቀድ ፡ አይቻልም ። ከዚህ ፡ የተቃረነ ፡ አስተያየት ፡ የይርጋን ፡ ሕግ ፡ ጨርሶ ፡ እንደማውደም ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ። ይህንኑ ፡ አስተሳሰብ ፡ በመከተል ፡ የደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ ስለ ፡ ረጅም ፡ ይዞታ ፡ የተደነገገውን ፡ ወይም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፪ሺ፪፻፲፱ ፡ የተመለከተውን ፡ ሕግ ፡ ውጤት ፡ በሚያሳጣው ፡ ዓይነት ፡ ሊጠቀምበት፡ አይቻልም፡" ብለው ፡ ጽፈዋል ። አሁን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በተለይም ፡ የካሳስዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ጉዳይ ፡ ሲያጋጥመው ፡ የሰጣቸውን ፡ ውሳኔዎች ፡ እንመልከት ።

---

24. ይህ ፡ ብዙ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የሚጠቀሙበት ፡ አስተሳሰብ ፡ ነው ፡ ለምሳሌ ፡ ማዞና ፡ ማዞ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፡ ቍ ፡ ፮፻፯-፮፻፱ ፡ ገጽ ፡ ፲፻፵፱-፲፻፵፫ ፡ ተመልከት ።
25. ቻሊስ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳፰ ።
26. ፕላኒዮልና ፡ ሪፔር ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ- ፯፻፳፩ ፡ ገጽ ፡ ፳፯ ፡
27. ማዞና ፡ ማዞ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ አርእስት ፡ ቁ ፡ ፯፻፳ ገጽ ፡ ፲፻፵፫ ፡

አላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ በሌላ ፡ በሕግ ፡ በታገደ ፡ ክስ ፡ ምትክ ፡ ተተክቶ ፡ ሲቀርብ ፡ ተቀባይነት ፡ አይኖረውም ፡ የሚሉ ፡ ብዙ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ አሉ ።[28]

በክላየት ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ የከሳሿን ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳይቀበለው ፡ የቀረው ፡ ክሱን ፡ መፍቀድ ፡ ከሳሿ ፡ በመጀመሪያ ፡ በብድር ፡ ውል ፡ ላይ ያቀረበችውን ፡ ክስ ፡ ያገዱትን ፡ ቍ. ፩ሺ፫፻፱፷፩ ፡ እና ፡ ቍ. ፩፻፫፻፱፷፪ ፡ እንደ ፡ መሻር ፡ የሚቆጠር ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ በብሪያኖ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ከሳሹ ፡ ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተውን ፡ ክስ ፡ ያቀረበው ፡ ቍ. ፩ሺ፯፻፯፫ ፡ የሚያዘውን ፡ ለመፈጸም ፡ ባለመቻሉ ፡ ስለሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀርቷል ። ይህንኑ ፡ የሚመስለው ፡ ጉዳይ በከሳሽ ፡ በደሚዜል ፡ ደጉስት ፡ ደ ፡ ሲንስሲኒና ፡ በተከሳሽ ፡ በግሩምባህ ፡ ኤ ፡ ኮምፓኚ ፡[29] የቀረበው ፡ ጉዳይ ፡ ነው ።ከሳሽ ፡ ክሱን ፡ ያቀረበችው ፡ የጠፋባትን ፡ የጌጣ ፡ ጌጥ ፡ ማስቀመጫ ፡ ለማስመለስ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ለያዘው ፡ ሰው ፡ ፲፯ሺ ፡ ፍራንክ ፡ ስለከፈለች ፤ ዕቃውን ፡ ከሸጠው ፡ ሰው ፡ በአላግባብ ፡ በመበልጸግ ፡ ክስ ፡ መሠረት ፡ የከፈለችው ፡ እንዲመልስላት ፡ ለማድረግ ፡ ነበር ። ሻጩ ፡ ዕቃውን ፡ የገዛው ፡ ከሌባ ፡ ላይ ፡ ነበር ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሳሿ ፡ በቍ. ፪ሺ፪፻፸፱ ፡ እና ፡ በቍ. ፪ሺ፪፻፹ ፡ መሠረት፡ ነጋዴው ፡ ዕቃውን ፡ ሲገዛ ፡ ጥፋት ፡ ማድረጉን ፡ ለማስረዳት ፡ አትችልም ፡ የሚል ፡ ግምት ፡ ስለገባው ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ በኩባንያው ፡ ላይ ፡ ያቀረበችውን ፡ ክስ ፡ ውድቅ ፡ አደረገው ።

፪/ ከሳሹ ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችል ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ስላጓደለ ፡ ክሱን ፡ ከማቅረብ ፡ ታግዷል ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ በአላግባብ፡ መበልጸግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላልን ? የመጀመሪያውን ፡ ክስ ፡ ከማቅረብ ፡ የታገደው ፡ ሕጉ ፡ የሚያዘውን ፡ ባለማወቁ ፡ ወይም ፡ በቸልተኝነት ፡ ምክንያት ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ነው ።[30] ይህ ፡ ሲሆን ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ በታገደው ፡ ክስ ፡ ምትክ ፡ ሊተካ ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ ማንንም ፡ ጸሐፊ ፡ አላገኘንም ። ፕላንዮልና ፡ ሪፔር ፡ በሕግ ፡ እክልና ፡ በከሳሹ ፡ ቀጥታዊ ፡ ምክንያት ፡ በሚፈጠር ፡ እክል ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አያደርጉም ፤ ሁለቱንም ፡ ዓይነት ፡ እክሎች ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ ሽፍጥ ፡ ማስከተል ፡ አይገባቸውም ፡ በሚል ፡ መስመር ፡ ስለሚመለከቷቸው ፡ እንደሚከተለው ፡ ይጽፋሉ ፡—

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ያንድ ፡ ወገን ፡ መበልጸግና ፡ የሌላው ፡ ወገን ፡ መደህየት ፡ የተያያዙ ፡ ቢሆኑም ፡ አንድ ፡ የሕግ ፡ አንቀጽ ፡ የካሣ ፡ መክፈሉን ፡ ጉዳይ ፡ የሚያግድ ፡

28. ፕላኒዮልና ፡ ሪፔር ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ ፫፯ ፡ ገጽ ፡ ፷፯ ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ (፩) ፡ (፫-፯) ፡ ገጽ ፡ ፷፯ ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡
29. (፩—፫) ዲ- ፒ ፲፱፻፴፩ - ፩ - ፩፻፳፱
30. በተጨማሪም ፡ ያልታወቀና ፡ ያልተገመተ ፡ ስህተት ፡ ባንዳንድ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ይጨመራል ። የሚከተሉት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቨርሶ ፡ ክስ ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ይፈቅዳሉ ። ቻሊስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳፩ ፤ ኮሊንና ፡ ካፒታ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ (፲፫ኛ ፡ እትም) ፡ ቮልዩም ፡ ፪ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፲፯ ፤ ዦስራ ፡ ኰር ፡ ደ ፡ ድርዋ ፡ ሲቪል ፡ ፓሲቲፍ ፡ ፍራንሴ ፡ (፪ኛ ፡ እትም)፡ ቮልዩም ፡ ፪ ፡ ቍጥር ፡ ፭፻፵፯ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፲፯ ፤ ሪፔር ፡ ላ ፡ ሬግል ፡ ሞራል ፡ (፪ኛ ፡ እትም) ፤ ገጽ ፡ ፩፻፶ ። በመጻሕፍት ፡ ቤታችን ፡ የሚገኘው ፡ የሪፔር ፡ መጽሐፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚናገረው ፡ ስለ ውል ፡ መፍረስ ፡ ወይም ፡ መለወጥ ፡ ስለሆነ ፡ የቻሊስን ፡ “የማይገመት ፡ ስህተት” ከጽሑፌ ፡ አስወግጀዋለሁ ።

መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ መወሰን ፡ ያዳግታል ። ለምሳሌ ፡ ከሳሹ ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ ዕቃ ፡ ይሰጥና ፡ ዋጋውን ፡ ወደፊት ፡ እንዲከፍል ፡ ይዋዋላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሌሎች ፡ ባለገንዘቦች ፡ ቅድሚያ ፡ የሚያሰጠውን ፡ መያዣ ፡ መጠየቅ ፡ ሲችል ፡ ሳይጠይቅ ፡ ይቀራል። ስለዚህም ፡ ከሌሎች ፡ ባለገንዘቦች ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ መብት ፡ እኩል ፡ ወይም ፡ ያነሰ ፡ ይሆናል ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ በአከፋፈል ፡ አንድ ፡ ባለገንዘብ ፡ ከሌሎች ፡ ባለገንዘቦች ፡ ቅድሚያ ፡ ሊያሰጡት ፡ የሚችሉትን ፡ ፎርማሊቴዎች ፡ ካላሟላ ፡ በስተቀር ፡ ቅድሚያ አይሰጠውም ፡ የሚለው ፡ ሕግ ፡ ሰውየው ፡ ምንም ፡ ሌሎቹን ፡ ባለገንዘቦች ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ቢጠቅማቸውም ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግን ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ክስ ፡ እንዳያቀርብ ፡ አይከለክለውምን ? መልሱ ፡ ይከለክለዋል ፡ የሚል ፡ መሆን፡ አለ በት ፡ እንላለን ።[31] ማርቲና ፡ ሬኖም ፡ ይህንኑ ፡ አስተያየት ፡ ይደግፋሉ ። እነር ሱም ፡ "የሚገባው ፡ የክስ ፡ መንገድ ፡ በሕግ ፡ የታገደ ፡ ሲሆን ፡ ደ ፡ ኢን ፡ ሬም፡ ቬርስ፡ ክስ ፡ ሊተካው ፡ አይችልም ። ለምሳሌ ፡ ሕጉ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ መያዣ ፡ የሆነ ውን ፡ ንብረት ፡ ሳያስመዘግብ ፡ሲቀር ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ከርሱ ፡ መብት ፡ ጋር ፡ የተስተካከለ ፡ መብት ፡ የሚኖራቸውን ፡ ሌሎች ፡ አበዳሪዎች ፡ አላግባብ ፡ ተጠቅመ ዋል ፡ ብሎ ፡ ሊከስ ፡ አይችልም ።"[32] ይላሉ ፡ (ዲ - ፩ሺ፱፻፷፬ ፡ ፩ሺ፩፻፷፱)

ሩዋስት ፡ ደግሞ ፡ ጉዳዩን ፡ እንደሚከተለው ፡ አድርጎ ፡ አሳምሮ ፡ ገልጾታል ። በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ማዕበል ፡ ውስጥ ፡ ለገባ፡ ሰው ፡ የደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ ማምለጫ ፡ ጀልባ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።[33]

አንድ ፡ ሰው ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችል ፡ የነበረውን ፡ ክስ ፡ በገዛ ፡ ጥፋቱ ፡ ምክንያት ፡ ማቅረብ ፡ ሲያቅተው ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግን ፡ አርእስተ ፡ ክስ ፡ አድርጎ ፡ የሚያቀር በውን ፡ ክስ ፡ ውድቅ ፡ ያደረጉ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔዎች ፡ አሉ ።[34] ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ በ፩ሺ፱፻፷፬ ፡ የተወሰነው ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ከሳሹ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ የልጁ ፡ ባል ፡ ቤት ፡ እንዲሠራ ፡ ገንዘብ ፡ አበደረው ። ቤቱ ፡ ተሰርቶ ፡ ሲያልቅ ፡ የከ ሳሹ ፡ ልጅ ፡ ባል ፡ የሽርክና፡ ማኅበር ፡ ስለገባ ፡ ቤቱንም ፡ መሬቱንም ፡ መዋጮ ፡ አደ ረገው ። ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ ማኅበሩ ፡ ከሰረና ፡ ሂሳብ ፡ ተጣራ ። ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ በተ መሠረተ ፡ ክስ ፡ ከሳሹ ፡ ሌሎቹን ፡ የማኅበሩን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ከሰሳቸው ። ክር ክሩም ፡ የመሬቱ ፡ ዋጋ ፡ ጨምሯል ፡ ይህም ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ ለልጄ ፡ ባል ፡ ገንዘብ፡ አበድሬው ፡ በዚህ ፡ ገንዘብ ፡ መሬቱ ፡ ላይ ፡ ቤት ፡ ስለሰራበት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የመ ሬቱ ፡ ዋጋ ፡ ጭማሪ ፡ በቅድሚያ ፡ ለኔ ፡ መከፈል ፡ አለበት ፡ ከሌሎቹ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ መብት ፡ የተሰጠኝ ፡ እንደሆን ፡ ግን ፡ እነሱ ፡ ያላግባብ ፡ በለጸጉ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ነበር ። ቍ ፡ ፪ሺ፩፻፫ ፡ (፬) ፡ እና ፡ (፭) ፡ በሚያዙት ፡ መሠረት ፡ የቅድ ሚያ ፡ መብት ፡ ይዞ ፡ ባለመቆየቱ ፡ የከሳሹ ፡ ክስ ፡ ውድቅ ፡ ሆነ ።

---

31. ፐላኒዮልና ፡ ሪፔር ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፡ ቍ ፯፻፷፪ ፡ ገጽ ፡ ፷፰ ፡
32. ማርቲና ፡ ሬይኖ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፡ ቍ ፡ ፫፻፶፫ ፡ (፪) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷-፴፪ ፡
33. ሩዋስ ፡ ላንሪሽስማ ፡ ሳን ፡ ኮዝ ፡ ኤ ፡ ላ ፡ ዡሪስፕሩዳንስ ፡ ሲቪል "ሬቩ ትሪሜስቴል ፡ ድሩዋ ፡ ሲቪል፡" ፲፱፻፳፪ ገጽ ፡ ፹፯ ፡ ድራኪዲስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፡ ገጽ ፡ ፳፻፹፭
34. ከሳሽ ፡ ክሬዲ ፡ ፎንሲየር ፡ ዶ ፡ ፍራንስ ፡ ተከሳሽ ፡ አራዘ ፡ ዲ ፡ ፩ሺ፷፻፹፱- ፩-፫፻፺፫ ፤ ከሳሽ ፡ ዣክ ፡ ተከሳሽ ፡ ላቤል ፡ ፍሬር ፡ ኤ ፡ ቤርቲኖ ፡ ዠን ፡ ዴ ፡ ፲፱፻፲፫ - ፩ሺ፩፻፴፫ ፡ በተጨማሪ ፡ በሌሎች ፡ የሕግ ጉዳይ ፡ ማከማቻ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ።
35. ከሳሽ ፡ ሎሬንስ ፡ ሲንዲክ ፡ ደ ፡ ላ ፡ ፋዪት ፡ ሶሲያል ፡ ሚፕል ፡ ኤ ፡ ታራይር ፤ ተከሳሽ ፡ ማርትይ ፡ ዲ ፡ ፒ ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ፩ - ፩፻፷፱ ፡

፫/ ከሳሹ ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ ሲችል ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ክሱን ፡ ማቅረብ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ የሚነሳው ፡ አንዱ ፡ ተዋዋይ ፡ ወገን ፡ ቢከስርና ፡ በውል ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ በማይጠቅምበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።[36] ስለዚህም ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ የሚቀርበው ፡ በሌላ ፡ በሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላልን ?

ቁጥራቸው ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ከሆነ ፡ ጸሐፊዎች ፡ በስተቀር ፡ ጸሐፊዎች ፡ በእንደ ዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ሁለተኛ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይቻላል ፡ ይላሉ ። ይህ፡ሁኔታ ፡ ከላይ፡ ከተጠቀሱትና ፡ ወደፊት ፡ ከሚጠቀሱት ፡ ሁኔታዎች ፡ የሚለየው ፡ ባላግባብ ፡ መበል ጸግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተው ፡ ክስና ፡ በውል ፡ የሚመሠረተው ፡ ክስ ፡ የሚመለከቱት ፡ ሁለት ፡ የተለያዩ ፡ ወገኖችን ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። በተጨማሪ ፡ ሁለተኛው ፡ ክስ ፡ ሊተካ የሚችለው ፡ ሶስተኛው ፡ ወገን ፡ የበለጸገው ፡ አለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሲሆን ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባም ። ፕላንዮልና ፡ ሪፔር ፡[37] እንደሚያመለክቱት ፡ የሶስ ተኛው ፡ ወገን ፡ መበልጸግ ፡ ከከሳሽ ፡ ሃብት ፡ መቀነስ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ቢሆንም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ። ምክንያቱም ፡ የሶስተኛው ፡ ወገን ፡ መበልጸግ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚኖረው ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ የበለጸገው ፡ ወገን ፡ ለብልጽግናው ፡ ምክንያት ፡ የሌለው ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያልተከፈለው፡ ወገን፡ የደ፡ ኢን፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ፡ ማቅረብ፡ ይችላል ። ምክንያቱም ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ሲያጋጥም ፡ ክሱን ፡ መፍቀድ ፡ ሕጉ ፡ የከለከለውን ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ ማግኘትን ፡ ስለማያስከትል ፡ ነው ። ማለ ትም ፡ ጥቅም ፡ አይሰጥም ፡ እንጂ ፡ በውል ፡ የተመሠረተው ፡ ክስ ፡ አሁንም ፡ ሊቀ ርብ ፡ ስለሚችል ፡ ነው ።

ድራኪድስም ፡[38] ቢሆን ፡ ፍትሕ ፡ ስለሚፈቅደውና ፡ የክሱ ፡ ተተክቶ ፡ መቅረብ፡ የሕጉን ፡ አቋም ፡ ስለማያናጋ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ክስ ፡ እንዲቀርብ ፡ መፈቀድ፡ አለበት፡ ይላል ።

ሼቫልየር ፡[39] ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ፡ መከልከል ፡ ያለበት፡ ሕግን ፡ የመሸሽያ ፡ ዘዴ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡ ባይ ፡ ስለሆነ ፡ ባሁኑ ፡ ሁኔታ ፡ የክሱ ፡ መፈቀድ ፡ ተገቢ ፡ ነው ፡ ይላል ፡ "በውል ፡ የተመሠረተው ፡ ክስ ፡ በሁለተኛው ፡ ተዋዋይ ፡ መክሰር ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡ ሶስተኛውን ፡ ወገን ፡ በመክሰስ ፡ ያላግባብ ፡ የያዘውን ፡ ሃብት ፡ እንዲመልስ ፡ ማድረግ ፡ የሚቻል" ፡ ሲል ፡ አትቷል ።

ኤስማይን ፡[40] ባንድ ፡ የካስሰዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጉዳይ ፡ ቀርቦ ለት ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ አስተያየቱን ፡ ሲሰጥ "ይህ ፡ ክስ ፡ በሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ በመቅረቡ ፡ ከሳሹ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ሕግ ፡ ስላልተላለፈ ፡ የደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ የሚታገድበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ፡" ብሏል ።

---

36. ማርቲና ፡ ሬይኖ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርእስት ፡ ፫፻፶፫ ፡ (፪) ገጽ ፡ ፫፻፳፩
37. ፕላኒዮልና ፡ ሪፔር ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ ፡ ፯፻፳፫ ፡ (፪) ገጽ ፡ ፸፪ ፡
38. ድራኪዲስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፹፯
39. ጂ ፡ ሼቫልዬ ፡ "አብዘርቫሲዮን ፡ ሱር ፡ ላ ፡ ሪፔቲስዮን ፡ ዴዘንሪሽማን ፡ ኖን ፡ ኮዜ" ሉ ፡ ድሩዋ ፡ ፕሬቬ ፡ አ ፡ ሚሊየ ፡ ዲዩ ፡ በንቲየም ፡ ሲየክል ፡ (፲፱፻፶፱) ፡ ቮልዩም ፪ ገጽ ፡ ፪ ፡ ፪፻፵፰
40. በግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፹፩ ፡ ጉሬ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፹፩ ፡ የቀረበ ።

አብዛኞቹ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ከሚሰጡት ፡ አስተያየት ፡ በመለየት ፡ ጎሬ ፡ በንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ክሱን ፡ መፍቀድ ፡ ሕጉን፡መተላለፍን ፡ ስለሚያስከትል ፡ መፈቀድ ፡ የለበትም ፡ ይላል ። አስተሳሰቡ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።[41] ተተኪውን ፡ ክስ ፡ መፍቀድ ፡ ከሳሽ ፡ በሶስተኛ፡ ወገን፡ ላይ፡ ቀጥታዊ ፡ ክስ፡ እንዲያመጣ ፡ መፍቀድ ፡ ነው ።[42]

እንደ ፡ ደንቡ፡ግን፡ አንድ ፡ አበዳሪ ፡ ቀጥታዊ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ ከተበዳሪው ፡ በተበደሩ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ባሁኑ ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ክሱ ፡ የሚቀርበው ፡ በሶስተኛ ፡ ደረጃ ፡ ተበዳሪ ፡ ላይ ፡ ሳይሆን ፡ በደፈናው ፡ ተካፋይ ፡ በሆነ ፡ በሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ነው ።

አልሞሰኒኖም ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ በቀላሉ ፡ እንዲፈቀድ ፡ አያደርግም ።[43] ከሳሹ ፡ ሶስተኛውን ፡ ወገን ፡ መክሰስ ፡ የሚችለው ፡ የከሰረው ፡ ወገን ፡ አበዳሪ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። ሌሎች ፡ አበዳሪዎች ፡ ካሉ ፡ ግን ፡ ተተኪውን ፡ ክስ ፡ መፍቀድ ፡ ከሌሎቹ ፡ ይልቅ ፡ ቅድሚያ ፡ መስጠት ፡ ስለሚሆን ፡ አይገባም ፡ ይላል ። ስለዚህ ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ አበዳሪ ፡ ተቆጥሮ ፡ ከሶስተኛው ፡ ወገን ፡ ንብረት ፡ በመከፈል ፡ የሚያደርሰውን ፡ መቀበል ፡ አለበት ።

ፍርድ ፡ ቤቶቹም ፡ የያዙት ፡ አስተያየት ፡ አብዛኞቹ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ካሉት ፡ ጋር ፡ የሚስማማ ፡ ነው ። በ፩ሺ፱፻፷ ፡ የካሳስዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህንኑ ፡ መስመር ፡ በመከተል ፡ የሚከተለውን ፡ አንድ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ አጽንቶታል ።[44]

አንድ ፡ ሰው ፡ ከአንድ ፡ ኩባንያ ፡ ላይ ፡ ቤት ፡ ገዛና ፡ ለማደስ ፡ የሥራ ፡ ተቋራጭ፡ ቀጠረ ፤ በመሀሉ ፡ ስለከሰረ ፡ ኩባንያውንም ፡ የሥራ ፡ ተቋራጩንም ፡ ለመክፈል ፡ ሳይችል ፡ ቀረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኩባንያው ፡ ቤቱን ፡ መልሶ ፡ ወሰደ ። የሥራው ፡ ተቋራጭ ፡ የቤቱን ፡ ገዢ ፡ በውላቸው ፡ መሠረት ፡ ለመክሰስ ፡ ይችል ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ገዢ ፡ ስለከሰረ ፡ እርሱን ፡ መክሰሱ ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ ስለማይሰጠው ፡ ባላግባብ ፡ መበልጸግ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ በኩባንያው ፡ ላይ ፡ አቀረበ ፡ ይህንንም ፡ ያደረገበት ፡ ምክንያት ፡ የቤቱ ፡ ባለቤት ፡ በከሳሽ ፡ ሥራና ፡ ንብረት ፡ ስለበለጸገ ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክሱን ፡ ተቀብሎታል ። በይግባኝ ፡ ላይ ፡ የከሳስዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርዱን ፡ አጽንቶታል ።

፩/ ሃብቱ ፡ ያላግባብ ፡ የተቀነሰበት ፡ ወገን ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ሲችል ፡ ይህንትቶ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላልን ?

የጸሐፊዎች ፡ አስተያየት ፡ የሚያዘነብለው ፡ አይችልም ፡ ወደሚለው ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ማዞና ፡ ማዞ ፡ "ሃብቱ ፡ የተቀነሰበት ፡ ወገን ፡ በውል ፡ ከውል ፡ ውጪ ፡ ባለ ፡

41. ጐሬ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ ፩፻፹ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፹፩

42. ቍ. ፩ሺ፩፻፷፭ ፡ ውል ፡ ውጤት ፡ የሚኖረው ፡ በተዋዋዮች ፡ መሐል ፡ ነው ፡ ይላል ። በቍ፡ ፩ሺ፩፻፷፯ መሠረት ፡ ግን ፡ አበዳሪ ፡ የተበደረውን ፡ ተበዳሪ ፡ መክሰስ ፡ ይችላል ። ይህ ፡ የሚቻለው ፡ ግን ፡ የመጀመሪያው ፡ ተበዳሪ ፡ የራሱን ፡ ተበዳሪ ፡ ለመክሰስ ፡ መብት ፡ ሲኖረው ፡ ነው ።

43. አልሞሰኒኖ ፡ ላንሪሽስማ ፡ ሳን፡ኮዝ ፡ ኤ ፡ ሳን ፡ ካራክቴር ፡ ሱብሲዲየር ፡ (፩ሺ፱፻፴፩) ፡ ቍ. ፹፫ ፡ ገጽ ፩፻፷፯ እና ፡ ተከታይ ፤ በቻሊስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳፱-፩፻፳፫ ፡ ውስጥ ፡ እንደቀረበው ።

44. ከሳሽ ፡ ሶሲየቴ ፡ ዲዝቢታሲዮ ፡ ቦን ፡ ማርሼ ፡ ደ ፡ ሳን ፡ ስርቫን ፡ ተከሳሽ ፡ ጕርኾ ፡ ዲ ፡ ኤች ፡ ፲፱፻፵ ፡ ፩፻፶ ፤ በከፊል ፡ በማዞና ፡ ማዞ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፮፻፵፱-፮፻፵፫ ፡ ፱ሺ፮፻፵፰-፮፻፵፱ ውስጥ ፡ እንደተገለጠ ።

ግዴታ ፡ በማይገባ ፡ በመክፈል ፡ ባልተፈቀደ ፡ ውክልና ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ በግዙፍ ፡ መብት ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ የሚችል ፡ ከሆነ ፡ የደ ፡ ኤን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ የተከታይነት ፡ ጠባይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ የክስ ፡ መሠረቶች ፡ ትቶ ፡ ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ መሠረት ፡ ክሱን ፡ ከማቅረብ ፡ ያግደዋል ።"[45]

በማርቲና ፡ ሬኖ ፡ አስተያየት ፡ "ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ሕጎች ፡ የተፈጠሩት ፡ በዳኝነት ፡ ሲሆን ፡ ላፈጣጠራቸውም ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ጉድለት ፡ ለማሟላት ፡ ስለሆነ ፡ ከሳሽ ፡ ሊጠቀምባቸው ፡ የሚችለው ፡ ሕጉ ሌላ ፡ የክስ ፡ ዘዴ ፡ ሳይሰጠው ፡ ሲቀር ፡ ብቻ ፡ ነው ።"[46]

ጎሬም ፡ ለከሳሹ ፡ ምርጫ ፡ አይፈቅድም ፤ ይህንንም ፡ የሚለው ፡ በፈረንሣዊ ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ ደረጃ ፡ አመዳደብ ፡ መሠረት ፡ ነው ።[47] በዚህ ፡ የሕግ ፡ ሃሳብ ፡ መሠረት ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎችና ፡ ከልማድ ፡ የሚመነጩ ፡ ሕጎች ፡ የሚታሰቡት ፡ ከሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ ከወጡት ፡ ሕጎች ፡ በታች ፡ ነው ። ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስም ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተፈጠረ ፡ ሃሳብ ፡ ስለሆነ ፡ ሕጉ ፡ ለከሳሹ ፡ ሌላ ፡ የክስ ፡ መንገድ ፡ ሲፈቅድለት ፡ ይኸኛው ፡ ቀርቶ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ሊተካ ፡ አይችልም ።[48] በፕላንዮልና ፡ ሪፔር ፡[49] ፡ አስተያየት ፡ የክስ ፡ ዘዴ ፡ ማማረጥ ፡ ጉዳይ ፡ በውል ፡ ውስጥ ፡ ሊነሳ ፡ አይችልም ፡ ስልጣን ፡ ሳያገኝም ፡ በሚሠራ ፡ ወኪል፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የመነሳቱ ፡ ዕድል ፡ በጣም ፡ የመነመነ ፡ ነው ። የመምረጡ ፡ ጉዳይ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ በሚነሳ ፡ ክስ ፡ ውስጥ ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ የማይሠራበት ፡ ምክንያት ፡ በመበልጸጉና ፡ ሀብት ፡ በማጣቱ ፡ መካከል ፡ የምክንያታዊ ፡ ግንኙነት ፡ እንዲኖር ፡ ስለሚያስፈልግ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሳሹ ፡ የፈለገውን ፡ የክስ ፡ ዓይነት ፡ ለመምረጥ ፡ ሙሉ ፡ መብት ፡ እንዲኖረው ፡ ያስፈልጋል ፡ ወደሚሉት ፡ ጸሐፊዎች ፡ እናምራ ። ቻሊስ ፡[50] እንደሚለው ፡ ይህን ፡ አስተያየት ፡ የሚያቀርቡት ፡ አዳዲስ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የሚሉት ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ተከታይነት ፡ ጠባይ ፡ የሚሠራው ፡ ሕጉ የሚያዘውን ፡ ባልፈጸመ ፡ ከሳሽ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ ቻሊስ ፡ እንደሚለው ፡ ኤስማይን፡ ለቁ ፡ ፩ሺ፰፻፲፩ ፡ ፩-ሺ ፩፻፷፩ ፡በሰጠው ፡ አስተያየታዊ ፡ ማብራሪያ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ተከታይነት ፡ እንደሚከተለው ፡ መገለጽ ፡ አለበት ፡ ብሏል ።

<u>የደ ፡ ኤን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ</u> ፡ መቅረብ ፡ የማይችለው ፡ ከሳሹ ፡ በይርጋ ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ የሚገባውን ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ባለመቻሉ ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ሳይችል ፡ ሲቀር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

45. ማዞና ፡ ማዞ ፡ <u>ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት</u> ፡ ቊ ፡ ፯፻፺ ፡ ገጽ ፡ ፯፻፹፱ ፡
46. ማርቲና ፡ ሬይኖ ፡ <u>ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት</u> ፡ ቊ ፡ ፫፻፶፫ ፡ (፱) ገጽ ፡ ፫፻፹
47. ጐሬ ፡ <u>ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት</u> ፡ ቊ- ፩፻፺፱-፱፻፬- (ገጽ ፡ ፱፻፪-፱፻፬) ፡ ይህ ፡ የሕግ ፡ ደረጃ ፡ አመዳደብ ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ መጨረሻው ፡ ላይ ፡ ይዘረዘራል ።
48. እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቊ ፱፻፹፰ ፡ ገጽ ፡ ፫፻-፫፻፩
49. ፕላኒዮልና ፡ ሪፔር ፡ <u>ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት</u> ፡ ቊ- ፯፻፹፫ ፡ (፩) ፡ ገጽ ፡ ፫፱ ፡
50. ቻሊስ ፡ <u>ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት</u> ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳፩ ፡
51. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳፯

በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በቤልጅግና ፡ በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ተመሳሳይነት ፡[52] ስላለ ፡ የቤልጅግ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የሚሰጡትን ፡ አስተያየት ፡ መመልከት ፡ ይጠቅማል ። ሩትቤርት ፡[53] ሁለት ፡ ክሶች ፡ ሊቀርቡ ፡ ሲችሉ ፡ ከሳሹ ፡ በአንደኛው ፡ ብቻ ፡ እንዲወሰን ፡ ማድረግ ፡ ምክንያቱ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ፡ ይላል ። አልሞሲኖና ፡[54] ቤጌም ፡ ተመሳሳይ ፡ አስተያየት ፡ አላቸው ፡ ይባላል ።

እንደ ፡ ምሁራት ፡ በአስተያየት ፡ ሳይለያዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ "አንድ ፡ ከሳሽ ፡ ሌላ ፡ የክስ ፡ መዋጮ ፡ ሲኖረው ፡ ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ሊተካው ፡ አይችልም ፤" ይላሉ ። ከክልየትና ፡ ብርያኖ ፡ ጉዳዮች ፡ ጀምረው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ሁልጊዜ ፡ ቦታውን ፡ ለሌላው ፡ ክስ ፡ መልቀቅ ፡ እንዳለበት ፡ ወስነዋል ። ለምሳሌ ፡ በ፩ሺ፱፻፵፱ ፡ የካሳስዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደሚከተለው ፡ ብሏል ።

"ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ለመቅረብ ፡ የሚችለው ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ውል ፡ ሳይኖርና ፡ ሃብቱ ፡ የተቀነሰበት ፡ ወገን ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ በሚደርስ ፡ ግዴታ ፡ መክሰስ ፡ ሳይችል ፡ ሲቀር ፡ ብቻ ፡ ነው ።"[56]
በ፲፱፻፶፩ ፡ ደግሞ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደሚከተለው ፡ የመጀመሪያ ፡ ሃሳቡን ፡ መልሶ ፡ አቅርቦታል ።

"የደ ፡ ኤን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ በተፈጥሮው ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ወይንም ፡ በተከታይነት ፡ ብቻ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ስለሆነ ፡ ክሱ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ በውል ፡ ወይም ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ በሚፈጠር ፡ ግዴታ ፡ ሊመሠረት ፡ የማይችል ፡ ሲሆን ፡ ብቻ ነው ።"[57]

እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ አነጋገር ፡ ጉዳዩን ፡ በደንብ ፡ አይገልጸውም ፡ ምክንያቱም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተውን ፡ ክስ ፡ ያልተቀበለው ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ሊተካ ፡ ስለማይችል ፡ ሳይሆን ፡ ከሳሹ ፡ ሕጉ ፡ የሚያዘውን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ የክልየትና ፡ የብርያኖ ፡ ጉዳዮች ፡ ሁለቱም ፡ ተቀባይነት ፡ ያላገኙት ፡ ሕጉ ፡ የሚያዘውን ፡ ስለሚጻረሩ ፡ ነው ።

ኢንሳይክሎፒዲ ፡ ዳሎዝ ፡[58] ይህንኑ ፡ ሲያረጋግጥ ፡ እንደ ፡ ቻሊስ ፡[59] ያሉ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ደግሞ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ተመሳሳይ ፡ ውሳኔ ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ነበር ፡ ይላሉ ። ለማንኛውም ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አስተያየት ፡ የደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ክስ ፡ ለፍትሕ ፡

---

52. ቻሊስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፰ ፤
53. ሩትቤር ፡ "ዱ ፡ ኳራክቴር ፡ ኖን ፡ ሱብሲዲዮር ፡ ደላክሲዮን ፡ ደላንሪሽስማ ፡ ሳን ፡ ኮዝ" ሬቩ ፡ ዱ ፡ ድሮዋ ፡ ቤልዥ ፡ ፩ሺ፱፻፴፯ ፡ ቍ ፲፫ ፡ ገጽ ፡ ፵ ፤ በቻሊስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፰ ፡ እንደቀረበው ።
54. አልሞሲኒኖ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ ፹፯ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳፯ ፡
55. ቤጌ ፡ "ላንሪሽስማ ፡ ሳን ፡ ኮዝ" ፓሪ ፡ ፩ሺ፱፻፶፰ ፡ ቍ ፩፻፶፯ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፶፫ ፡ ቍ ፩፻፶፬ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፷፰
56. ቡል ፡ ካሳሲዮ ፡ ሲቪል ፡ ፩ሺ፱፻፵፱ ፡ ፲፻፶፩ ፡ በድራኪዲስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፭ እንደተጻፈ ።
57. ቡል ፡ ካሳስዮ ፡ ሲቪል ፡ ፩ሺ፱፻፶፩-፩-፳፯ ፡ በድራካዲስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፭ እንደተጻፈ
58. ዳሎዝ ፡ ኤንሲክሎፒዲ ፡ ዡሪዲክ ፡ ደ ፡ ድሩዋ ፡ ሲቪል ፡ (፲፱፻፶፱) ቮልዩም ፡ ፪ ፡ አንሪሽዘማ ፡ ሳን ፡ ኮዝ ቍ ፩፻፴፭
59. ቻሊስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፴

ሲባል ፡ በዳኝነት ፡ የተፈጠረ ፡ ስለሆነ ፡ ከሌላ ፡ ምንጭ ፡ ከመነጩ ፡ የክስ ፡ መነሻ ዎች ፡ ጋር ፡ ሊመጣጠን ፡ አይችልም ፡ ባዮች ፡ ናቸው ።

፫/ ከላይ ፡ ለተጠቀሱት ፡ አራት ፡ ሁኔታዎች ፡ አምስተኛ ፡ መጨመር ፡ ይቻላል። ጉዳዩ ፡ ግልጽ ፡ በመሆኑ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ጸሐፊዎች ፡ በጽሑፋቸው ፡ ውስጥ ፡ አይጨ ምሩትም ።[60] ይህ ፡ የሚሆነው ፡ ሃብቱ ፡ የተቀነሰበት ፡ ወገን ፡ በውል ፡ ወይም ፡ ከውል ውጭ ፡ ግዴታ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ በማይችልበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ሕጉ ፡ ለሁኔታው ፡ የሚሰጠው ፡ የክስ ፡ መሠረት ፡ የለም ፡ ስለዚህ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስን ፡ ማቅረብ ፡ ሕጉን ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ አይጻረርም ፡ እንዲያውም ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ያለመሟላት ፡ ለማሻሻል ፡ ሲባል ፡ የተፈጠረ ፡ ክስ ፡ ሆኖ ፡ ይገ ኛል ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ክሱን ፡ የማይፈቅድ ፡ አይገኝም ።

የሚከተሉት ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮች ፡ ሌላ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችል ፡ ክስ ፡ ሳይኖር፡ ያላግባብ፡ መበልጸግን ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይቻላል ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡[61] ምን ፡ ማለት ፡ እንደ ሆነ ፡ ያስረዳሉ ።

በመጀመሪያው ፡ ጉዳይ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ በፈረንሣይ ፡ ሃገር ፡ ውስጥ ፡ ኑዛዜ ፡ ሳታ ደርግ ፡ ካረፈች ፡ በኋላ ፡ ንብረቷ ፡ ይገባቸዋል ፡ ለተባሉ ፡ ወራሾች ፡ ተሰጠ ። አንድ ፡ ሥራው ፡ የሰውን ፡ ትውልድ ፡ ማጥናት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ መውረስ ፡ የሚገባቸው ፡ የሟቿ የወንድም ፡ ልጆች ፡ መኖራቸውን ፡ በምርምር ፡ ደረሰበት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነርሱን ፡ አግኝቶ ፡ ውርስ ፡ እንዳላቸው ፡ ከነገራቸው ፡ በኋላ ፡ መጠኑንና ፡ የሚገኝበትን ፡ ዘዴ ፡ እንዲነግራቸው ፡ ከፈለጉ ፡ ከውርሱ ፡ ሊያካፍሉት ፡ ውል ፡ እንዲገቡ ፡ ጠየቃቸው ። ውርስ ፡ እንዳላቸው ፡ ካወቁ ፡ በኋላ ፡ በፈረንሣይ ፡ የሚገኘውን ፡ የአሜሪካን ፡ ቆንሲል፡ አግኝተው ፡ ጉዳዩን ፡ እንዲያጣራላቸው ፡ ከጠየቁ ፡ በኋላ ፡ ዕውነት ፡ ሆኖ ፡ ስላገ ኙት ፡ መዋዋል ፡ አለመፈለጋቸውን ፡ ለሰውየው ፡ ነግረው ፡ የሚገባቸውን ፡ ድርሻ ፡ አገኙ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ የሚያጠናው ፡ ሰው ፡ ለሰጣቸው ፡ መረጃ ፡ ገን ዘብ ፡ እንዲከፍሉት ፡ ክስ ፡ አቀረበ ፡ ተከሳሾቹም ፡ የከሳሽ ፡ ጉዳይ ፡ ውድቅ ፡ እንዲሆንላቸው ፡ ጥያቄ ፡ አቀረቡ ፤ የሰጡትም ፡ ምክንያት ፡ ክሱ ፡ በውል ፡ ወይንም በእንደራሴነት ፡ መጠን ፡ ያልተፈጸመ ፡ በመሆኑ ፡ መነሾ ፡ ሊኖረው ፡ የማይችል ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ነበር ። ክሱ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ አይቶ ፡ በሌላ ፡ ሰው፡ ምክንያት ፡ የሚበለጽግ ፡ ሰው ፡ የሚገባውን ፡ ክፍያ ፡ ካላደረገ ፡ በደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ መክሰስ ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡ ክሱን ፡ ተቀበለው ፤ በይግባኝ ፡ የካሳሲዮን ፡ ፍርድ፡ ቤትም ፡ ፍርዱን ፡ አጸናው ።

ሁለተኛው ፡ ጉዳይ ፡ ደግሞ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነበር ።[62] ከሳሽ ፡ በተከሳሽ ፡ ቤት ፡ በግርድና ፡ ተቀጥራ ፡ ስትሠራ ፡ ከቆየች ፡ በኋላ ፡ ተከሳሽ ፡ ሚስቱን ፡ ፈታ ፤ ከዚ ያም ፡ ከሳሽን ፡ በውሽምነት ፡ ያዛት ። እንደሚያገባት ፡ ከገለጸላትም ፡ በኋላ ፡ ከርሱ ፡ ደመወዝ ፡ መቀበሏን ፡ ትታ ፡ አብረው ፡ ኑሯቸውን ፡ ቀጠሉ ። ሰባት ፡ ዓመት ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ መተሳሰር ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ሊያገባት ፡ እንደማይፈቅድ ፡ ነገራትና ፡ ሁኔታው፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ደረሰ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሳሽ ፡ ሰላሳ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ፍራንክ ፡ በመጠ የቅ ፡ ከሰሰችው ። ለክሷ ፡ መሠረት ፡ አድርጋ ፡ ያቀረበችው ፡ ሁለት ፡ ነገር ፡ ነበር ።

60. ድራኪዲስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፭፻፹፰- ከሚገኙት ፡ ጥቂቶቹ ፡ አንዱ ፡ ነው ።

61. ከሳሽ ፡ ኮንሰር ፡ ዱቡርግ ፡ ተከሳሽ ፡ አንትዋን ፡ ዲ ፡ ፩ሺ፱፻፳- ፱- ፫፻፴፪

62. ከሳሽ ፡ ለብላን ፡ ተከሳሽ ፡ ደምቪያል ፡ ዲ ፲፱፻፳፰- ፱- ፩፻፳፱ ፡

የመጀመሪያው ፡ ሊያገባት ፡ ቃል ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ቃሉን ፡ ባለመጠበቁ ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ ለሰባት ፡ ዓመት ፡ ገንዘብ ፡ ሳትከፈል ፡ ስላገለገለችው ፡ ነው ። የመጀመሪያው የክስ ፡ መሠረት ፡ የኛን ፡ ዓላማ ፡ የማይመለከት ፡ ስለሆነ ፡ ሁለተኛውን ፡ ብቻ ፡ እን መለከታለን ።[63] በሁለተኛው ፡ የክስ ፡ መሠረት ፡ የተመለከተውን ፡ ክስ ፡ የካሳስዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተመልክቶ ፡ የተፈጸመ ፡ ውል ፡ ስለሌለ ፡ ከሳሽ ፡ በደ ፡ ኢን ፡ ሬም ፡ ቬርሶ ፡ ገንዘቧን ፡ መከፈል ፡ ይገባታል ፡ ሲል ፡ ፈረደ ። የሰጠውም ፡ ምክንያት ፡ ተከ ሳሿ ፡ በከሳሽ ፡ ጉልበት ፡ በመጠቀምና ፡ ገንዘብ ፡ ባለመክፈሉ ፡ ለገረዶች ፡ መከፈል ፡ የሚኖርበትን ፡ ገንዘብ ፡ ስላዳነ ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ በልጽጓል ፡ የሚል ፡ ነበር ።

፫/ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ብቻ ፡ ተጠቃሽ ፡ የሚሆንበት ፡ ጊዜ ።

ከላይ ፡ በቀረቡት ፡ የጸሐፊዎች ፡ አስተያየቶችና ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውሳኔዎች ፡ አላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ በተከታይነት ፡ ወይም ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ብቻ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችል ፡ ክስ ፡ ነው ፡ ለሚለው ፡ መሠረተ ፡ ሃሳብ ፡ መግለጫ ሆነው ፡ የሚቀርቡ ፡ ሁለት ፡ ንጥረ ፡ አሳቦች ፡ እንዳሉ ፡ እንረዳለን ።

አንደኛው ፡ ምክንያት ፡ በሕጎች ፡ የበላይና ፡ የበታች ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ነው ። የዚህ ፡ ሃሳብ ፡ ደጋፊዎች ፡ በፈረንሣይ ፡ የሕግ ፡ ቅንጅት ፡ መሠረት ፡ በሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ የወጡት ፡ ሕጎች ፡ የበላይነት ፡ ደረጃ ፡ ሲሰጣቸው ፡ ሌሎች ፡ ሕጎች ፡ የበታች ፡ ናቸው ።[64] ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ በልማድ ፡ የተፈጠረና ፡ ከሱ ፡ የመነጨው ፡ ክስ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚጨበጥ ፡ ትርጉም ፡ የተሰጠው ፡ ስለሆነ ፡ ደረጃው ፡ የበታችነት ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ሕጉ ፡ አንድ ፡ መፍትሔ ፡ በሚያበረክትበት ፡ ጊዜ ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ አይችልም ።

በሩዋስት ፡ አስተያየት ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ምንጭ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሕግ ፡ ነው ። አንድ ፡ ሰው ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ምክንያት ፡ አላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ የለበትም ፡ ከሚል ፡ ፍትሐዊ ፡ አስተያየት ፡ የመነጨ ፡ ነው ። ይህን ፡ ሃሳብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የመብትና ፡ ግዴታ ፡ ምንጭ ፡ አድርገው ፡ የተወሰነ ፡ መልክ ፡ ሰጥተውታል ። ጎሬም ፡[65] ተመሳ ሳይ ፡ አስተያየት ፡ አለው ። ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ሕግ ፡ ከልማድ ፡ የመነጨ ፡ ነው ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ለልማድ ፡ ሕግ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ትርጉም ፡ ይሰጠዋል ። በርሱ ፡ አስተያየት የልማድ ፡ ሕግ ፡ "ሕግ ፡ አውጪ ፡ ክፍል ፡ ካወጣው ፡ ሕግ ፡ በስተቀር ፡ ሌላውን ፡ ሁሉ ፡ የሚጨምር ፡ ነው ።" ከሩዋስት ፡ ጋር ፡ የማይስማማው ፡ ይህ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ስለመጣበት ፡ መንገድ ፡ ነው ። በሩዋስት ፡ አስተያየት ፡ "ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ሕግ፡ የተፈጠረው ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሳይሆን ፡ በልማድ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ግን ፡ ልማዱን ፡ ሕግ ፡ እንዲሆን ፡ አድርገውታል ።"[67] በጎሬ ፡ አስተያየት ፡ ግን ፡

63. ስለ ፡ ምን ፡ ሥርዐት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ አልጨመርንም ፡
64. ሩዋስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ. ፴፰ና ፡ የሚከተለው ፡ ድራኪዲስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አር ዕስት ፡ ቍ. ፴፫ ፡ ገጽ ፡ ፮፻፬-፮፻፮ ፡ ውስጥ ፡ እንደተጠቀሰ ፤ ጉሬ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ. ፩፻፬ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፯-፩፻፱ ፤ ፐላኒዮልና ፡ ሪፔር ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ. ፯፻፷፮ ፡ ገጽ ፡ ፳፯ ፡
65. ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቍ.—፩፻፭ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፹ ፴፰ ፡ ቀጥሎ ።
66. እዚያው ፡
67. ሩዋስ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ቍ. ፴፰ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፬ ፡ ማስታወሻ ፡ ቍ. ፩ ፡ በቍ. ፩፻፪ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፰ ፡ እንደቀረበው ።

ልማዱ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዋጋ ፡ እንዲሰጠው ፡ ባይደረግ ፡ ኖሮ ፡ ልማድ ፡ ሆኖ ፡ ይቀር፡ ስለነበረ ፡ የሕጉ ፡ ምንጭ ፡ መሆን ፡ ያለባቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ፡ የሚል ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የራሱንና ፡ የሩዋስትን ፡ ክርክር ፡ በመያዝ ፡ ቦንካስ ፡[68] ያቀረበውን ፡ ትችት ፡ ተቋቁሟል ። ቦንካስ ፡ የሚለው ፡ ያላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ ክስ ፡ ሁለተኛ ፡ ተጠቃሽነት ፡ በልማድ ፡ ሕግና ፡ በተጻፈው ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ በመመልከት ፡ የተፈጠረ ፡ ሁኔታ ፡ አይደለም ፡ነው ። ጎሬ ፡ ግን ፡ ለሩዋስት ፡ ሲከራከር ፡ ሩዋስት ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ከተጻፈ ፡ ሕግ ፡ በታች ፡ ነው ፡ አላለም ፡ ሲል ፡ ተከራክሯል ። ሩዋስት ፡ ያመለከተው ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ዘዴ ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ባወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ስለዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ቢኖርም ፡ ደረጃው፡ ከተጻፈው ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ ሊመጣጠን ፡ እንደማይችል ፡ ነው ። የልማድ ፡ ሕግ ፡ የሚያገለግለው ፡ በደንበኛው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ጉድለቶች ፡ ለማሟላት ፡ ብቻ ፡ ነው ።[69]

በዚህ ፡ ረገድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተግባሩን ፡ ያከናወነው ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰጠው ፡ ሐተታ ፡ የቀረበለትን ፡ ጉዳይ ፡ ለመወሰን ፡ ከሚያስፈልገው ፡ በላይ ፡ መሆን ፡ የለበትም ፡ በሚለው ፡ ፅንሰ—አሳብ ፡ በመመራት ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በዚህ ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ውሳኔ ፡ ባይሰጥም ፡ እንኳ ፡ የጥያቄውን ፡ አሳሳቢ ፡ ሁኔታ ፡ በመመልከት ፡ የሚከተለውን ፡ አስተያየት ፡ ሰጥቷል ። "ኢጣሊያ ፡ ሙሉ ፡ ገዥነቷን ፡ ከለቀቀችበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዙፋን ፡ በመስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እስከ ፡ ተረከበበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ውሉና ፡ ከውሉ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት የነበራቸው ፡ ንዑሳን ፡ ደንቦች ፡ ጸንተው ፡ ነበሩ ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ ይቻላል ።"

ከ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኋላ ፡ ውሉ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ፈጽሞ ፡ ውድቅ ፡ መሆኑ ፡ እና ፡ ይሠራበት ፡ እንዳልነበረ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ "አንድ ፡ ውል ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ የሚቆጠረው ፡ ውሉን ፡ ባደረጉት ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ብቻ ፡ ነው።"[5] ኤርትራም ፡ በፌዴራሲዮኑ ፡ መሠረት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋር ፡ በመዋሃዷ ፡ የአንድ ፡ ልዩ ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ አካል ፡ ክፍል ፡ ሆነች ። በመንግሥታት ፡ ሕግ ፡ ፅንሰ—አሳቦች ፡ መሠረት ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ አካል ፡ ሌላው ፡ መንግሥት ፡ በገባበት ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆን ፡ አይገደድም ። ስለዚህ ፡ ውሉ ፡ ከ፲፱፻፵፭፡ ዓ ፡ ም ፡ በኋላ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ይሠራበት ፡ አልነበረም ። ይሁንና ፡ በኢጣሊያ ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት ፡ መፈጸምና ፡ በፌዴራሲዮን ፡ መመሥረት ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ ውሉ ፡ ጸንቶ ፡ ይሠራበት ፡ አልነበረም፡ለማለት ፡ ይቻላልን?

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በዚህ ፡ በተባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ውሉ ፡ ጸንቶ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ፡ ያለበትን ፡ ምክንያት ፡ አልገለጸም ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ በመንግሥታት ፡ ሕግ ፡ ፅንሰ—ሐሳቦች ፡ የሚደገፍ ፡ አይመስልም ። የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚስማሙበት ፡ አንድ ፡ ፅንሰ ፡ አሳብ ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ የአንድን ፡ ግዛት ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት ፡ የሚረከበው ፡ ሀገር ፡ ያስረካቢውን ፡

---

4. የኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ (፩)
5. የኢንተርናሲዮናል ፡ ቋሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሰርተን ፡ ጀርመን ፡ ኢንተረስትስ ፡ ኢን ፡ ፖሊሽ ፡ አፐር ፡ ሲሌሺያ ፡ በሚለው ፡ ጉዳይ ፡ ፒ- ሲ- አይ- ጄ- ሴር ኤ- ቁጥር ፯ ፡ ገጽ ፡ ፳፱ ፡ (፲፱፻፳፮ ፡ እ- ኤ- አ-)

አገር ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ ጨምሮ ፡ አይረከብም ፡፡ ስለዚህ ፡ ያስረካቢው አገር ፡ የሕዝብ ፡ መብት ፡ ነክ ፡ ሕግ ፡ (ፓብሊክ ፡ ሎው) ፡ የአገሪቷ ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ጸንቶ ፡ ሊቆይ ፡ አይችልም ፡፡[6] በአገሮች ፡ መካከል ፡ የሚደረጉ ፡ ውሎች ፡ በነዚሁ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ የሕዝብ ፡ መብት ፡ ነክ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ናቸው ፡፡[7] ስለዚህ ፡ የአሁኑ ፡ ውል ፡ ኢጣሊያ ፡ በኤርትራ ፡ ላይ ፡ የነበራትን ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት ፡ ካጣችበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ውድቅ ፡ ሆኗል ፡፡ ይኸውም ፡ በኢጣሊያ ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት ፡ መፈጸምና ፡ በፌዴራሲዮኑ ፡ መመሥረት ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ውሉ ፡ ጸንቶ ፡ የማይሠራበት ፡ ምክንያት ፡ የኢጣሊያ ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት በእንግሊዝ ፡ ሙሉ ፡ ገዥነት ፡ በመተካቱ ፡ ነው ፡፡[8]

እስካሁን ፡ የተመለከትነው ፡ ውሉ ፡ ጸንቶ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉን ፡ ነበር ፡፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ የተያያዘና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ ሌላ ፡ ጥያቄ ፡ ደግሞ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ "ተዛማጅ ፡ ደንቦች" ፡ ብሎ ፡ የጠቀሰው ፡ የ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቍጥር ፡ ፷፻፵፯ ፡ ሕግ ፡ ጸንቶ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉን ፡ ነው ፡፡ ይህ ፡ በሃይማኖት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተፈጸመ ፡ ጋብቻ መፍረስ ፡ የለበትም ፡ የሚለው ፡ ክርክር ፡ የተመሠረተው ፡ ከ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ውል ፡ ይልቅ ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ነበር ፡፡

የፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ውሳኔ ፡ የሚለው ፡ ውሉ ፡ የማያገለግል ፡ ከሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቍጥር ፡ ፷፻፵፯ ፡ ሕግም ፡ በኤርትራ ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ነው ፡፡ አስተያየቱን ፡ ለመደገፍ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ መስሎ፡ የሚታየውን ፡ አንድ ፡ ኢጣሊያዊ ፡ የሕግ ፡ ባለሙያ ፡ የሰጡትን ፡ አስተያየት ፡ ጠቅሷል ፡፡ ይኸውም ፡ "በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ሲሰረዝ ፡ በውሉ ፡ ምክንያት ፡ የወጡ ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡ ይሰረዛሉ ፡፡ ለነኚህ ፡ ደንቦች ፡ መሠረዣም ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ማረጋገጫ ፡ ለመስጠት ፡ ደንብ ፡ ማውጣት ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ፡" ፡ የሚል ፡ ነው ፡፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ነገሩን ፡ ከሚፈርስ ፡ ጣራ ፡ ጋር ፡ በማነፃፀር ፡ ተናግሯል ፡፡ አንድ ከጣራው ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ የመብራት ፡ ማንጠልጠያ ፡ ጣራው ፡ ሲወድቅ ፡ አብሮ ፡ መውደቁ ፡ አይቀርም ፡ ብሏል ፡፡ ይህ ፡ ምሳሌ ፡ የአቀራረብ ፡ ውበት ፡ ቢኖረውም ፡ ጉዳዩን ፡ በትክክል ፡ አያስረዳም ፡፡ በትክክለኛ ፡ የአስተሳሰብ ፡ ዘዴ ፡ መሠረት ፡ ውሉ ፡ ጸንቶ ፡ የሚቆይበት ፡ ዘመን ፡ ሲፈጸም ፡ በውሉ ፡ ምክንያት ፡ የተደነገገው ፡ ደንብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መቆየት ፡ ወዲያውኑ ፡ እንዲፈጸም ፡ ያስፈልጋል ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ፡፡ የጀርመን ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህንኑ ፡ የመሰለ ፡ ጉዳይ ፡ አጋጥሞት ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ አስተያየት ፡ በመቀበል ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ "በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሥምምነቱ ፡ ጽኑነት ፡ ቢፈጸምም ፡ በስምምነቱ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፉት ፡ ደንቦች ፡ የአገሩ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ በሆኑበት ፡ መጠን ፡ ጽኑነታቸውን ፡ ሳያጡ ፡ ይቆያሉ ፡፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ረገድ ፡ ጽኑነትን ፡ ማጣት ፡ ውስጣዊ ፡ ጽኑነትን ፡ ላይነካ ፡ ይችላል"[9] ፡ የሚል ፡ ነው ፡፡ (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው) ፡፡

6. አር ፡ ፒ ፡ ኤ ፡ ኮኔል ፡ ዘሎው ፡ ኦቭ ስቴት ፡ ሳክሴሽን ፡ (፲፱፻፶፯ ፡ እ- ኤ- አ-) ገጽ ፩፻፲፩
7. ለምሳሌ ያህል ፡ የተሻሻለውን ፡ የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ- ም- የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቍ ፡ ፩፻፳፱ ፡ ይለከቷል ፡፡
8. አር ፡ ፒ ፡ ኤ ኮኔል ኢንተርናሺናል ሎው (፲፱፻፷፩ እ- ኤ- አ-) ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፳፫
9. ኤስ - ኤች- ፡ ከሳሽ ፡ ኤል- ሲ.ኤች- ተከሳሽ ፤ በፓሪስ ፡ (ሬይሸስጊሪስት ፡ ጀርመን ፡ ፲፱፻፲፬ ፡ እ- ኤ- አ-)፤ እንትስይዱንግን ፡ ዴስ ፡ ራይሽስጌሪስትስ ፡ ኢን ፡ ዚቤልዘበን ፡ ቦልዩም ፡ ፹፩ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፹፬ ፡ አር ስታንገር ፡ ማትሪያልስ ፡ ኦን ፡ ፓብሊክ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ሎው ፡ ውስጥ ፡ እንደተጻፈ ፡ (፲፱፻፷፭ ፡ እ፦ ኤ ፡ አ ፡ ያልታተመ ፡ በቀ- ኃ- ሥ- ዩኒቨ- የሕግ ፡ ቤት ፡ መጻሕፍት ፡ ገጽ ፡ ፬፻፶፯ ፡፡

የዚህን ፡ አስተሳሰብ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ቀላል ፡ ምሳሌ ፡ በመውሰድ ፡ ለመረዳት ይቻላል ። በሁለት ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ውል ፡ ቢደረግና ፡ በዚህ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ አንዱ ፡ አገር ፡ የቀረጥና ፡ የታሪፍ ፡ አከፋፈል ፡ ደንቦችን ፡ ቢያሻሽል ፡ እነዚህም ፡ ደንቦች ፡ በሕግ ፡ ጸንተው ፡ ቢወጡ ፡ ዋናው ፡ ውል ፡ ፈረሰ ፡ ተብሎ እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ ሳይፋቁ ፡ ይችላሉ ። አለበለዚያ ፡ የውሉ ፡ ሕጋዊ ፡ ጽኑነት ፡ እንደ ተፈጸመ ፡ ጉዳዩን ፡ የሚመለከተው ፡ ማንኛውም ፡ የአገሪቷ ፡ ሕግ ፡ እንዳልነበረ ፡ ይሆናል ። እነዚህ ፡ ከአንድ ፡ ውል ፡ ጋር ፡ የተዛመዱ ፡ ደንቦች ፡ ውሉ ፡ ውጤት ፡ የሌለው እንደሆነ ፡ ወዲያው ፡ ውጤት ፡ የሌላቸው ፡ የሚሆኑበትንና ፡ የማይሆኑበትን ፡ ጊዜ ፡ ለመለየት ፡ የሚያስችል ፡ ጠቅላላ ፡ መምሪያ ፡ መስጠት ፡ ቀላል ፡ አይደለም ። እያንዳንዱ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጉዳይ ፡ በየግሉ ፡ መመርመር ፡ አለበት ። የያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ መለየት ፡ አግባብ ፡ ያለውንም ፡ ሕግ ፡ ይለውጠው ፡ ይሆናል ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ለሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚያገለግል ፡ ጠቅላላ ፡ መምሪያ ፡ በመፍጠር ፡ ፈንታ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ በመመልከት ፡ የሚነሱትን ፡ ጥያቄዎች ፡ ብቻ ፡ መመለስ ፡ ነበረበት ። በዚህ ፡ የትሪንጋሊን ፡ ጉዳይ ፡ በሚመለከተው ፡ የተለየ ፡ ሁኔታ ፡ ብቻ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስተያየትና ፡ ፅንሰ ፡ አሳቡን ፡ የተጠቀመበት ፡ ዘዴ ፡ ትክክል ፡ ይመስላል ። ስምምነቱ ፡ ስለተሻረ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፵፯ ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ይሆናል ፤ ሕጉ ፡ ወደ ፡ ውሉ ፡ የሚመራ ፡ በመሆኑ ፡ የውሉ ፡ መፍረስ ፡ የሕጉንም ፡ መሰረዝ ፡ ያስከትላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

የጋብቻው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ውሉና ፡ ከርሱም ፡ ጋር ፡ የተያያዙት ፡ ደንቦች ፡ የተሰረዙ ፡ በመሆናቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጋብቻውን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፡ እንዳልነበረ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቆጠርና ፡ የአስመራ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሑፍም ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ እንዲታረም ፡ አዘዘ ።

የጋብቻው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ውሉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የማይውል ፡ ውድቅ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ሲሆን ፡ አከራካሪ ፡ ጥያቄ ፡ የሚያስነሳው ፡ የጋብቻው ፡ "እንዳልነበረ" ፡ ሆኖ ፡ መወሰድ ፡ ነው ። የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አባባል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፡ የሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ጋብቻ ፡ መጀመሪያውኑ ፡ እንዳልተፈጸመ ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠራል ፡ የሚል ፡ ከሆነ ፡ ሁለት ፡ አስቸጋሪ ፡ ውጤቶች ፡ ይፈጠራሉ ። አንደኛ ፡ ስምምነቱ ፡ ውድቅ ፡ ከሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ የተፈጸሙ ፡ የኤርትራ ፡ ጋብቻዎች ፡ ሁሉ ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነው ። ሁለተኛ ፡ ጋብቻው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ረገድ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ ለምሳሌ ፡ አንዱ ፡ ያገባው ፡ ሰው ፡ ኑዛዜ ፡ ሳይሰጥ ፡ ከሞተው ፡ ባለቤቱ ፡ ይዞታ ፡ ሥር ፡ የነበረውን ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ የመውረስ ፡ መብት ፡ ተፈጻሚነት ፡ የለውም ፡ ማለት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ውጤቶች ፡ የሚያጠራጥሩ ፡ ሲሆኑ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ እና ፡ ፌዴራሲዮኑ ፡ እንደተፈጸመ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ በኅዳር ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጸናው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የዚህ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ውጤት ፡ እናገኛለን ። በዚህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ተጋቢዎቹ ፡ በሃይማኖታቸው ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ የጋብቻቸውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከፈጸሙ ፡ በክብር ፡ መዝገብ ፡ ቢመዘገብ ፡ ባይመዘገብ ፡ ጋብቻው ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።[10] ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ባሁኑ ፡ ጉዳይ ፡ አከራካሪው ፡ ነገር

10. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ፭፻፹፯ ፣ ፭፻፹፱ ፣ ፮፻፭ ፣ ፮፻፲፯ ።

ውሉ ፡ የጸና ፡ ከሆነ ፡ ጋብቻውን ፡ ለማፍረስ ፡ ይቻል ፡ ነበር ፡ ወይ ፡ የሚለው ፡ ብቻ ፡ ነበር ። እዚህ ፡ ላይ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አባባል ፡ ቅር ፡ የሚያሰኝ ፡ ሲሆን ፡ ያመጣው ፡ ውጤት ፡ ግን ፡ ትክክለኛ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፡ ብቻ ፡ ያለውን ፡ ጉዳይ ፡ በመመርመር ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ በውስጣዊ ፡ ሕግ ፡ የሚያስከትለውን ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ ለሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ ለሌላ ፡ ጸሐፊ ፡ ትቶታል ።

CASE COMMENT

INTERNATIONAL LAW : STATE SUCCESSION
TRINGALI CARMELO TERESA v. MALTESE VINCENZE

Supreme Court of Eritrea - Civ. Case No. 590/62

*by Fasil Nahum**

In 1958,** the plaintiff, Tringali Carmelo Teresa, and the defendant, Maltese Vincenze, celebrated a marriage in Eritrea following the rites of the Roman Catholic Church. The marriage was subsequently registered by the officer of civil status of the municipality of Asmara. In August 1962, Plaintiff petitioned the Supreme Court in Asmara to declare the marriage juridically non-existent for purposes of the civil law, to declare null and void of any juridical power the entry of the marriage in the register of civil status of the municipality of Asmara, and to order the officer of civil status to correct the register accordingly.

To understand the problems raised by this petition, one must bear in mind the relevant historical background. In 1929 Italy and the Holy See entered into a Concordat (treaty) under which Italy agreed to recognise religious marriages celebrated in Italian territory following the rites of the Roman Catholic Church for civil law purposes. The Italian Government subsequently promulgated a law, No. 847 of 1929, to enforce the Concordat. This law also extended the application of the Concordat to all Italian colonies, including Eritrea.

Formal Italian sovereignty over Eritrea came to an end through the Peace Treaty of September 15, 1947, signed by Italy and the four allied powers.[1] In reality Italy had ceased to exercise any control over Eritrea in 1941. "The final disposal ... (of Eritrea was to be) determined jointly by the governments of the Soviet Union, of the United Kingdom, of the United States, and of France within one year from the coming into force of the present Treaty, in the manner laid down in the joint declaration of February 10, 1947, issued by the said Governments...."[2]

Since these powers did not agree as to what was to happen to Eritrea, the responsibility to decide its future status was transferred to the United Nations General Assembly following the procedures laid down in the declaration. In December 1950, the United Nations General Assembly passed a resolution which became the basis for the federation between Ethiopia and Eritrea. This legal instrument was adopted by Ethiopia and Eritrea in September 1952. Later, on November 15, 1962,

* *Faculty of Law, Haile Sellassie I University*

** All dates are given according to the Gregorian Calendar.

1. "Italy renounces all right and title to ... Eritrea." Art. 23 (1) The Peace Treaty.
2. Art. 23 (3), The Peace Treaty.

Order No. 27 of 1962[3] was issued by Ethiopia, terminating the federation and thus making Eritrea part of a unified Empire.

The major issue raised by this case is whether the Concordat of 1929 entered into by Italy and the Holy See was still in force in Eritrea at the time of the parties' marriage in 1958. Under the Concordat, civil courts would be bound by the religious rules of the Catholic Church regarding, for example, dissolution of marriages. Thus, if the Concordat was in effect, an annulment could be granted only if sanctioned by Church authorities. It appears that no such sanction had been given in this case.

By 1958 Eritrea and the federation had succeeded to the sovereignty formerly exercised by Italy. Whether Eritrea was still bound by the Concordat depends on the principles of the law of nations governing the rights and duties of such successor states. In dealing with this issue, the Supreme Court stated that an "undisputed principle of public international law provides that in the succession of States, the successor State does not inherit *ipso jure* the treaties of the States from which it derives." Furthermore, the Court held that "a limitation on the jurisdiction of one State in favour of another may be admitted only if and to the extent that the State concerned agrees, and not as a result of a law existing before the State came into being."

The Court by this last remark simply means that the Concordat would be in force in Eritrea only if Eritrea had ratified it subsequent to assuming sovereignty. Under the Eritrean Constitution[4] the power of ratifying international agreements is expressly reserved to the Emperor as Sovereign of the Federation. Since the Emperor never took steps to ratify the Concordat, the Court rightly concluded that the Concordat of 1929 between Italy and the Holy See had ceased to be in force in Eritrea by 1958.

The Court did not determine at what point prior to 1958 the Concordat became ineffective, whether it did so with the end of *de facto* Italian presence and rule in 1941, or with the Peace Treaty of 1947, or with the termination of the British Civil Administration and the creation of the Federation with Ethiopia in 1952. Since the marriage in question took place in 1958, the Court did not have to commit itself to any of these possible choices.

In this respect the Court acted within the generally held principle that a court should not decide more than is necessary for the disposition of the case before it. Although the Court did not decide the issue, however, it did indicate some concern over the question, stating that, "Perhaps it can be argued that in the interim between the time when Italy gave up its sovereignty over Eritrea, and the time when the Ethiopian Crown assumed it on September 11, 1952, the Concordat and the related norms could be considered to have been in force."

There is, indeed, no question but that after 1952 the Concordat had ceased to be in force in Eritrea. Generally speaking, "a treaty only creates law as between

3. An Order to Provide for the Termination of the Federal Status of Eritrea and the Application to Eritrea of the System of Unitary Administration of the Empire to Ethiopia, *Neg. Gaz.* No. 3 Year 22nd.
4. The Eritrean Constitution, Art. 5 (1).

the States which are parties to it."[5] Eritrea had through the Federation assimilated itself to Ethiopia, thereby becoming part of a different international personality. Under the principles of the law of nations such international personality is not required to be bound by treaties entered into by another State; thus the Concordat had no force in Eritrea after 1952. But may one go further and conclude that even during the interim period before the Federation the Concordat had ceased to be in force?

The Court gave no reason why it thought that the Concordat might have remained in force in this interim period, and it appears that such an argument would be rebutted by the principles of the law of nations. There is general agreement among international jurists today on the principle that a State which succeeds another State in sovereignty over a territory is not a successor to the constitutional authority of the predecessor State. It follows from this that the public law of the predecessor State cannot survive the end of its sovereignty.[6] Treaties entered into between States form part of the public law of such States.[7] It thus follows that the Concordat ceased to have force in Eritrea from the time that the Italian State lost its sovereignty over it. This means that even during the interim period, the Concordat had lost its force because Italian sovereignty had given place to British effective sovereignty.[8]

So far we have been dealing with the effectiveness of the Concordat. There is a related and necessary question regarding the effectiveness of what the Court referred to as the "related norms," namely, law No. 847 of 1929. It was this legislation, rather than the Concordat itself that was the immediate basis of the claimed indissolvability of the religious marriage.

The Court held that once the Concordat became ineffective, law No. 847 of 1929 ceased to be in force in Eritrea. To support its view, the Court quoted an Italian authority's statement: "If a treaty is extinguished for any reason whatsoever, the norms set up as a result of the treaty also become extinguished, without the necessity of any declaration to this effect." The Court analogised the situation to a collapsing roof. A chandelier hanging from the roof would have to come down as the roof does. The chandelier analogy is colourful, but not very precise. It is not *necessary*, as a matter of logic, that the norms set up as a result of a treaty automatically become ineffective as soon as the treaty itself is extinguished. This was recognised by the German Reichsgericht, the highest German court, when it was confronted with the same issue. It held that, "even if it be admitted that the binding force of the Convention under international law ... ceases ipso facto ... the contents of the Convention, insofar as they have become part of our civil law, do not cease to be valid ... *The international validity and the internal effectiveness are not necessarily interdependent.*"[9] (Emphasis added).

5. The Permanent Court of International Justice, in the case of *Certain German Interests in Polish Upper Silesia*, P.C.I.J., Ser. A No. 7 p. 29 (1926).
6. R.P. O'Connell, *The Law of State Succession* (1956). p. 211.
7. Refer for instance to Art. 122 of the Ethiopian Revised Constitution of 1955.
8. R.P. O'Connell, *International Law* (1965), vol. I p. 368.
9. S.H.H. v. L.CH. in Paris (Reichsgericht, Germany, 1914), *Entscheidungen des Reichsgerichts in Zivilsachen* vol. 85 p. 374; as found in R. Stanger, *Materials on Public International Law* (1965, unpublished, Law Library, H.S.I.University), p. 496.

One can see the basis for this position by taking a simple example. If a bi-lateral commercial treaty is entered into by which one State undertakes to amend its municipal regulations on custom duties and tariffs, these regulations, if enacted, are not necessarily and automatically made ineffective if the treaty is abrogated. If the contrary is argued, then the state may be left unexpectedly with no law at all on an important subject of tax regulation, if the former law must be treated as repealed.

It is not easy to make a general rule as to when such norms automatically become ineffective and when not. Each case has to be examined individually. Differences in fact may result in a difference of law. The Court should not have tried to create a universal principle but only solved the questions raised by the particular facts. In the particular circumstances of the *Tringali* case, the Court's reasoning and application of the principle seem sound. In the absence of the Concordat, law No. 847 is useless; the legislation refers to the Concordat and the ineffectiveness of the Concordat results in the ineffectiveness of the legislation as well.

Since the Concordat and its related norms had, at the time of the parties' marriage, ceased to be effective, the Court granted the petition that the marriage be declared juridically non-existent for purposes of the civil law and ordered the correction of the register of civil status of the municipalty of Asmara accordingly.

While the conclusion that the Concordat no longer had effect at the time of the parties' marriage is unimpeachable, serious questions can be raised from the perspective of domestic law whether the marriage should have been declared "non-existent." If the court really meant that the civil law status of the parties was as if their marriage had never occurred, it would seem to have adopted two rather troublesome sets of results. First, *all* Eritrean marriages entered into in the Catholic Church during the period of the Concordat's ineffectiveness would seem to be null and void; second, none of the civil incidents of marriage - - for example, the right of the spouse to share communal property held with an intestate deceased spouse - - would seem to apply. Such results are questionable. The opposite result would have been reached, for example, under the Civil Code of 1960 which became applicable in Eritrea in November 1962 upon dissolution of the Federation. Under the Code, any marriage celebrated in accordance with the rites of the parties' religion is by that fact valid, whether or not registered by the officer of civil status.[10] In this case, however, the issue was only whether dissolution could be authorised despite the Concordat. While the Court's language may have been unfortunate, its result was correct. This paper has been concerned only with the International Law aspects of the case, and leaves to another court and another writer the troublesome problem of the domestic impact of this decision.

10. Civ. C. Arts. 577, 579, 605, 697 ff.

የጊዜው ፡ አሳሳቢ ፡ ጉዳይ ፡

የአውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቀሙትን ፡ ሀብቶች ፡ የሚያስለቅቅበት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

ሃሪሰን ፡ ሲ ፡ ዳኒንግ ፡*

የአውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ በ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአዋጅ ፡ ተቋቋመ ።[1] ምንም ፡ እንኳን ፡ የአውራ ፡ ጎዳናዎች ፡ መሥራትና ፡ መጠበቅ ፡ ሥልጣን ፡ ከሥራና ፡ ማመላለሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የተዛወረበት ፡ ምክንያት ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ግልጽ ፡ ባይሆንም ፡ የሥልጣን ፡ ማዛወሩ ፡ የተደረገው ፡ የአስተዳደር ፡ ቅልጥፍናን ፡ ለማግኘት ፡ ይመስላል ።[2] እንዲያውም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አውራ ፡ ጎዳናዎች ፡ እቅዶች ፡ ከውጭ ፡ ከተገኙት ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታዎች ፡ አብዛኛውን ፡ የሰጠው ፡ ለማደሻና ፡ ለልማት ፡ የቆመው ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ባንክ ፡ በ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የመጀመሪያውን ፡ የ፭ ፡ ሚሊዮን ፡ የአሜሪካን ፡ ብር ፡ ብድር ፡ እንዲሰጥ ፡ ይህን ፡ የአስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ ለውጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ሁኔታ ፡ አድርጎ ፡ የገመተው ፡ ይመስላል ።[3] የተቋቋመበት ፡ ምክንያቶች ፡ ግልጽ ፡ ባይሆኑም ፡ የአውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ሥራዎችን ፡ ከሚያከናውኑትና ፡ ጠቃሚ ፡ ከሆ

---

* በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ረዳት ፡ ዲንና ፡ ረዳት ፡ ፕሮፌሰር ። በአውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለሚደረገው ፡ የመሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ ለጸሐፊው ፡ መግለጫ ፡ በመስጠት ፡ የሚከተሉት ፡ ሰዎች ፡ ስለአደረጉት ፡ እርዳታ ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ፦ አቶ ፡ ሽፈራው ፡ ብዙነህ ፡ በአውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ምክትል ፡ ዋና ፡ መሃንዲስ ፤ አቶ ፡ ዘውዱ ፡ መሸሻ ፡ በአውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የሕግ ፡ መኰንን ፤ አቶ ፡ ከበደ ፡ በየነ ፡ በአውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የመተላለፊያ ፡ መብት ፡ መኰንን ፤ አቶ ፡ ሰይፉ ፡ የተሻወርቅ ፡ በአውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ምክትል ፡ የመተላለፊያ ፡ መኰንን ፤ ሻለቃ ፡ ለማ ፡ ገብረጻድቅ ፡ በአውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ከመተላለፊያ ፡ መብት ፡ ቅርንጫፍ ፡ ሚስተር ፡ ፓርክ ፡ ዊልሰን ፡ በአውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የቀድሞ ፡ የገንዘብና ፡ ያስተዳደር ፡ ሥራ አስኪያጅ ፤ ሚስተር ፡ ሮበርት ፡ ስኰት ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሕግ ፡ ጠበቃ ።

1. የአውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፤ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ .ም . አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፲፭ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፳ ። ይህ ፡ አዋጅ ፡ የጸደቀው ፡ ጥር ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሲሆን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋለው ፡ ከዚሁ ፡ ቀን ፡ጀምሮ ፡ ነው ።
2. ሐምሌ ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጁን ፡ ከአረቀቁት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ከሆኑት ፡ ከሚስተር ፡ ሮበርት ፡ ስኰት ፡ ጋራ ፡ የተደረገ ፡ ኢንተርቪው ። ለመጀመሪያ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ የባለሥልጣኑ ሥራ ፡ አስኪያጆችና ፡ ሠራተኞች ፡ የተገኙት ፡ ከአሜሪካን ፡ ቢሮ ፡ ኦቭ ፡ ፓብሊክ ፡ ሮድስ ፡ ነው ። ይህም ፡ ድርጅት ፡ ምናልባት ፡ ለመሥራት ፡ የፈለገው ፡ ከአንድ ፡ ራሱን ፡ ከቻለ ፡ ድርጅት ፡ ጋር ፡ ነው ።
3. ይህ ፡ ለውጥ ፡ ተፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ የሚታወቀው ፡ ከአዋጁ ፡ መግቢያ ፡ ነው ፦
"የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችንን ፡ የማመላለሻ ፡ ጎዳናዎችና ፡ ሥራ ፡ ለማሻሻል ፡ ምኞታችን ፡ ስለሆነ ፤ ይህንንም ፡ ምኞታችንን ፡ ለመፈጸም ፡ ለማደሻና ፡ ለልማት ፡ ከቆመ ፡ ከኢንተርናሲዮናል ፡ ባንክ ፡ ጋር ፡ ስምምነት ፡ ስላደረግን ፡ ኀብረቱንም ፡ ለማግኘት ፤ የአውራ ፡ ጎዳናዎችን ፡ ማስፋፊያና ፡ መጠበቂያ ፡ ፕሮግራም ፡ አድሚኒስትራሲዮን ፡ ማሻሻል ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆነ" ፤ የአውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፲፭ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፳ ። ራሱን ፡ የቻለ ፡ ባለሥልጣን ፡ ማቋቋም ፡ በገንዘብ ፡ ነክ ፡ ጉዳዮች ፡ የበለጠ ፡ ታማኝነትና ፡ የተሻለ ፡ አስተዳደር ፡ የሚያስገኝ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ ታስቦ ፡ ነው ።

ኑት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ድርጅቶች ፡ አንዱ ፡ መሆኑን ፡ አሳይቷል ።[4]

የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አውራ ፡ ጐዳናዎችን ፡ ለመሥራትና ፡ ለመጠገን ፡ ስለሆነ ፡[5] ባለሥልጣኑ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ትን ፡ መሬቶች ፡ ለመውሰድ ፡ የሚያስችል ፡ ሥልጣን ፡ መሰጠቱ ፡ ተገቢ ፡ ነው ።[6] የአ ውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፳(መ) ፡ እንደሚለው ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ "ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ አድ ርጐ ፡ የግል ፡ መሬቶችን ፡ ለመውሰድና ፡ በመሬቶች ፡ ላይ ፡ የሚገኙት ፡ ቤቶች ፡ አዝመ ራዎች ፡ አታክልቶችና ፡ ሌሎችም ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ የሚገባውን ፡ ግም ት ፡ ለመወሰን ፡"[7] ይችላል ።

---

4. በተቋቋመ ፡ በመጀመሪያዎቹ ፡ አሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ሰፋ ፡ ካለው ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ዎችን ፡ የመጠገንና ፡ የማሻሻል ፡ ሥራ ፡ ሌላ ፡ ከ፭፻፶ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ የሚበልጡ ፡ በበጋም ፡ ሆነ ፡ በክረምት ፡ ወራት ፡ የሚያገለግሉትን ፡ መንገዶች ፡ በመሥራትና ፡ በማደስ ፡ ረድቷል ። የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ኢትዮፒያ ፡- ፕሮግሬስ ፡ ኢን ፡ ሃይ ፡ ዌይ ፡ ትራንስፖርት ፡ (፲፱፻፷፯ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) ፡ ገጽ ፡ ፪ ። ከ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ የበጀት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ለአውራ ፡ ጐ ዳና ፡ ሥራና ፡ ማደሻ ፡ የአሜሪካን ፡ ፶፰ሚሊዮን ፡ ወጪ ፡ ሲደረግ ፡ ከዚህም ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ ፳፪ ፡ እጅ ፡ የተገኘው ፡ ከውጭ ፡ ብድሮችና ፡ እርዳታዎች ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ እርእስት ፡ በገጽ ፡ ፬ ፡ ይመለከቷል ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥም ፡ ለአውራ ፡ ጐዳና ፡ ጥበቃ ፡ የአሜሪካን ፡ ፵፯ ፡ ሚሊዮን ፡ ያህል ፡ ወጪ ፡ ሆኗል ። ከዚያው ።
5. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ በማዘጋጃ ፡ ቤቶች ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የአውራ ፡ ጐዳናን ፡ ሥራ ፡ የሚያከናውነው ፡ በተለዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ ብቻ ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለ ሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ ለባለሥልጣኑ ፡ "የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታች ንን ፡ የአውራ ፡ ጐዳናዎች ፡ ማሻሻልና ፡ መጠበቅ ፡" ተግባር ፡ ቢሰጥም ፡ በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ በግልጽ ፡ ታውቀው ፡ የተዛወሩት ፡ ተግባሮች ፡ "ከዚህ ፡ በፊት ፡ በሥራና ፡ ማመላለሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይሠራ ፡ የነበ ረው ፡ ሥራ ፡ ተግባርና ፡ ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡" ናቸው ። አንቀጽ ፡ ፫ ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተ ቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፲፭ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፳ ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የሥራና ፡ ማመላለሻ ፡ ሚኒስትር ፡ "የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችንን ፡ መን ገዶች ፡ ድልድዮችን ፡ ለመሥራትና ፡ እየተጠባበቀም ፡ ለማደስ ፡ አላፊ ፡" ቢሆን ፡ የሚኒስትሮችን ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ የሚወስን ፡ ትእዛዝ ፡ ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፳ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፭ (ለ) ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ቁጥጥር ፡ ስር ፡ ያሉት ፡ ማዘ ጋጃ ፡ ቤቶች ፡ "መንገዶችን ፡ አደባባዮችን ፤ ድልድዮችን ፤ መንሸርሸሪያዎችንና ፡ የአትክልት ፡ ቦታዎ ችን ፡ መክፈት ፡ ማስቀረት ፤ መጠበቅ ፤" የመሳሰሉትን ፡ ጉዳዮች ፡ ለመወሰን ፡ እንዲችሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቷቸዋል ፤ አንቀጽ ፡ ፬ ፡ (፫) ፡ (ሀ) ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤቶች ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፤ ቁጥር ፡ ፸፬ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፬ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፯ ። በተጨማሪም ፡ የጐዳናዎችና ፡ መንገዶች ፡ አከፋፈል ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፷፯ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፲ ፡ (ተቀጣይ) ፡ አንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ ይመለከቷል ። በተግባር ፡ ላይ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤቶች ፡ ከአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ጋራ ፡ የተለየ ፡ ስምምነት ፡ ካላደረጉ ፡ በቀር ፡ መንገድ ፡ የመሥራትና ፡ የመጠበቅ ፡ ተግባራቸውን ፡ ራሳቸው ፡ ሲያከናውኑ ፡ ቆይተዋል ።
6. የዚሁ ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፲ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡- "በዚህ ፡ አዋጅ ፡ በ፳ኛው ፡ ክፍል ፡ (መ) እንደተመ ለከተው ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ አድርጐ ፡ በግል ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ለመግባት ፡ ወይም ፡ መሬቶ ችን ፡ ለመውሰድ ፡ ለባለሥልጣኑ ፡ የተሰጠው ፡ መብት ፡ በማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደገና ፡ መታየት ፡ ወይም ፡ መፈቀድ ፡ የለበትም ። በመሬቶቹ ፡ ላይ ፡ ስለሚገኙት ፡ ቤቶች ፤ አዝመራዎች ፡ አታክልቶች ፤ ወይም ፡ ሌሎች ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ባለሥልጣኑ ፡ የወሰነው ፡ ግምት ፡ በሚ ገባ ፡ መሆኑንና ፡ አለመሆኑን ፤ ወይም ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ባለጥቅሞች ፡ በሆኑት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የግምት ፡ አከፋፈል ፡ ይመርመርልኝ ፡ ሲል ፡ በተወሰደው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ መሬቱ ፡ ባለበት ፡ አውራጃ ፡ በሚገኘው ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኑ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይችላል" ። ምንም ፡ እንኳን ፡ አዋጁ ፡ ያሜሪካኖችን ፡ አባባል ፡ ተከትሎ ፡ "የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ አድርጐ ፡ --- መሬቶችን ፡" መውሰድ ፡ (ኤሚነንት ፡ ዶሚይን ፡) ቢልም ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አባባል ፡ "ንብረትን ፡ ማስለቀቅ ፡" በሚለው ፡ ሐረግ ፡ እንጠቀማለን ።
7. አንቀጽ ፡ ፳ ፡ (መ) ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፲፭ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፳ ። በተጨማሪም ፡ የ፲፱፻፵፯ን ፡ ዓ ፡ ም ፡ መምሪያ ፡ ቍጥር ፡ ፴፭ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፬ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ ይመለከቷል ።

ስለዚህም ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፰ (መ) ፡ የሚገባው ፡ ግምት ፡ ከሚወሰንላቸው ፡ ነገሮች ፡ ጥንትም ፡ ሆነ ፡ አሁን ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ግምት ፡ የሚታየው ፡ የንብረት ፡ ዓይነት ፡ የሆነውን ፡ መሬትን ከዝርዝሩ ፡ ትቶታል ።[8] ይህም ፡ በግድፈት ፡ ወይም ፡ በስህተት ፡ የተደረገ ፡ አይደለም ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣንም ፡ ከ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ የግል ፡ የሆኑ መሬቶችን ፡ የሚወስደው ፡ ምንም ፡ ግምት ፡ ሳይሰጥ ፡ ነው።[9] ለዚህም ፡ የተሰጠው ፡ ምክንያት ፤ አውራ ፡ ጐዳናው ፡ ሲሠራ ፡ በአካባቢው ፡ ያለውን ፡ የመሬት ፡ ዋጋ ፡ ከፍ ፡ ስለሚያደርገው ፡ ይህ ፡ የዋጋ ፡ ጭማሪ ፡ አውራ ፡ ጐዳናው ፡ ካመጣቸው ፡ ሌሎች ፡ ጥቅሞች ፡ ጋራ ፡ ሲደመር ፡ ለመንገዱ ፡ ሥራ ፡ ሲባል ፡ መሬታቸው ፡ በከፊል ፡ ለተወሰደባቸው ፡ ባለ ፡ ንብረቶች ፡ በቂ ፡ ግምት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ነው ።[10] ይህ ፡ አስተያየት ፡ ቢኖርም ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ በተወሰደው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ለሚገኙት ፡ ቤትን ፡ ለመሳሰሉት ፡ ንብረቶች ፡ በአዋጁ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፰ (መ) ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የሚገባውን ፡ ግምት ፡ ሰጥቷል ።[11]

---

8. አንቀጽ ፡ ፳፰ (መ) ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ ከመሬቱ ፡ ላይ ፡ ለተወሰዱት ፡ ንብረቶች ፡ ነው ፡ ስለሚል ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ወይም ፡ አሸዋ ፡ ላሉት ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ ለሚገኙት ፡ ንብረቶች ፡ ግምት ፡ እንዳይሰጥ ፡ የሚከለክል ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተገምቷል ። እንዲህ ፡ ዓይነቱን ፡ ለመሥሪያ ፡ የሚያገለግሉ ፡ ንብረቶች ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ በብዛት ፡ ሲወስድ ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ የሚከፍለው ፡ ላስከተለው ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ለምሳሌ ፡ ድንጋይ ፡ በሚፈለጥበት ፡ ቦታ ፡ አጠገብ ፡ ለጠፋው ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ ግምት ፡ ይከፈላል ። ይህም ፡ ተግባር ፡ ክስ ፡ እንዲበዛ ፡ ሲያደርግ ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣንን ፡ የማይደግፉ ፡ ፍርዶችም ፡ አሉባቸው። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ጣፋ ፡ ሰኚ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ (ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጥፍርድ ፡ ቤት ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፪፻፺፩/፺፮ ፡ ዓ ፡ ም) (ያልታተመ)። በከፊል ፡ ሲነበብ ፡ "የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ በመሬቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ ከውኃ ፡ በታች ፡ ያለውም ፡ ጭምር ፡ የመንግሥት ፡ ንብረቱ ፡ ነው ፡" በሚለው ፡ የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተሻሽሎ ፡ በወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴ ፡ ምክንያት ፡ የነዚህ ፡ የድንጋይ ፡ ፈለጣ ፡ ጉዳዮች ፡ አወሳሰን ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆኗል ። ከመሬት ፡ በታች ፡ የሚገኙት ፡ ድንጋይና ፡ ሌላም ፡ ለመሥሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ንብረቶች ፡ ለግል ፡ ንብረትነት ፡ የተፈቀዱ ፡ ናቸው ፡ ከተባሉ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ "የመለቀቃቸው ፡" ጥያቄ ፡ የሚነሳው ።
9. ከአቶ ፡ ከበደ ፡ በየነ ፤ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የመተላለፊያ ፡ መኰንን ፡ ጋራ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተደረገ ፡ ኢንተርቪው ። የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፰ (መ) ፡ ለአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሬት ፡ እንዲወስድና ፡ ላንዳንድ ፡ ለተጠቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ እንዲሰጥ ፡ ስለሆነ ፡ አንዳንድ ፡ የባለሥልጣኑ ፡ ባልደረቦች ፡ እንደሚሉት ፡ ባለሥልጣኑ ፡ ለሌሎች ፡ ንብረቶች ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ እንዳይከፍል ፡ ስለታገደ ፡ በዚህ ፡ አስተሳሰብ ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ አከፋፈሉን ፡ ሊለውጥ ፡ ቢፈልግም ፡ በዚህ ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ አይችልም ፡ ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የሥራ ፡ ሠፈር ፡ እንዲሆን ፡ ሲወሰድ ፡ ተመሳሳይ ፡ ወይም ፡ የሚስተካከለው ፡ መሬት ፡ ከመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ መሬት ፡ ለተወሰደበት ፡ ባለንብረት ፡ ተሰጥቶአል ። ለተወሰደበት ፡ መሬት ፡ ምትክ ፡ የተሰጠው ፡ አዲስ ፡ መሬት ፡ በዋጋ የሚመጣጠነው ፡ ከሆነ ፡ ባለመሬቱ ፡ እንዲለቅ ፡ ለተገደደበት ፡ መሬት ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ ተከፍሎታል ፡ ማለት ፡ ነው ።
10. ከአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ባልደረቦች ፡ ጋራ ፡ በተደረጉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኢንተርቪዎች ፡ የተገኙ ። የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ በተዘጋጀበት ፡ ጊዜ ፡ ጸሐፊው ፡ ይህ ፡ ምክንያት ፡ ታስቦ ፡ ወይም ፡ ተገልጾ ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ የሚያስደፍር ፡ ማስረጃ ፡ አላገኘም ።
11. የሚታመኑ ፡ ማስረጃዎችን ፡ ለማግኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ቢሆንም ፡ የተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ብዙ ፡ አልነበረም ። ለመጀመሪያዎቹ ፡ ጥቂት ፡ ዓመታት ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ተግባር ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የነበሩትን ፡ አውራ ፡ ጐዳናዎች ፡ ወደ ፡ ጥቅም ፡ መመለስ ፡ ስለነበረ ፡ ብዙ ፡ የመሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ ችግር ፡ አልገጠመውም ። እንዲያውም ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የመተላለፊያ ፡ ቅርንጫፍ ፡ የተቋቋመው ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ይመስላል ። መልካም ፡ ምሳሌዎች ፡ የሚሆኑ ፡ በቅርቡ ፡ የተከፈሉ ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ የተገለጹት ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡- የኢትዮጵያ ፡ $፱ሺ ፪፻፷ ከ፺ ፡ ሣንቲም ፡ ለ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እና ፡ የኢትዮጵያ ፡ $፮ሺ ፯፻፴፰ ፡ ለ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ። ለነዚህ ፡ ዓመቶች ፡ ዓመታዊውን ፡ ሪፖርት ፡ በቅደም ፡ ተከተልነታቸው ፡ በገጽ ፡ ፵፬ ፡ እና ፡ በገጽ ፡ ፵፫ ፡ ይመለከቷል ፡ ምናልባትም ፡ በተጨማሪ ፡ በመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ መሬትም ፡ በከፊል ፡ እንደ ፡ ኪሣራ ፡ ግምት ፡ ሳይሰጥ ፡ አልቀረም ።

የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ እና ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ መንግሥት ፡

የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ የወጣው ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ እንዲለቀቅ ፡ ከተደረገ ፡ ለተወሰደው ፡ ንብረት ፡ በግልጽ ፡ ግምት ፡ መሰጠት ፡ አለበት ፡ በማይለው ፡ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሠረት ፡ ነው ።[12] ነገር፡ ግን ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተሻሽሎ ፡ የወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ንብረት ፡ ትክክለኛው ፡ ግምት ፡ እንዲሰጠው ፡ በግልጽ ፡ ያዛል ። የዚህም ፡ ሕገ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ እንደሚለው ፡ "በዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፰፤ ወይም ፡ ፮ ፡ እንደተመለከተው ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ ግል ፡ ንብረቶች ፡ መወሰድ ፡ (ኤክስፕሮፕሪዬሽን) ፡ በተለይ ፡ በሚወጣው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖና ፤ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ተስማምቶበት ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በሚወጣው ፡ በሚኒስትር ፡ ትእዛዝ ፡ " ካልሆነ ፡"---በቀር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ንብረቱ ፡ አይወሰድበትም ።" በተጨማሪም፡ "በሕግ ፡ የተወሰነ ፡ የተቆረጠ ፡ ትክክለኛ ፡ ግምት ፡ አስቀድሞ ፡ ካልተከፈለ ፡ በቀር ፡ በግምቱም ፡ስምምነት ፡ ባልተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ በዳኝነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ካልተወሰነ ፡ በቀር ፡" ንብረቱ ፡ አይወሰድም ።[13]

---

12. የዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ የሚለው ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ተወላጆች ፡ በሕግ ፡ እንደተጻፈው ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ከሚያስፈልግበት ፡ ጊዜ ፡ በቀር ፡ በእጃቸው ፡ የያዙትን ፡ ገንዘባቸውንና ፡ ውለታቸውን ፡ ማንም ፡ ሊወስድባቸው ፡ አይችልም ፡" ነው ። ለእንግሊዘኛ ፡ አንባብያን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ፖልና ፡ ክላፐም ፡ ኢትዮፕያን ፡ ኮንስቲቱሽናል ፡ ዲቬሎፕመንት ፡ (፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ በገጾች ፡ ፫፻፳፯ — ፫፻፴ ፡ እና ፡ በኢትዮፒያን ፡ አብዘርቨር ፡ (፲፱፻፷፱ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ ቮልዩም ፡ ፭ ፡ በገጾች ፡ ፫፻፷፫ ፡ ፫፻፷፭ ፡ በሙሉ ፡ ታትሞ ፡ ይገኛል ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ታትሞ ፡ ያልወጣ ፡ ስለ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የተጻፈ ፡ አንድ ፡ ማብራሪያ ፡ ኅተታ ፡ በመንግሥት ፡ መወረስ ፡ ስለ ፡ ማይገባቸው ፡ መሬቶች ፡ ሲያወሳ ፡ የሚከተለውን ፡ አስተያየት ፡ ሰጥቷል ፡ መንግሥት ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ለሕዝብ ፡ ደህንነት ፡ የሚጠቅሙ ፡ እንደ ፡ ምሽጐች ፡ ጐዳኖች ፡ ገበያዎች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፤ ትምህርት ፡ ቤቶች ፤ ሆስፒታሎች ፤ ከተማዎች ፡ ወይም ፡ ሌሎችም ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ ድርጅት ፡ ለመሥራት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ካገኘው ፡ በሕጉ ፡ እንደተወሰነው ፡ የምክር ፡ ቤቶቹ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ከወሰኑ ፡ ባለመሬቱ ፡ በሕግ ፡ የተወሰነውን ፡ ተመጣጣኝ፡ ግምት ፡ ይሰጠዋል ፡ ባለንብረቱ ፡ ከፈቀደም ፡ ሌላ ፡ ንብረት ፡ ይሰጠዋል ፡" (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው) ። ክፍል ፡ ፫፮ ፤ ደምሴ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትና ፡ ምክር ፡ ቤት ፤ ታሪካዊ ፡ መዝገብ ። [ያዘጋጇው ፡ ማስታወሻ ፡ ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ በመጀመሪያ ፡ የተዘጋጀው ፡ ባማርኛ ፡ ቢሆንም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተሰጠው ፡ በኤስ ፡ ራይት ፡ አማካኝነት ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ከተተረጐመውና ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ በፓልና ፡ ክላፐም ፡ መጽሐፍ ፡ በገጾች ፡ ፫፻፵፩ ፤ ፵፻፵፬ ፡ ከሚገኘው ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ በመተርጐም ፡ የተገኘ ፡ ነው ። ይህም ፡ የሆነው ፡ የመጀመሪያው ፡ ጽሑፍ ፡ ባለመገኘቱ ፡ መሆኑን ፡ እንገልጻለን ።]
13. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ። አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ በተጨማሪ ፡ የተባለው ፡ የሚኒስትር ፡ ትእዛዝ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ተስማምቶበት ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ መውጣት ፡ አለበት ፡ ይላል። የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አንዱ ፡ ችሎት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ "ስለ ፡ ግል ፡ ንብረቶች ፡ መወሰድ ፡ (ኤክስፕሮፕሪዬሺን ፡) በተለይ ፡ በሚወጣው ፡ ሕግ ፡ " የሚለው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ንብረትን ፡ ስለ ማስለቀቅ ፡ የተደነገጉትን ፡ ደንቦች ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ተገቢ ፡ አስተያየት ፡ ሰጥቷል ፡ ሳክሬት ፡ ሶቼታ ፡ አኖኒማ ፡ ከሳሽ ፤ የማዕድንና ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ሚኒስቴር ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፤ የኢት ፡ ሕገ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፬ ፡ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፯) ፡ ገጾች ፡ ፶፮-፶፱ ። የፍትሐ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ መሠረት ፡ ስለ፡ ግል ፡ ንብረት ፡ መወሰድ ፡ በተለይ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ስላልነበረ ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ፡የሆነ ፡ መሬት ፡ የማስለቀቅ ፡ ተግባር ፡ ሊከናወን ፡ አይችልም ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ ሰጥቷል ። ሐጂ ፡ አሊ ፡ አሕመድ ፡ አቦኝ ፡ ከሳሽ ፤ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ተሠሳሽ ፤ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቍጥር ፡ ፷፻፴፪/፶) (ያልታተመ) ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ እና ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ለተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ በተሰጠው ፡ አተረጓጐም ፡ ላይ ፡ በተመሠረተው ፡ የባለሥልጣኑ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ተግባር ፡ መካከል ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ መቃረን ፡ ቢኖርም ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱም ፡ ከታወጀ ፡ በኋላ ፡ የባለሥልጣኑ ፡ መሥሪያ ቤት ፡ ተግባር ፡ አልተለወጠም ። እንዲያውም ፡ ይህ ፡ ተግባር ፡ ተቃውሞ ፡ የገጠመው አልፎ ፡ አልፎ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ ንብረታቸው ፡ የተወሰደባቸው ፡ ባለንብረቶች ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ ወደ ፡ አካባቢያቸው ፡ በመምጣቱ ፡ ስለሚደሰቱ ፡ እና ፡ ለተ ወሰዱባቸው ፡ ቤቶች ፡ አዝመራዎችና ፡ "ሌሎችም ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡" የተሰጣቸው ፡ ግምት ፡ አጥጋቢ ፡ ሆኖ ፡ ስለአገኙት ፡ ይመስላል ። እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ታትሞ ፡ በወጣው ፡ አንድ ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ባለንብረት ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ በተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ስለ ፡ ግምት ፡ አከፋፈል፡ የሚመለከቱትን ፡ አንቀጾች ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ ተቃራኒ ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ ሲቃወም ፡ ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግን ፡ አዋጁም ፡ ሆነ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ "የጠቅላላውን ፡ ጥቅም ፡" እንዲጠብቁ ፡ የታሰቡ ፡ ስለሆኑ ፡ ስለ ፡ ግምት አከፋፈል ፡ የሚመለከቱ ፡ የአዋጁ ፡ አንቀጾች ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ አይቃረኑም ፡ ብሎ ፡ ወሰነ ።[14] ይህም ፡ ውጤት ፡ የተገኘው ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የግል ፡ ንብረትን ፡ የማስለቀቅ ሥልጣን ፡ የሚሰጡትን ፡ የአዋጁን ፡ አንቀጾች ፡ በሕገ ፡ መን ግሥቱ ፡ መሠረት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚያስችለውን ፡ የተሻሻለውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳይመለከት ፡ ነው ። "የበላይ ፡ ሕግን ፡" የሚገልጸው ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ "ይህ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ ከምትሆንባቸው ፡ ከኢ ንተርናሲዮናል ፡ ውሎች ፡ ከዓለም ፡ ስምምነቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ ሆኖ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ይሆናል ። ወደ ፡ ፊትም ፡ የሚ ሠሩ ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ ፍርዶች ፡ ውሳኔዎች ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ ፡ ሲሆኑ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ ።" (አንክ ሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው ።) የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣንም ፡ ሥራውን ፡ የሚያከናው ንበት ፡ ሕግ ፡ የታወጀው ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ ስለሆነ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እሱን ፡ የሚ መለከት ፡ አይደለም ፡ ሊል ፡ ይችላል ።[15]

14\. የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ እና ፡ አስካንስካ ፡ ኩባንያ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ ኮሎኔል ፡ መብራቱ ፡ ፍስሐ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፤ የኢት ፡ ሕገ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፪ (ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፲፱፻፶፯) ፡ ገጾች ፡ ፴፫-፴፯ ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ይህ ፡ ድንጋይ ፡ መፍለጥን ፡ የሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ቢሆን ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በግል ፡ ንብረት ፡ ከተያዘ ፡ መሬት ፡ ድንጋይ ፡ እንዳይፈለጥ ፡ ብሎ ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ፍርድም ፡ የግል ፡ ባለ ፡ ንብ ረቱ ፡ "ስለ ፡ ግምት ፡ መጠየቅ ፡ ነገር ፡ --- የሚያቀርቡት ፡ ክርክር ፡ ቢኖር ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ አያግድም" ቢልም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የወሰድነው ፡ የፍርድ ፡ አተረጓጐም ፡ ተገቢ ፡ ይመስላል ። ከዚያው ፡ በገጽ ፡፴፯።

15\. ይህን ፡ አስተሳሰብ ፡ የ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የቴሌፎን ፡ አገልግሎት ፡ አዋጅን ፡ ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ፡ ቊጥር ፡ ፩፻፲፬ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፱ኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፲፩ ፡ በሚመለከተው ፡ በክቡር ፡ ልጅ ፡ አር አያ ፡ አበበ ፡ ከሳሽ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ጉዳይ ፡ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፯) ፡ የኢት ፡ ሕግ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፪ ፡ ገጾች ፡ ፫፻ ፡ ፫፻፪ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ተጠቅሞበታል ። ስለ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪፡ ትርጉም ፡ ለመረዳት ፡ ፖልና ፡ ክላፕሃም ፡ ኢትዮፕያን ፡ ኮንስቲቱሽናል ፡ ዲቬሎፕመንት ፡ ቮልዩም ፡ ፩ (፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ፡ ገጾች ፡ ፬፻፲፬-፬፻፲፯ ፤ እና ፡ ሚንስ ፡ "በመንግሥት ፡ የአስተዳደር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተወሰኑ ፡ ጉዳዮችን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የማየት ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተደገፈ ፡ ሥልጣን ፡ መነሻ ፡ ጥያቄዎች ፡" የኢት ፡ ሕገ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፫ ፡ (፲፱፻፶፰ ፡ዓ ፡ ም ፡) ገጾች ፡ ፩፻፶፪ ፡ ፩፻፶፬ ፤ ይመለከታል ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ላስለቀቀው ፡ መሬት ፡ ግምት ባለመስጠቱ ፡ እርምጃው ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋራ ፡ ለመቃረኑ ፡ እርግጠኛ ፡ ለመሆን ባይቻልም ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ በተጨማሪ ፡ ለመቃወም ፡ የሚቻለው ፡ ባለሥልጣኑ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለእርምጃው ፡ መሠረት ፡ አድርጐ ፡ የቆጠራቸውን ፡ የአዋጁን ፡ አንቀጾች ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለሚሽራቸው ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔሩም ፡ ሕግ ፡ ንብረትን ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ፡ የተጻፉ ፡ የራሱ ፡ ድንጋጌዎች፡ አሉት ፤ እነዚህም ፡ ድንጋጌዎች ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የሚፈጽማቸውን ፡ የመሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ ተግባር ፡ የሚመለከቱ ፡ ይመስላሉ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፷ — ፩ሺ፬፻፹፰ ፡ ስለ ፡ ኪሣራ ፡ ግምት፡ አከፋፈልና ፡ "የአስተዳደር ፡ ክፍሎች ፡" የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ሲያስለቅቁ ፡ ሊከተሉት ፡ የሚገባቸውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይደነግጋል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ "የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡" የሚለው ፡ አነጋገር ፡ (ሕጉ ፡ መጀመሪያ ፡ በተጻፈበት ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ቋንቋ ፡ ላድሚኒስትራሲዮን ፡ የሚል ፡ ነው ፡) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ባይተረጐምም ፡ ለማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸውን ፡ እንደ ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ያሉትን ፡ የሚያጠቃልል ነው ፡ ቢባል ፡ ተገቢ ፡ አተረጓጎም ፡ ይመስላል ።[16] መሬቱ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ አዝመራዎች ፡ ባይኖሩትም ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍሉ ፡ ላስለቀቀው ፡ መሬት ፡ ተገቢውን ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ በገንዘብም ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ መሬት እንዲከፍል ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ያስገድደዋል ። ስለዚህም ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፸፬(፩) እንዲህ ፡ ይላል ፦ "ስለ ፡ መሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ የሚከፈለው ፡ ትክክል ፡ የሆነ ፡ ግምት ፡ ወይም ፡ መሰል ፡ ምትኩ ፡ መሬቱን ፡ ከማስለቀቁ ፡ የተነሣ ፡ በደረሰውና ፡ በተረጋገ

16. በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የመሬት ፡ ማስለቀቂያ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እነማን ፡ መሆናቸው ፡ በሙሉ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። አንዱም ፡ አስተሳሰብ ፡ ሚኒስቴሮች ፡ በተፈጥሯቸው ፡ የመሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ ሲኖራቸው ፡ ሌሎች ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ ግን ፡ በግልጽ ፡ ሥልጣኑ ፡ ካልተሰጣቸው ፡ አይችሉም ፡ ይላል ። ሚኒስቴሮች ፡ ያልሆኑ ፡ የመሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ምሳሌዎች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡— የ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፺፱ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፯ ፡ አንቀጽ ፡ ፮ ፡ (ሀ) ፤ የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኤሌትሪክ ፡ መብራትና ፡ ኃይል ፡ ባለ ሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲፫ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፭ ፡ አንቀጽ ፡ ፬ (ሠ) ፤ የ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፴፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፭ ፡ አንቀጽ ፡ ፯ (ሰ) ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ለሚኒስቴሮችም ፡ ንብረት ፡ የማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። ለምሳሌ ፡ የባሕር ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፴፯ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ አንቀጽ ፡ ፵፯ ፡ ለአገር ፡ መከላከያ ፡ ሚኒስቴር ፡ ለባሕር ፡ ክፍል ፡ የሚጠቅሙትን ፡ ንብረቶች ፡ እንዲያስለቅቅ ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ። ለባሕር ፡ መከላከያ ፡ ጉዳዮች ፡ ንብረትን ፡ የማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ የተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ ይህ ፡ ሥልጣን ፡ የሚኒስትሮችን ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ በሚወስን ፡ ትእዛዝ ፡ (ማሻሻያ ፡ ቍ. ፪) ፲፱፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቍጥር ፡ ፵፮ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፫ኛ ፡ ዓመት ፤ ቍጥር ፡ ፳፫ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፬ ፡ መሠረት ፤ ቀጥተኛ ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ መገናኛ ፡ ሚኒስቴር ፡ ተዛውሮአል ። በተጨማሪ ፡ የ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፖስታ ፡ አገልግሎት ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፵ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፳፪ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፫ ፡ ይመለከቷል ። ይህም ፡ አንቀጽ ፡ "ራሱን ፡ የቻለ" ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ የተባለውን ፡ የፖስታ ፡ ቤት ፡ የንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ። ኮንሴስዮን ፡ የተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ለመፈጸም ፡ ውል ፡ የገቡትም ፡ ጭምር ፡ በኮንሴሲዮኑ ፡ ስምምነት ፡ በግልጽ ፡ ሥልጣን ፡ ከተሰጣቸው ፡ ንብረትን ፡ ሊያስለቅቁ ፡ ይችላሉ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፷፪ ።

ጠው ፡ ጉዳት ፡ ልክ ፡ ይሆናል" (እንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው) ።[17] የታወቀ ፡ የመሬት ፡ ገበያ ፡ ካለ ፡ መሬቱ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ አዝመራዎች ፡ ቢኖሩትም ፡ ባይኖሩትም ፡ በገበያው ፡ ያለው ፡ የመሬቱ ፡ ዋጋ ፡ በባለንብረቱ ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ የተረጋገጠ ፡ ጉዳት ፡ ለመወሰኛ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የመሬት ፡ ገበያ ፡ ባይኖርም ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ እንዲከፈል ፡ የሚያስገድድበት ፡ ጉዳት ፡ ይደርሳል ።

መሬቱ ፡ ቢለማም ፡ ባይለማም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የኪሣራ፡ ግምት ፡እንዲከፈል ፡ ማስገደዱ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መሬት ፡ እንዲያስለቅቅ ፡ ሥልጣን ፡ ከሚሰጠው ፡ ድንጋጌ ፡ በቀር ፡ መሬት ፡ ማስለቀቅን ፡ የሚመለከቱት ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ቊጥሮች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሻራቸውም ፡ ግልጽ ፡ ነው ።[18] በጣም ፡ ሰፊ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡[19] ስለተሻሩ ፡ ሕጐች ፡ የሚናገረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፫ሺ፫፻፵፯ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡- "ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ ተጽፈው ፡ ይሠራባቸው ፡ የነበሩት ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለተተካ ፡ ተሽረዋል ።" ስለ ፡ መሬት ፡ ማስለቀቅ ፡ ጉዳይ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ ተመልክቷል ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፭ (መ) ፡ እና ፡ አንቀጽ ፡ ፲ ፡ መሬት ፡ ስለማስለቀቅ ፡ የተደነገጉ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ይሠራባቸው ፡ የነበሩ ፡ ደንቦች ፡ ናቸው ፤ እነዚህ ፡ የቀድሞ ፡ ደንቦች ፡ እንዳይሻሩ ፡ የሚያደርግ፡ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ድንጋጌ ፡ ስለሌለ ፡ ደንቦቹ ፡ መሻራቸው ፡ የማይካድ ፡ ነው።

የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ግን ፡ ይኸንን ፡ ውጤት ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ አልተቀበለውም ።[20] የዚህም ፡ ምክንያት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግን ፡ ከተ

17. ሕጉ መጀመሪያ ፡ በተጻፈበት ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ቋንቋ ፡ ፩ሺ፱፻፸፱ ፡ (፩) የሚለው ፡ የኪሣራ ፡ ግምቱ ፡ *égale à la valeur du dommage actuel et certain* መሆን ፡ አለበት ፡ ነው ። በእንግሊዘኛው ፡ አክችዋል ፡ (*actual*) የሚለው ፡ ቃል ፡ "ያሁን ፡ የሆነ ፡" የማለት ፡ ስሜት ፡ እንጂ ፡ "በእርግጥ ፡ የደረሰ ፡" የሚለውን ፡ ስሜት ፡ የያዘ ፡ አይደለም ። የተርጓሚው ፡ ማስታወሻ ፡- የአማርኛው ፡ ቅጂ ፡ የፈረንሳይኛው ፡ ቅጂ ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉም ፡ ነው ።

18. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ለአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ሆነ ፡ ለሌላ ፡ በስም ፡ የተጠቀሰ ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅት ፡ የንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ አይሰጥም ። ስለዚህም ፡ ለአውራ ፡ ጐዳና፡ባለሥልጣን፡ንብረት ፡ ለማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ የሚሰጠውን ፡ የተቋቋመበትን ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ እንዳልተሻረ ፡ አድርጐ ፡ መቁጠር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ምክንያቱም ፡ አለዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ባለሥልጣኑ ፡ ይህን ፡ የሚያስችለው ፡ ሥልጣን ፡ አይኖረውም ። ከላይ ፡ የሚገኘው ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፲፮ን ፡ ይመለከቷል ።

19. ፺ ፡ ክሽችኖቪች ፡ "ሕግና ፡ ባሕል ፡ (ልማድ ፡) በኢትዮጵያ ፡" የኢት ፡ ሕግ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፪ ፡ (፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ፤ ገጾች ፡ ፬፻፩ ፡ ፬፻፬-፬፻፭ ፤ ፺ ፡ ክሽኖቢች ፡ "ኤ ፡ ኒው ፡ ሌጅስሌቲቭ ፡ አፕሮች ፡ ቱ ፡ ካስተመሪ ፡ ሎው ፡- ዘ ፡ 'ሪፒልስ' ፡ ፕሮቪዠን ፡ ኦቭ ፡ ዘ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሲቪል ፡ ኮድ ፡ ኦቭ፡፲፱፻፷ ፡ ጆርናል ፡ ኦቭ ፡ ኢትዮፒያን ፡ ስታዲስ ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ቊጥር ፡ (፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) ፡ገጽ፡ ፶፰ ፡ ይመለከቷል ። በተጨማሪም ፡ የሚከተሉትን ፡ ይመለከቷል ፡- አር ፡ ሴድለር ፡ "ዘ ፡ ዲቬለፕመንት ፡ ኦቭ ፡ ሊጋል ፡ ሲስተምስ ፡- ዘ ፡ ኢትዮፕያን ፡ ኤክስፒርየንስ ፡" ፡ አዮዋ ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፡ ቮልዩም ፡ ፶፫ (፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) ፡ ገጾች ፡ ፭፻፷፪ ፡ ፭፻፲፬—፮፻፪ ፺ ፡ ቫንደርሊንደን ፡ "ስለ ፡ 'የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ምንጮች ፡ መግቢያ ፡' የተሰጠ ፡ ተጨማሪ ፡ ማብራሪያ" ፤ የኢት ፡ ሕግ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፫ (፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም) ፡ ገጾች ፡ ፯፻፳፱ ፡ ፯፻፴ ፤ ፺ ፡ ክሽችኖቪች ፡ "ሕጉን ፡ ጥንታዊ ፡ ማድረግ ፡ አይሆንምን ? ሕግና ፡ ምንጮቹ ፡" የኢት ፡ ሕግ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፫ ፡ (፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጾች ፡ ፯፻፱ ፡ ፯፻፲፱-፯፻፲፯ ፤ ፺ ፡ ቫንደርሊንደን ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፡ መግቢያ ። ከ፲፫ኛው ፡ እስከ ፡ ፳ኛው ፡ መቶ ዓመት ፡" የኢት ፡ ሕግ ፡ መ ፡ ቮልዩም ፡ ፫ (፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ፡ ገጾች ፡ ፩፻፶፱ ፡ ፪፻፲፱—፪፻፲፭ ።

20. ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቅሙትን ፡ ሀብቶች ፡ ስለማስለቀቅ ፡ የተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፫ሺ፫፻፵፯ ፡ መሻራቸውን ፡ ቢቀበሉም ፡ ይህ ፡ እምቢተኛነት ፡ አሁንም ፡ አለ ። በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፯ ፡ የተጠቀሰውንና ፡ አሁን ፡ በይግባኝ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ችሎት ፡ የቀረበውን ፡ ጣፋ ፡ ሰፒ ፡ ከሳሽ ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ተከሳሽ ፡ ጉዳይ ፡ ይመለከቷል።

ከተለ ፡ የመሬት ፡ ማስለቀቂያ ፡ ዋጋ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ስለሚል ፡ "ፍሬያማ" ፡ የአውራ ፡ ጐዳናን ፡ ሥራ ፡ ይቀንሳል ፡ የሚል ፡ ፍርሃት ፡ ይመስላል ። ይህም ፡ ፍርሃት ፡ አንዳንዱን ፡ የባለሥልጣኑን ፡ ሠራተኞች ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ እንዳይሆን ፡ እና ፡ ባለሥልጣኑ ፡ መሬት ፡ ባስለቀቀ ፡ ጊዜ ፡ ለመሬቱ ፡ ሳይሆን ፡ በመሬቱ ፡ ለሚገኙ ፡ ቤቶች ፡ አዝመራዎችና ፡ ሌሎችም ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ብቻ ፡ የኪሣራ ፡ ግምት ፡ እንዲከፈል ፡ የሚያደርገው ፡ የቀድሞው ፡ ሕግ ፡ እንደገና ፡ እንዲወጣ ፡ እንዲከራከሩ ፡ አድርጓቸዋል ።[21]

ይህ ፡ ፍርሃት ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ሲታይ ፡ ተገቢ ፡ ቢመስልም ፡ ስለ ፡ ኪሣራ ፡ ግምት ፡ አከፋፈል ፡ የተደነገጉትን ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ደንቦች ፡ በጥንቃቄ ፡ መመርመር ፡ የአውራ ፡ ጐዳናዎችን ፡ ሥራና ፡ እድገት ፡ የመሰለ ፡ እቅድ ፡ በገንዘብ ፡ እጥረት ፡ ያሰናክላል ፡ የሚለውን ፡ ፍርሃት ፡ ለማስወገድ ፡ ሳያስችል ፡ አይቀርም ። በእርግጥ ፡ ዋናው ፡ ችግር ፡ የኪሳራ ፡ ግምት ፡ አወሳሰን ፡ ዘዴ ፡ ነው ። የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ ለተወሰደ ፡ "ንብረት ፡" "በሕግ ፡ የተወሰነ ፡ የተቆረጠ ፡ ትክክለኛ ፡ ግምት ፡" ፡ እንዲሰጥ ፡ ያዛል ። ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደተባለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ ከንብረቶች ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ የያዘ ፡ ስለሆነ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ "ንብረት ፡" ሲል ፡ መሬትን ፡ አይጠቀልልም ፡ ብሎ ፡ መከራከር ፡ አያዋጣም ።[22] ይህም ፡ አባባል ፡ የለማውንም ፡ ሆነ ፡ ያልለማውን ፡ መሬት ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። መሬት ፡ "ንብረት" ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ቢሆንም ፡ መሬት ፡ እንዲለቀቅ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈለው ፡ "በሕግ ፡ የተወሰነ ፡ የተቆረጠ ፡ ትክክለኛ ፡ ግምት" ፡ ምን ፡ ማለት ፡ እንደሆነ ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ሁኔታ ፡ አያስረዳም ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመንግሥትና ፡ በግል ፡ ባለንብረት ፡ ጥቅሞች ፡ መካከል ፡ ትክክለኛ ፡ ሚዛናዊ ፡ ሁኔታን ፡ በመፍጠር ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከሚለው ፡ ጋራ ፡ የሚስማሙ ፡ በመሆናቸው ፡[23] በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የኪሳራ ፡ ግምት ፡

21. የድሮው ፡ ደንብ ፡ እንደገና ፡ ቢደነገግ ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ለመጠቀም ፡ ስለማይችል ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ መከራከሪያው ፡ በይበልጥ ፡ የተዳከመ ፡ እንደሚሆንበት ፡ መገንዘብ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሚወጣ ፡ ማንኛውም ፡ ሕግ ፡ ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ መስማማት ፡ ይኖርበታል ። ይህም ፡ ማለት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ በሚጠይቀው ፡ መሠረት ፡ ለሕዝብ ፡ ተፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የሚወሰድ ፡ ንብረት ፡ ሁሉ ፡ ትክክለኛ ፡ ግምት ፡ እንዲከፈልበት ፡ ያስፈልጋል ። ስለ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ከላይ ፡ ገጽ ፪፻፲፩ ይመለከቷል ።

22. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ እና ፡ የኢትዮጵያም ፡ ልማድ ፡ በጠቅላላው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የከተማ ፡ ቦታዎችም ፡ ሆኑ ፡ የባላገር ፡ የርሻ ፡ መሬቶች ፡ በቤተ ፡ ሰብም ፡ ሆነ ፡ በያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ባለመብትነት ፡ ሥር ፡ ቢገኙም ፡ የግል ፡ ንብረቶች ፡ መሆናቸውን ፡ በግልጽ ፡ ያስረዳሉ ። ስለ ፡ ሌሎች ፡ የመሬት ፡ ዓይነቶች ፡ ትንሽ ፡ የሚያጠራጥር ፡ ጉዳይ ፡ አለ ። ለምሳሌም ፡ "የግጦሽ ፡ መሬት" በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፲፱፻፵ ፡ (መ) እንደተጠቀሰው ።

23. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ መብቶች ፡ የሚጠበቁት ፡ "በሕግ ፡ መሠረት" ነው ። "ትክክለኛ ፡ ግምት ፡ " በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ "በሕግ ፡ መሠረት" የሚለው ፡ አለመኖሩን ፡ መገንዘብ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቍ ፡ ፵፬ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደተመለከተው ፡ የሚከተሉት ፡ ሁለት ፡ ሁኔታዎች ፡ ካልተሟሉ ፡ በቀር ፡ የማንኛውም ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ እንዳይወሰድ ፡ ይከለክላል ። እነሱም ፡ በመጀመሪያ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ "ተስማምቶበት" ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በሚወጣው ፡ በሚኒስትር ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ ሲኖርበት ፡ የስምምነቱ ፡ ዓይነት ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ አልተገለጸም ። በተጨማሪ ፡ በሕግ ፡ የተወሰነ ፡ የተቆረጠ ፡ ትክክለኛ ፡ ግምት ፡ እንዲከፈልና ፡ በግምቱም ፡ ስምምነት ፡ ባልተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ በዳኝነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መወሰን ፡ ይኖርበታል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ግምት ፡ የሚወሰንበትን ፡ አኳኋን ፡ የሚገልጸው ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ ቢሆን ፡ የሰው ፡ ንብረት ፡ ሲወሰድ ፡ ትክክለኛ ፡ ግምት ፡ የመስጠት ፡ አስፈላጊነት ፡ የመነጨው ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የአንድ ፡ ሕግን ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊነት ፡ ለማረጋገጥ ፡ ያለውን ፡ እንደገና ፡ የማየት ፡ ሥልጣን ፡ ቢጠቀምበት ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ግምት ፡ የወጣ ፡ ሕግን ፡ "ትክክለኛ ፡ ግምት" ሊያሰጥ ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ ለመሰረዝ ፡ ይችላል ።

ሲወሰን ፡ መደረግ ፡ ያለባቸውን ፡ ነገሮች ፡ በጥንቃቄ ፡ ማረጋገጥ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ነው ፡፡

